www.nesiha.com

# ነሲሐ

የእውቀት ማዕድ

ቅጽ 1 ቁጥር 1 መጋቢት 2011

Barruu Nasihaa

## የኢትዮጵያ ሙስሊሞች
## ተቋማዊ የለውጥ ጉዞ
### ተግዳሮቶች እና መፍትሄዎቻቸው







ነሲሐ ቲቪ
እጅ ከምን?

መንፈሳዊ ጉዞ
በሸሪዓ ሚዛን

ነሲሓ
የዕውቀት ማዕድ

ቅጽ 1 ቁጥር 1 | መጋቢት 2011

WWW.NESIHA.COM

# በውስጥ ገጾች

| | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ የለውጥ ጉዞ ተግዳሮቶች እና መፍትሄዎች | 6 |
| ነሲሓ ቲቪ... እጅ ከምን ? | 4 |
| የመጽሐፍ ዳሰሳ | 16 |
| የሰላም ዋጋ | 12 |
| መንፈሳዊ ጉዞ ... | 15 |

## ነሲሓ የዕውቀት ማዕድ

| | |
|---|---|
| የኢስላም ውበት | 18 |
| ከቁርኣን አሻራ | 19 |
| የነብያት ጥሪ | 20 |
| የሱትራ ብይን | 22 |
| ለዓለማት እዝነት | 23 |
| ልብህን መርምር | 24 |
| ውዴታን በተግባር | 25 |
| ስለ ኢስላም አጭር ማብራሪያ | 27 |
| ፈታዋ | 29 |

የነሲሓ መልእክቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች በቀጣይ እትሞች ላይ ይጠብቁ

وَمِن آياتِهِ خَلقُ السَّماواتِ وَالأَرضِ وَاختِلافُ أَلسِنَتِكُم وَأَلوانِكُم إِنَّ في ذٰلِكَ لَآياتٍ لِلعالِمينَ

## ነሲሓ ቤተሰብ

| | |
|---|---|
| ጠቃሚ ነጥቦች ለባለትዳሮች | 32 |
| የምዕመናን እናቶች ታሪክ | 33 |
| የልጆችህ ጓደኞች እነማን ናቸው? | 34 |
| እንዴት ልገመግመው? | 35 |
| ሸይኽ ባሲጢ ሲዘከሩ... | 36 |
| የእናት ጡት ... የጤና ስንቅ | 37 |

## ✍ ነሲሓ ብዕር

| | |
|---|---|
| ለምን ተፈጠርክ? | 39 |
| የአል ሑሱኑ ሰላሳህ ጭብጦች | 40 |
| ፍትሕን እንጠብቅ | 41 |
| ለሌሎች ምን አበርክተሃል? | 42 |
| የምርጦች ምርጥ | 43 |
| ቁርኣን የአላህ ንግግር | 44 |
| አደብን ተማር | 45 |
| ክብር ለሰሓቦች | 46 |
| የመልካም መክፈቻ ሁን! | 47 |

# አዲኑ ነሲሓ

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው፡፡ የአላህ ሰላም እና እዝነት የነብያት መደምደሚያ በሆኑት መልዕክተኛው ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሳያብራሩልን ያለፉት ምንም አይነት ጉዳይ የለም፡፡ መልዕክታቸውን በሙሉ አድርሰው ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ ከዓብዱላህ ኢብን ዓምር ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ የተከበሩት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ለህዝቦቹ የሚያውቅላቸውን መልካም ነገር የሚያመለክታቸው፤ ከሚያውቅላቸውም መጥፎ ነገርም የሚያስጠነቅቃቸው ቢሆን እንጅ ከእኔ በፊት ማንም ነብይ አልተላከም!›› ሙስሊም ዘግበውታል

በነብያት አንደበት ከተብራሩት ጉልህ እውነታዎች ሁሉ ታላቁ፤ የአላህን ብቸኛ ተመላኪነቱን ማረጋገጥ “ተውሒድ” ነው፡፡ ሙስሊሞች በዕለት ተዕለት ኑሯቸው ኢስላምን ይኖሩት ዘንድ የነብዩን ሱና ማጥናትና ማወቃቸው ግዴታ ነው፡፡

ነሲሓ መፅሔት ሸሪዓዊ ዕውቀትንና ጠቃሚ የአኗኗር ትምህርቶችን ወቅታዊ በሆነ መልኩ ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ በማድረስ ረገድ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት እነሆ አንድ ብላ ጥረቷን ጀምራለች።

የነብያት ውርስ የሆነውን ሸሪዓዊ ዕውቀት ከምንጩ በመቅዳት ለህዝባችን ማድረስ፤ ኡማውን ለሚገጥሙት ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች መፍትሄዎችን ማመላከት እና ቀናውን የሰለፎች ጎዳና ማብራራት የነሲሓ መፅሔት ተቀዳሚ ተልእኮ ነው። በተለያዩ መደቦች የተከፋፈሉ መልእክቶች ለንባብ የሚበቁ ሲሆን፤ ወሳኝ ኢስላማዊ ትምህርቶች በነሲሓ አበይት፤ የትዳር ህይወት፣ የልጆች አስተዳደግ እና የመግባባት ክህሎቶችን በነሲሓ ቤተሰብ መደቦች ያገኛሉ። የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ታሳቢ በማድረግም በአረብኛ እና በተለያዩ የሐገራችን ቋንቋዎች ኮፒ ተደርገው ሊሰራጩ የሚችሉ አጫጭር መልእክቶች የሚቀርቡበት መደብ አለን። የተለያዩ ታዋቂ ኡስታዞች የራሳቸውን አምድ ይዘው ጠቃሚ መልእክቶችን ያደርሷችኋል። ፈታዋና የተለያዩ ጠቃሚ የእውቀት ማዕዶችም ተካተዋል።

አንባቢዎች አስተያየት፣ ጥቆማ እና መልእክቶቻቸውን በመላክ ለመፅሔቷ እድገት ከጎናችን እንዲቆሙ አደራ ስንል ከወዲሁ ስለተሳትፏችሁ እያመሰገንን ነው።

የዝግጅት ክፍሉ


**በአል ሐበሻ ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ኃ.የተ.የግ. ማህበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ መጽሔት**

**ዋና አዘጋጅ**

**ናስር ሱለይማን**

አድራሻ፡ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 1620

**ኤዲቲንግ ማኔጀር**

ሳላሕ አሕመድ

**ሲኒየር ኤዲተር**

ሙሐመድ ኢብራሂም

**ግራፊክስ ዲዛይን**

ሐይደር ከድር

**አምደኞች**

1) አቡ ሑነይፍ ኢልያስ አሕመድ
2) አቡ ፈውዛን አሕመድ ሙሐመድ
3) አቡ ዐብዲላህ አሕመድ ኣደም
4) አቡ ኢብራሂም ሙሐመድ ኢብራሂም
5) አቡ ጁነይድ ሳላሕ አሕመድ
6) አቡ ዑሠይሚን ኑጋ
7) አቡ ሀምዛ ጀማል ያሲን
8) አቡ ከውሠር ሻሚል ሙዘሚል
9) ኡሙ ዐብዲላህ ነፊሳ ሙሐመድ
10) አቡ ሐማድ ሐይደር ኸድር

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

ኮ/ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፣ ወረዳ 7 ሳራ የገበያ ማዕከል ቢሮ ቁጥር 315

**መጽሔቱን ለማከፋፈል**
09 10 98 55 64

www.nesiha.com

ነሲሓ መጽሔት | Nesiha Magazine

@nesihablog

# ነሲሓ ቲቪ . . . እጅ ከምን?

ነቢዩ(ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በአንድ ሐዲሳቸው ... «ዲን ማለት ነሲሓ ነው» አሉ። ሶሐቦችም የአላህ መልእክተኛ ሆይ ለማን ነው?» ሲሏቸው፤ እሳቸውም «ለአላህ፣ ለኪታቦቹና ለመልእክተኛው እንዲሁም ለሙስሊሙ አመራሮችና ለመላው ማህበረሰብ ነው» በማለት መልሰውላቸዋል። (ሙስሊም ዘግበውታል)

'ነሲሓ' ማለት በመልካም ኒያ ለሌላ ሰው ምክርን መለገስ፣ ግሳፄን ማድረስና ከጥፋት ማስጠንቀቅ ነው። ነሲሓ ለአላህ ብቻ ተብሎ በኢኽላስ የሚፈፀም ዒባዳ ነው። ይህን ታላቅ ዒባዳ በተግባር ላይ ለማዋል ውጥን የያዙ ወንድሞች በ1998 ዓ.ል 'ሀ' ብለው 'ነሲሓ Google Group'ን በመክፈት ነበር ወደ ስራ የገቡት። በኢሜል ግሩፑ በተለያዩ ቋንቋዎች ጠቃሚ ኢስላማዊ ትምህርቶችን እስከ አስራ አምስት ሺህ ለሚደርሱ ሰብስክራይብ ላደረጉ ኢሜሎች ያሰራጩ ነበር።

እንዲሁም 'ነሲሓ ፓልቶክ ሩም' ተከፍቶ የተለያዩ ደርሶችና ሙሐደራዎች ለ24 ሰዓት ከኢትዮጵያ እና ከአሜሪካ በመተካካት በቀጥታ በኢንተርኔት እየተሰራጩ ብዙዎችን ተጠቃሚ አድርገው ነበር።

ይህን ተከትሎ እያደገ የመጣውን የዒልም ፈላጊዎችን ጉጉት ለማርካት 'ነሲሓ ስቱዲዮ' የአያሌ ኡስታዞችን ዳዕዋዎችና ዱሩሶች በድምፅ በማዘጋጀት ማዳረሱን ተያያዘች። በኢንተርኔት በይነ መረብ ዳዕዋውን ለማሰራጨት የተከፈተው www.nesiha.com ለኢንተርኔት ተጠቃሚው ሙስሊም የበኩሉን አበርክቷል።

ቀስበቀስ ተፅእኖ ፈጣሪነቱ እየጎላ በመጣው ፌስቡክም 'ነሲሓ የውይይት መድረክ' በግሩፕ መልክ፣ 'እምነትህን ጠብቅ'፣ 'ተንቢሀት'፣ 'ፊቅህን ለመረዳት' እና በሌሎችም ፔጆች ሸሪዓዊ እውቀትን ለማዳረስ ተሞክሯል። ከፌስቡክ ባሻገር እንደቴሌግራም እና ዋትሳፕ ባሉ የማህበራዊ ሚድያዎች እንዲሁም በተለያዩ ፓምፍሌቶች ዳዕዋዎች ተሰራጭተዋል።

እነሆ ዛሬ በነሲሓ ስቱዲዮ ተዘጋጅተው እናደምጣቸው የነበሩ ሙሐደራዎችን በአላህ ፈቃድ በየቤታችን በቴሌቭዥኖች እንድንመለከት ሁኗል። ይህ አላህ ሸሪዓዊ እውቀትን ለህዝበ ሙስሊሙ እንዲደርስ ከሚያመቻቸው መንገድ አንዱ ነው።

"ኢስላማዊ እውቀት ለሁሉም!" በሚል መሪ ቃል ሙስሊሙን ማህበረሰብ ለማገልገል በያዝነው አመት አጋማሽ በሙከራ ስርጭት ለአየር የበቃው ነሲሓ ቲቪ ሙሉ በሙሉ ሸሪዓዊ እውቀትን መሰረት ያደረጉ የዳእዋ እና የትምህርት ፕሮግራሞች ሊቀርቡበት ታስቧል።

ነሲሓ ቲቪ ሰፊ ክፍተት በሚታይባቸው የኪታብ ቂርአት ደርሶች በተጨማሪ በጣቢያው በሚተላለፉት 'ተውሒድ የነብያት ጥሪ'፣ 'የታላቆች ታላቅ'፣ 'የኑሕ መርከብ' እና ሌሎች ቤተሰባዊ እና ማህበራዊ አጀንዳዎችን የሚዳስሱ ፕሮግራሞቹ ታዳሚያንን የሸሪዓዊ ዕውቀት ተቋዳሽ ለማድረግ በአላህ ፍቃድ ቆርጦ ተነስቷል።

በተጨማሪም በ'ነሲሓ አካዳሚ' መርሐ ግብሩ ዘመናዊ የርቀት ትምህርት አሰጣጥ መንገዶችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎችን በሰርተፊኬት እና በዲፕሎማ ለማስመረቅ መዘጋጀቱ ጣቢያው ይዞት የመጣውን አዲስ አቀራረብ በእጅጉ ያጎላዋል።

ነሲሓ ቲቪ ከመሰረታዊ እና ከአስተማማኝ ምንጮች የተቀዳ ኢስላማዊ እውቀትን በዘመናዊና ቀለል ባለ መንገድ በየቤቱ ተደራሽ ማድረግ ራዕዩ ነው። የቴሌቭዥን ጣቢያው ዳዕዋን ትምህርት ተኮር በማድረግ የሙስሊሙን ንቃተ ህሊና ማዳበር እና ቁርአንና ሱናን የህይወት መሰረት በማድረግ ቀደምት ሰለፎች ዘንድ የነበረውን ግንዛቤ ማስተዋወቅ ተቀዳሚ ተልዕኮው አድርጓል። በዚህም ነሲሓ ቲቪ ከቴሌቭዥን ጣቢያነት ባሻገር በየቤቱ የሚገኝ ቋሚ መድረሳ ይሆናል።

ነሲሓ ቲቪ እውቀትን ለመማር ምቹ ሁኔታ የሌላቸውን ሙስሊሞች በያሉበት በመድረስ ኢስላምን ይማሩ ዘንድ ማመቻቸትና ኢልምን ከማስፋፋት አንፃር ታላቅ ሚና መጫወት ይፈልጋል። የሙስሊሙን አመለካከት የሚበክሉ ፅንፈኛ አስተሳሰቦችን በማረቅ የአህሉሱና ወልጀማዓን ሚዛናዊ እይታ ማስተማር፤ የሰለፎችን ቀና ጎዳና በማስተዋወቅ ተግባራዊ አርዓያነታቸውን ማስረፅ ዓላማው አድርጓል።

**መጋቢት 1/2011 በአላህ ፈቃድ ነሲሓ ቲቪ ሙሉ ስርጭት ይጀምራል።**

ነሲሓ ቲቪ ታዳጊዎችና ወጣቶችን በኢልም በመኮትኮት የወደፊት ዱዓቶችን ለማፍራት መሰረት መጣል ይሻል። ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ወሳኝ ሚና ከግንዛቤ በማስገባት ሸሪዓዊ ህይወትን ይመሩ ዘንድ ሊያውቋቸው የሚገቡ ህግጋትን ማብራራት ስራው ያደርጋል።

ነሲሓ ቲቪ ሙስሊሙ በሀገሪቱ ከሚኖሩ ሌሎች ወገኖች ጋር በሰላም እና በመከባበር እንዲሁም ህልውናውን በማያሳጣው የጋራ መተባበር ይኖር ዘንድ የሚረዱ አስተምህሮቶችን ሲያስተላልፍ ሙስሊም ላልሆኑ ወገኖች የኢስላምን ውበት ማሳየትና ስለ ኢስላም ያሏቸውን የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ለማስተካከል ይተጋል።

'ነሲሓ አካዳሚ' በነሲሓ ቲቪ የሚተላለፉ ተከታታይ ትምህርቶች ላይ የተመረኮዘ መርሃ ግብር ሲሆን ትምህርቱ ሁለት አይነት እርከኖች ይኖሩታል:

የመጀመሪያው 'መሰረታዊ የዲን ትምህርት ለሁሉም' በሚል መሪ ቃል የሚያካሂደው ሲሆን ይህ ለጀማሪዎች እንዲስማማ ተደርጎ የተቀረፀ መርሃ ግብር በውስጡ የተፍሲር፣ የሐዲሥ፣ የፊቅህ፣ የተዉሒድ፣ የሲራ፣ የዐረብኛ ቋንቋ እና የተርቢያ ዘርፎችን ያካተተ ይሆናል። ይህ ተማሪዎቹ ትምህርቶቹን ከተከታተሉ የማጠናቀቂያ ፈተና ወስደው ሰርተፊኬት የሚያገኙበት ልዩ የትምህርት መርሐ–ግብር ነው።

ሁለተኛው 'ነሲሓ ተከታታይ የኪታብ ቂራአት' ሲሆን ይህ እርከን የተለያዩ እውቅ ኪታቦችን መማር የሚሹ ተማሪዎችን (ጠለበተል ዒልም) ን ታሳቢ ያደረገ ነው። በተለያየ ግዜ የሚተላለፉ የኪታብ ቂራአት ፕሮግራሞች ሲጠናቀቁ፤ ማንኛውም ተማሪ በአካዳሚው ለዚህ ትምህርት የሚሰጠውን ፈተና በመውሰድ በተማረው ኪታብ ላይ የተገደበ የተሳትፎ የምስክር ወረቀት ያገኛል። እንዲሁም የተለያዩ ኪታቦችን በርቀት በመማር ነጥቦችን በማሰባሰብ የነሲሓ አካዳሚን የዲፕሎማ መስፈርት ሲያሟላ የዲፕሎማ ሰርተፊኬት ፈተናዎችን በመውሰድ እንደውጤቱ የዲፕሎማ ሰርቲፊኬት ያገኛል።
መጋቢት 1/2011 በአላህ ፈቃድ ነሲሓ ቲቪ ሙሉ ስርጭት ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል።

ይህ እንግዲህ በጎግል ግሩፕ የተነሳው የነሲሓ የዳዕዋ ትግል ዛሬ ላይ የደረሰበት አበርክቶት ነው። አላህ ፅናቱን ሰጥቷቸው እንደስማቸው ነሲሓን ለህዝበ ሙስሊሙ የሚያዳርሱ እንዲሆኑ እንመኛለን። በዳዕዋዎቻቸውም ሙስሊሙን ብቻ ሳይሆን ሙስሊም ያልሆነውንም ጭምር ወደ ኢስላም የሚጠሩና የድካማቸውንም ፍሬ አላህ በዱኒያም ሆነ በአኼራም እንዲያሳያቸው እንለምናለን።
አሚን!

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

## መልዕክቶቻችሁ

**ቅድሚያ ከነፍስያህ ጋር ተዋወቅ !!**

ታዋቂ ለመሆን የምትሰራው ስራ ዲንህን እየናደብህ እንደሆነ ምን ያክል ቆም ብለህ አሰበሀል??

የራስህ አድናቂም አትሁን ! !

ስለ ፊትና በርካታ አሀዲሶችን የዘገቡት ታላቁ ሶሀቢይ ሁዘይፋህ ኢብኑል የማን ረዲየሏሁ ዓንሁ አንድ ቀን ሰዎችን ኢማም ሆነው ካሰገዱዋቸው በኋላ እንዲህ አሉ " *ከዚህ በኋላ ለየብቻ ስገዱ ወይንም ሌላ ኢማም ፈልጉ ። እኔ በማሰግድበት ጊዜ ከናንተ ሁሉ የተሻልኩ መስሎ ታይቶኛልና* " ብለው ነበር። (ሸርሀ ዑምደቱል ፊቅህ 1/138-139)

Aman Ibrahim Abu muhammed

ውድ የነሲሓ መፅሄት አዘጋጆች አላህ መልካሙን ይመንዳቹህ እጅግ አስደስታቹሀናል ስራቹሁን ቀደም ባሉ ጊዜያትም ተመልክተን ረክተንባቹዋል ጀዛኩሙሏህ። ፍፁማዊነት ከማንም አይጠበቅምና በተቻለ መጠን ክፍተቶችን ለማጥበብ ጣሩ አሏህ ከናንተ ጋር ይሁን።

Abduselam Jemal

ውድ የነሲሓ ቲቪና መፅሔት መጀመር በሀገሪቱ ኢስላማዊ ዕውቀት እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ ። በተለይ በአሁኑ ወቅት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ለተዘፈቀባቸው ዲናዊ ችግሮች ዋነኛው መንስኤ የእውቀት ማነስ መሆኑ ልብ ይሏል።.....አላህ ቀጥተኛውን መንገድ ይምራን! አሚን ።

Abduselam Mahmud

# ነሲሓ

## አበይት

- የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ የለውጥ ጉዞ ተግዳሮቶች እና መፍትሄዎች
- የሰላም ዋጋ
- መንፈሳዊ ጉዞ በሸሪዓ እይታ
- የመጽሐፍ ዳሰሳ





# የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ የለውጥ ጉዞ ተግዳሮቶች እና መፍትሄዎች

ሙስሊሞች ወንድማማቾች እንደ መሆናቸው በጋራ አጀንዳዎች ላይ ምክክር።በማድረግ በትብብር መስራት፣ ልዩነታቸውን በቁርአን እና በሐዲሥ ዳኝነት መፍታት፣ ስህተታቸውን በሚዛናዊነትና በመቆርቆር ስሜት መተራረም፣ ሲያስፈልግም ግሳጼን መለዋወጥ መለያ ባህሪያቸው ነው።

﴿ وَالمُؤمِنونَ وَالمُؤمِناتُ بَعضُهُم أَولِياءُ بَعضٍ يَأمُرونَ بِالمَعروفِ وَيَنهَونَ عَنِ المُنكَرِ وَيُقيمونَ الصَّلاةَ وَيُؤتونَ الزَّكاةَ وَيُطيعونَ اللَّهَ وَرَسولَهُ أُولٰئِكَ سَيَرحَمُهُمُ اللَّهُ إِنَّ اللَّهَ عَزيزٌ حَكيمٌ ﴾

*{ምእመናን እና ምእመናትም ከፊሎቻቸው ለከፊሎቹ ረዳቶች ናቸው። በበጎ ነገር ያዛሉ፤ከክፉም ይከለክላሉ፤ ሶላትንም አዘውትረው ይሰግዳሉ፤ ዘካንም ይሰጣሉ፤ አላህን እና መልዕክተኛውንም ይታዛዛሉ። እነዚያን አላህ በእርግጥ።ያዝንላቸዋል፤ አላህ አሸናፊው ጥበበኛው ነውና} [አት-ተውባህ 71]*

ሙስሊሞች የአላህን ዲን በመተግበር ለሚቀጥለው ትውልድ በንጹህነቱ ለማስተላለፍ ይጥራሉ።በዚህ ረገድ ታላቅ አደራ የተጣለባቸውና የመሪነቱንም መዘውር የጨበጡት የነብያት ወራሾች የሆኑት ዑለማዎች መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡

ባለፉት ክፍለ ዘመናት የሀገራችን ሙስሊም ተደራራቢ ጫናዎችን በመቋቋም ዲኑን ጠብቆ ለዚህ መድረሱ የሚታወቅ ነው። ኢስላም ተጠብቆ ለዚህ ትውልድ ይደርስ ዘንድ ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት የሙስሊሙ መሪዎች እና ዑለማዎች መሆናቸውም አያጠያይቅም። አላህ ለዋሉት ውለታ ሁሉ መልካምን ይመነዳቸው ዘንድ እንለምነዋለን።

ሆኖም በዚህ ሂደት ከአፄዎቹ ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ጫናዎች ምክንያት ዳዕዋው ብዙ ተግዳሮት እና ውጣውረዶችን አሳልፏል። በቅርብ ከተከሰቱት ጭቆናዎች መካከል ላለፉት ሰባት አመታት በሙስሊሙ ላይ ተጋርጦ የቆየው ችግር ቀዳሚ ተጠቃሽ ነው። ሰፊው ሙስሊም ህብረተሰብ ይህንን ታላቅ በደል ባለመቀበሉ ለተለያዩ እንግልቶች ቢዳረግም፤ አላህይህንን ግፍ በስተመጨረሻ ማብቂያ አድርጎለታል፤ አል-ሐምዱሊላህ!

ሆኖም ሀይማኖታዊ ተቋማችንን የሚመለከተው ለውጥ በሂደት የሚፈጸም በመሆኑ የተለያዩ መሰናክሎችን እያስተናገደ ይገኛል። የተቋማዊ ለውጥ ኮሚቴው ጥረት ሲጀመር አሁን ያለው መጅሊስ የእርምት እርምጃዎች እንዲወስድ እና በስሩ ባሉ መስጅዶች እና ተቋማትም አካታች አገልግሎት እንዲሰጥ የመስራት ግዴታ እንዳለበት ማሳሰብ እና ተግባራዊነቱንም መከታተል ከኮሚቴው የምንጠብቀው ተግባር ነበር። የህዝቡን እሮሮ በመስማት መደበኛው የሙስሊሞች የዳዕዋና የማስተማር እንቅስቃሴ ወደ ነበረበት እንዲመጣ፤ የተባረሩ ኢማሞች እና ኡስታዞችም ወደ ቀድሞ ቦታቸው እንዲመለሱ፤ ከመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ አንስቶ እስከ ፌደራል ጠ/ም/ቤቱ ያሉት አካላት ገንቢ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ በማስተባበር ረገድ ኮሚቴው የሚጠበቅበትን ሀላፊነት መወጣት ነበረበት።

ይሁንና የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ እነኝህ ስራዎች የሚጠበቁበት ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ወደ መሬት የወረደ ስራ መከወን ተስኖታል። ኮሚቴው የስብጥር እና ሚዛናዊነት ችግሩ የሚጠበቅበትን እንዳያደርግ እንቅፋት የሆነበት ቢሆንም ይህን ተከትሎ የመጣው አለመግባባት እና የእርስ በርስ ሽኩቻ ስራዎች በተገቢው ፍጥነት እንዳይሄዱ አድርጓል።

**ሙስሊሞች የአላህን ዲን በመተግበር ለሚቀጥለው ትውልድ በንጹህነቱ ለማስተላለፍ ይጥራሉ። በዚህ ረገድ ታላቅ አደራ የተጣለባቸውና የመሪነቱንም መዘውር የጨበጡት የነብያት ወራሾች የሆኑት ዑለማዎች መሆናቸው ግልፅ ነው።**

ኮሚቴው በረቂቅ ሰነድ ደረጃ የህግ እና የመጅሊስ መዋቅር ስራዎችን ቢያጠናቅቅም የዑለሞች መግባቢያ ስምምነት ሰነድ ላይ ግን ስራውን የሚያስተጓጉል እንቅፋት ገጥሞታል።

እንቅፋት የሆነው ሀሳብ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ የሚያዘጋጀው የዑለሞች መስማሚያ ሰነድ ለሀገራችን ሙስሊም የእምነት ነክ ጉዳዮች የአሽዓሪያና ማቱሪዲያ ዓቂዳ ገዥ መዝሀብ ማድረግ አለበት መባሉ ነው። በተጨማሪም ሱፊያ እና ጡሩቆቹ እሱን ተከትለው የመጡም ቢድዓዎች ተቃውሞ እንዳይደርስባቸው ተቋማዊ ማዕቀፍ ኖሯቸው በሰነዱ ውስጥ ይካተቱልን የሚል ሙግት መነሳቱ ነው።

በእነዚህ አካላት ግፊት የሚደረግበት ሀሳብ መላውን ሙስሊም የማያስማማ፣ ለአንድ ወገን የሚያደላ፣ የሙስሊሙን አንድነት የሚሸረሽር፣ እንደቀደመው ግዜ ሙስሊሙን ከራሱ ተቋም (መጅሊስ) እና ከሚያስተዳድራቸው መሳጅዶችና መድረሳዎች በወሀብያ ተለጣፊ ስም ሰዎችን ለማባረር የሚያመች፣ መጅሊስን ከነብልሹ አሰራሩ እንዲቀጥል የሚያደርግ፣ በሱፍያ ስም የሙስሊሙን ገንዘብ እንዲበዘብዙ የሚፈቅድ በአጠቃላይ በተጠናከረ እና ህጋዊ በሆነ መልኩ የሙስሊሙን ግፍና ጭቆና የሚያስቀጥል ሀሳብ ነው። ከምንም በላይ የተነሳው ሙግት ከሸሪዓ የሚጣረስ ግልፅ ስህተት በመሆኑ ይህንን ለማረምና የተቋማዊ ለውጡ ኮሚቴ ስራ የተጓተተባቸውን እነዚህን ነጥቦች እየለየን እናያለን።

## 1. አሽዓሪያና ማቱሪዲያ እንደ ገዥ ዓቂዳ እንዴት?

በዑለሞች መግባቢያ ሰነድ ላይ እንዲካተት የቀረበው የመጀመሪያው አግላይ መስፈርት የአሽዓሪያና የማቱሪዲያ ዐቂዳ በእምነት አረዳድ ፈለግነት በሰነዱ ውስጥ ይካተት የሚለው ሙግት ነው። ይህ ግፊት ከሸሪዓ አንጻር ተቀባይነት እንደሌለው የሚያሳዩ የተለያዩ ነጥቦችን እንመልከት ...

➢ በቅድሚያ ይህ ሰነድ በብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መካከል በዐቂዳ እና በሌሎች ወሳኝ ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ልዩነቶችን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ የመሰረት ድንጋይ የሚያኖር እንደመሆኑ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ የሚያግዙ ጥቅል ነጥቦችን ያዘለ መነሻ እንጂ ዝርዝር ርዕሶች የሚዳሰሱበት የውይይት መቋጫ አይደለም፤ መሆንም አይችልም! ባለንበት ሂደት ላይ ዝርዝር የውዝግብ አጀንዳዎች (ከዚህ ሰነድ ጋር በተያያዘ ለውይይት እንዲቀርቡ መፈቀዳቸው ተአማኒነትን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል።

➢ የተለያዩ ወገኖች በሚሳተፉበት የስምምነት ሰነድ ላይ የአንድን ቡድን የአስተሳሰብ መስመር የትክክለኝነት ሚዛን አድርጎ መሰየም የተገኘውን ታሪካዊ እድል የሚያጨልምና የአንድነት ውይይቱን የሚያጨናግፍ የአካሄድ ስህተት ነው፤ ትብብርንና የጋራ መግባባትን መሰረት ባደረገ የመነሻ ሰነድ ላይ አንድ ወገን ገና ከጅምሩ የራሱን መደምደሚያ በሌሎች ላይ የሚጭን ከሆነ የሌላኛው ወገን ተሳትፎ ትርጉም ያጣል። ሌላው አካል የሚተማመንባቸውና እንደ አርኣያ የሚወስዳቸው እጅግ ብዙ ዓሊሞች ከመኖራቸው ጋር የአንዳቸውም አስተምህሮ ወይም መፅሀፍ በመመዘኛነት እንዲጠቀስ አልጠየቀም።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሮል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

➢ አላህ በቁርአኑ በሙስሊሞች መካከል የሚነሱ ውዝግቦችን ወደ አላህ እና ወደ መልእክተኛው እንጂ ፍፁምነት ወዳልተሰጣቸው ግለሰቦችና መዝሃቦች እንድንመልስ አላዘዘንም ...

﴿يا أَيُّهَا الَّذين َآمَنوا أَطيعُوا اللَّهَ وَأَطيعُوا الرَّسول َوَأُولِي الأَمرِ مِنكُم فَإِن تَنازَعتُم في شَيءٍ فَرُدّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسولِ إِن كُنتُم تُؤمِنونَ بِاللَّهِ وَاليَومِ الآخِرِ ذلِكَ خَيرٌ وَأَحسَن ُتَأويلًا﴾

*{በምንም ነገር ብትወዛገቡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው መልሱት፤ ይህ የተሻለና መመለሻው (ውጤቱ) ይበልጥ መልካም የሆነ ነው።} [አን-ኒሳእ 59]*

ውዝግብን ወደ አላህ መመለስ ማለት ወደ ቁርአን መመለስ እንደሆነ፤ ወደ መልዕክተኛው መመለስ ከርሳቸው ህልፈት በኋላ የሚተገበረው ደግሞ ወደ ሱናቸው በመመለስ እንደሆነ የታወቀ ነው። [በተፍሲር አጥ-ጠበሪ የሰፈሩትን ጥቅሶች ይመልከቱ] ስለሆነም ሀይማኖታዊ ውዝግቦች ሁሉ በአላህና በመልዕክተኛው ቃል ዳኝነት ሊቋጩ ይገባል። በእንዲህ አይነት ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ውዝግቦችን ሊፈታ የሚችለው ብቸኛው ፍርድ ከበላይ የሚመጣ አምላካዊ ብይን ብቻ ነውና!

• እውነታውን ካየን ትክክለኛው ዐቂዳ ባልተወሳሰበ ስልት በቁርአንና በሐዲሥ ላይ ሰፍሯል ... አል-ሙዘኒይ (264 ዓ.ሂ) ከአል-ኢማም አሽ-ሻፊዒ (204 ዓ.ሂ) አጣቅሰው እንዳስተላለፉት አል-ኢማም ማሊክ (179 ዓ.ሂ) በተውሂድ ላይ ስለሚነሳ «ከላም» ተጠይቀው እንዲህ አሉ ...

***«መልዕክተኛው ሕዝባቸውን ስለ መፀዳዳት ስርዓት አስተምረው ስለ 'ተውሒድ' አላስተማሩም ብሎ መገመት ዘበት ነው!..» ["ዘም-ሙ'ል-ከላም ወአህሊሂ" /አል-ሀረዊ (4/282-283) ቁጥር 1128፣ "አሓዲሥ ፊ ዘም-ሚ'ል-ከላሚ ወአህሊሂ" /አቡ'ል-ፈድል አል-ሙቅሪእ/ ገፅ 92]***

በቁርአንና በሐዲሥ ማስረጃዎች አተረጓጎም ላይ አለመግባባት በሚኖርበት ሁኔታ ደግሞ ከላይ እንደተጠቀሰው በዑለማዎች ስምምነት የፀደቁ የመረጃ አቀራረብ ስልቶችን መጠቀም ተገቢ ይሆናል። ይህን የመረጃ አቀራረብ ስልት አንዳንዶች ለምን እንደማይቀበሉት ወደ ኋላ እንመለስበታለን።

➢ በዚህ ሰነድ ላይ ይጠቀስ እየተባለ ግፊት የሚደረግበት የአሽዓሪያና ማቱሪዲያ ዓቂዳ ከጊዜ በኋላ የመጣ አስተሳሰብ እንጂ በቀደመው ትውልድ (ሰለፎች) ዘንድ የሚታወቅ አልነበረም። የአሽዓሪያ ዓቂዳ መስራች ተደርገው የሚታዩት አቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ በአመዛኙ የባለታሪኮች አባባል መሰረት የተወለዱት በ260 ዓ.ሂ ነው። የማቱሪዲያው መስራች አቡ-መንሱር ሙሐመድ አል-ማቱሪዲም ቢሆን የሞቱት በ333 ዓ.ሂ ነበር። እነኚህ ሰዎች ከዚያ በፊት የማይታወቅ አዲስ የእምነት ግንዛቤ ይዘው መጥተው እንደሆነ በፊት ያልነበረ ፈሊጥ ሁሉ ሊወገዝ እንጂ ሊወደስ አይገባም፤ ቀድሞ የነበረውን ፋና የሚከተሉ ከነበሩ ደግሞ አዲስ ነገር አላመጡምና ከእነርሱ በፊት የነበረውን የሶሓቦች፣ የታቢዒዮችና የአትባዕ አት'ታቢዒን ምርጥ ትውልዶችን ፋና እንደምንከተል መግለጽ በቂ ነው፤ ውዝግብ የሚፈታበት አይነተኛ መንገድ ከውዝግቡ በፊት ወደ ነበረው የስምምነት አቋም መመለስ ነውና።

አሽዐሪይ-ያዎችና ማቱሪዲያዎች የአላህ ባህሪያትን አስመልክቶ ያመጡት አዲስ ፈሊጥ በአበው ትውልዶች (ሰለፍ) በአንድ ድምፅ በተወገዙት ጭፍራዎች (በጀህሚያዎችና ሙዕተዚላዎች) አካሄድ ተፅእኖ ስር ያደረ ነበር። የዚህን ታሪካዊ ሂደት በአጭሩ ለመዳሰስ የሚከተከለውን እናያለን ...

ስለፈጣሪ ማንነትና ስለርሱ መብቶች ሊያስተምሩ የተላኩት የአላህ መልዕተኛ ﷺ ከማንኛውም ሰው የበለጠ ስለጌታቸው ማንነት የሚያውቁና ቁርአንን በንግግራቸውና በተግባራቸው አብራርተው የሚገልፁ፣ እንዲሁም ለህዝበ-ሙስሊሙ የሚቆረቆሩ ቅን ነበሩ። ይህ ከመሆኑ ጋር ኢስላምን ለመማር አዋቂውም አላዋቂውም፣ ከተሜውም አገሬውም፣ ትልቁም ትንሹም ሁሉም ከተለያየ የግንዛቤ ደረጃቸው ጋር ወደርሳቸው ሲመጡ አንዱን ከሌላው ሳይለዩ የአላህን ባህሪያት ያዘሉትን ቁርአናዊ አንቀፆችና ነብያዊ አስተምህሮቶች ያለ "ማስጠንቀቂያ" በገሀድ ያስተላልፉ ነበር። ግልፅ መልዕክቶቻቸው የተፈለጉ ባይሆን ኖሮ የግድ የ"ተእዊል" ማብራሪያዎችን በማከል ተከታዮቻቸውን ከውዥንብር ያድኑ ነበር!

**ቀድሞውኑ ከመላው ህዝበ ሙስሊም አካሄድ ያፈነገጡት ሙዕተዚላዎች ብዙም ሳይቆዩ በዚህ ጥሪ ተማረኩ።**

ሶሓቦችም የቁርአንን ቋንቋ ከሌሎች በተሻለ መልኩ የሚረዱ ከመሆናቸው ጋር በቁርአን ስለሰፈሩት የአላህ ስሞችና መገለጫዎች አንድም ጥራዝ ነጠቅ ጥያቄ ወይም የተለየ ማብራሪያ ሳያነሱ ትውልዳቸው ተገባደደ። ሆኖም ወደሚቀጥሉት ትውልዶች በጥራት እየተላለፈ የነበረውን የእምነት አደራ የሚያደፈርሱ አዳዲስ ፈሊጦች ገና ከረፋዱ ማጎጥጎጥ ቢጀምሩም የከፋው ዱብዳ የተከሰተው ግን በሁለተኛው ምዕተ-አመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ነበር። በተለያዩ የግሪክና የሮማን ሚዛን-የለሽ ፍልስፍናዎች የታነፁ ግለሰቦች አላህ በቁርአኑ፣ መልዕክተኛው ደግሞ በአስተምህሮቶቻቸው ያፀደቋቸውን የጌታችንን ስሞችና ባህሪያት በመላው ህዝበ ሙስሊም ዘንድ ባልተለመዱ ፈሊጦች ማስተባበልና ትርጉማቸውን ማዛባት ጀመሩ። በዚህም ሂደት የፈጣሪን ህልውና ትርጉም በሚያሳጡ ንግግሮች መዘላበድ ቀጠሉ።

በኢስላም ታሪክ ውስጥ የዚህን እንግዳ ፈሊጥ የመሰረት ድንጋይ በማኖሩ የሚታወቀው ግለሰብ አል-ጀዕድ ኢብኑ ዲርሀም ተብሎ ይጠራል። አንዳንድ ሊቃውንትና የታሪክ ዘጋቢዎች እንደሚያስገነዝቡት ግለሰቡ የጥመቱን ፅንሰ-ሀሳብ የወሰደው ከአባን ኢብኑ ሰምዓን ሲሆን እርሱ ደግሞ 'ጣሉት' ከተባለ የለቢድ ኢብኑ'ል-አዕሰም እህት ልጅ ነው የተማረው፤ ጣሉት ደግሞ ከአጎቱ ለቢድ! ለቢድ ኢብኑ'ል-አዕሰም እንደሚታወቀው በመልዕክተኛው ላይ ድግምት የተበተበው አይሁዳዊ ግለሰብ ነው!

*[ኢብኑ ዐሳኪር - "ታሪኹ ዲመሽቅ" (72/99-100)፣ ኢብኑ'ል-አሢር - "አል-ካሚል ፊ'ት-ታሪኽ" (6/149)፣ ኢብኑ ከሢር - "አል-ቢዳያህ ወ'ን-ኒሃያህ" (13/147) ..እና ሌሎች መዛግብትን ይመልከቱ]*

ይህንን ጥመት ከርሱ ወርሶ ከሌሎች ፈሊጦች ጋር በመቀየጥ በተባው ልሳኑ ወደ ሕዝበ-ሙስሊሙ መርዙን የረጨው ጋሻ ጃግሬው አል-ጀህም ኢብኑ ሰፍዋን (128 ዓ.ሂ) ነበር። እርሱ ለአላህ ምንም አይነት ስምና ባህሪይ ማፅደቅ እርሱን ከፍጡር ጋር ማመሳሰል እንደሆነ ሰበከ። ቀድሞውኑ ከመላው ህዝበ ሙስሊም አካሄድ ያፈነገጡት ሙዕተዚላዎች ብዙም ሳይቆዩ በዚህ ጥሪ ተማረኩ።

በዚህም የተነሳ በሙሉም ይሁን በከፊል የአላህን ስሞችና ባህሪያት ቀጥተኛ መልዕክት ላለመቀበል ትርጉማቸውን የሚያዛቡ ሁሉ ሰለፎች ዘንድ "ጀህሚይ-ያህ" جهمية በሚል መጠሪያ ስር ይካተቱ ነበር። ይኸኛውን የቢድዓ ጎዳና ከሌሎቹ የከፋ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ሁለት ነገሮች ይጠቀሳሉ ... አንደኛው ጉዳዩ በቀጥታ ከጌታ ማንነትና ህልውና ጋር የተያያዘ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የዚህኛው ቢድዓ አራማጆች የቁርአንና የሐዲሥ አስተምህሮትን በተለያዩ ተፃራሪ «ፍልስፍናዊ» ፈሊጦች በድፍረት መጋፈጣቸው ነው! ከነሱ በፊት የነበሩት የቢድዓ አራማጆች የቁርአንና የሐዲሥን ትክክለኛ መልዕክት በማዛባት፣ በመጨመርና በመቀነስ አዳዲስ የጥመት ጎዳናዎችን ቢደለድሉም እንደነኚህ መለኮታዊ መመሪያዎችን ከመሰረቱ ገሽሽ በማድረግ ለቁንፅል አእምሯዊ ፈሊጦቻቸው ቅድሚያ ለመስጠት አልዳዱም ነበር!

ሁኔታውን በጣም ያባባሰው ደግሞ በ"መእሙን" የኸሊፋነት ዘመን (198 - 218 ዓ.ሂ) የተከፈተው በር ነበር! የተለያዩ የግሪክና የህንድ ቀደምት ፈላስፋዎች መለኮታዊ የእምነት ጉዳዮችን ጨምሮ በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ የፃፏቸውን ድርሳናት ከቤዛንታይን ግዛቶች (በተለይ ከቆጵሮስ) በማስላክ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ እንዲተረጎሙ አደረገ! ይህ ደግሞ ለግድፈቶቹ ዋነኛ መንስኤ የሆነው "ዒልሙ'ል-ከላም" እንዲስፋፋ ትልቅ እገዛ አደረገ።

በዚህ ላይ ኸሊፋው አዲሱን ፈሊጣዊ እምነት በህዝበ-ሙስሊሙ ላይ በስልጣኑ ሃይል ለመጫን ትዕዛዙን በሁሉም ግዛቶች በተዋረድ አስተላለፈ! ከርሱ በኋላ የተተኩት ሁለት ኸሊፋዎችም በደመነፍስ ዱካውን ተከተሉ! በነዚህ ጊዜያት የተወሰኑ ዑለማዎች ተገድለዋል፤ ብዙዎች ተሰድደዋል፤ ተገርፈዋል፤ አል ኢማም አሕመድ የደረሰባቸው አሰቃቂ ግርፋትና እስር አንድ ናሙና ነው።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . . .

ይህ የጀህሚያዎች አባዜ እያደር ወደ ሌሎች በሚዛመትበት ጊዜ ከነርሱ ጋር ሙግት የገጠሙ አንዳንድ የሱና ግለሰቦች የተወሰኑ ፍልስፍናዊ መንደርደሪያዎችን አምነው በመቀበላቸው በአንዳንድ አጀንዳዎች ላይ በጀህሚያዎችና በሰለፎች መሃል ለመስፈር ተገደዱ። አብዛኛዎቹን የአላህ ባህሪያት ተቀብለው አድራጎታዊ መገለጫዎችን ብቻ ነጥለው አስቀሩ። ከነዚህም መካከል "ኢብኑ ኩል-ላብ" በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። አልኢማም አሕመድ በኢብኑ ኩል-ላብና በተከታዮቹ ላይ ጠንከር ያለ ውግዘትን ይሰነዝሩ እንደነበር ይታወቃል።

ታዲያ እነዚህ አንጃዎች ቅርፃቸውን ከያዙ በኋላ የተወለዱት የአሽዓሪያ መስራች አቡ'ል-ሐሰን አልአሽዓሪ ከልጅነታቸው ጀምሮ በእንጀራ አባታቸው አቡ-ዓሊ አልጀባኢ አማካኝነት በተወገዘው የሙዕተዚላ ፍልስፍናዊ አቋም ላይ ታንፀው ያደጉ ኋላም እስከ አርባ አመታቸው በዚሁ አቋም ላይ የዘለቁ ናቸው። ከዚያም በአዕምሯቸው ለተፈጠሩ ጥያቄዎች ምላሽ በማጣታቸው የመዕተዚላን አቋም ትተው የኩል-ላቢያዎችን አቋም ከቃላት ማስተካከያ ጋር ሲያራምዱ ቆይተዋል። በስተመጨረሻ የአል-ኢማም አሕመድ እና መሰል የሱና ኢማሞች መንገድ ላይ መሆናቸውን አሳውቀው በ324 ዓ.ሂ አርፈዋል፤ ለዚህም እማኝ ከሚሆኑ ድርሳናቸው መካከል “አል-ኢባናህ ዐን ኡሱሊ'ድ-ዲያናህ”፣ “መቃላቱ'ል-ኢስላሚይ-ዩን ወ'ኽቲላፉ'ል-ሙሶል-ሊን”፤ “ሪሳላህ ኢላ አህሊ'ሥ-ሠኻር” እና ሌሎች መፅሀፎች ይገኛሉ። በሌላ በኩል የማቱሪዲያው ዓቂዳ መስራች አቡ-መንሱር ሙሐመድ ቢን መህሙድ አልማቱሪዲ አሰመርቀንዲ የተወለዱበት አመት በትክክል ባይታወቅም የሞቱት ግን በ333 ዓ.ሂ ነበር። ይህ ማለት ከአቡል ሐሰን አልአሽዓሪ ጋር ተቀራራቢ በሆነ ዘመን የኖሩ እና ከላይ ያሳለፍናቸው ክስተቶች ካለፉ በኋላ የመጡ ሰው ናቸው።

ታዲያ በነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ላይ በወረደ ወሕይ እና ሶሐቦቻቸው በተረዱት ግንዛቤ ተደላድሎ የተቀመጠውን ግልፅ ኢስላማዊ እምነት ይህ ሁሉ ታሪክ ካለፈ በኋላ በመጡ ሰዎች ያውም ኋላ ላይ የተውት በሆነ አካሄድ ለመረዳት መሞከርና ለሙስሊሞች መመሪያ እንዲሆን ማሰብ እንዴት ከጤነኛ ሰው ይጠበቃል?

➢ አቡ'ል ሐሰን አል-አሽዐሪይ ለአርባ አመታት ከቆዩበት የሙዕተዚላዎች እምነት የወጡ ግዜ በኢብኑ ኩልላብ ስልት የተመሰጡት የኢብኑ ኩልላብ ተከታዮች ራሳቸውን በአህሉሱንና ስያሜ ከመጥራታቸው ባሻገር ለጀህሚያዎችና ለሙዕተዚላዎች ጥመት እርሳቸው በለመዱት ፍልስፍናዊ ሙግት መልስ የሚሰጡ በመሆናቸው ነበር። በስተመጨረሻ ወደ ትክክለኛው የሰለፎች አቋም ጠቅልለው ከመመለሳቸው በፊት በኢብኑ ኩልላብ የዐቂዳ መስመር ላይ በአብዛኛው በቃላት ላይ የተገደቡ ማስተካከያዎችን አክለው የከሸኑት መዝሃብ ከርሳቸው መመለስ በኋላም በስማቸው የሚጠራ ሆኖ ተሰራጭቷል። የዚህ አካሄድ ተከታዮች የሙዕተዚላዎችን ስህተት የሚያጋልጡ በርካታ ምላሾችን በመፃፋቸውና፤ ከዘመናት በኋላም አንዳንድ መሪዎችና ባለስልጣናት መልዕክታቸውን በማራመዳቸው ስርጭቱ አይሏል።

ሆኖም የአሽዓሪዮችን የዘመናት የእምነት ጉዞ ያስተዋለ ቡድኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጀመሪያውን ፈር እየለቀቀና ይበልጥ በፍልስፍና ውስጥ እየሰመጠ እንደሄደ ማስተዋል ይችላል! ይህም ማለት ኢብኑ ኩልላብና አል-አሽዐሪይ ኋላ ላይ ከመጡት ከነአል-ባቂላኒ በተሻለ መልኩ ለሰለፎች አካሄድ ቅርብ ነበሩ። እንደ አልባቂላኒ እና ኢብኑ ፉረክ ያሉት የቀድሞዎቹ የአሽዓሪያ መሪዎች የሚያፀድቋቸውን በርካታ ባህሪያት ደግሞ ከነርሱ በኋላ የመጡት እንደ አልጁወይኒይ እና አር-ራዚ ያሉት በማስተባበል ከሙዕተዚላዎች አቋም ጋር እጅግ የሚቀራረብ አካሄድ መስርተዋል! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአሽዐሪይ-ያህ ቡድን በቁርአንና በሐዲሥ ከፀደቁት የአላህ ባህሪያት መካከል ሰባቱን ብቻ በመቀበል ላይ ተወስነዋል! (እነሱንም በተገቢው መልኩ ባፀደቁ!!)

**በነዚህ ጊዜያት የተወሰኑ ዑለማዎች ተገድለዋል፤ ብዙዎች ተሰድደዋል፤ ተገርፈዋል፤ አል ኢማም አሕመድ የደረሰባቸው አሰቃቂ ግርፋትና እስር አንድ ናሙና ነው።**

ከዚህም ባሻገር በኢማን ላይ ያላቸው የ'ኢርጃእ' አቋም፣ በቀደር ላይ ያላቸው የ'ጀበሪያ' አቋም እና በሌሎች በርካታ የእምነት አጀንዳዎች ላይም በጀህሚይ-ያዎች ተፅዕኖ ስር በማደራቸው ከትክክለኛው ነብያዊ ፋና በጣም ርቀዋል! ሌላው ቀርቶ የቁርአንና የሐዲሥ መረጃዎችን ቀጥተኛ መልዕክት የሚያዛቡባቸው ስልቶችና የሚሰጧቸው ትርጓሜዎች ሰለፎች በአንድ ድምፅ ካወገዟቸው ከጥንቶቹ ጀህሚያዎችና ሙዕተዚላዎች በቀጥታ የተኮረጁ እንደሆኑ ለማወቅ ብዙ መልፋት አይጠበቅም፡ ለምሳሌ፡-

•“አላህ ያለ ቦታ ነው ያለው!” የሚለው የአሻዒራህ መፈክር ከአንዳንድ ሙዕተዚላዎች በቀጥታ የተወረሰ መሆኑን ለማረጋገጥ “መቃላቱ'ል-ኢስላሚይ-ዩን” የተሰኘውን አቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ ከኢብኑ-ኪላብ መንገድ ከተመለሱ በኋላ በከተቡት መፅሐፍ ጥራዝ 1 ገፅ 237 ይመልከቱ፤ ሙዕተዚላዎች ስለቦታ ያላቸውን ውዝግብ በገለፁበት አጋጣሚ እንዲህ ይላሉ፡-

«የተወሰኑ ተናጋሪዎችም፡- "አላህ ያለቦታ ነው ያለው፤ ይልቁንም (ዝንተ አለሙን) ከነበረበት ሳይወገድ ነው ያለው!" አሉ፤ ይህም የሂሻም አልፉወጢ፣ የዐባድ ኢብኑ ሱለይማን፣ የአቡ ዙፈርና የሌሎች ሙዕተዚላዎች አቋም ነው።»

• ከዚያም ቀጥለው (በዚያው ገፅ ላይ) እንዲህ አሉ፡- «ሙዕተዚላዎች "አርረሕማኑ ዐለ'ል ዐርሺ'ስተዋ" ስለሚለው የአላህ ቃል "ተቆጣጠረ ማለት ነው!" አሉ!» ይህ አሽዐሪያዎች የሚያስተጋቡት ትርጓሜ (ኢስተውላ) የመዝሀቡ ቁንጮ የሆኑት አቡልሐሰን ቀድሞ ለአርባ አመታት የቆዩበት የሙዕተዚላዎች አቋም እንደሆነ በግልፅ ተናግረዋል።

• እንዲሁም አንዳንድ (ከአሽዐሪይ-ያዎች በፊት የነበሩ) ቀደምት ሊቃውንት ለጀህሚያዎች ውዥንብር ምላሽ ለመስጠት ያዘጋጇቸውን መፃህፍት ስናስተውል የዛኔው የጀህሚያዎች ጥመት መነሻና የውዥንብር ስልት ከዛሬው የአሽዐሪያህ አካሄድ ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይ መሆኑን በቀላሉ ማየት ይቻላል! ለዚህ ጥሩ ማሳያ ከሚሆኑት ምሳሌዎች አል-ኢማም ዐብዱ'ል-ዐዚዝ አል-ኪናኒ (በ 240 ዓ.ሂ ያረፉ የሻፊዒይ ቅርብ ተማሪ) ያዘጋጁትን "አል ሐይደህ ወሊ'ዕቲዛር" የተሰኘው ፅሑፍ፣ አል-ኢማም ዑሥማን ኢብኑ ሰዒድ አድ-ዳሪሚይ (በ 280 ዓ.ሂ ያረፉ) ... ቢሽር አል-መሪሲ (218 ዓ.ሂ) በተባለው አንድ የጀህሚይ-ያህ አቀንቃኝ ላይ የፃፉት ምላሽና የኢማሞች ኢማም በመባል የሚታወቁት ኢብኑ ኹዘይማህ (በ311 ያረፉ) ያዘጋጁት "ኪታቡ ተውሒድ" የተሰኘው ድርሳን ይጠቀሳሉ !

➢ የኋለኞቹ አሽዐሪያዎች በመረጃ አቀራረብ ሂደት ከብዙሃኑ ሊቃውንትና ሙስሊሞች እምነት ጋር የሚጣረሱ ፈሊጦችን ያራምዳሉ፤ ከነዚህም መካከል፡-

- “አእምሯዊ አስረጀችን ከቁርአን እና ከሐዲስ ማስቀደም ግዴታ ነው”

- -“ቃላዊ መረጃዎች (ቁርኣንና ሐዲሥ) እርግጠኝነትን አያስገኙም!”

- “የቁርኣንና የሐዲሥ ጉልህ መልዕክቶችን በአእምሯዊ ማስረጃዎች ሳይመዝኑ መቀበል ወደ ኩፍር ያደርሳል!” ይህ አቋማቸውን የመሪዎቻቸውን ንግግሮች ዋቢ በማድረግ ስናረጋግጥ የዘመናችን አሻዒራዎች ቁርኣንና ሐዲሥን መሰረት አድርጎ ለመስማማት የሚያቅማሙት ለምንድነው የሚለው እንቆቅልሽ መልስ ያገኛል!

የኋለኞቹ የአሽዐሪያ ተጠሪዎች እምነት ነክ ጉዳዮች ላይ በመረጃ አቀራርብ ረገድ "አእምሯዊ" ሲሉ የሚጠሯቸውን መረጃዎች ከቁርኣንና ከሐዲሥ መልእክት ጋር ማጣጣም ካልቻሉ “አእምሯዊ አስረጀች"ን ማስቀደም ግዴታ እንደሆነ በግልፅ ይናገራሉ! ብሎም ይህንን ፍልስፍና የሁሉም አሻሚ ጉዳዮች መመዘኛ በማድረግ "አጠቃላይ ቀኖና/መርሆ" قانون كلي አድርገው ሰይመውታል። [ለምሳሌ፡- "አሳሱ አት-ተቅዲስ" የተሰኘውን የአል ፈኽሩ አር-ራዚ ድርሰት ከገፅ 172 እንከ 173 ፣ እንዲሁም "አል አርበዒን" የተሰኘውን የርሳቸውን ፅሑፍ ገፅ 115 ይመልከቱ]

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . . .

• ከዚህም አልፎ «የ"ነቅል" ማስረጃዎች (ቁርኣንና ሐዲሥ) እርግጠኝነትን አያስገኙም!» የሚለው አቋም የሙዕተዚላዎችና የአብዛኛዎቹ አሽዐሪይ-ዮች እምነት መሆኑን በግልፅ ከተናዘዙት የአሽዐሪይ-ያህ ታላላቅ አቀንቃኞች መካከል ዐዱዱ'ድ-ዲን አል-ኢይጂ እና አሽ-ሸሪፍ አል-ጁርጃኒይ ይገኛሉ። ["አል-መዋቂፍ" ቅፅ 1 ገፅ 205፣ እንዲሁም "ሸርሑ'ል-መዋቂፍ" (ከሓሺያ ጋር የታተመው) ቅፅ 1 ገፅ 51]

• ይባስ ብሎ አቡበክር ኢብኑ'ል-ዐረቢ አል-ማሊኪይ "ቃኑን አት-ተእዊል" በተሰኘው መፅሀፋቸው እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል፦ «ፈጣሪን አሊያም ከባህሪያቱ የትኛውንም ለማወቅ "ሰምዕ" /ቁርኣንዊና ሐዲሳዊ ማስረጃ/ መንገድ ሊሆን አይችልም..»! ["ቃኑን አት-ተእዊል" ገፅ 462]

• ማቱሪዲያዎችም ከዚህ ብዙ የራቁ አይደሉም፤ የመዝሃቡ መስራች አቡ መንሱር አል-ማቱሪዲ በተፍሲራቸው እንዲህ ብለዋል፦ «{ከመልእተኞች (መምጣት) በኋላ ሰዎች በአላህ ላይ የሚያቀርቡት) አስረጅ እንዳይኖራቸው (አበሳሪና አስጠንቃቂ መልእተኞችን ላክን)} የሚለው የአላህ ቃል "ትክክለኛ አስረጅ" /ሙግት ብቻ ያልሆነ/ የሚለውን መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም ይህ የሚሆነው በ"ሰምዕ" /በቁርኣንዊና ሐዲሳዊ ማስረጃ/ በሚታወቁት ዒባዳዎችና ሸሪዐዊ ህግጋት ላይ ብቻ ነው፤ ዲን ግን በግዴታነት የሚያዘው በ"ዐቅል" / በአእምሯዊ አስረጆች/ በመሆኑ በርሱ ጉዳይ በአላህ ላይ የሚያቀርቡት አስረጅ የላቸውም.... ሆኖም የመልእክተኞች መነሳት ሙግታቸውን ጭራሹኑ ለማስቀረት ነው። ምንም እንኳ መረጃ ባይኖራቸውም» ["ተእዊላቱ አህሊ'ሱን-ናህ" /አቡ መንሱር አል-ማቱሪዲይ/ (3/421)]

• በተመሳሳይ መልኩ የኋለኞቹ አሻዒራዎች ዘንድ እንደ ታላቅ ኢማም የሚቆጠሩት አል-ፈኽሩ አር-ራዚ በሱርቱ ጣሃ ተፍሲር ላይ እንዲህ ይላሉ ... «አላህንና ዲንን ማወቅን ከቁርኣንና ከሱንና እንቀስማለን የሚሉትን "ሐሸዊያዎች" ንግግር ብልሹነት (አንቀጹ) ታመላክታለች»!! [አል-ፈኽሩ አር-ራዚ፤ መፋቲሑል-ገይብ (22/56)]

• ከአሽዐሪይ-ያህ ታላላቅ አራማጆች አንዱ የሆነው አስ-ሰኑሲ (895 ዓ.ሂ) "የክህደት /የኩፍር/ መሠረቶች ስድስት ናቸው.." ብሎ አምስቱን ዘርዝሮ ስድስተኛውን እንዲህ ሲል ገለፀ፦ «በእምነት መሠረቶች ላይ የቁርኣንና የሐዲሥ ጉልህ መልዕክቶችን በአእምሯዊ ማስረጃዎችና በቁርጠኛ ሸሪዓዊ እውነታዎች ሳይመዝኑ እንዳሉ መያዝ..» ["ሸርሑ ኡም-ሚ'ል-በራሂን" ገፅ 81]

• እንደዚሁም አስ-ሷዊ እንዲህ ይላል፦ «...የቁርኣንና የሐዲሥ ጉልህ መልዕክቶችን መያዝ ከኩፍር መሠረቶች ነውና!»!! ["ሓሺየቱ'ስ-ሷዊ ዓላ ተፍሲሪ'ል-ጀላለይን" (3/9)]

ስለሆነም ለቁርኣንና ለሐዲሥ ያለው ምልከታ እንዲህ የወረደን ጭራሽ እስከኩፍር የሚያደርስ መዝሀብ በሰነዱ ወስጥ ከመረጃ ምንጮች መሃል መጥቀስ የህዝበ ሙስሊሙን አደራ መብላትና ታሪክ የማይሽረው ስህተት መፈፀም ይሆናል።

➢ የአሽዐሪያዎች መዝሃብ ዋነኛ አካል የሆነው "ዒልሙ'ል-ከላም" በሰለፎች ስምምነት የተወገዘ ነበር። በዚህ ረገድ የተናገሩም ሆነ በ"ሰነድ" ያሰፈሩ በርካታ መዛግብት ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል፦ "ዘም-ሙ'ል-ከላሚ ወአህሊህ" የተባለውን የአቡ ኢስማዒል አል-ሀረዊ (481 ዓ.ሂ) ባለ አምስት ጥራዝ ጥንቅር ቢመለከቱ መልካም ነው።

ዒልሙ'ል-ከላም" ስለፈጣሪ መኖርና መሰል እምነታዊ ጉዳዮች በፍልስፍናዊ መንገድ የሚያጠና አካሄድ ሲሆን አብዛኛዎቹ መርሆዎቹ ከጥንቶቹ የግሪክ ፈላስፋዎች አስተምህሮት የተቀዱ ናቸው!! የተለያዩ የተሳሳቱ ጭፍራዎች በአላህ ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ በተሳሳተ የእምነት ጎዳና ላይ እንዲያዘግሙ እውነተኛ መነሻ የሆናቸው ይኸው ፍልስፍና ነው! ይዘቱ ቀጥተኛ አእምሯዊ ስልቶች ላይ የተገነባ ቢመስላቸውም እውነታው ግን በውስጡ ከትክክለኛ ግንዛቤ የራቁ መንደርደሪያ ሀሳቦችና ድምዳሜዎች የተሰገሰጉበት ረጅም የሙግት ጎዳና መሆኑ ነው!

**«አንድ ሰው ከ"[ዒልመ'ል] -ከላም" ይልቅ ከሽርክ በስተቀር ባሉት አላህ በከለከላቸው ሁሉም (ሀጢያቶች) ቢፈተን ይሻለዋል! በርግጥ ከ"ከላም" ባለቤቶች ሙስሊም ይናገረዋል ብዬ ያልጠረጠርኩትን ነገር ሰምቻለሁ!»**

ታዲያ ሰለፎች ይህንን መጤ አካሄድ አጥብቀው የኮነኑት አንዳንዶች እንደሚገምቱት በአዳዲስ ፍልስፍናዊ ቃላት የተሞላ ስለሆነ ወይም ይዘቱን ስላልተረዱ አይደለም፤ ከመሠረታዊ የዲን መርሆዎች ጋር ከመጣረስ አልፎ ወደ ክህደትና ጥርጣሬ አዘቅቶች አንሸራቶ ስለሚያስገባ እንጂ! አል-ኢማም አቡ ዩሱፍ (182 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል ... «ዲንን በ"ከላም" የፈለገ ሰው ዚንዲቅ (ከእምነት የወጣ ከሃዲ) ይሆናል..!»[አል-ላለካኢይ "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሲን-ናህ" (1/166)፣ ኢብኑ በጥ-ጣህ "አል– ኢባናህ" (አል-ኪታቡ'ል-አው-ወል) (2/537-538)፣ አቡ ኢስማዒል አል ሀረዊ "ዘም–ሙ'ል-ከላሚ ወአህሊህ" (4/210)] አል-ኢማም ማሊክም ይህንኑ ማለታቸው ተዘግቧል፤

አል-ኢማም አሽ-ሻፊዒይ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ ሰው ከ"[ዒልመ'ል]-ከላም" ይልቅ ከሽርክ በስተቀር ባሉት አላህ በከለከላቸው ሁሉም (ሀጢያቶች) ቢፈተን ይሻለዋል! በርግጥ ከ"ከላም" ባለቤቶች ሙስሊም ይናገረዋል ብዬ ያልጠረጠርኩትን ነገር ሰምቻለሁ!» [ኢብኑ አቢ ሓትም "አዳቡ'ሽ-ሻፊዒይ ወመናቂቡህ" ገፅ 137፣ "ዘም-ሙ'ል-ከላሚ ወአህሊህ" አቡ ኢስማዒል አል-ሀረዊ (4/306-307) ቁጥር 1164፣ አቡ ኑዐይም "ሒልየቱ'ል-አውሊያእ" (9/111-112)፣ አል-በይሀቂይ "መናቂቡ'ሽ-ሻፊዒይ" (1/453-454)..እና ሌሎች መዛግብት ላይ በትክክለኛ ሰነድ ሰፍሯል]

በዚሁ አካሄድ ላይ ዕድሜያቸውን የፈጁ ሙግተኞች ከቀናው ቁርኣናዊ መንገድ ከማፈንገጣቸው ባሻገር መጨረሻቸው ግራ መጋባት፣ መጠራጠርና መቆጨት መሆኑን የአብዛኛዎቹ ታሪክ ይመሰክራል! ቀድሞውኑ በእምነት ጉዳይ ላይ የፈጣሪን ግልፅ መመሪያ ወደኋላ ገሸሽ አድርጎ ኢስላምን ከማያውቁ ፈላስፋዎች የሀሳብ ቅርጫት የተቀዳውን መርሆ የማራመድ ውጤት ይህ እንጂ ምን ሊሆን ይችላል?! እንዴትስ የዚህ ታላቅ መለኮታዊ ሀይማኖት ባለቤቶች በእምነታቸው መሠረቶች ላይ የሌሎች ጥገኛ ሊሆኑ ይችላሉ?!

**በእንዲህ አይነት ውዥንብር ላይ የተመሰረተ መዝሀብን ለየዋሁ የሀገራችን ሙስሊም መምረጥስ ተኩላን ለእረኝነት ከመምረጥ አይብስም?!**

➢ አሽዓሪያዎች የፈጣሪ መኖርን በነርሱ ፍልስፍናዊ ትንታኔ ለማረጋገጥ ፍጠረተ ዓለሙን ማስተዋልን የማንኛውም ሙስሊም ተቀዳሚ ግዴታ አድርገውታል፤ ይህን ያላደረገ ሁሉ በእምነት ጉዳይ ጭፍን ተከታይ /ሙቀሊድ/ እንደሆነ ይስማማሉ፤ ይህም ከሙዕተዚላዎች ከተወረሱ የመዝሀቡ ቅሪቶች አንዱ መሆኑን አንዱ የአሽዐሪያ ተጠሪ አቡ ጀዕፈር አስ-ሲምናኒ አምነዋል። [ፈትሑ'ልባሪ (1/71)፣ እንዲሁም (13/349) ይመልከቱ]

ነገሩ በዚህ ሳያበቃ በነርሱ አገላለፅ የሙቀሊድን (የአብዛኛውን ሙስሊም ማህበረሰብ) እምነት ትክክለኝነት አስመልክቶ ይወዛገባሉ፤ እምነታቸው ትክክል ነው ወይስ ውድቅ? አስ-ሰኑሲ "ሸርሕ አልኩብራ" በተሰኘው ማብራሪያቸው ገፅ 39 በዚህ ረገድ ያለውን "ኺላፍ" ከዘረዘሩ በኋላ (አብዛኛው ሙስሊም) "ካፊሮች" መሆናቸውን መርጠዋል! ታዲያ ይህን መሰል ፅንፈኛ መዝሃብ በየዋሁ ህዝባችን ፊት መጋረጥ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

➢ የሰለፎችን የዐቂዳ አረዳድ በጥቅልና በተናጠል በትክክለኛ ሰነድ የዘገቡ እጅግ ብዙ ጥንታዊ መፅሀፎችን በቅንነት ያመሳከረ ሁሉ የዛሬው የአሻዒራህ ዐቂዳ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ዘመናት እንኳን ሊታወቅ ይቅርና ጭራሽ ያልነበረ መሆኑን አይጠራጠርም።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . . .

• እንደናሙና የታላቁን ኢማም አል-ቡኻሪ ምስክርነትን እንጥቀስ፤ የሙስሊሞችን ዐቂዳ ሲያስተላልፉ እንዲህ ብለዋል ... «ከሒጃዝ፣ ከመካ፣ ከመዲና፣ ከኩፋ፣ ከበስራ፣ ከዋሲጥ፣ ከበግዳድ ፣ ከሻም እና ከግብፅ ነዋሪዎች ከአንድ ሺህ በላይ የሆኑ የእውቀት ባለቤቶችን አግኝቻለሁ፤ ከአርባ ስድስት አመታት በፊት ጀምሮ ከትውልድ ትውልድ በተለያዩ ዘመናት ሁሉንም በህይወት ሳሉ በተደጋጋሚ አግኝቻቸዋለሁ! ..... ከነርሱም ውስጥ በነዚህ ጉዳዮች ላይ አንዳቸውም ሲወዛገቡ አላየሁም ..» ካሉ በኋላ የጠቀሱት የመጀመሪያው ነጥብ ተግባርን ከእምነት ከሚነጥሉት ከአሽዐሪያዎችና ከማቱሪዲያዎች የ"ኢርጃእ" መዝሀብ ጋር ይጣረሳል፤ ይኸውም ... «ዲን (እምነት) ንግግርና ተግባር ነው»! የሚል ነበር። [ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱንናህ (1/194)]

• እንደዚሁም ሁለቱ ታላላቅ የሐዲሥ ኢማሞች አቡ ሓቲም እና አቡ ዙርዓ የዑለማዎችን እምነት ሲያስተላልፉ እንዲህ አሉ ... «ሒጃዝም ይሁን ዒራቅ፣ ሻምም ይሁን የመን በሚገኙት በሁሉም ከተሞች የነበሩ ዑለማዎችን አግኝተናል፤ ከእምነታቸው መካከል፡- ኢማን ንግግርና ተግባር ነው፤ ይጨምራል፤ ይቀንሳልም..» በማለት ዝርዝሩን የጀመሩበት ነጥብ እንዲሁ ከሁለቱ መዝሃቦች የ"ኢርጃእ" እምነት ጋር ይጣረሳል፤ ቀጥለውም አልፍ ብለው እንዲህ አሉ... «አላህም በመፅሐፉና በመልእክተኛው አንደበት ራሱን እንደገለፀው በዐርሹ ላይ መሆኑና ከፍጡራን የተነጠለ /ከፍጥረተ አለሙ ውጭ ያለ/ መሆኑን ስለ ሁኔታው ሳይገልፁ (ማመን)..» [ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱንናህ /አል-ላለካኢይ/ (1/198)]

• የኢማሞች ኢማም በመባል የሚታወቁት ኢብኑ ኹዘይማህ አላህ ለራሱ ስላፀደቀው ፊት وجه ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡- «እኛና ሁሉም ዑለማዎቻችን-ሒጃዝ፣ ቲሃማ፣ የመን፣ ዒራቅ፣ ሻም፣ ሚስር (ግብፅ) ያሉት- መንገዳችን ለአላህ ራሱ ያፀደቀውን ማፅደቃችን ነው፤ ይህንን በአንደበታችን ስናረጋግጥና በልቦናችን ስናምን የፈጣሪያችንን ፊት ከፍጡራን መካከል ከአንዱም ፊት ጋር ሳናመሳስል ነው፤ ጌታችን ፍጡራንን ከመምሰል የላቀ ነው፤ ባህሪያቱን ከሚያስተባብሉት ንግግርም የከበረ ነው..!» ["አት-ተውሂድ" /ኢብኑ ኹዘይማህ/ (1/26)]

ከዚያም በኋላ የአሽዐሪያ መዝሃብ ለብዙ ዘመናት ባዕድ ሆኖ እንደቆየ የሚያሳዩ አመላካቾች አሉ፤ ከነርሱ መካከል "አል-ቃዲር ቢላህ" የተባለው የዓባሲያው ኸሊፋ ያዋቀረው የሰለፎችን ዐቂዳህ የያዘ አጭር ጥንቅር በሁሉም ግዛቱ ለሙስሊሞች እንዲሰራጭና በየመስጂዶች እንዲነበብ፣ ዑለማዎችም የፅሁፍ ማረጋገጫቸውን እንዲያኖሩበት ማድረጉ ይጠቀሳል፤ ከርሱም ሞት በኋላ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ዑለማዎች ተሰባስበው ይህንና መሰል የሰለፎችን ዐቂዳ ያዘሉ ጥራዞችን በህብረት እያነበቡ የሚያረጋግጡባቸው በርካታ ሁኔታዎች አልፈዋል! [ለዋቢነት፡- "አል-ሙንተዘም ፊ ታሪኺ'ል-ሙሉኪ ወል-ኡመም" /ኢብኑ'ል-ጀውዚይ/ (15/279-282) እንዲሁም (16/105- 106)፤ "አል-ቢዳያህ ወን-ኒሃያህ" /ኢብኑ ከሢር/ (15/685) ይመልከቱ።]

ታዋቂው ዓሊም ኢብኑ ዐብዲ'ል-ሃዲ ጀምዑ'ል-ጁዩሺ ወድ-ደሳኪር ዐላ'ብኒ ዓሳኪር በተሰኘ መፅሀፋቸው ከተለያዩ የፊቅህ መዝሃቦች የተውጣጡና በተለያዩ የሸሪዓ ዘርፎች የታወቁ የአሽዓሪያን መንገድ የሚያወግዙ ከአራት መቶ በላይ ዓሊሞችን ጠቅሰዋል:: ከዚያም የሚከተለውን አስፍረዋል ... «በአላህ ይሁንብኝ፤ በአላህ ይሁንብኝ፤ በአላህ ይሁንብኝ፤ ሳንጠቅስ የተውናቸው ከጠቀስናቸው ይበዛሉ፤ ከበፊቱ ቀናቸው ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እነርሱን /አሽዐሪዮችን/ ርቀው ያገለሉትን ሁሉ አንድ በአንድ መከታተል ብንይዝ ኖሮ ከአስር ሺህ ያልፉ ነበር!» ["ጀምዑ'ል-ጁዩሺ ወድ-ደሳኪር ዐላ'ብኒ ዓሳኪር" /ኢብኑ ዐብዲ'ል-ሃዲ/ ገፅ 320 (በአዲሱ የዳሩ'ል-ዐቂዳህ እትም መሰረት)]

እንግዲህ እውነታው ይህን ይመስላል፤ አሽዓሪያና ማቱሪዲያ በፍልስፍና ተደግፈው የሚውተረተሩ አንጃዎች እንጂ አብዛኛው ሙስሊም በተለይም ቀደምት አበው (ሰለፍ) ጭራሹኑ የማያውቋቸው መጤ እምነቶች ናቸው። ይህን ሁሉ የተወገዘ ሀሳብ የያዘን አስተሳሰብ ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መመሪያ ካልሆነ ብሎ መሞገት ለህዝበ ሙስሊሙ ማሰብ ነውን?

**የሙስሊሙን የተውሒድ እምነት ወደሚፃረር አስተሳሰብ ከመጣራት ሰህቦችና ተከታዮቻቸው የነበሩበትን ጎዳና ማመላከት ከሁሉም አይበጅምን?**

**2. ሱፊያ እና ጡሩቆቹ ለአኽላቅ እና የነፍስ እነፃ ይጠቅማል በሚል በዑለሞች መስማሚያ ሰነድ ላይ እንዲጠቀሱ የሚጠይቁ አካላት ስህተት ...**

➢ በዑለሞች የትብብር ሰነድ ላይ እንዲካተት የሚነሳው ይህ ጥያቄ ከላይ እንዳሳለፍነው ሁሉ በጋራ መግባቢያ ሰነድ ላይ ሊጠቀስ የማይታሰብ የእስካሁኑን መጅሊስ አግላይ ሌጋሲ የሚያስቀጥል ነው። መጅሊስን የሁላችን ተቋም ለማድረግ የጋራ መግባባትንና ትብብር ስምምነት በሚሰፍርበት ሰነድ ላይ የአንድ ወገንን ፍላጎትና ከፋፋይ ድምዳሜ ለማስፈር መጣር ይህን መልካም እድል ማደናቀደፍ ነው።

➢ ዲናችን የሱፍያም ይሁን ሌሎች ሴክቶች መምጣት በፊት የተሟላ ነው፤ አላህም ይህንን አሳውቆናል። አኽላቅ እና መንፈሳዊ እነፃን ለማግኘት በሱፍያ መንገድ መኳዝ ያስፈልጋል ማለት ከሱፍያ መምጣት ከረጅም ግዜ በፊት የተሟላውንእስልምና ጎደሎ አድርጎ መሳል ነው።

አላህ እንዲህ ይላል ...

﴿اليَومَ أَكمَلت ُلَكُم دينَكُم وَأَتمَمتُ عَلَيكُم نِعمَتي وَرَضيتُ لَكُمُ الإِسلامَ دينًا﴾

*«ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ:: ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ:: ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ:: » [ሱረቱ'ል-ማኢዳህ 3]*

➢ የአላህ መልዕክተኛ ካነገቧቸው ተቀዳሚ ተልዕኮዎች መካከል የኡማውን ምግባርና ባህሪ ማነፅ ይገኝበታል። በሱፍያ መስመር ካልሆነ የኡማው አኽላቅ አይስተካከልም ማለት የነብያችንን ሚና ማሳነስ ነው። በእርግጥ መልእክተኛው ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከማንም የበለጡ ወደር የሌላቸው ባለ መልካም ባህሪ እና አርአያ ነበሩ። አላህ እንዲህ ብሏል ...

﴿وَإِنَّكَ لَعَلى خُلُقٍ عَظيمٍ﴾

***{አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ}*** [አል-ቀለም : 4]

የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم እንዲህ ብለዋል...

إنما بعثْتُ لأتمم مكارم اْلخَلق

***« እኔ የተላኩት መልካም ባህሪን ለሟሟላት ነው»*** ታዲያ ከነብያችን ወዲያ ምን አይነት የስብእና እነፃ ልናገኝ ነው?

➢ ሙስሊሞች ስብእናቸውን ማነፅ ያለባቸው በሱፍያ ጡሩቆች ነው ሲባል በአለማችን ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ የሱፍያ ጡሩቆች ተፈልስፈዋል። ለሁሉም ተመሳሳይ ምልከታ የለም፤ ሰህቦች ከነበሩበት ትክክለኛው የኢስላም ጎዳና ያላቸው ርቀትም በእጅጉ ይለያያል።

ከፊሎቹ ከኢስላም መሰረታዊ መመሪየዎች በመራቅ በነ"ሐል-ላጅ" እና ኢብኑ ዐረቢ ፍልስፍና ፍጥረታት እና አላህን አንድ ያደረጉ (የሁሉሊያ) ዓቂዳ አላቸው። ሌሎቹ መሻይኾችን መቀደስን እና ቀብር አምልኮን መሰረታቸው አድርገዋል።

ዝቅተኛ የሚባለው የጥፋት ደረጃ እንኳ በመጤ የቢድዓ አስተሳሰቦች የታጀበ ነው። ታዲያ በምስኪኑ የኢትዮጵያ ሙስሊም ላይ እንዲጫን የሚፈልጉት የትኛውን ጦሪቃ ነው?

የሙስሊሙን የተውሂድ እምነት ወደሚፃረር አስተሳሰብ ከመጣራት ሰህቦችና ተከታዮቻቸው የነበሩበትን ጎዳና ማመላከት ለሁሉም አይበጅምን?

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . . .

*ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .*

➢ የመጀመሪያዎቹ ሱፍዮች ነፍስን ማጥራት/ተዝኪየተ-ነፍስ/ እና ኢባዳን ብቻ ይበልጥ ትኩረት የቸሩ ከመሆናቸው የዘለለ ችግር የለባቸውም ለሚባለው፤ የሱፍያ አካሄድ መጀመሪያ ከነበረበት ሁኔታ ፈር እየለቀቀ በየጊዜውም ከትክክለኛው ኢስላም እየራቀ መምጣቱ ግልፅ ነው። ከ"ትክክለኛ" ተሰውፍ ጋር ተያይዘው የሚጠቀሱት እነፉደይል ኢብኑ ዒያድ፣ ቢሽር አል-ሓፊ፤ ሰህል አት-ተስቱሪ እና ሌሎች የዲን መሪዎች ከስያሜው ጋር የነበራቸው ዝምድና አነጋጋሪ ቢሆንም አሁን ባለው የተደራጀ የሱፍያ መንገዶች ተጨባጭ ግን ወራሽ እንደሌላቸው አንጠራጠርም። ደግሞም በሰለፎች ዘንድ የታዩ የሱፍያ አዝማሚያዎችም ከጠንካራ ትችት አልተረፉም። ከዚህ ባሻገር ሙስሊሞችን ቁርአን እና ሱናን ሰሀቦች በተረዱት እና በኖሩት መንገድ መከተልን እንጂ ኃላ የመጡ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን እንዲከተሉ መምከር የአሊሞች አስተምህሮት መሆን የለበትም።

## 3. መውሊድ የሰነዱ አካል ተደርጎ ይጠቀስ የሚለው ሙግት ያቀፈው ህፀፅ

ከላይ ያሳለፍናቸውን ሙግቶች በመደርደር የተቋማዊ ለውጡን ኮሚቴ የዑለማ መግባቢያ ሰነድ ዝግጅት ሲሞግቱ የነበሩ አካላት ካቀረቧቸው የአሽአሪያና የሱፍያ መንገዶችን እንከተል ጥያቄ ባልተናነሰ መልኩ የሚጠይቁት የመውሊድን ህጋዊነት ማስፅደቅ ነው።

➢ እንዲህ ያሉ የውዝግብ ርእሶችን በ"አንድነት" ሰነድ ላይ እንዲሰፍሩ መጠይቅ የሚያስከትለውን መዘዝና የሚያመላክተውን መነሻ ከላይ አሳልፈናል። የስምምነት ሰነዱ የአንድ ወገንን ፍላጎት መሰረት እንደማያደርግ እየተገለፀ፤ መውሊድን ካላፀደቃችሁ ማለት ሙስሊሙ ተቋሞቹን ነፃ የሚያደርግበትን ታሪካዊ እድል የሚያደናቅፍ ሳንካ መሆኑ ግልፅ ነው።

➢ ይህ በአል በወቅቱ ብሄራዊ ሆኖ ሲታወጅ በተወሰኑ ሰዎች የተጠየቁ እንደ ሚዕራጅ አይነት ሌሎች በአላትም ነበሩ። በሺዓ አመለካከት የተሳቡት ደግሞ አሹራን ይጠይቃሉ። አንዳንድ አጥኚዎች ብዙ የሙብት ጥያቄዎች ያልሉትን ሙስሊም ህብረተሰብ ለመደለል የታወጀ በአል መሆኑን ያሰምሩበታል። ያም ሆነ ይህ፤ ይህ ሰነድ ኡለማዎችን እንዲያግባባ የተዘጋጀ እንደመሆኑ መሰረት የሚያደርገው ሸሪዓዊ መነሻን እንጂ ብሔራዊ በአል መሆኑን አይደለም።

➢ ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ መውሊድ እንዳይጠፋ ዋስትና ይሆነን ዘንድ በሰነዱ ይካተት ለሚለው ምክንያት፤ በሀገሪቱ የሚሰራበት ህግ ለግላዊ አመለካከቶች ዋስትና ስለሚሰጥ በዛው መንገድ መስተናገድ ያለበት እንጂ የዑለማዎች ሰነድ ላይ ይግባ ብሎ መሞገት ወኃ የማይቋጥር ሙግት ነው። በተመሳሳይ መልኩ መውሊድን የሚሰብኩ ሰዎችን መረጃ መጠየቅ እና ቢድዓ መሆኑን መግለፅ ሙብት ነው። ስለሆነም የመውሊድ አጀንዳ መካተት ውዝግብን እንጂ የሚያስገኘው ትርፍ የለም።

➢ በኢስላም ውስጥ የተደነገጉት ሁለት አመታዊ ዒዶች ብቻ መሆናቸው በሶሒሕ ሐዲሥ የተገለፀ ነው። አል-ኢማም አንነ-ሳኢይ እና አል-ኢማም አሕመድ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መዲና በመጡ ጊዜ ነዋሪዎቹ ሁለት የሚጫወቱባቸው በአላት ነበሯቸው፤ እነዚህ ሁለት ቀናት ምን እንደሆኑ ሲጠይቁ ከኢስላም በፊት በጃሂሊያ የሚዝናኑባቸው በአላት መሆናቸውን ነገሯቸው፤ እሳቸውም:- «አላህ እነርሱን በሁለት የተሻሉ የበአል ቀናት ተክቶላችኃል፤ እነሱም የውመል አድሃ እና ዒድ አል-ፊጥርን» ሰነዱ ውስጥ መጥቀስ ካለብን ሙስሊሞችን ሁሉ አንድ የሚያደርጉት እነዚህ በአላትን እንጂ የኺላፍ አጀንዳ ልናካትት አይገባም።

➢ መውሊድ በሰለፎች ዘንድ የማይታወቅና ቆይቶ የተፈጠረ ቢድዓ መሆኑ በሁሉም ወገኖች ይታመናል። ውዝግቡ ጥሩ ቢድዓ ነው ወይስ በጥቅሉ የተወገዘው ቢድዓህ ውስጥ ይካተታል? የሚል ነው።

**ሙስሊሞች በቁርአን እና ሱና በመዳኘት ልዩነቶችን ለማጥበብ ብሎም ለማስወገድ መጣር እንደሚገባቸውም እሙን ነው።**

የአላህ መልዕክተኛ አማናቸውን ተወጥተው በዲኑ ላይ የሚታከሉ አዳዲስ ነገሮችን አስጠንቅቀውን ሳለ፤ ለነብዩ ያለንን ውዴታ ለመግለፅ ነው በሚል ምክንያት መውሊድን በሙስሊሙ ላይ ለማፅናት ማሰብ፤ በአንድ በኩል የአላህ መልእክተኛን አማናን የማድረሳቸውና ዲኑም የመሟላቱን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ መክተት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከማንም በላይ ለነብዩ ውዴታ የቸሩትን መውሊድን የማያውቁ በብርቁ ክፍለ ዘመን (ኸይሩል ቁሩን) የኖሩ የዚህ ኡማ ቀዳሚ ትውልዶችን በልጠ ለመታየት መሞከር ነው። ሁለቱም ለሙስሊሙ አይበጁም!

ከላይ እንዳሳለፍነው ለስምምነቱ ስኬት እና ዘላቂነት ብሎም ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ አደረጃጀት እንቅፋት የሆኑ ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ተለይተው በዝርዝር እርምት የሚሆን ምክር ቀርቧል። ለፅሁፉ መቋጫ፣ ለኮሚቴውም ጥቆማ ይሆን ዘንድ አጭር ጥቆማና መደምደሚያ እነሆ … ሙስሊሞች በቁርአን እና ሱና በመዳኘት ልዩነቶችን ለማጥበብ ብሎም ለማስወገድ መጣር እንደሚገባቸውም እሙን ነው።

ከልዩነት ጋር ኢስላማዊ ወንድማማችነትን መጠበቅ እና በጋራ አጀንዳዎች ላይ መተባበር በኢስላም ጥላ ስር ላሉ ሁሉ የተደነገገ ነው። ሆኖም እስካሁን ባለው ሂደት፤ አንዳንድ አካላት የአሽዓሪያ/ማትሩዲያ ፍልስፍናዎች እና የሱፍያ ጡሩቆች በሰነዱ ላይ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ገዥ መዝሀቦች ሆነው በግልጽ መስፈር እንዳለባቸው በመሞገታቸው የኮሚቴው የማስፈጸም ችግሮች ይበልጥ እየተወሳሰቡ ስኬትም እያዳገተው መጥቷል። ከዚህ አንጻር ሁለት ችግሮችን የሚፈቱ ሃሳቦችን እንመልከት …

1. የዚህ ሰነድ አላማ፤ በብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መካከል በዐቂዳ እና በሌሎች ወሳኝ ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ልዩነቶችን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ የመሰረት ድንጋይ የሚያኖር ነው። ይህም ማለት ተቃራኒ አመለካከት ያላቸውን ኡለማዎች በማቀራረብ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ የሚያግዙ ጥቅል ነጥቦችን ያዘለ መነሻ ለማዘጋጀት የሚደረግ ሙከራ እንጂ ዝርዝር ርዕሶች የሚዳሰሱበት እና የውይይት መቋጫ ላይ የሚደርሱበት መሆን አይችልም! የስምምነት አንቀጾች ጥቅል እና መሰረታዊ መርሆዎችን እንጂ ዝርዝር የኺላፍ ጉዳዮችን ማቀፍ የለባቸውም።

በዑለሞች መግባቢያ ሰነድ መንደርደሪያ ላይ እንደተገለጸው … «ይህ ሰነድ የአንድ ወገን አስተሳሰብ በገዥነት የሚካተትበት ስላልሆነ አወዛጋቢ ጉዳዮች ጥንቃቄ ላይ ላለመግባት ተደርጓል» ኮሚቴው ለዚህ የሰጠው ትኩረት እና ያደረገው ጥንቃቄ በእጅጉ የሚደገፍ ሆኖ በሰነዱ ላይ ያሉት አንዳንድ ከጥንቃቄ እርምጃዎቹ ያመለጡ አወዛጋቢ ጉዳዮች መቀነሳቸው ግድ ይላል። ከነዚህም ውስጥ አንዳንድ ነጥቦች የኡለማ ምክር ቤቱ በሚያዘጋጀው የስራ አፈጻጸም እቅድ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ስለዚህም በጥቂት ነጥቦች መብቃቃት እና ወደፊት ኡለማዎች በጥልቅ ውይይቶች ዝርዝር የመግባቢያ ነጥቦችን እንዲያቀርቡ መጋበዝ የተሻለ ነው።

2. እስከዛሬ ባለው የሙስሊሞች የትግል ሂደት ለመቅረፍ የሞከሯቸው ችግሮች ከፊሎቹ በራሳቸው መግባባት እና የሰከነ ውይይት የሚፈቷቸው ሲሆን ብዙዎቹ ግን ለመንግስት እና ለባለድርሻ አካላት አቤት ሲሉ የቀዩባቸው ጉዳዮች ናቸው። ሙስሊሞችን የሚወክለው መጅሊስ ከአደረጃጀትም ይሁን ከህጋዊነት አንጻር በቂ መሰረት ስለሌለው ችግሮችን ለመቅረፍ የመጀመሪያው እርምጃ መጅሊሱን ማስተካከል እና ችግሮቹን መፍታት መሆኑ ታምኖበት ባለ ዘጠኝ አባላቱ ኮሚቴ ተቋቁሟል። በአላህ ፍቃድ አሁን የተገኘውን እድል ለመጠቀም፤ ኮሚቴው ንኡሳን ኮሚቴዎችን በማዋቀር ያደረገዉን ያላሰለሰ ጥረት እያደነቅን፤ ሶስተኛውና የኡለማዎችን የአለመግባባት ችግር ለመፍታት ጥረት የሚያደርገው ኮሚቴ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ስራው ውስብስብ እና ግዜ የሚወስድ ሆኗል።

የአንድነት እና መግባባት ችግር የውስጥ ችግር በመሆኑ ችግሩን ግዜ ወስዶ የሚፈታ የኡለማዎች ም/ቤት ማቋቋም መልካም እርምጃ ነው። ኮሚቴው ለቀጣይ የኡለማዎች ጉዞ መነሻ (Roadmap) በመስጠት ጉዳዩን መስመር ካስያዘ ኡለማዎቹ ሰፊ ግዜ ወስደው በመግባባት በአላህ ፍቃድ ለጥሩ ወጤት ይበቃሉ። ይህ ግዜን እና እድልን ከመጠቀም አንጻር ወሳኝ ይሆናል።

ወላሁ አዕለም ወሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞



# የሰላም ዋጋ

ሸይኽ ኢልያስ አሕመድ

አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - የሻውን መስራት የሚችል፣ ፍጥረተ-ዐለሙን በሙሉ ስልጣን የሚቆጣጠር እና የሚያስተናብር፣ ክስተቶችን የሚቀያይርና በጥበብ የሚያስኬድ ፍፁም ጌታ ነው። እርሱ የሚወስናቸውና የሚፈፅማቸው ድርጊቶች ሁሌም ቢሆን በጥበብ የታጀቡ ናቸው። ታዲያ ነገሮች ሲቀያየሩ ሁኔታዎች ሲፈራረቁ ሙስሊሞች ሁል ጊዜም ቢሆን አዳዲስ ክስተቶችንና ሁኔታዎችን የሚያስተናግዱባቸው መርሆዎች አሏቸው።

ግን ብዙዎች ምናልባት ነገሮችን በምን መልኩ ማስተናገድ እንዳለባቸው፤ ችግሮችን ወይም ፈተናዎችን በምን መልኩ መጋፈጥ እንደሚገባቸው ላይረዱ ይችላሉ። ያም ሆነ ይህ ኢስላም ለሁሉም ችግር መፍትሄ ያለው ሁለንተናዊ የሕይወት መንገድ ነው። ታዲያ ሁሉንም ህዝብ የሚመለከቱ አስፈላጊ እና አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ ሰዎች በስሜት እየተነዱ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ብዙ ዋጋዎችን ሊያስከፍሏቸው ይችላሉ። ስለዚህ ነገሮችን ረጋ ብሎ ማጤን ፤ ሳይቸኩሉ አመሳክሮና አስተውሎ መንቀሳቀስ ተገቢ ነው።

ከዚህ አንፃር አሁን ባለንበት ጊዜ በአገራችን እየተከሰቱ ያሉ በርካታ ክስተቶች አሉ፤ እና ሰዎች ደግሞ እነዚህን ክስተቶች የሚጋፈጡባቸው ስሜቶች እና ግንዛቤዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ሁላችንንም ሊያስማሙ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች አሉ፤ ከነዚህ ነጥቦችን ውስጥ አብዛኛዎቹ ወይም ሁሉም ነጥቦች ሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉ፤ ሰዎች ሙስሊም ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን ሙስሊም ባይሆኑ እንኳን ሊስማሙባቸው የሚገቡ ርእሶች ናቸው። እናም ከአብዛኃኛዎቹ ወንድሞች እና እህቶች የተሰወሩ ሁነው ሳይሆን መታዋወስ ጠቃሚነት አለውና ለመመካከር ያህል ነው ማለት ነው።

የመጀመሪያው ነጥብ የሰላም ዋጋን እና አስፈላጊነትን የተመለከተ ነው ፤ አንዳንድ ሰዎች ዘንድ ስለሰላም አስፈላጊነት መናገር የተወሰኑ ፖለቲከኞችና ካድሬዎች ድርሻ ይመስላቸዋል፤ ይህ ስሕተት ነው። ሰላም እና መረጋጋት አላህ ለህዝቦች ከሚሰጣቸው በርካታ ፀጋዎች መካከል ከዋነኞቹ የሚመደብ ነው።

ለዚህም ነው አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - በተለያዩ የቁርአን አንቀጾች ላይ የሰላምን አስፈላጊነት እና የዋጋውን ትልቅነት ብሎም በተለያዩ ህዝቦች ላይ የዋለው ትልቅ ፀጋ እና ውለታ መሆኑንም የሚገልፀው፤ ስለዚህ ይህ ምስጋና የሚያስፈልገው ትልቅ ከአላህ ዘንድ የተሰጠን ፀጋ ነው ማለት ነው።

ለምሳሌ ፦

[فَلْيَعْبُدُوا رَبَّ هَٰذَا الْبَيْتِ ::الَّذِي أَطْعَمَهُم مِّن جُوعٍ وَآمَنَهُم مِّنْ خَوْفٍ ]

ይላል [|የዚህን ቤት ጌታ ይግገዙ ያምልኩ |] ካለ በኋላ [| ያ! ከረኃብ በኋላ ያበላቸው , ከፍርሃትም በኋላ ሰላምን የሰጣቸው ጌታ |] ይላል (ቁረይሽ ፥ 3-4)

ልብ ሊባል የሚገው አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - ምግብ ማጣትን እና ሰላም ማጣትን አንድ ላይ አቆራኝቶ ጠቅሷቸዋል። ይህ ደግሞ በዚህ አንቀጽ ላይ ብቻ አይደለም። በሱረቱ-ንሕል ፥ 112 ላይ :-

وَضَرَبَ اللَّهُ مَثَلًا قَرْيَةً كَانَتْ آمِنَةً مُّطْمَئِنَّةً يَأْتِيهَا رِزْقُهَا رَغَدًا مِّن كُلِّ مَكَانٍ فَكَفَرَتْ بِأَنْعُمِ اللَّهِ فَأَذَاقَهَا اللَّهُ لِبَاسَ الْجُوعِ وَالْخَوْفِ بِمَا كَانُوا يَصْنَعُونَ

ሰላም እና መረጋጋት ሰፍኖባት የነበረችን አንዲትን መንደር ወይም አካባቢ እንደምሳሌ ጠቀሰ፤ የዚህ መንደር ሲሳይ ከሁሉም ቦታ በምቾት ወደ እነሱ ይመጣላቸው ይፈስላቸው ነበር እና በድሎትና በፍሰኃ እየኖሩ ነበር ማለት ነው። ታዲያ እነሱ የአላህን ፀጋ አላመሰገኑም [ فَكَفَرَتْ بِأَنْعُمِ اللَّهِ ] [| በአላህ ፀጋዎች ካዱ |] በምስጋና ፋንታ ክህደትን አስከተሉ፤ እናም ውጤቱ ምን እንደሆነ ሲያወሳ [ فَأَذَاقَهَا اللَّهُ لِبَاسَ الْجُوعِ وَالْخَوْفِ بِمَا كَانُوا يَصْنَعُونَ ] [| የረኃብ እና የፍርሃት ልባስን አለበሳቸው |] ለምን? [ بِمَا كَانُوا يَصْنَعُونَ ] [| ይሰሩት በነበሩት ስራ የተነሳ |] ማለት ነው።

**እንዳንድ ሰዎች ዘንድ ስለ ሰላም አስፈላጊነት መናገር የተወሰኑ ፖለቲከኞችና ካድሬዎች ድርሻ ይመስላቸዋል፤**

እናም ሰላምን ማጣት ምግብን ከማጣት ጋር የተቆራኘው ምናልባት የሰላም ዋጋ ከምግብ ዋጋ ጋራ ግንኙነት ስላለው ይሆናል። ማለትም ሰዎች ልክ ምግብ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ ሰላምም ያስፈጋቸዋል ማለት ነው።

እንዲሁም አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - ምን ይላል :-

أَوَلَمْ يَرَوْا أَنَّا جَعَلْنَا حَرَمًا آمِنًا وَيُتَخَطَّفُ النَّاسُ مِنْ حَوْلِهِمْ ۚ

(ዐንከቡት ፥ 67).

[| "ሐረም"ን ጸጥተኛ እንዳደረግንላቸው አይመለከቱም ወይ? |] ሐረም ማለት : በመካ እና በመዲና ክልል ውስጥ የሚገኝ በሌሎች ቦታዎች የተፈቀዱ አንዳንድ ተግባራት የሚከለከሉበት የተከበረ የፀጥታ ክልል እንደማለት ነው። እናም ይህንን የፀጥታ ክልል አላደረግንላቸውም ወይ? ማለት በፊት ከኢብራሒም - ዐለይሂ ሰላም - ዘመን ጀምሮ የተደነገገ ፀጥታን የሚያሰፍን ህግ በመኖሩ የተነሳ በሰላም መኖር ችለው የለ ወይ? እንደማለት ነው።

ነገር ግን በዙሪያቸው ያለውን ሲመለከቱ ደግሞ [ وَيُتَخَطَّفُ النَّاسُ مِنْ حَوْلِهِمْ ] ሰዎች በግድ ከሃገራቸው እየተጠለፉ እየተወሰዱ ባሉበት ሁኔታ ላይ እነሱ ግን ሰላም መሆናቸውን አይመለከቱም ወይ ማለት ነው። ይህ ትልቅ ትምህርት ነው።

ሰዎች የሰላምን ዋጋ ለማወቅ ችግር በራሳቸው ላይ እስኪደርስ መጠበቅ የለባቸውም። ብልጥ ሰው ከሌሎች ችግር ትምህርት ይወስዳል፤ ሞኝ ደግሞ እንደሚታወቀው በራሱ ላይ ከደረሰ በኋላ ብቻ ነው ትምህርት የሚወስደው፤ በጣም ደግሞ የለየለት ከሆነ በራሱ ላይ ችግር ቢደርስ ራሱ ይህ ትምህርት ሊሆነው አይችልም ማለት ነው። አላህን ከዚህ ሰላም እንዲያደርገን እንጠይቀዋለን!

እንደዚሁም በሌላ አንቀጽ ላይ አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - :-

أَوَلَمْ نُمَكِّن لَّهُمْ حَرَمًا آمِنًا يُجْبَىٰ إِلَيْهِ ثَمَرَاتُ كُلِّ شَيْءٍ رِّزْقًا مِّن لَّدُنَّا ..

(ቀሰስ ፥ 57).

[| ፀጥተኛ የሆነ ሰላም የሰፈነበት የ"ሐረም" ክልል አላመቻቸንላቸውም ወይ? የሁሉም ነገር ፍሬዎች ወደሱ የሚወሰዱበት የሚጋዙበት ሃገር አልሰጥናቸውም ወይ? |] ይለናል። ስለዚህ አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - ይህንን የሰላም ትልቅ ፀጋ ለከሁዲያኑ የሚያስታውሰው ያለምክንያት አይደለም፤ ዋጋው በጣም ከፍ ያለ ስለሆነ ነው።

በዚህም የተነሳ ኢስላም ይህንን ሰላም ሊያናጋ ሁከትን ሊያስነሳ የሚችልን ሰበብ ሁሉ ከመጀመሪያዉኑ ከልክሏል። የሰዎችን ነፍስ ያለአግባብ መግደል፣ የሰዎችን ንብረት ያለአግባብ መቀማት ብሎም እንኳን የሰዎችን አይደለም የራስንም ነፍስ ማጥፋትን እጅግ አድርጎ ኮንኗል፤ የራስንም ንብረትም ያለአግባብ ማጥፋትንም እንደዚሁ ከልክሏል። እንኳን ማውደም ይቅር እና ያለአግባብ ማባከን ራሱ ተከልክሏል።




ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

በጥቅሉ ስለሰላም በብዛት የሚወሳበት እና የሚዘከርበት ምክንያት ሰዎች ሰላም ከሌለ ሕይወታቸው ውጥንቅጥ ውስጥ ይገባል፤ ሕይወታቸው ሲባል ደግሞ እምነታቸውም እዚህ ውስጥ ይካተታል። ስለዚህ ለዲኑ የሚጨነቅ ሰው ለሰላምም መጨነቅ ይገባዋል። ሰላም በሌለበት ሁኔታ መስጂዶች ውስጥ ተገናኝተው ሙስሊሞች ዲናቸውን መማማር ይከብዳቸዋል፤ የሰዎች ሁሉ ትኩረት ወደ ሌላ ነገር ነው የሚያዘነብለው ፤ ሌላው ቀርቶ ሰዎች እውነታን እንዲረዱ፣ ኢስላምን እራሱ በተገቢው መልኩ እንዲገነዘቡ ሰላም አንድ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ለዚህም ደግሞ ማሳያ እንዲሆን አንድ የታወቀ ክስተት አለ፤ መልእክተኛው ሙሐመድ - ዐለይሂ ሶላቱ ወሰላም - ነብይ ሆነው ከተላኩበት ጊዜ አንስቶ ሰዎችን ወደ አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - ሲጣሩ ነበረ ፤ እናም የተወሰኑ ሰዎች በዚህ ጥሪያቸው ተማርከው ኢስላምን ተቀብለዋል።

ከዚያ በኋላ በ6ኛው አመተ ሂጅራ መልእክተኛው - ዐለይሂ ሶላቱ ወሰላም - ከሶሓቦቻቸው ጋራ ከመዲና ተነስተው ወደ መካ ዑምራ ለማድረግ ተጉዘው ነበረ እና እነዚያ በመካ የነበሩ ከሀዲያን ሙስሊሞቹ ወደ መካ ዘልቀው የዑምራ ስርአት እንዲያከናውኑ አልፈቀዱላቸውም። እናም በዚያው ሁኔታ ላይ በሁለቱ ወገኖች መካከል የሰላም ስምምነት ተፈፅሞ ነበረ፤ ይህ | صلح الحديبية| "ሱልሑል ሑደይቢያ" ተብሎ ይታወቃል።

እናም በስምምነቱ ውስጥ ከተካተቱት ቁም-ነገሮች መካከል አንዱ:- ሁለቱም ወገኖች ለ10 አመታት ያክል ውጊያን እንዲያቆሙ ልክ ያው የተኩስ አቁም ስምምነት ፈፀሙ ማለት ነው። ታዲያ ከዚህ ስምምነት በኋላ ወደ አገራቸው ወደመዲና እየተመለሱ እያሉ አላህ - ሱብሓነሁ ወተዓላ - በመልእክተኛው ላይ አንድን የቁርአን ምዕራፍ አወረደ።

إِنَّا فَتَحْنَا لَكَ فَتْحًا مُّبِينًا| (ፈትሕ ፥ 1)

[| ግልፅ የሆነ መክፈትን ከፍተንልሃል |] ይላቸዋል "ፈትሕ" የሚለው ቃል በዚህ አገባብ ድልን የሚያበስር ነው ፤ እናም አብዛኃኛዎቹ የኢስላም ሊቃውንት , አብዛኃኛዎቹ የተፍሲር አዋቂዎች ይህንን "ፈትሕ" በዚህ አንቀጽ ላይ "ፈትሕ" ተብሎ የተሰየመው "ሱልሕ ሑደይቢያ" ያ! በሑደይቢያ ያደረጉት ስምምነት ራሱ እንደሆነ ይናገራሉ።

ኢብኑ መሥዑድ እና ሌሎችም ሶሓቦች ይህን አስመልክቶ ምን ይላሉ :-

"|إنكم تعدون الفتح فتح مكة، ونحن نعد الفتح صلح الحديبية|"

እናንተ እንደ ድል ወይም አገርን መቆጣጠር የምትቆጥሩት | فتح مكة| "ፈትሕ መካ" ወይም የመካ መከፈት ነው መካ በሙስሊሞች እጅ ተመልሶ መሆኗን ነው ፤ ነገር ግን እኛ እንደፈትሕ የምንቆጥረው "ሱልሑል ሑደይቢያ"ን ነው ይሉናል፤ የሑደይቢያን ስምምነት ነው።

ነገር ግን እኛ እንደ "ፈትህ" የምንቆጥረው "ሱልሕ አልሑደይቢያ"ን ነው - የሑደይቢያን ስምምነት።

እንደዚሁም ጃቢር -ረዲየላሁ ተዓላ ዐንሁ- ምን ይላሉ

"|ما كنا نعد الفتح إلا يوم الحديبية|"

"ፈትህ" ብለን የምንቆጥረው "የውመል ሁደይቢያ" የሁደይቢያን ቀን እንጂ ሌላን አልነበረም ይላሉ። ልክ እንደዚሁ አነስ ኢብን ማሊክ - ረዲየላሁ ተዓላ ዓንሁ -

إِنَّا فَتَحنا لَكَ فَتحًا مُبينًا

አልፈትህ:1] የሚለውን አንቀፅ ሲያብራሩ ምን አሉ ... "አልሑደይቢያህ" ይህ "ፈትህ" የተባለው ሑደይቢያ ነው፤ የሑደይቢያ ስምምነት ማለታቸው ነው። ይህንን አልቡኻሪ እና ሌሎች ዘግበውታል።

**ንግግራችን የሚያመጣውን ተፅእኖ ሳናስብ እንዲሁ ያከገደብ ድጋፍን ወይም ተቃውሞን እንሰነዝራለን። ይህ ደግሞ ከተጠያቂነት አያድነንም።**

ታዲያ መልእክተኛው - ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም - ከዚህ በፊት እንደ በድር ዘመቻ ያሉ ድልን የተቀናጁባቸው ክስተቶች ነበሩ። ግን ከነዚህ በተለየ መልኩ አላህ - ሱብሐነሁ ወተዐላ - ይህን የሰላም ስምምነት "ፈትህ" ብሎ የጠራበት ምክንያት ምን ይሆን? ይህም ግልፅ በሆነ ምክንያት ነው፤ ዑለማዎች በተለያዩ ኪታቦቻቸው ላይ አስፍረውታል።

ነገር ግን ከቀደምት የኢስላም ሊቃውንት ንግግሮች መካከል አንዱን ለመጥቀስ ያህል አልኢማም አ'ዙህሪይ - ሙሐመድ ኢብኑ ሺሀብ አዙህሪይ ታላቁ ታቢዒይ - ይህን አስመልክቶ ኢብኑ ኢስሀቅ እንደሚያስተላልፉት እና ኢብኑ ሂሻም በታወቀው የሲራ መፅሀፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት (አ'ዙህሪይ) ምን ይላሉ ...

" ما فتح في الاسلام فتح قبله كان أعظم منه|"

"በኢስላም ከሱ ማለትም ከ"ሱልሕ አልሁደይቢያ" የበለጠ ድል ኖሮ አያውቅም" ትልቁ ድል ይህ ነው ይላሉ።

በመቀጠልም (አ'ዙህሪይ) ከዛ በፊት ሰዎች የነበሩበትን ሁኔታ ሲያወሱ ...

"|إنما كان القتال حيث التقى الناس|"

ከዛ በፊት ግን "ሰዎች እንደጠላት ሲገናኙ ውጊያ መከሰቱ አይቀርም ነበረ"

"|فلما كانت الهدنة وضعت الحرب وأمن الناس كلهم بعضهم بعضا ,فالتقَوا فتفاوضوا في الحديث والمنازعة ,فلم يكلم أحد بالإسلام يعقل شيئا إلا دخل فيه|"

"ነገር ግን ይህ የሰላም ስምምነት ሲፀድቅ ጦርነትም ሲቀር እንደዚሁም ሰዎች ከፊሎች ለከፊሎች ሰላምን ሲሰጡ ማለት እርስ በርስ መተማመን በመካከላቸው ሲሰፍን እና ተገናኝተው በንግግር አንድ ሁለት መባባል ሲጀምሩ - በመረጃ መወያየት ሲጀምሩ -" ምን ሆነ ይሉናል "አዕምሮው ክፍት የሆነ ግንዛቤ ያለው ሰው ሁሉ ስለኢስላም ሲነገረው ቀጥታ ወደ ኢስላም መግባት እንጂ ሌላ አማራጭ አልነበረውም"

ስለዚህ ይህ ዲንን ለማሰራጨት ይበልጥ የተመቸ ነበረ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ኢስላም ባብዛኛው በምን እንደተስፋፋ የሚያሳይ ነው። ቀጥሎ (አ'ዙህሪይ) ምን ይላሉ ...

"|فلقد دخل في تينك السنتين في الإسلام مثل من كان في الإسلام قبل ذلك وأكثر|"

"በርግጥም በነዚህ ሁለት አመታት ውስጥ" ማለትም ነብዩ - ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም - ሁደይቢያ ስምምነት ከፈፀሙበት አንስቶ መካን እስኪቆጣጠሩ ባሉት "ሁለት አመታት ውስጥ" ይላሉ።

እንዲያውም ሁለት አመት እራሱ አይሞላም ምክንያቱም የሁደይቢያ ስምምነት በ6ኛው አመተ ሂጅራ በዙልቂዕዳ ወር ነበር ከዛ መልእክተኛው - ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም - መካን የተቆጣጠሩት በ8ኛው አመተ ሂጅራ በረመዳን ወር ነበር።

ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚያ በመካ የነበሩ የአጋርያኑ መሪዎች እና ባላባቶች የአስር አመቱን የሰላም ስምምነት በማፍረሳቸው እና ካፈረሱ ሌሎች ወገኖች ጋር አብረው በመተባበራቸው ነው።

ያም ሆነ ይህ አ'ዙህሪ ንግግራቸውን ሲቀጥሉ ...

"|فلقد دخل في تينك السنتين في الإسلام مثل من كان في الإسلام قبل ذلك وأكثر|"

"በነዚህ በሁለት አመታት ብቻ ከዛ በፊት ከሰለመው ወይም ኢስላምን ከተቀበለው ሰው የማይተናነስ ወይም የሚበልጥ ሰው ኢስላምን ተቀብሏል" ይሉናል።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

*ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .*

ምን ማለት ነው መልእክተኛው -ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም - ጥሪያቸውን ከጀመሩበት ግዜ አንስቶ እስከ "ሱልህ አልሑደይቢያ" ድረስ 19 አመታት አልፈዋል፤ ማለትም ከሒጅራ ስድስተኛ አመት ላይ እንደሆነ አውቀናል፣ ከዛ በፊት ደግሞ በመካ ያሳለፏቸው 13 አመታት አሉ፤ እና እነዚህን አንድ ላይ ስንደምር 19 አመታት አሉ ማለት ነው። እና በ19 አመታት ከሰለመው ህዝብ በሁለት አመቱ የሰላም ግዜ የሰለመው ህዝብ ቁጥር ያየለ ነው ማለት ነው።

ይህንን ኢብን ሒሻም በሲራ መፅሀፋቸው ሲያብራሩ ምን ይላሉ ...

"‖والدليل على قول الزهري أن رسول الله خرج إلى الحديبية في ألف وأربع مائة‖"

"ይህንን የአልኢማም አዙህሪን ንግግርን ትክክለኝነት የሚያሳየው ነገር መልእክተኛው - ዓለይሂ ሰላቱ ወሰላም - ወደ ሁደይቢያ ሲሄዱ 1400 ያክል ተከታዮችን ይዘው ነው የተጓዙት"

ይህ እንግዲህ አልቡኻሪ እና ሙስሊም ላይ ጭምር ያለ ትክክለኛ ዘገባ ነው። አንዳንድ ዘገባዎች ላይ አንዳንድ ሶሐቦች "1500 ነበሩ" ይላሉ። ያም ሆነ ይህ በ1400 እና በ1500 መካከል ነበረ ቁጥራቸው። እናም "‖خرج إلى الحديبية في ألف وأربع مائة‖" ጃቢር ኢብን ዓብዲላህ በሚያስተላልፉት ዘገባ ላይ "1400 ያክል" እንደነበሩ ተነግሯል።

"‖ثم خرج فى عام فتح مكة بعد ذلك بسنتين فى عشرة آلاف‖"

"ከዛ በኋላ ከሁለት አመት በኋላ ብቻ መካን ለመቆጣጠር ባደረጉት ጉዞ ላይ አስር ሺህ ተዋጊ ይዘው ነው የገቡት"

ስለዚህ በሁደይቢያ ስምምነት ላይ ከፍ አድርገን 1500 ነበሩ ብንል እንኳ ሁለት አመት ባልሞላች የሰላም ግዜ 8500 ያክል አዲስ ተከታይ አፍርተው ነበር። ከዛ በፊት ግን 1500 ብቻ ያክል ነበሩ። ልብ በሉ ይሄ በጦርነት እና መሰል ክስተቶች ላይ የማይሳተፉትን ሴቶችን፣ ህፃናትንና ትላልቅ ሰዎችን ወይም በሆነ አጋጣሚ ሳይመቻቸው የቀሩትን የሚያካትት አይደለም። ነገር ግን (ይህ) የለውጡ ማሳያ ነው። ሁለት አመት ባልሞላ ግዜ ውስጥ ያገኙት ትርፍ በ19 አመታት ውስጥ ካገኙት ትርፍ የላቀ ነው። ያውም በብዙ እጥፍ!

ስለዚህ ሰላም እና መረጋጋት ለዲን፣ ለዳዕዋ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው። ነገር ግን ይህንን ብዙዎች ባለመገንዘብ ምናልባት ሰላምን የሚያደፈርሱ ክስተቶች ላይ በቀጥታ ባይሳተፉ ራሱ በተዘዋዋሪ የሚሳተፉባቸው አጋጣሚዎች አሉ።

ቀጥታ ተሳትፈው ሰዎችን የሚገድሉ ወይ ንብረትን የሚያወድሙትን - እንዲያው ስለነሱ ብዙ ማለት የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ሆኖም ግን ከኋላ ሆነን በንግግር እና በመሰል ድጋፎች ሰዎች እርስ በርስ እንዲባሉ፣ ሰላም እንዲጠፋ፣ ሁከት እንዲጎለብት አስተዋፅኦ የምናደርግ ብዙ ልንንኖር እንችላለን።

ንግግራችን የሚያመጣውን ተፅእኖ ሳናስብ እንዲሁ ያለገደብ ድጋፍን ወይም ተቃውሞን እንሰነዝራለን። ይህ ደግሞ ከተጠያቂነት አያድነንም። ሀላፊነት የጎደላቸውን ቃላት እንዲሁ መሰንዘር ማብቃት ይጠበቅበታል። አንዳንድ ግዜኮ የትላልቅ እልቂቶች መነሻ ንግግር ሊሆን ይችላል። ጦር ያልፈታውን ወሬ ይፈታዋል ነው ነገሩ።

ችግሮች በተፈጠሩ ቁጥር ገና ሳይባባሱ የማረጋጋት ስራ መስራት የሁሉም ሀላፊነት ሊሆን ይገባዋል። ትንሽ እሳት ደግሞ ቶሎ አስፈላጊውን እርምጃ ካልተወሰደ አገር ልታጠፋ ትችላለች። ለሁከትና ለአላስፈላጊ እልቂት የሚያበቁ ክስተቶችን ባጠቃላይ ገና ሳያድጉ በፊት ቶሎ የማርገብና የማረጋጋት ስራን መስራት ልማዳችን ሊሆን ይገባል።

**ብዙዎች ባለመገንዘብ ምናልባት ሰላምን የሚያደፈርሱ ክስተቶች ላይ በቀጥታ ባይሳተፉ ራሱ በተዘዋዋሪ የሚሳተፉባቸው አጋጣሚዎች አሉ።**

አንዳንድ ግዜ ደግሞ ቃል ባንናገር እንኳ የሆነ ቦታ መገኘታችን ብቻ የአንድ ወገን ደጋፊ ተደርገን እንታሰብና ያ ወገን የሚፈፅመውን ጥፋት ሁሉ የምንደግፍ ሊመስል ይችላል። በተለይ ተሰሚነት ያለን ሰዎች ከሆንን!! ይህንን የሚያሳይ አንድ ምሳሌ ከታሪክ ልጥቀስ ...

አዩብ አ'ሲኽቲያኒ - ረሂመሁላህ - በኢብን አሽዓስ የፈተና ወቅት የተከሰተን አንድ ክስተት ሲያወሳልን የሚከተለውን ይላል። የኢብን አሽዕስ ፈተና ማለት - ዓብደረህማን ኢብን አሽዓስ በተባለው ግለሰብ መሪነት የተነሳ አንድ ፈተና ነበር።

ይህም አልሐጃጅ ኢብኑ ዩሱፍ በነበረው የበደል አቋም የተነሳ እሱ ላይ አምፀው የወጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ እና እነዚህ አማፅያን በተቻላቸው አቅም የሰዎችን ልብ ለመማረክ ከነሱ ጋር የተወሰኑ ዓሊሞችን ለመቀላቀል ይሞክሩ ነበር።

አዩብ አሲኽቲያኒ እንደሚለው ...

"‖قيل لابن الأشعث إن أردت أن يقتلوا حولك كما قتلوا يوم الجمل حول جمل عائشة فأخرج معك مسلم بن يسار فأخرجه مكرها‖"

ለኢብኑል አሽዓስ ምን ተባለ "ሰዎች ልክ በአዒሻ ግመል ዙሪያ ሁነው ህይወታቸውን ሰውተው ለመከላከል እንደተዋጉት በአንተም ዙሪያ ሁነው ህይወታቸውን እየሰው እንዲዋጉልህ ከፈለክ ሙስሊም ኢብን የሳርን ይዘህ ውጣ" ማለት ሰዎች ይህን ሰው ስለሚወዱት እሱ ከነርሱ ጋር በሚሆንበት አጋጣሚ ለመከላከል ብለው ትልቅ መስዋእትነት ይከፍላሉ ለማለት ፈልገው ነው። እናም ይህን ሲሰማ ሳይፈልግ በግድ ከነርሱ ጋር እንዲቀላቀል ብሎ ይዞት ሄደ።

አዩብ (አ'ሲኽቲያኒ) ከአቡ ቂላባ በሚያስተላልፈው ምን ይላል አቡ ቂላባ ለሙስሊም ቢን የሳር እንዲህ አለው - ይህ እንግዲህ ያ ክስተት ካለፈ በኋላ ነው - ...

"‖قال أيوب عن أبي قلابة قال لي مسلم بن يسار أحمد الله إليك أني لم أرم بسهم ولم أضرب فيها بسيف‖"

"እኔ አላህን አወድሳለሁ - አመሰግናለሁ - ምክንያቱም አንድም ቀስት አልወረወርኩም በሰይፍም አንድም ቢሆን አልተማታሁም" አሉ፤ ያው ይዘውኝ ወጡ እንጂ አልተዋጋሁም ማለታቸው ነው። በዚህ ግዜ አቡቂላባ ምን አልኩት አለ ...

"‖قلت له فكيف بمن رآك بين الصفين فقال هذا مسلم بن يسار لن يقاتل إلا على حق فقاتل حتى قتل‖"

"ታዲያ መዋጋቱንስ አልተዋጋህም ይባል አንተን በሁለቱ የጦር ሰልፎች መካከል ላይ ያየ 'ይህኮ ሙስሊም ኢብኑ የሳር ነው እሱ የሚዋጋው ሀቅ ላይ ቢሆን እንጂ ለሌላ አይደለም' ብሎ አንተን ተከትሎ ተጋድሎ የሞተ ሰውንስ አስመልክቶ እንዴት ታደርጋለህ?" አላቸው።

ይህን ሲላቸው ሙስሊም ኢብኑ የሳር አለቀሱ ...

"‖فبكى والله حتى وددت أن الأرض انشقت فدخلت فيها‖"

"በጣም አለቀሰ፤ ከማልቀሱ የተነሳ ምድር ተሰንጥቃ ውስጥ ብገባ ወይም ብትውጠኝ ተመኘሁኝ" አለ። ማለት ሙስሊም ኢብኑ የሳር - ረሂመሁላህ - በጣም ከመፀፀታቸው የተነሳ በዚህ መልኩ ሲያለቅሱ ለምን ይህን ተናገርኩኝ ብዬ ተቆጨሁኝ ማለቱ ነው። ይህ ክስተት አልቡኻሪ 'ታሪኹል ከቢር' በተሰኘው መፅሀፋቸው እንዲሁም ኢብኑ ዓሳኪር እና አልፈሰዊ "ፊል ኪታብ አልመእሪፈቲ ወታሪኽ" ያሰፈሩት ነው። ]]]

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

***መፍቻ:-***

[[[ ]]] ...... የሸይኽ ኢልያስ ንግግር መነሻና ማብቂያ

{ } .... የቁርአን አንቀጽ በዐረበኛ

[| |] .... የቁርአን አንቀፅ አማርኛ ትርጉም

| | .... ዓረብኛ ቃል በዓረበኛ ሲፃፍ

" " .... ዓረብኛ ቃል በአማርኛ ሲፃፍ

‖" "‖ .... የሶሓቦች ንግግር

( ) ..... ወደ ፅሁፍ የገለበጠው ሰው ጭማሪ

==========================

✍ ድምጹን ወደ ጽሁፍ የገለበጠው :-

**ወንድም አሕመድ የሕያ**

# መንፈሳዊ ጉዞ በሸሪዓ እይታ

በሀገራችን እና በብዙ ሀገራት በሚኖሩ የሌላ እምነት ተከታዮች ዘንድ ከተለመዱ ተግባራት አንዱ 'መንፈሳዊ ጉዞ' ነው፡፡ ይህ አይነቱ ጉዞ ሰዎች ቅዱስነቱን ወደሚያምኑበት ስፍራ ወይም ቅዱሳን መሆናቸው የሚታመንባቸው ሰዎች ወደተቀበሩበት ቦታ የሚደረግ ሲሆን፤ ከየሄዱበት ስፍራ በረከትንና ፈውስን የመሳሰሉ ጥቅሞችን ይከጅላሉ፡፡ መነሻው በጥቂት አስተባባሪዎች እና ተሳታፊዎች ቅንጅት ይከወን የነበረ ቢሆንም ቀስ በቀስ ነጋዴዎች ስርአት እያስያዙትና የጉዞ ማህበራት በማቋቋም እያደራጁት ሄደዋል፡፡

ይህንን ተሞክሮ ወደ ሙስሊሙ በማምጣት የታላላቅ ሰዎችን ቅዱስነት እና ወልይነት አጉልቶ መስበክ፣ ወደቀብራቸውም ጉዞ ማድረግ፣ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በቀብራቸው ዙርያ ማዘጋጀት በተደራጀ መልኩ ቀጥሏል፡፡ ከዚህ ቀደም ባልተደራጀ መልኩ ጉዞዎችን የሚያስተናግዱ እንደ ነጃሺ፣ አናጂና፣ አብሬት፣ ቃጥባሬ እና መሰል ቦታዎች አሁን አሁን ሌሎች ጋር የተለመደውን የጉዞ አደረጃጀት በመከተል መጠናከረቸውን የሚያሳዩ ማስታወቂያዎችና እና እንቅስቃሴዎች በመስጂዶቻችን ላይ በስፋት እየታዩ ነው፡፡

ባእድ አምልኮ የሚፈፀምባቸውን የቀብር ስፍራዎች፤ ቅርስን በመንከባከብ እና ባህላዊ እሴቶች በመጠበቅ ስም ለማነፅ በከፍተኛ በጀት የሚበጅቱት የአንዳንድ ሀገራት ኤምባሲዎች አላማ ከህዝበ ሙስሊሙ የተደበቀ አይደለም፡፡ በሌሎች እምነቶች ተፅእኖ ስር የወደቁትን የሱፊያ አስተሳሰብ መስመሮች ለሙስሊሙ ህብረተሰቡ በማስተዋወቅ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መገለጫ አድርገው በማቅረብ ሙስሊሙን እኛ እናውቅልሀለን የሚሉት ወገኖች አላማም አጠያያቂ ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ አይነቱ ጉዞ በሸሪአ እንዴት ይታያል የሚለውን ለመቃኘት ብንሞክር፤

1) ነቢያችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) "ወደ ሶስት ቦታዎች ካልሆነ ጓዝን ጠቅልሎ ጉዞ አይወጣም፤ መስጅድ አልሐረም (መካ) መስጂድ አነበዊ (መዲና) እና መስጂድ አልዓቅሷ" ማለታቸው በሰሒሕ ቡኻሪ እና ሌሎችም ድርሳናት ተዘግቧል

ይህ ሐዲስ እንደሚጠቁመው አምልኮትን ፍለጋ አንድን ቦታ በማላቅ የሚደረግ ጉዞ ወደ ሶስቱ መስጅዶች ካልሆነ ወደ ሌላ ቦታ መሄድን ይከለክላል፡፡ ይህ ሰዎች አንድን ቦታ በተለየ ቀድሰው በቦታው የሚገኘን ቀብር ወይም ሌላ ነገር በማላቅ ወደ ማምለክ(ሽርክ) እንዳይገቡና ከዲናቸው እንዳይወጡ ለመጠበቅ ሲባል ነው፡፡

ከዚህም በመነሳት፤ አንድን ቦታ በማላቅ ወይም ከሌሎች ቦታዎች ይልቅ አምልኮት ተቀባይነት ያገኙበታል በሚል ግምት፤ ከሶስቱ መስጅዶች ውጭ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ ሀራም ነው፡፡ ይህ አላህን በሰላት ዱአ እና መሰል ኢባዳዎች ማምለክን ይመለከታል፡፡ ስለት በማስገባት፣ ድረሱልን ወይም አማልዱኝ በማለት ቅዱሳንን መማፀን ግን ባእድ አምልኮ ነውና በእጅጉ ከዚህ የከበደ የሽርክ ተግባር ነው፡፡

2) ነብያችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በአንድ ሐዲስ … "ከናንተ በፊት የነበሩትን ፈለግ ስንዝር በስንዝር፣ ክንድ በክንድ ትከተላላችሁ፤ የአርጃኖ ጉድጓድ ቢገቡ እንኳ ትከተሏቸዋላችሁ" አሉ፤ ይህን የሚሰሙት ሶሐቦችም "የአላህ መልእክተኛ ሆይ የየሁዳና ነሳራዎችን (ፈለግ ማለት ነው) ?" ብለው ሲጠይቋቸው እሳቸውም "ታዲያስ?" ብለው መለሱላቸው፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፤

"ከህዝቦች የተመሳሰለ እርሱ ከነርሱ ነው፡፡" (አቡ ዳውድ ዘግበውታል)

በአምልኮት ተግባራቸው እና ሌሎች በሚለዩባቸው ባህልና ልማዶች አርአያ አድርጎ መከተል የማይፈቀድ ክልክል ተግባር ነው፡፡ ቅዱሳንን በማላቅ አላማ የሚካሄዱ ጉዞዎች የሌሎችን የአምልኮ ተግባራት በመኮረጅ ኢስላማዊ ቅብ መቀባት በመሆኑ መመሳሰል (ተሸቡህ) ነውና አይፈቀድም፡፡

**በዲናችን አንድን ቦታ በማላቅ ወይም ከፍ በማድረግ ወደዛ ስፍራ ሄዶ አምልኮትን መፈፀም የሚፈቀደው ወደ ሶስቱ መስጅዶች ብቻ ነው።**

3) ሸሪዓችን ከተደነገጉት ሶስቱ መስጂዶች ውጭ አንድን ቦታ በማላቅ ወይም አንዳች ጥቅም በመፈለግ የሚደረግ የጀመዓ ጉዞ ነብያችንም ሆኑ ሶሐቦቻቸው በኖሩበት ጊዜ የማይታወቅ የቢድአ ተግባር ነው፡፡ ወደ ተለያዩ ዶሪሆች እና መሳጂዶች የሚደረገው ጉዞ በእስልምናችን የማይታወቅ ነብያችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ያላዘዙት መጤ የቢድአ ተግባር ነው፡፡ ነብያችንም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሸሪዓችንን በሚገባ አስተምረው እሳቸው ያላዘዙትን ከመፈፀም በብርቱ አስጠንቅቀው አልፈዋል፡፡ እናታችን አዒሻ ባስተላለፉት ሐዲስ ነብያችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል "የኛ ትእዛዝ የሌለበትን (የአምልኮ) ስራ የሰራ፤ (ስራው) ተመላሽ ነው" ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

ስለሆነም ይህ በሸሪዓ እንዲጎበኝ ወዳልታዘዘ ቦታ በመጓዝ አጅር አገኛለሁ ብሎ መሳተፍ አላህም ሆነ መልእክተኛው ያላዘዙትን መስራት በመሆኑ አደገኛ የቢድዓ ወንጀል ነው፡፡

4) አላህ ዲናችንን የተሟላ እና ምንም አይነት ጭማሪም ሆነ ማሻሻያ የማይሻ የማይፈልግ ለሁሉም ዘመንና ቦታ የሚሆን ሐይማኖት አድርጎታል፡፡ መንፈሳዊ ጉዞ ታላላቅ የዲን መሪዎች በኖሩባቸው የኢስላም ቀዳሚ ዘመናት ሙስሊሞች የማያውቁት ከሌሎች የተኮረጀ እንግዳ ስራ ነው፡፡

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا

***«ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡ » [ሱረቱ'ል-ማኢዳህ 3]***

በመሆኑም፤ ከሰሞኑ መንፈሳዊ ጉዞ በሚል በተለያዩ መስጅዶች እየተዋወቀ ያለው ጥሪ ትኩረት አድርገን ካልተከላከልነው ለብዙ ጥፋቶች የሚያጋልጥ ነው፡፡ በሸሪአችን በግልፅ የተከለከለ በመሆኑ ሙስሊሙ እንዲጠነቀቅ፣ ራሱንና ቤተሰቡን በዲን ስም ከሚፈፀም ጥፋት እንዲጠብቅ እናሳስባለን፡፡

5) ጁንዱብ ኢብኑ አብደላህ ባስተላለፉት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ሰለላሁ ዓለይሁ ወሰለም) ከመሞታቸው ከአምስት ቀናት በፊት እንዲህ ሲሉ ሰምቻለው ብለዋል ‹‹ከእናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦች የነቢያቸውንና የደጋግ ባሮችን ቀብር መስገጃ ስፍራ አደረጉ፡፡ አደራ! ቀብሮችን መስገጃ እንዳታደርጉ ከልክያችኃለው›› ሙስሊም ዘግበውታል

በነዚህ አካባቢዎች፤ መቃብሮች ከአንድ ስንዝር በላይ ከፍ እንዳይሉ፣ እንዳይገነቡና እንዳይቀቡ እንዲሁም መቃብሮች መስጂድ ተደርገው እንዳይያዙ የሚከለክሉ ነብያዊ ትእዛዛትን የተቃረነ ተግባር በስፋት ይፈፀማል፡፡ ጃቢር እንዲህ ብለዋል ‹‹የአላህ መልዕክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ቀብርን በጀሶ መመረግ፣ ላዩ ላይ መቀመጥ፣ ከላዩ መገንባት፣ ከአፈሩ ውጭ መጨመርና ቀብር ላይ መፃፍ ከልክለዋል፡፡››

## ማደናገሪያዎች እና ምላሾቻቸው

1) አንዳንዶች እነዚህን ጉዞዎች በቀብር ዚያራ በማስታከክ ህጋዊነትን ለማላበስ፤ ‹‹ቀብርን መጐብኘት ከልክያችሁ ነበር አሁን ግን ጐብኙ›› የሚለውን የነብያችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሐዲስ ይጠቅሳሉ፡፡

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ .........

ነብያችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ቀብር ዘይረዋል፣ ዘይሩ ብለውም አዘዋል። የዚያራው ዋነኛ አላማ አኼራን ማስታወስ እንደሆነም ተናግረዋል። እሳቸውም ሆኑ ሶሐቦቻቸው ቀብር ለመዘየር ብለው ጉዞ አልወጡም፣ ሌሎች እንዲወጡም አልፈቀዱም። በመመርመር ላይ ያለነው ግን በአካባቢ የሚገኝን ቀብር ስለመዘየር ሳይሆን በቀብር ዚያራ አላማ ከሚኖሩበት ከተማ ወይም ሀገር ወደ ሌላ ቦታ ጉዞ ማድረግን ነው። ቀብር ዚያራ ለማድረግ የሚፈልግ በአካባቢው ወደሚገኝ መቃብር መሄድ እንጂ ጉዞ በሚያስወጣ ርቀት የሚገኝ ቀብርን ለመዘየር መነሳት ክልክል መሆኑ ያሳለፍነው ሐዲስ ግልፅ መረጃ ነው።

2) ነቢዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የኡሁድ ሸሂዶችን ቀብር ለመዘየር መውጣታቸውን እንደማስረጃ በመጥቀስ ጉዞ ወጥቶ ቀብር ዚያራ እንደሚቻል የሚሞግቱም አሉ። ኡሁድ ባሁኑ የከተማው ሁኔታ በመዲና ከተማ ለነብዩ መስጂድ ቅርብ ከሚባሉ ቦታዎች አንዱ ሲሆን ቀድሞ በነበረው የከተማዋ ሁኔታም ቢሆን ጉዞ የሚያሰኝ ርቀት ላይ የሚገኝ አለመሆኑ ግልፅ ነው።

3) ነቢዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የእናታቸውን ቀብር መዘየራቸውን በመጥቀስ ለቀብር ዚያራ ሲባል ርቀት ጉዞ መሄድ እንደሚቻል ይሞግታሉ። ነቢዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የእናታቸውን ቀብር የዘየሩት መካን ለመክፈት በተጓዙት ዘመቻ ላይ እግረ መንገዳቸውን እንጂ በዚያራ አላማ ስንቅ ሰንቀውና ጓዝ ሸክፈው አልነበረም።

4) አንዳንዶች አቡ ሑረይራ ከልካይ ሀዲሶችን ከማወቃቸው ጋር ጡር ወደተባለው ተራራ መሄዳቸው እንደሚፈቀድ ያሳይል ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ሀቅን ለመደበቅ ሆን ብለው ካልሞከሩ በቀር፤ አል ኢማም ማሊክ እና አስሀቡሱነን በዘገቡት እና ይህ ክስተት በተወሳበት ሀዲስ ላይ አቡሁረይራ ከጉዞ ሲመለሱ ያገኛቸው አቡ በስራ አልጊፋሪይ ከሶስቱ መስጂዶች ውጭ ወደ ሌላ ስፍራ ለኢባዳ ጉዞ ማድረግ እንደማይፈቀድ መረጃ በመጥቀስ፤ "ከመሄድህ በፊት ባገኝህ ኖሮ (ጉዞ) አትወጣም ነበር" ብለው ስራቸው ተገቢ እንዳልነበረ አስታውሰዋቸዋል። አቡሁረይራም ተቀበሉ እንጂ አልሞገቱም።

5) የሀዲሱ ክልከላ የሚመለከተው ወደ መስጂዶች የሚደረግን ጉዞ እንጂ ቀብሮች እና የዚያራ ቦታዎችን አይመለከትም ይላሉ። የሀዲሱ ክልከላ መስጂዶች ቢልም ከላይ የተጠቀሰው ሀዲስ፤ የነብያት እና ሷሊሆች ቀብር እንዲሁም ታዋቂ እና ታሪካዊ ቦታዎችንም ክልከላው እንደሚመለከት የአቡ በስራ ግንዛቤ እና የአቡሁረይራ መስማማት ግልፅ መረጃ ነው። ኢብኑ ተይሚያህ ረሂመሁላህ እንዲህ ብለዋል፤ “ይህ ክልከላ ወደ መስጂዶችም ሆነ ወደ አላህ ለመቃረብ በሚፈፀም ማንኛውም ጉዞ ግብ የሚደረጉ ቦታዎችን ይመለከታል።” ካሉ በኋላ በአቡ በስራ እና በአቡ ሁረይራ መካከል የተከሰተውን ክስተት ጠቅሰው እንዲህ አሉ። “ጡር እና መሰል አንቢያዎችን ያስተናገዱ ቦታዎች በዚህ ሀዲስ ክልከላ ውስጥ እንደሚገቡ ሀዲሱን ያስተላለፈው ይህ ሰሐቢይ ተገንዝቧል... ይህ ታሪካዊ ቦታዎችን ከተመለከተ የአምልኮ ቤቶችም በዋናነት ክልከላው ይመለከታቸዋል።” ኢቅቲዷኡ ሲራጥ ቅፅ 2 ገፅ 645

6) በሀዲሱ ላይ በተፈቀደው መሰረት የነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጂድ ስንሄድ ከጎን የሚገኘው ቀብራቸው ጋር ሄደን እንዘይራለን። ይህ ቀብሮችን ለመዘየር በማሰብ መጓዝ እንደሚቻል መረጃ ነው በኛለትም ይሞግታሉ።

የነብዩን መስጂድ ለመዘየር የሄደ ሰው በዛው ወደ ነቢዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ቀብር ሄዶ መዘየር ይችላል። በጥቅሉ የሳቸው ንግግር እንደሚያመለክተው ጉዞ ማድረግ ያለብን ወደ ሶስቱ መስጆዶች ብቻ ነው። በጉዞዬ ቀብራቸውን መዘየር እንጂ መስጂዳቸውን መዘየርን አላማ አላደረኩም በማለት መጓዝ የሳቸውን ክልከላ መጣስ ነው።

**ጡር እና መሰል አንቢያዎችን ያስተናገዱ ቦታዎች በዚህ ሀዲስ ክልከላ ውስጥ እንደሚገቡ ሀዲሱን ያስተካከፈው ይህ ሰሐቢይ ተገንዝቧል...**

በዚሁ አጋጣሚ የምናነሳው፤ ቀብርን መዘየር ሙስተሐብ ሲሆን የሳቸውን ቀብር መዘየር ደግሞ ታላቅ መልካም ነገር ነው። የርሳቸውም ቀብር ከዚህ እንደሚካተት ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ከእርሳቸው ቀብር ጋር ተያይዘው የሚወሩ ሐዲሦች የሚነገሩት ሐዲሶች ዶኢፍ ወይም ጭራሹኑ የተቀጠፉ መውዱእ ናቸው።

በመጨረሻም ከጉብኝት እና ጉዞ ጋር በተያያዘ፤ ውቅሮ የሚገኘው የነጃሺ ቀብር ተገንብቶ በላዩ ላይ መስጂድ ተሰርቶበታል። ይህ ፍፁም የተከለከለ መሆኑን ለማስታወስ እንወዳለን። ምንም እንኳ ታላቁን ነጃሺ ቢን አስሀማ (ረሂመሁላህ) የምናከብርና የምንወድ ብንሆንም ከሱ ፍቃድና ፍላጎት ውጪ እነዚህ ነቢያዊ ትእዛዛትን በመጣስ በቀብሩ ላይ የሚደረጉት ክልክል ተግባራት ሁሉ ውግዝ ናቸው።

ብዙ አላዋቂዎች ወደ ቀብሩ ሄደው ስለት በማስገባት ከጭንቅ እንዲያወጣቸው እና ሀጃቸውን እንዲያወጣላቸው ይለምናሉ።

ወደ አላህ ብቻ ሊዘረጉት የሚገባውን እጃቸውን በማንሳት የሚፈልጉት ሁሉ እንዲሰጣቸው ነጃሺን ይማፀናሉ። ነጃሺን በምሳሌነት ጠቀስን እንጂ በየአካባቢው ይህ አይነቱ ፈተና ይገኛል። ይህ ግልፅ የጃሂሊያ ተግባር ወደሚፈፀምበት ቦታ የጉዞ ጥሪ ማስተጋባት ፍፁም ስህተት ነው።

መንፈሳዊ ጉዞ እየተባለ በሚካሄድ መጤ ተግባር ላይ መሳተፍ የነብዩን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ክልከላ መጣስ ከከባድ ወንጀል አንስቶ እስከ ቢድዓ እና ሺርክ የሚያደርሱ ጥፋቶችን ሊያስከትል እንደሚችል አውቀናል። ይህንን መልእክት ሁሉም ሊያስተጋባውና ሙስሊሙን ሊያነቃ ይገባል።

አላህ ባነበብነው የምንጠቀም ያድርገን!

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞




# “ምክር ለወጣቶች በቀደምት ሰለፎች”

ይህ መፅሀፍ በቅርቡ የታተመ ሲሆን ኡስታዝ ሱልጣን ኸድር ከዓረብኛ ወደ አማርኛ የተረጎመው አነስ ያለ ግን ታላቅ ጥቅም ያዘለ መፅሀፍ ነው።

መፅሀፉ "ምክር ለወጣቶች በቀደምት ሰለፎች" የሚል ስያሜ ያለው ሲሆን በህይወት አንዴ የሚገኘውን የወጣትነት አፍላ ዘመን እንዴት በመልካም ሁኔታ ማሳለፍ እንዳለብን የሚጠቁሙ ወሳኝ ምክሮችን በ46 ገፆች አስፍሯል።

የመፅሀፉ አዘጋጅ ሸይኽ ዓብዱረዛቅ ቢን ዓብዱልሙሕሲን አልአባድ አልበድር ይባላሉ። እሳቸውም ሆነ አባታቸው እውቅ ዓሊሞች ሲሆኑ በሳዑዲ ዓረቢያ መዲና ከተማ ዒልምን በማስተማር ላይ የተሰማሩ ታላላቅ ምሁራን ናቸው - አላህ ሁለታቸውንም ይጠብቃቸው።

መፅሐፉ ቀደምት የኢስላም ምሁራን (ሰለፎች) ለወጣቶች ያስተላለፏቸውን ወርቃማ ምክሮች በጥቂቱ ያቀርባል። ኡስታዝ ሱልጣን አላህ ምንዳውን ያብዛለትና በጥሩ አቀራረብ ጥቅል ምክሮችን መርጦ የተረጎመ ሲሆን ከምክሮቹም ባሻገር መለስተኛ ማስታወሻዎችን አክሎበታል።

መፅሀፉ አስራ አምስት ጥቅል ምክሮችን በምዕራፍ ከፋፍሎ ቢይዝም በተመሳሳይ አውድ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የሰለፎችን ንግግሮች በየምዕራፉ አካቷል። ከመነሻው ስለምክር አስፈላጊነት፣ ስለዕውቀትና ደረጃው እያወሳ፣ ስለወጣትነት ላቅ ያለደረጃ የሚያነሱ ምክሮችን ያስከትላል። ስለ ጊዜ አጠቃቀም፣ ስለሞትና አኼይራ፣ ዱኒያን ስለመናቅ እና መልካም ስራ የሚያስታውሱ ምክሮችም ተካተዋል።

ራስን ስለመቻል፣ ስለመልካም ባህሪ በዒባዳ ላይ ስለመጠንከር እና ሌሎችም ወጣቶችን የሚመለከቱ ምክሮች በዚህ መፅሀፍ ቀርበዋል። አላህ ፀሀፊውንና ተርጓሚውን ምንዳቸውን የብዛላቸው። መፅሀፍን የሚያነቡ ወጣቶችም ባነበቡት ተጠቃሚ የሚሆኑ አላህ ያድርጋቸው።አሚን

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞



# ነሲሓ

## የዕወቀት ማዕድ

⇒ የኢስላም ውበት
⇒ ከቁርኣን አሻራ
⇒ የነብያት ጥሪ
⇒ የሱትራ ብይን
⇒ የታላቆች ታላቅ
⇒ ልብህን መርምር
⇒ ውዴታን በተግባር
⇒ ስለ - ኢስላም አጭር ማብራሪያ
⇒ ፈታዋ





# የኢስላም ውበት

ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው:: የአላህ ሰላም እና እዝነት የመልዕክተኞች ሁሉ መደምደሚያ በሆኑት ነብይ በሙሀመድ በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን::

ኢስላም ማለት ከአላህ በቀር በሀቅ የሚመለክ አምላክ የለም ሙሀመድ ﷺየአላህ መልዕክተኛ ናቸው:: ብሎ በልቦና ማመን፣ በአንደበት መመስከር እና በተግባርም ማረጋገጥ ሲሆን፤ በስድስቱ የእምነት መሰረቶች ማመን እና አምስቱን የኢስላም መሰረቶች መተግበር፣ እንዲሁም ይሄንኑ ተግባር ባማረ መልኩ ማከናወን (ኢህሳንን) ያጠቃልላል::

ኢስላም፤ አላህ የነብያትንና የመልዕክተኞች (ሩስሎች) መደምደሚያ በሆኑት ሙሀመድ ኢብን ዐብደላህ ላይ ያወረደው የመልዕክቶቹ ሁሉ መቋጫ ነው:: አላህ ዘንድም ከኢስላም በቀር ተቀባይነት ያለው ሀይማኖት የለም:: ይህንን እውነተኛ ሀይማኖት አላህ ገር እና ቀላል፣ አዳጋችም ሆነ አስቸጋሪ ነገር የሌለበት አድርጎታል:: አማኞችን ከአቅም በላይ የሆነ ትዕዛዝ አላዘዛቸውም፣ የማይችሉትንም ግዴታ አላደረገባቸውም::

ኢስላም፤ መሰረቱ የአላህ አንድነት (ተውሒድ)፣ መነሻው ሀቅና እዝነት፣ መለያው እውነተኝነት፣ መሽከርከሪያ ዛቢያው ፍትህ ነው:: ኢስላም ሰዎችን ለመንፈሳዊ ህይወታቸውም ሆነ ለዓለማዊ ኑሮቸው ጠቃሚ ወደ ሆነ ነገር ሁሉ የሚመራ፣ በአንጻሩም ጎጂ ከሆነ ነገር ሁሉ የሚያስጠነቅቅ ሀይማኖት ነው::

ኢስላም፤ አላህ የሰው ልጆችን እምነት እና ባህሪ ያስተካከለበት፣ የዱንያን እና የአኼራ ህይወት ያሳመረበት፣ የተራራቁ አመለካከቶችን እና የተለያዩ ዝንባሌዎችን አንድ በማድረግ ከንቱ ከሆነ ጽልመት አጥርቶ ወደ እውነት የመራበት ሀይማኖት ነው:: አጠቃላይ ህግጋቱም ሆነ መልዕክቶቹ ፍጹም በሆነ መልኩ ተብራርተዋል::

ኢስላም ሀቅን እንጂ አልተናገረም ! በእውነት እና በፍትህ እንጂ አልፈረደም ! ትክክለኛ እምነትን እና ቀና የሆኑ ተግባራትን አስተምሮል፣ በእውነት ኢስላምን የሚኖር ሰው ግሩም ባህሪን እና የላቀ ስርዓትን ይላበሳል::

## የኢስላም መልዕክት የሚከተሉትን አላማዎች ያካትታል፡-

1_ የመጀመሪያ ዓላማው የሰው ልጆችን ከፈጣሪያቸው ጋር ማስተዋወቅ ሲሆን፤ ያማሩ ስሞቹ ወደር እንደሌላቸው፣ መልካም ባህርያቱ ምሳሌ እንደሌላቸው፣ በጥበብ የተሞሉ ስራዎቹንም ማንም እንደማይጋራው፣ እንዲሁም በፍፁም ቢጤ እንደሌለው አምልኮም ለእርሱ ብቻ እንደሚገባ ያስተምራል::

2_ የሰው ልጆች አላህ የደነገጋቸውን እና በዱንያም ሆነ በአኼራ ስኬታማ የሚያደርጋቸውን ትዕዛዛቱን በመፈፀም፣ ከከለከላቸውም ነገሮች በመቆጠብ፣ አጋር የሌለውን አላህን ብቻ እንዲያመልኩ ይጣራል::

3_ የሰው ልጆች ከሞት በኋላ የሚኖራቸውን ዕጣ ፈንታ፣ ከሞት በኋላ እስከ ሚቀሰቀሱ እና በትንሳኤ ቀን የሚያጋጥማቸውን ክስተት ያስተምራል:: አላህም ባሮቹን በመጪው አለም እንደሚተሳሰባቸው ይናገራል:: የመልካም ስራ ዋጋ መልካም፣ የክፉ ስራ ምንዳም ክፉ በመሆኑ እንደየስራቸው መጨረሻቸው ጀነት ወይም እሳት እንደሚሆን ያስገነዝባቸዋል::

እንደሚታወቀው ኢስላም የግለሰቦችንም ሆነ የኢስላማዊ ማህበረሰቦችን ሕይወት በዱኒያም ሆነ በአኺራ ለስኬት በሚያበቃቸው መልኩ ስርዓት አስይዟል:: ለምሳሌ፡- ትዳርን ፈቀደ አበረታታም! በአንፃሩም ዝሙትንና ግብረ-ሰዶማዊነትን እንዲሁም መሰል ፀያፍ ተግባራትን ከለከለ:: ዝምድናን መቀጠልን፣ለፍጡራን ማዘንን፣ ድሆችንና ችግረኞችን መንከባከብን ግዴታ አደረገ:: መልካም ፀባይን ሁሉ አስተማረ::

ከመጥፎ ፀባይም ሁሉ አስጠነቀቀ:: ለተከታዮቹ ከንግድ፣ ከኪራይና ከመሳሰሉት የገቢ ምንጮች የሚገኝን ሀላል ትርፍ ፈቀደ:: አራጣን እና ሊሎችን ማጭበርበር ያለባቸውን የንግድ እንቅስቃሴዎች በሙሉ እርም አደረገ:: ጠርዘኝነትን ከልክሎ ማዕከላዊ አመለካከትን ያሰፍናል፡፡

ሰዎች ለህግጋቱ ከመገዛትና የሌሎችን መብት ከመጠበቅ አኳያ ስለሚለያዩ ዝሙት፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣትና በመሳሰሉት የአላህን ሕግ በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ቅጣትን ደንግጎል:: እንዲሁም በሰዎች ደም፣ ንብረትና ክብር ላይ በሚፈፀሙ እንደ ግድያ፣ ስርቆት፣ ስም ማጥፋት፣ የሰዎችን ንብረት ያለአግባብ መውሰድ የመሳሰሉት ወንጀሎችም ላይ ገሳጭ ቅጣቶችን ደንግጓል:: ቅጣቶቹ በደል የሌለባቸው ፍጹም ፍትሀዊ ናቸው::

ኢስላም በገዢና በተገዢ መካከል ያለውን ግንኙነት በመወሰን አስተዳደርን ስርዓት አስይዟል:: በኢስላማዊ ስርዓት ማህበረሰቡ ወንጀልነክ ባልሆኑ ነገሮች ሁሉ ለገዢው መደብ ታዛዥ እንዲሆን ግዴታ አድርጎል:: በግለሰቦችና ባጠቃላይ ማህበረሰቡ ላይ በሚያስከትለው መዘዝ ሳቢያ በመሪዎች ላይ የሚደረግ አመጽን ከልክሏል::

በመጨረሻም ይህችን አጠር ያለች መልዕክት በዚህ ማጠቃለያ ሀሳብ እንቋጫለን::

ኢስላም መልካም ባህሪንና ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነትን ለተከታዮቹ አስተምሮል:: በሰው ልጆችና በጌታቸው፣ በግለሰቦችና በሚኖሩበት ማህበረሰብ መካከል በሁሉም መስክ ትክክለኛና መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ያስችላል:: በአንጻሩም መጥፎ ከሆኑ ባህሪያትና ለመልካም ግንኙነት መሻከር ምክንያት ከሚሆኑ ነገሮች ሁሉ አስጠንቅቋል:: ይህም የኢስላምን ሙሉዕነትና በሁሉም ጎኑ ለሰው ልጆች የሚበጅ እንደሆነ በጉልህ የሚያሳይ ነው::

ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው::

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞



# ከቁርካን ከሻራ

ምስጋና ለአለማት ጌታ ለሆነው አላህ ተገባው። የአላህ ሰላትና ሰላም በተወዳጁ ነብያችን፡ በቤተሰባቸው፡ በባልደረቦቻቸው፡ እንዲሁም የእነርሱን ፈለግ በመልካም በተከተሉ ሁሉ ላይ ይሁን።

ይህ ቁርአን ለየትኛውም መፅሃፍ ተስጥቶ ያልታየና ያልተሰማ ክብርና ተአምራትን የያዘ ብቸኛውና ብርቅዬው መፅሃፍ ነው። የሰው ልጆች ከጨለማ ወደ ብርሃን ሊወጡበትና የህይወታቸው መመሪያ ያደርጉት ዘንድ ከአላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) የወረደ የተከበረ የእርሱ ንግግር ነው። ስለዚህ ባጠቃላይ የሰው ልጆች። ለየት ባለ መልኩ ደግሞ ሙስሊሞች። ህይወታቸውን በእምነትም ይሁን በስነምግባር፤ በፓለቲካም ይሁን በኢኮኖሚ ባጠቃላይ በሁሉም የህይወት ዘርፋቸው አንድና ቀጥተኛ መንገድን ከፈለጉ ይህንን ታላቅ መፅሃፍ ማጥናትና መመርመር ግድ ይላቸዋል። የወረደበትም ብቸኛው አላማም ይህ ነው። አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ይህን ሲናገር እንዲህ ብሏል፦

كِتَابٌ أَنزَلْنَاهُ إِلَيْكَ مُبَارَكٌ لِّيَدَّبَّرُوا آيَاتِهِ وَلِيَتَذَكَّرَ أُولُو الْأَلْبَابِ [٣٨:٢٩] "

ይህ ወደ አንተ ያወረድነው ብሩክ መፅሃፍ ነው። አንቀፆቹን እንዲያስተነትኑና የአእምሮ ባለቤቶችም እንዲገሰፁበት (አወረድነው) " (ሷድ 29)

የሚገርመው ግን ብዙ ሙስሊሞች ከዚህ ታላቅ መመሪያቸው ርቀውና ችላ ብለው ይገኛሉ::ሻል ያሉት ደግሞ ፊደሎቹን ከመሽምደድና አቀራሩን (አነባበቡን) ለማሳመር ከመጨነቅ የዘለለ ግብ የሌላቸው ሆነው ነው ሚስተዋሉት። በእርግጥ ይህ ሲባል ቁርአንን በማንበብ (በመቅራት) አሊያ በመሽምደድ ብቻ ከፍተኛን ምንዳ እንደሚያስገኝ ማስተባበል አይደለም! በፍፁም! እንደውም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ይህን ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል ፦

" من قرأ حرفا من كتاب الله فله به حسنة
والحسنة بعشر امثالها لا أقول "الم" حرف
ولكن:ألف حرف ولام حرف وميم حرف"

" ከአላህ መፅሃፍ አንድን ፊደል ያነበበ አንድ የመልካም ምንዳ (ሃሰና) አለው። እያንዳንዱ ምንዳም በአስር (ይባዛል)" አሊፍ ላም ሚም" አንድ ፊደል ነው አልልም። ይልቁንም "አሊፍ" አንድ ፊደል ነው። "ላም" አንድ ፊደል ነው። "ሚም" አንድ ፊደል ነው።" ቲርሚዚ ዘግበውታል።

እንግዲህ ቁርአንን ቃሉን በማንበብ ብቻ ይህን ያህል ምንዳ ቢያስገኝም ግና ከዋናው አላማ ማለትም ህይወትን ሁሉ በእርሱ የህይወት ቀመር ማስኳዝ ከሚለው አላማ ግን ሊያዘናጋን ፈፅሞ አይገባም። ታዲያ ጊዜ ሳይሄድብን ህይወትን ሳናጣ ይህንን እንቁ መፅሃፍ መሪ ብርሃን ለማድረግ ሌት ከቀን ሳንል መጣርና መልፋት ይጠበቅብናል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ቅድሚያ እርሱን እያዩ በሚገባ ከማንበብ በመጀመር ፍቺውን በመረዳት ሊጠና ይገባል። አንዳንድ ሰው አይገባኝም በማለት አይቀራም። አንዳንዱ ደግሞ እድሜዬ ሄዷል እንዴት ችዬ እቀራዋለው በማለት እራሱን ከቁርአን ያገላል።



በፍፁም ይህ ሁሉ ስህተት ነው። ኧረ እንዲያውም የአላህን (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ቃል ማስተባበል እንዳይሆንብንም ያሰጋል። ምክንያቱም እርሱ ነጭ ጥቁር ሴት ወንድ ልጅ አዋቂ ብሎ ሳይለይና ሳይገድብ ይህንን ታላቅ ቁርአን ለመቅራት፤ የህይወቱ መመሪያ ለማድረግ ለፈለገ ሁሉ ገርና ቀላል እዳደረገው እንዲህ ሲል ተናግሯል።

وَلَقَدْ يَسَّرْنَا الْقُرْآنَ لِلذِّكْرِ فَهَلْ مِن مُّدَّكِرٍ [٥٤:١٧]

" ቁርአንንም ለመገንዘብ በእርግጥ አገራነው።ተገንዛቢ አለን?" ( ቀመር 17)

እንግዲህ ከዚህ የፈጣሪ አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ብስራት በውሃላ ለማንኛውም ሰው በራሱና በቁርአን መካከል ግርዶ ሊያደርግ አይቻለውም። ይልቁንስ አላህ ዕርሱን ለቁርአኑ እንዲያገራው እየለመነ ጥረት ሊያደርግ ግድ ይላል።

አንጠራጠር ተራራን ሊንድና ሊያንኮታኩት የደረሰ ተአምር የኛን ልብ የማያርድበት ምክንያት ፈፅሞ አይኖርም።እንከንና ወለምታው የኛ ሆኖ ነው እንጂ ። አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ይህንን ሲናገር እንዲህ ብሏል።

لَوْ أَنزَلْنَا هَٰذَا الْقُرْآنَ عَلَىٰ جَبَلٍ لَّرَأَيْتَهُ خَاشِعًا مُّتَصَدِّعًا مِّنْ خَشْيَةِ اللَّهِ ۚ وَتِلْكَ الْأَمْثَالُ نَضْرِبُهَا لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ

" [٥٩:٢١]

ይህንን ቁርአን በተራራ ላይ ብናወርደው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ (የተነሳ ) ተዋራጅና ተሰንጣቂ ሆኖ ባየኸው ነበር። ይህችንም ምሳሌ ያስተነትኑ ዘንድ ለሰዎች እንገልፃታለን።" (አል ሃሽር 21)

እንግዲህ ይህ ከሆነ እውነታውና ተጨባጩ ሙስሊሞችን፡ በተለየ መልኩ ደግሞ ከእነርሱ ውስጥ ከቁርአን የራቁና አሊያ የሚቀሩት ሆነው ግና ለፊደሎቹና ለድምፁ በመጨነቅ ላይ ብቻ ተወጥረው በርሱ መስራትን፡ በርሱ መኖርን ግን አይኑን ላፈር ላሉ፤ እንዲሁም ሙስሊም ላልሆኑና የሰላምን ፍኖት በህይወታቸው ለሚያቀነቅኑ ሁሉ ወደዚህ ታላቅና እንከን የለሽ ቅዱስ መፅሃፍ እንዲመጡ፤ የያዘውን የሚስጥር ካዝና እንዲመረምሩ ልባዊ ጥሪያችንን እናቀርብላቸዋለን።

እንዴታ በርሱ የተናገረ እውነተኛ ነው። በርሱ የፈረደ ፍትሃዊ ነው። በርሱ የኖረ ነፃ ነው። በእርግጥም አንብበው መርምረው የህይወት መመሪያ ሊያደርጉት የሚገባው ብቸኛው መፅሃፍ ቁርአን ነው።

✍ ኡሙ ዐብዲላህ ነፊሳ ሙሐመድ

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ከተውሒድ ማህደር

## የነብያት ጥሪ

ይህንን አጭር መልዕክት ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ለማስተላለፍ ለረዳን አላህ ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን:: የአላህ ሰላትና ሰላም በመልዕክተኛው በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን::

አላህ እንዲህ ይላል :-

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا [٥:٣]

(**ዛሬ ሀይማኖታችሁን ሞላሁላችሁ:: ፀጋዬንም በእናንተ ላይ ፈፀምኩ:: ኢስላምንም ከሀይማኖት በኩል ለእናንተ ወደድኩ**) አል ማኢዳህ 3

በዚህ አንቀጽ እንደተገለፀው የአላህ ዲን ሙሉ በሆነ መልኩ በመልዕክተኛው ﷺአማካኝነት ተላልፏል:: ለኛ የሚበጅ ነገር ሆኖ ሳይጠቁሙን ያለፉት ነገር የለም:: ከዓብዲላህ ኢብን ዓምር ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ የተከበሩት የአላህ መልዕክተኛ ﷺእንዲህ ይላሉ:-

**‹‹ለህዝቦቹ የሚያውቀውን መልካም ነገር መጠቆምና ከሚያውቅላቸው ክፉ ነገር ማስጠንቀቅ ግዴታ ቢሆንበት አንጂ ከእኔ በፊት (አንድም) ነቢይ አልነበረም››** ::

ነብያት ይዘዋቸዉ ከመጡት መልዕክቶች ተቀዳሚ አጀንዳ አድርገዉ ያብራሩት በአላህ አንድነት ማመንና ብቸኛ ተመላኪነቱን ማረጋገጥ **ተውሒድን** ነዉ:: ይህ የነብያት ፈለግ ነዉ::ይህ ፈለጋቸዉ የሙስሊሞችን የዳእዋ አካሄድ የሚቀርፅ ነዉ:: ትክክለኛ ዳዕዋ በዋነኝነት ከሚንቀሳቀስባቸው መሰረታዊ ነጥቦች መካከል ዋነኞቹ በተውሒድ በሱናና በዒልም የታነፀ ማህበረሰብ ማፍራት ነዉ::

እያንዳንዱ ሙስሊም ሊያውቃቸው የሚገቡ መሰረታዊ ቁርዓናዊና ሀዲሳዊ ትምህርቶችን በተከበሩት በመልዕክተኛው ባልደረቦች(ሰሀቦች) ግንዛቤ መረዳት ይገባዋል::

**☑ አላህ እኛን የፈጠረን በእርሱ ላይ ማንንም ሳናጋራ ልናመልከው ነው:: ይህንንም ቀጥሎ ያለው አንቀፅ ይጠቁመናል::**

((وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ)) الذاريات: ٥٦

(**ጋኔንንም ይሁን ሰውን ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም**) አልዛሪያት 56

የአላህም መልዕክተኛ ﷺቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ ይህንኑ እዉነታ እንዲህ በማለት ይገልፁታል

***((አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት እርሱን ሊያመልኩት ከእርሱም ጋር ማንንም ላያጋሩ ነው::))***

### አምልኮ (ዒባዳ)

ዒባዳ አላህ ለሚወዳቸው ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ንግግሮች እና ተግባሮች ሁሉ የተሰጠ ስያሜ ነው:: የአምልኮ ዓይነቶች ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ:- ሰላት፣ ሩኩዕ፣ ሱጁድ ፣ እርድ(ዘብህ) ፣ ኹሹእ (መተናነስ)፣ መመካት፣ዱዓእ፣ፍራቻ(ኸዉፍ) ፣ተስፋ ማድረግ (ረጃዕ)፣ ጠዋፍ እና መሐላ እንዲሁም ሌሎች አላህ የደነገጋቸው የአምልኮ ዘርፎች ሁሉ ዒባዳ ይባላሉ:: አላህ እንዲህ ይላል:-

***(ስግደቴ አምልኮቴም ህይወቴም ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል)*** *አል-አንዓም162*

የአላህ መልዕክተኛ ﷺበሀዲሰል ቁድስ አላህ እንዲህ እንዳለ ይገልፃሉ ((**ባሪያዬ እኔ ግዴታ ያደረግኩበትን ነገሮች ከመፈፀሙ በተሻለ ወደ እኔ የቀረበ የሚያደርገዉ ስራ የለም::**)) ቡኻሪ ዘግበዉታል

አላህ መልዕክተኞችን የላከው ወደ እርሱ አምልኮት እንዲጣሩና በእርሱ አምልኮ ላይ የሚፈፀም ሽርክን (ማጋራትን) እንዲያወግዙ ነው::አላህ እንዲህ ይላል:-

((وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولًا أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَاجْتَنِبُوا الطَّاغُوتَ)) النحل: ٣٦

***(በየህዝቡም ሁሉ ዉስጥ አላህን አምልኩ ጣዖትንም ራቁ በማለት መልዕክተኞችን በእርግጥ ልከናል)*** *አል ነህል 36*

> **ነብያት ይዘዋቸዉ ከመጡት መልዕክቶች ተቀዳሚ አጀንዳ አድርገዉ ያብራሩት በአላህ አንድነት ማመንና ብቸኛ ተመላኪነቱን ማረጋገጥ ተውሒድን ነዉ።**

### የአምልኮ የሚገነባባቸው መሰረቶች ሶስት ናቸው:-

አንደኛ:- ለተመላኪው በሙሉ ልብ መውደድ:: አላህ እንዲህ ይላል:-

‹‹እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው::›› (አል በቀራህ 165)

ሁለተኛ:- በሙሉ ልብ መከጀል። አላህ እንዲህ ይላል:-

**‹‹እዝነቱንም ይከጅላሉ::››** (አል ኢስራህ 57)

ሶስተኛ:- በሙሉ ልብ መፍራት። አላህ እንዲህ ይላል:-

**‹‹ቅጣቱንም ይፈራሉ::››** (አል ኢስራህ 57)

አላህ እነዚህን ሶስት ታላላቅ መሰረቶች በፋቲሃ ምዕራፍ እንዲህ በማለት አካቷቸዋል::

الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ * الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ * مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ
الفاتحة: ١ - ٤

**‹‹ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤ እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ:: የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው::››** (አል ፋቲሃ 1-3)

በመጀመሪያው አንቀጽ ውዴታ ተጠቅሷል:: ምክንያቱም አላህ ባለ ውለታ ነው:: ባለውለታ ደግሞ በዋለው ልክ ይወደዋል::

በሁለተኛው አንቀጽ ክጃላ ተጠቁሟል::

ሶስተኛው አንቀጽ ላይ ደግሞ ፍራቻ ተጠቅሷል::

ምክንያቱም የምንዳና የመተሳሰብ ቀን ንጉስ ከቅጣቱ ይፈራል:: ስለዚህም ነው አላህ በማስከተል እንዲህ ያለው إِيَّاكَ نَعْبُدُማለትም የነዚህ ሶስቱ ባለቤት ጌታ ሆይ ይህ አንቀጽ الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَበሚጠቁመው ውዴታህ፣ ይህ አንቀጽ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِበጠቆመው ክጃላህና ይህ አንቀጽ (( مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ በጠቆመው ፍራቻህ አመልክሃለው ማለት ነው::

### አምልኮ በሁለት መሰፈርቶች እንጂ ተቀባይነት የለውም፦

1ኛ:- አምልኮን ለተመላኪው ብቻ ለይቶ መስጠት:: አላህ ለእርሱ ፊት ብቻ ጥርት የተደረገን ስራ እንጂ አይቀበልም:: አላህ እንዲህ ይላል:-

‹‹የአላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊግገዙት... እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)::›› (አል በይነህ 5)

‹‹ንቁ! ፍጹም ጥሩ የኾነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው::›› (ዙመር 3)

አላህን «ሃይማኖቴን ለእርሱ ያጠራሁ ኾኜ እግገዛዋለሁ» በል:: (ዙመር 14)

2ኛ:- መልዕክተኛውን ﷺተከታይ መሆን:: አላህ ማንኛውም ስራ የመልዕክተኛውን ﷺ መመሪያ ያልተስማማ ከሆነ አይቀበልም::

አላህ እንዲህ ይላል:-

«መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት:: ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ::» (አል ሀሸር7)

*«በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)::»(አል ኒሳህ 65)*

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . . .

ነብዩም ﷺእንዲህ ብለዋል

*«በዚህ ዲናችን ውሰጥ ከሱ ያልሆነን አዲስ ነገር የፈጠረ ስራው ተመላሽ ነው፡፡»*

ለአላህ ብቻ በመለየት ያልተሰራና ትክክለኛ ያልሆነ ስራ ትርጉም የለውም፡፡ እነዚህን ሁለት መስፈርቶች አካተው ከያዙ አንቀፆች ውሰጥ የሚከተለው በአል ከህፍ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የተወሳው የአላህ ቃል አንዱ ነው፡፡

«እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ፡፡ የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ፡፡ በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው፡፡ (አል ከህፍ ፀ0)

## ተውሒድ

አላህን በጌትነቱ በብቸኛ ተመላኪነቱ በስሞቹ እና በባህሪያቱ ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ተውሒድ በ ሦስት የሚከፈል ሲሆን እነሱም፡

### 1. ተውሒደ አል - ሩቡቢያህ

አላህን በስራዎቹ አንድ ማድረግ፡፡ ይህም ማለት፤ መፍጠር፣ሲሳይን መስጠት፣ነገሮችን ማስተናበር፣ መግደል እና ህያው ማድረግ በመሳሰሉት ድርጊቶቹ አላህን ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው፡፡

ከአላህ ሌላ ፈጣሪ የለም፡፡ አላህ ይህንን እንዲህ በማለት ይገልፅልናል፡- *(አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው)* አል-ዙመር 62

ከአላህ ሌላ ሲሳይን የሚሰጥ የለም፡፡ ይህንን በማስመልከት አላህ እንዲህ ይላል፡- ***(በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለም ሲሳዩ አላህ ዘንድ ያለ ቢሆን እንጂ) ሁድ 6***

ከአላህ ሌላ ነገሮችን የሚያስተናብር የለም፡፡ ይህንን በማስመልከት አላህ እንዲህ ይላል፡- ***(ነገርን ሁሉ ከሰማይ ወደ ምድር ያስተናብራል) አል-ሰጅዳህ***

ከአላህ ሌላ ህያው ሊያደርግ እንዲሁም ሊገድል የሚችል የለም፡፡ ይህንን በማስመልከት አላህ እንዲህ ይላል፡-

***(እርሱ ህያው ያደርጋል ይገላልም ወደርሱም ትመለሳላችሁ)*** *ዩኑስ 56*

ይህን ዓይነቱን የተውሒድ ክፍል በረሱል ዘመን የነበሩ ከሀዲያን አጋሪዎች ያልካዱት ቢሆንም ከባዕድ አምልኮ ባለመላቀቃቸዉ ወደ ኢስላም ሊያስገባቸው አልቻለም፡፡ አላህም ይህን የተውሒድ ክፍል ማረጋገጣቸውን በማስመልከት እንዲህ ይላል፡-

***(ሰማያትና ምድርንም የፈጠረ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው በእርግጥ አላህ ነው ይላሉ)*** *ሉቅማን 25*

### 2 - ተውሒድ አል - ኡሉሂያህ

አላህን በአምልኮ አንድ ማድረግ፡፡ በዱዓእ (ልመና)፣ በፍራቻ፣በመመካት፣እርዳታን እና ጥበቃን በመጠየቅ እንዲሁም እርሱ ባሮቹን ባዘዘባቸው ሌሎች አምልኮቶች ሁሉ ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው፡፡

**የአምልኮ ዓይነቶችን ሁሉ ያለምንም አጋር ለርሱ ብቻ ማድረግን ግዴታ ያደርጋል፡፡**

ከአላህ ሌላ ማንንም አንለምንም፡፡ አላህ እርሱን ብቻ መለመን እንዳለብን ሲነግረን እንዲህ ይላል፡

***(ጌታችሁም አለ! ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና)*** *አል-ጋፊር 60*

ከአላህ ሌላ አምልኮታዊ የሆነ ፍራቻን ማንንም ቢሆን አንፈራም፡፡ አላህ እንዲህ ይለናል፡-

***(አትፍሯቸውም አማኞች የሆናችሁ እንደሆነ {እኔን ብቻ} ፍሩኝ)*** *አል-ኢምራን175*

ከአላህ ሌላ በማንም አንመካም፡፡ አላህ አማኞች በእርሱ ላይ ብቻ ሊመኩ እንደሚገባ ሲገልፅ እንዲህ ይላል፡-

***(አማኞች እንደሆናችሁ በአላህ ላይ ብቻ ተመኩ)*** *አል-ማዒዳህ 23*

·ከአላህ ሌላ ፍጡራን በማይችሉት ጉዳይ ላይ እርዳታን ከአላህ ዉጪ ከማንም አንጠይቅም፡፡ ይህን በማስመልከት አላህ በሱረቱል ፋቲሀ ላይ ደጋግመን ምናነባቸዉን አንቀፆች አዉርዷል፡፡

((إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ)) الفاتحة: ٥

**(አንተን ብቻ እናመልካለን፤ ከአንተም ብቻ እርዳታ እንጠይቃለን)** አል-ፋቲሀ 5

· ከአላህ ሌላ ከማንም ጥበቃን አንጠይቅም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

***የሰዎች ጌታ በሆነው እጠበቃለሁ በል)*** *አል-ናስ 1*

ይህ የተውሒድ ክፍል የአላህ መልዕክተኞች ለሰው ልጆች ለማስተላለፍ ከአላህ ይዘው የመጡት ዋነኛው መልዕክት ነው፡፡ ሁሉም ነብያቶቸ የዳዕዋቸዉ ዋና ተልዕኮ አምልኮን ባጠቃላይ ለአላህ ብቻ ማድረግ (**ተውሒደል ኡሉሂያህ**) ነው፡፡ ይህንን አላህ በቀጣዩ አንቀፅ እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡

***(በየህዝቡም ሁሉ ዉስጥ አላህን አምልኩ ጣዖትንም ራቁ በማለት መልዕክተኞችን በእርግጥ ልከናል)*** *አል ነህል 36*

**ሁሉም ነብያቶቹ የዳዕዋቸዉ ዋና ተልዕኮ አምልኮን ባጠቃላይ ለአላህ ብቻ ማድረግ (ተውሒደል ኡሉሂያህ) ነው።**

ይህንኑ የተውሒድ ክፍል እና የነብያቶች መልዕክት ነዉ የፊተኞቹ ሆኑ በዘመናችን የሚገኙ አጋሪዎች ያስተባበሉት፡፡ የመካ ሙሽሪኮች መልዕክተኛው አንድን አምላክ ብቻ አምልኩ ባሏቸው ጊዜ የሰጡትን ምላሽ በተመለከተ አላህ እንዲህ ይላል፡-

***(አማልክቶቹን አንድ አምላክ አደረጋቸዉን? ይህ አስደናቂ ነገር ነው‹አሉ›)*** *ሷድ 5*

አላህ በየዘመናቱ ከላካቸው ነብያት (ኑህ፣ሁድ፣ሳልህ እና ሹዓይብ) ጥሪ ይህን ይመስል እንደነበር በተለያዩ አንቀፆች ገልፆልናል፡ -

***(ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ ከእርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም...)*** *አል-አእራፍ 59/65/73/85*

### 3 - ተውሒድ አል አስማዕ ወስሲፋት

በቁርዓን እና ትክክለኛ በሆኑ የመልዕክተኛው ሀዲሶች ውስጥ የመጡትን የአላህ ስሞች እና ባህሪያት ከማንም ስሞችና ባህሪያት ጋር ሳያመሳስሉ፣ ቃሉን ሳያዛቡ፣ ትርጉማቸዉን ሳይለውጡ ወይም ሳያስተባብሉ ለአላህ እንደሚገቡ በማመን ማፅደቅ ማለት ነው፡፡ የአላህ ስሞች ብዙ ናቸዉ፡፡ ከነርሱም መሀከል ለምሳሌ አል-ራህማን፣ አል-ሰሚዕ፣ አል-በሲር፣ አል-አዚዝ እና አል ሀኪም የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ አላህ በአጠቃላይ በስሞቹ እና በባህሪዎቹ እሱን የሚመስል እንደሌለ ሲገልፅ እንዲህ ይላል፡-

((لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ)) الشورى: ١١

***(እንደርሱ ያለ ምንም ነገር የለም፤ እርሱ ሰሚዉና ተመልካቹ ነው)*** *አል-ሹራ 11*

አላህን በመስማትም ይሁን በመመልከት ባህሪያቱ ፍፁም የሚመስለዉ የለም፡፡ ይህ አንቀፅ የአላህን ባህሪያት ዉድቅ ለሚያደርጉትም ይሁን በባህሪያቱ ከፍጡራን ጋር ለሚያመሳስሉት ሰዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ልንከተል የሚገባንን መርህ በሚገባ ቀርጿል፡፡አላህ እራሱን በገለፀባቸዉ ባህሪያቱ ስንገልፀዉ ከአምሳያ እናጠራዋለን!!

## ሽርክ

በአምልኮ ከአላህ ጋር ሌላን እኩል ማድረግ ማለት ነዉ፡፡ አምልኮን ከአላህ ዉጪ ለማንም ማዋል የሽርክ ተግባር ነዉ፡፡ ተዉሂድ ፍትህ ነዉ፡፡ ሽርክ ግን የበደሎች ሁሉ በደል ነዉ፡፡ በመሆኑም አላህ የማይምረዉ ከባድ ወንጀል ነዉ፡፡

((إِنَّ اللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَاءُ)) النساء : ٤٨

**"አላህ በእርሱ ላይ ማጋራትን (ሽርክን) በፍፁም አይምርም! ከሽርክ በታች ያለን (ኃጢአት) ለሚሻው ሠው ይምራል" አል-ኒሳዕ 48**

አንዳንድ ሰዎች ስለ ተውሒድ መስማት አይፈልጉም፡፡ የተለያዩ የኢባዳ አይነቶችን ለነብያት ፣ ለመላዕክት እና ለሷሊሆች ያዉላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ጭንቅ በሚገጥማቸዉ ጊዜ በቀብር ዙሪያ ጠዋፍ ያደርጋሉ፣ ከአላህ ዉጪ ማንም መፈፀም የማይችላቸዉን ጉዳዮች ለማስፈፀም ከምዕተ አመታት በፊት ለኖሩ ሰዎች የድረሱልን ጥሪ ያሰማሉ! ይማፀናሉ!! ልጅ ቢያጡ ለሚያመልኩት ሰዉ ስለት ይገባሉ፣ በስሙም ይምላሉ፡፡ በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች ይህ አይነቱ ቀብር አምልኮ ሰዎችን እየሸነገለ ይገኛል፡፡ ጁንዱብ ኢብኑ አብዱላህ ባስተላለፉት ሀዲስ ነብዩ ﷺእንዲህ ብለዋል፡- ***(አደራችሁን! ቀብሮችን የአምልኮ ስፍራ እንዳታረጉ፡፡ እኔ ከዚህ አይነቱ ተግባር እከለክላችለሁ፡፡)*** *ሙስሊም ዘግበዉታል*

***እዎ***! ታላቁ ነብይ ይህንን የተናገሩት ህይወታቸዉ ከማለፉ አምስት ቀናት ብቻ ቀደም ብለዉ ነበር፡፡ ደግመዉ ደጋግመዉ ተመሳሳይ መልዕክት አስተምረዋል፡፡ በዱንያ ቆይታቸዉ በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ሳይቀር ከቀብር አምልኮ አስጠንቅቀዋል፡፡ አጅግ በጣም የሚያሳዝነዉ፤ ሸይጣን ይህ አይነቱን ባዕድ አምልኮ የሚያስፋፋበትን ስልት መቀየሩ ነዉ፡፡አንዳንድ ሰዎች ‹ቅርስን መንከባከብ› ፣ ‹ታሪክን ማቆየት› እና መሰል ምክኒያቶችን በማቅረብ የቀብር አምልኮ ቦታዎች በብዙ ወጪ እያሻሻሉና እየገነቡ ይገኛሉ፡፡ ይህ አይነቱ ተግባር ባዕድ አምልኮን ያበረታታል፡፡ በቁርአንና በሱና የተጠቀሱ መረጃዎች አጅግ በጣም ግልፅና በርካታ ከመሆናቸዉ ጋር የተለያዩ ጦሪቃዎን የሚከተሉ ሙሪዶች አንዲያዉቋቸዉ አልተደረገም፡፡ አንድ ዒባዳ(አምልኮ) ተቀባይነት እንዲያገኝ ሁለት መስፈርቶች መሟላት አለባቸዉ፡፡ **በኢኽላስ ለአላህ ብቻ ሊፈፀም እና በነብዩ የአምልኮ ፈለግ መሰረት ሊተገበር ይገባዋል፡፡**

አላህ ቀጥተኛዉን መንገድ ሁላችንንም ይመራን ዘንድ እንለምነዋለን፡፡

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ፊቅህን ለመረዳት

## የሰጋጅ መከለያ ሱትራ የተደነገገ ስለመሆኑ

በጉዞ ላይም ሆነ ከጉዞ ውጭ፣በግዴታም ሆነ በሱንና ሶላት፣በመስጊድም ሆነ በሌላ ቦታ የሰጋጅ መከለያን (ሱትራ) ማድረግ የተደነገገ ነው፡፡

ነቢዩ ﷺ ፡- *<<አንዳችሁ በሚሰግድበት ጊዜ ወደ መከለያ (ሱትራ) ይስገድ፤ወደ መከለያውም ቀረብ ይበል፡፡>>* ብለዋልና፡፡ (በአቡ ዳዉድ የተዘገበ)

አል ኢማም አህመድ በዘገቡት ሀዲስ ወህብ (ረዐ) ፡- <<ነቢዩ ﷺ ሚና ላይ ሲያሰግዱን አንካሴ ከፊትለፊታቸው ተከሉና ሁለት ረከዓ መርተው አሰገዱን፡፡» ብለዋል።

### √ የሰጋጅ መከለያን የሚመለከት ብያኔ

መከለያ (ሱትራ) ማድረግ ለሰጋጅ ዋጅብ ነው፡፡ ነቢዩ ﷺ ኢማምም ሆነ ለብቻው የሚሰግድ ሰው መከለያ ነገር ከፊት ለፊቱ እንዲደርግ አዘው አበረታተዋል፡፡ በመሆኑም አንድ ሙስሊም በሚሰግድበት ጊዜ ከፊትለፊቱ መከለያ ነገር አድርጎ በርሱና በመከለያው መካከል ሰው አቋርጦ እንዳያልፍ መከልከል ይገበዋል፡፡

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- <<ወደ መከለያ እንጂ እንዳትሰግድ፣ ማንም ሰው ባንተና በመከለያው መካከል አቋርጦ እንዲያልፍ አታድርግ፤እምቢ (አቋርጣለሁ) ካለ ተፋለመው፡፡>> በኢብን ኹዘይማ ተዘግቧል።

### √ የሰጋጅ መከለያ ያዘለው ጥበብ

መከለያ (ሱትራ) ለሰጋጅ የተደነገገው በርካታ ጥበቦችን አካትቶ ሲሆን ከዚህ ውስጥ፡-

1- ትኩረቱንና ተመስጦውን የሚሻማ በመሆኑ በሚሰግድ ፊት ማቋረጥን ለመከልከል፡፡

2- ሰጋጁ ሙሉ ሃሳቡንና ትኩረቱን በሶላቱ ላይ እንዲያደርግና በሌላ ጣልቃ ገብ እንዳይወሰወስ ለማድረግ፡፡

3- በሴት በውሻ ወይም በአህያ አቋርጦ ማለፍ ሶላት እንዳይቋረጥ ጥንቃቄ ለማድረግ፡፡

ከአቡ ዘር በተላለፈው መሰረት የአላህ መልእክተኛ ﷺ ፡- <<አንዳችሁ ለመስገድ በሚነሳበት ጊዜ፤ የኮርቻ የኋላ መደገፊያ ያህል ነገር ከፊትለፊቱ ካለ መከለያ ይሆነዋል፤ የኮርቻ የኋላ መደገፊያ ያህል ነገር ከፊትለፊቱ ከሌለ ግን ሶላቱን አህያ፣ሴትና ጥቁር ውሻ ያቋርጥበታል፡፡>> አሉ ሲሉኝ፣ አቡ ዘር ሆይ! ጥቁር ዉሻን ከቀይ ወይም ከብጫ ዉሻ ምን ለየው? አልኳቸውና የወንድሜ ልጅ! አንተ እንደጠየከኝ ሁሉ እኔም የአላህ መልእክተኛን ﷺ ጠይቄ ፡-<<ጥቁር ዉሻ ሰይጣን ነው፡፡>> አሉ ብለውኛል፡፡ (ሙስሊም ዘግበውታል)

### √ ሱትራን ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች በከፊል

**1- መከለያ ማድረግ ለኢማም ወይም ለብቻው ለሚሰግድም ይሆናል፡፡ ተከትሎ ለሚሰግድ ሰው ኢማሙ ለርሱ መከለያው ነው፡፡**

ኢብን ዐባስ ባስተላለፉት መሰረት ፡- <<የአላህ መልእክተኛ ﷺ በሚና ሰዎችን በማሰገድ ላይ እያሉ፣ ያኔ ለአቅመ አዳም የደረስኩ ነበርኩ፤ አንድ እንስት አህያ ላይ የተቀመጠ ሰው አግኝቼ በአንዳንዶቹ የሶላት ሰፎች ፊት ለፊት አቋርጬ አለፍኩና ከአህያዪቱ ወርጄ እንድ ግጥ ለቀቅኳት፤ ከዚያ ወደ ሶላት ሰፉ ገባሁ፤ ማንም ሰውም ድርጊቴን አልተቃወመም፡፡>> ብለዋል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

ኢማሙ ነወዊ፤ ይህ ሀዲስ የኢማሙ ሱትራ የሰጋጆች ሱትራ መሆን እንደሚችል ያሳያል ብለዋል።

> **ነቢዩ ﷺ ኢማምም ሆነ ለብቻው የሚሰግድ ሰው መከለያ ነገር ከፊት ለፊቱ እንዲደርግ አዘው አበረታተዋል።**

የኢማሙ ሱትራ የሰጋጆችም ሱትራ ስለሆነ በመካከል ሰው ማለፉ ሳይሆን የሚከለከለው በኢማሙ ፊት ማለፉ ነው።

ኢብኑ አብድልበር አልኢስቲዝካር በሚለው መፅሀፋቸው ላይ ይህንን ሲያስረዱ፤ የኢማሙ ሱትራ የሰጋጆችም ሱትራ እንደሆነ ከሚያስረዱት መካከል ሂሻም ኢብንል ጋዚ ከናፍእ ናፍእ ደግሞ ከኢብኑ ኡመር የዘገቡት ሀዲስ ነው።

ኢብኑ ኡመር እንዲህ ብለዋል፤ የአላህ መልእክተኛ ዙህርን ወይም አስርን እያሰገዱ ሳለ እንስሳ ከፊታቸው ልታልፍ ስትሞክር ሊመልሷት ሞከሩ፤ ማለፊያውን ሲያጠቡባትም ትኬሻቸው ግድግዳውን እንደነካ አይቻለው። ከዛም ከበስተጀርባቸው አለፈች።» ይህም ከበስተጀርባ ስላለፈች ነው።

*«የኢማሙ ሱትራ የተከታዮች ሱትራ ነው» የሚለውንም ከኢብኑ ኡመር አብዱረዛቅ ዘንድ ተዘግቧል።*

**2- በሰጋጅ ሰው ፊት አቋርጦ ማለፍ አይፈቀድም፡፡ ያለፈ ሰው ሀጢያተኛ ይሆናል፡፡**

ነቢዩ ﷺእንዲህ ብለዋል ፡- <<በሚሰግድ ሰው ፊት አቋርጦ የሚያልፍ ሰው ምን (ያህል ከባድ ኃጢአት) እንዳለበት ቢያውቅ ኖሮ አቋርጦት ከሚያልፍ አርባ መቆም የተሻለ በሆነለት ነበር፡፡>> አቡ ነድር - ዘጋቢው - አርባ ቀን ወር ወይም ዓመት ይበሉ አላውቅም ብለዋል፡፡ (በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ)

አቋርጦ ማለፉ ከመከለያ ወዲያ ወይም ሰጋጁ መከለያ ካላደረገ ከሱጁዱ ቦታ ራቅ ብሎ ከሆነ ግን ይፈቀዳል፡፡

3- ሰጋጁ አቋርጦት የሚያልፈውን ሰው መከልከል አለበት፡፡

አቡ ሰዒድ አልኹድሪ ነቢዩ ﷺ፡- <<አንዳችሁ ከሰዎች የሚከልለውን ነገር ከፊቱ አድርጎ ከሰገደና ሌላ ሰው ከፊትለፊቱ አቋርጦ ማለፍ ቢፈልግ ይገፍትረው፣እምቢ ካለም ይፋለመው፤ሰይጣን እንጂ ሌላ አይደለምና፡፡>> ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋል፡፡ ይህንንም በቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

4- ከእውቀት ባለቤት ዑለማእ መካከል ከፊሎቹ፤ «አስቸጋሪ ሁኔታን ማስወገድ» ከሚል አጠቃላይ መርሕ መሰረት በመካው የተከበረ መስጊድ ሰጋጅ ፊት ማቋረጥን ፈቅደዋል፡፡ ይህም በተከበረው መስጊድ ውስጥ ሰጋጅ ፊት አቋርጦ ማለፍን መከልከል በአብዛኛው ከባድ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ ነው፡፡

5- ወደ ግድግዳ ወይም ከመስጊድ ምሶሶዎች መካከል ወይም ከመደርደሪያዎች ወደ አንዱ በመጠጋት ወይም እንደ ዱላ ያለ ነገር በማኖር መከለያ ማድረግ ይቻላል፡፡

6- በሰጋጁና በመከለያው መካከል ያለው ርቀት በአንድ ፍየል መተላፊያ በሚበቃ ያህል ይሰላል፡፡

ሰህል እንዲህ ብለዋል፡-

***<<በአላህ መልእክተኛ ﷺመስገጃና በግድግዳው መካከል የፍየል መተላለፊያ ያህል ርቀት ነበር፡፡>> በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ***

### ማሳሰቢያ!

የሴት ሶላትን መቁረጥ ከላይ በሰፈረውና

<<ሶላቱን...ያቋርጥበታል>> በሚለው ሐዲስ ውስጥ ሴትን ከአህያና ከጥቁር ዉሻ ጋር የሚያነጻጽር ነገር የለበትም፡፡

የሦስቱ በአንድ ዐረፍተ ነገር አገባብ ውስጥ መገኘት፣ የሦስቱ ማለፍ ሶላት እንዲቋረጥ የሚያደርግበት ምክንያት አንድ ዓይነት ነው ማለት አይደለም፡፡

ማለትም ጥቁር ዉሻ ሶላት የሚቆርጥበት ምክንያት በአህያ ወይም በሴት ሁኔታ ሶላቱ ከሚቋረጥበት ምክንያት ጋር አንድ ነው ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህም በሐዲሱ ውስጥ እንደ ተጠቀሰው ጥቁር ዉሻ ሰይጣን መሆኑ አህያ ወይም ሴት ሰይጣን ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ሦስቱ በአንድ አገባብ ቢቀርቡም የተለያየ ምክንያት አላቸው፡፡ የዉሻው ምክያት ከተቀሩት ሁለቱ ተለይቶ በሐዲሱ የተጠቀሰ መሆኑ የተለያዩ መሆናቸውን እንጂ ተመሳሳይ መሆናቸውን አያመለክትም።

የሴቷ ሶላት መቁረጥ ከሰጋጁ ቀረብ ብላ አጠገቡ ማለፏ የወንዱን ስሜት ሊቀሰቅስና በሶላቱ ላይ ያለውን ተመስጦና ትኩረቱን ሊበታትንበት ይችል ይሆናል፡፡ ስለዚህም ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ከሌላው ወንድ ተላላፊ ይበልጥ ሴት ተላላፊ ትኩረቱን ትስባለች፡፡ ለዚህ ነው -ይበልጥ የሚያውቀው አላህ ነው - በሸሪዓው የሶላትን ተመስጦና ኹሹዕ ለመጠበቅ ሲባል የሴት ልጅን በሰጋጅ ፊት ማለፍ ሶላትን ከሚቆርጡት አንዱ ያደረጋት፡፡

Source: www.amharicfiqh.com
*ከማስተካከያና ጭማሪዎች ጋር የቀረበ።*

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ለዓለማት እዝነት

## የ «ሙሐመድ» ﷺ

አላህ ሰላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን

"ሙሐመድ "ﷺየታላቅ ሰው ስም የታላቅ ስብዕና መጠሪያ ነው። ስለ ሙሐመድ ﷺብዙ ማወቅ ይጠበቅብሀል:: የሚከተለው ፁሁፍ ስለ ማንነታቸው መሠረታዊ ዕውቀት ሊያስጨብጥህ ይሞክራል::

"ሙሐመድ "ﷺማን ናቸው?

አላህ እንዲህ ብሏል፦ "አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፤ ለእናንተ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል (አርአያነት) አላችሁ" (ሱረቱል አህዛብ 21)

"ሙሐመድ "ﷺአላህ የሠው ልጆች እርሱን ብቻ እንዲያመልኩና ለህዝቦቻቸው ጥሪ እንዲያቀርቡ ከላካቸው ተከታታይ ነቢያት የመጨረሻው ነብይ መሆናቸውን እኛ ሙስሊሞች እናምናለን:: አደም፣ ኑህ፣ ኢብራሒም፣ ኢስማኢል፣ ኢስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዩሱፍ፣ ሙሳ፣ ዳውድ፣ ሱለይማን፣ ዒሳ (በሁሉም ላይ የአላህ ሰላምና እና ሠላት ይሁን) አንድ አይነት ሰማያዊ መልዕክት ያነገቡ ተከታታይ ነቢያቶች ናቸው::

አላህ ለሙሳ ተውራትን አውርዶለታል:: የሰዎች እጅ ገብቶበት ከመበረዙ በፊት የነበረው ኦሪት ከአላህ የወረደ መልዕክት መሆኑን እናምናለን:: እንደዚሁ አላህ ለዒሳ የኢንጂል መልዕክት አውርዶለታል:: ወንጌልም ከመበረዙ በፊት ከአላህ የወረደ መልዕክት መሆኑን እናምናለን:: ቁርዓን በነብዩ ሙሐመድ ﷺላይ ወርዷል። ነገር ግን የመጨረሻ መልዕክት ነውና ከመበረዝ የተጠበቀ ነው:: ቁርአን ቀድመው ከአላህ ለሠው ልጆች የወረዱ መልዕክቶችን የሚያብራራ ሆኖ ወርዷል:: እኛ ሙስሊሞች በዚህ እናምናለን!!

ቁርዓን የህይወት መንገድ ነው:: የመልዕክተኛው ባለቤት የምዕመናን እናት አዒሻ ስለ ባህሪያቸው ተጠይቃ የሠጠችው መልስ "በመሬት ላይ የሚራመድ ቁርዓን ነበሩ" የሚል ነበር። ይህ ማለት በዕለታዊ የህይወት ውጣ ውረዶች ውስጥ የቁርዓንን አስተምህሮት ተግባራዊ ያደርጉ ነበር ማለት ነው:: መልዕክተኛው (ሠላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የቁርዓንን የላቁ አስተምህሮቶች ወደ ተግባር እንዴት እንደቀየሩ ከብዙ በጥቂቱ ለመመልከት እንሞክር::

## አዛኙ ነብይ

አላህ እንዲህ ብሏል፦ "(ሙሐመድ ﷺሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም::" ሱረቱል አንቢያ 107

የአላህ መልዕክተኛ ለሰዎች ጥሪ ሲያደርጉ ወደ ሰላት፣ ጾምና ምጽዋት ብቻ አልነበረም:: መልካም ስነ ምግባርም የጥሪያቸው አንድ አካል ነበር:: አንድ ሰው ከሌሎች ሠዎች ጋር ያለውን ግንኙነት መልካም ማድረጉ ስለ አላህ ባለው እምነት ላይ ትጽዕኖ እንደሚኖረው አስተምረዋል:: «ከእናንተ ውስጥ በላጩ የተሻለ ስነ-ምግባር ያለው ሰው ነው» በማለት ሙስሊሞችን አስተምረዋል።

እምነት የአንደበት ምስክርነት ብቻ አይደለም:: በልብ የሰፈረው እምነት በተግባርም መረጋገጥ ይኖርበታል:: በርካታ የመልዕክተኛው ምክሮች እምነት ከተግባር ጋር ያለውን ትስስር ግልጽ አድርገው አስቀምጠዋል::

«በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ጎረቤቱን አያስቸግር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ እንግዳውን ያክበር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካምን ይናገር ወይንም ዝም ይበል::» ይህን ሀዲስ ቡኻሪ በሐዲስ ስብስቦቹ ቁጥር 6018 ላይ አስፍሮታል::

እኘህ የመጨረሻ መልዕክተኛ በሠው ልጆች መካከል መተዛዘን እና መከባበር እንዲኖር በጽኑ አስተምረዋል:: ቡኻሪ በቁጥር 5997 በዘገቡት ሐዲስ «(ለሌሎች) የማያዝን አላህ አያዝንለትም» በማለት የተናገሩትን እዚህ ላይ መጥቀስ ይቻላል::

በሌላ ነብያዊ ሐዲስ፤ አንዳንድ ባልደረቦቻቸው አላህ በጣኦታዊያን ላይ ቅጣቱን እንዲያወርድ ዱዓ ያደርጉ ዘንድ ጥያቄ ማቅረባቸውን ተወስቷል:: መልዕክተኛው ይህን ጥያቄ ለመቀበል ፍቃደኛ አልነበሩም:: የሰጡት ምላሽ «ተራጋሚ ሆኜ አልተላኩም፤የተላኩት ለእዝነት ነው » የሚል ነበር:: ሀዲሱን ሙስሊም በቁጥር 2599 ዘግበውታል።

## ይቅር ባዩ ነብይ

አላህ እንዲህ ብሏል፦

"ይቅርታም ያድርጉ:: (ጥፋተኞቹን) ይለፉም:: አላህ ለእናንተ ሊምር አትወዱምን አላህም መሓሪ አዛኝ ነው::" ሡረቱል ኑር 22



የአላህ መልዕክተኛ በጣም ይቅር ባይ ነበሩ:: ልባቸው ንፁህ ነበር። በርግጥስ ቁርዓን ከወረደበት ከዚያ ድንቅ ልብ እንዴት ገር አይሁን? ሠዎች ለሚፈጽሙባቸው መጥፎና አስቸጋሪ ድርጊቶች ይቅርታን ይለግሱ ነበር:: ሰዎች በርሳቸው ላይ የሚፈጽሙት ክፋት በጠነከረና በጨመረ ቁጥር ትዕግስትና ይቅር ባይነታቸው ይጨምር ነበር። በተለይም የሀይል ሚዛኑ ወደርሳቸው አድልቶ ጠላቶች በቁጥጥራቸው ስር ከሆኑ በኋላ ቻይ እና ይቅር ባይ መሆናቸው በገሀድ ታይቷል::

የረሡል ይቅር ባይነት የአንድ ሰሞን ግዜያዊ መገለጫ አልነበረም:: በሁሉም አስቸጋሪ እና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አብሯቸው ዘልቋል:: ብዙ በደሎች ቢፈራረሩቁባቸውም ይቅርታ አድራጊነታቸውን የሚፈታተኑ አልነበረም። በተከበረው ቁርዓን ላይ የሰፈረውን መልዕክት በተጨባጭ ተግብረዋል::

"ገር ፀባይን ያዝ:: በመልካምም እዘዝ:: ባለጌዎቹንም ተዋቸው::" (አዕራፍ 199) . . .

## እኩልነትና የዘር መድሎ

አላህ እንዲህ ብሏል፦ "አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው" ሡረቱል ሁጅራት 13

ስለ ሰው ልጆች ክብርና እኩልነት ከሙሐመድ )ﷺ ሰላምና ሰላት በርሳቸው ላይ ይሁን) የተሻለ ያስተማረ ማን አለ? በአላህ ዕይታ የሰው ልጆች ሁሉ እኩል እንደሆኑ አስተምረዋል:: ለዚህም ተከታዮቹን ሀዲሶች ማስተዋል በቂ ነው።

"የሁላችሁም አባት አደም ነው:: አደም (የተፈጠረው) ከአፈር ነው:: በዘሩ ወይንም በቆዳው ቀለም ምክንያት፤ ዓረብ የሆነው ዓረብ ባልሆነው ላይ፣ ጥቁሩ በነጩ ላይ ብልጫ የለውም:: ማንኛውም ሰው የተለየ በላጭነትና ክብር የሚያገኘው አላህን በመፍራት ብቻ ነው::" አህመድ በሀዲስ ቁጥር 23489 ዘግበውታል:: የሰው ልጆች በዘራቸውና በቆዳቸው ቀለም ምክንያት መናቅና መገለል እንዳይደርስባቸው እኩልነትን የሰበከ መልዕክት ነው::

በሌላ ሐዲስ ረሱል የሚከተለውን ብለው አስተምረዋል፤ «አላህ ወደ መልካችሁ እና ገንዘቦቻችሁ አይመለከትም:: ነገር ግን ወደ ልባችሁና ተግባራችሁ ይመለከታል» ሙስሊም በሐዲስ በቁጥር 2564 ዘግበውታል።

ቡኻሪ በዘገቡት ሌላ ሐዲስ፤ ከባልደረቦቻቸው መካከል አንዱ ‹‹የጥቁር ሴት ልጅ›› በማለት ተገቢ ባለሆነ መልኩ ሌላውን ሰው ሲጠራ ተሠማ:: የአላህ መልዕክተኛ በጣም ተቆጡ:: "በእናቱ (የቆዳ ቀለም) ልታነውረው ሞከርክን? አንተ በርግጥ መሐይምነት በውስጥህ ያለብህ ሰው ነህ" በማለት ወረፉት::

## መጥፎን በመልካም የሚመልስ ነብይ

አላህ እንዲህ ብሏል፦ "መልካሚቱና ክፉይቱም (ጸባይ) አይስተካከሉም:: በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ጸባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር:: ያን ጊዜ ያ ባንተና በእርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይኾናል::"

ሱረቱል ፉሲለት 34

መጥፎን ተግባር በመጥፎ አለመመለስ የመልዕክተኛው መገለጫ ነበር።«የአላህ መልዕክተኛ መጥፎን በመጥፎ፣ ክፋትን በክፋት አይመልሱም ነበር:: ይልቁንም ይቅር ባይ ነበሩ» ቡኻሪ በሀዲስ ቁጥር 4838 ዘግበውታል

ኢስላማዊ የታሪክ ድርሳናት፤ ታላቁ ነብይ ሙሐመድ ﷺየበደሏቸውን ሊበቀሉ የሚችሉባቸው ብዙ አጋጣሚዎች እንደነበሩና ሆኖም መበቀል እየቻሉ ይቅር ማለታቸውን በሚያስረዱ በርካታ ክስተቶች ታጭቀዋል::

አስቸጋሪና አስጨናቂ የህይወት ምዕራፎችን በጠንካራ ትዕግስት መጋፈጥ እንደሚያስፈልግ አስተምረዋል:: «ጠንካራ ሠው በትግል የሚያሸንፍ አይደለም:: ጠንካራ ሰው በቁጣ ወቅት እራሱን የሚቆጣጠር ነው» በማለት ምክር ሰጥተዋል::(ቡኻሪ 6114)

እርግጥ ነው ትዕግስትና መቻቻል እንዲሁም መጥፎን በመልካም መመለስ አንድ ሙስሊም ለራሱ የሚሠጠውን ግምትና ክብር አሉታዊ አያደርገውም:: ጥቃትና የሙብት ጥሰት ቢፈፀምበትም በዝምታ ይመልከት ማለትም አይደለም:: በደልን ከራስ ላይ የመከላከል መብትን ኢስላም ያከብራል:: በይቅርታ ማለፍን ግን ያበረታታል::

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞርል . . . . . . . . .

*ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .*

## ድርቅና የማያውቀው ጸባየ ለስላሳ

አላህ እንዲህ ብሏል፡- "ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብክላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር" አል ዒምራን 159

አነስ ኢብን ማሊክ ለ10 ዓመታት ከመልዕክተኛው ጋር በቅርብ አብሮነት ያገለገለ እድለኛ ወጣት ነበር፡፡ አነስ ስለ ባህሪያቸው እንዲህ ሲል ይናገራል፡፡ «በፍፁም አንድ ነገር ካደረግኩ በኋላ ለምን ይህን አደረግክ ብለው ወቀሳ ሰንዝረውብኝ አያውቁም፤ ያልሰራሁት ነገር ኖሮም (በወቀሳ) ለምን ይህን ነገር አልሠራህም ብለውኝ አያውቁም፡፡» አህመድ 12784 ዘግበውታል

አንድ ሰው የመልዕክተኛውን ክብር ዝቅ ለማድረግ ሞከረ፡፡ ባለቤታቸው አዒሻ ተቆጣች፡እርሳቸው ግን እንድታረጋጋ መከሯት፡፡ "አዒሻ ሆይ ተረጋጊ! አላህ ሩህሩህ ነው፤ በሁሉም ነገሮች ላይ ለስላሳነትን ይወዳል" ሲሉ ገሠጿት። ቡኻሪ በቁጥር 6024 ዘግበውታል

በሌላ ዘገባ ደግሞ «ማንኛውንም ነገር ውስጥ እዝነትና ልስላሴ ሲኖሩ ውበትን ያላብሱታል። ከምንም ነገር ላይ ሲጎድሉ ደግሞ ያጠለሹታል» በማለት መናገራቸውን ሙስሊም በቁጥር 2594 ዘግበውታል

## ከኩራት የራቀ ከሰዎች ተናናሽ

አላህ እንዲህ ብሏል፡- "የአልረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚኼዱት፣ ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው፡፡" ፉርቃን ፡ 63

የአላህ መልዕክተኛ ከኩራት የፀዳ ስብዕና ነበራቸው፡፡ ሲገቡ በደረሱበት ክፍት ቦታ ይቀመጣሉ፡ሰዎች ለርሳቸው ክብር ከመቀመጫቸው እንዳይነሱ ዘወትር ይከለክላሉ፡፡ ከባልደረቦቻቸው ለየት ያለ ልብስ አያደርጉም፡፡ ከችግረኛ ድሆች እንዲሁም እድሜያቸው ከገፋ ሽማግሌዎች ጋር ቆይታ ያደርጋሉ፡፡ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ረዳት አልባ ሴቶች ድጋፍ እንዲያገኙ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ ከሌሎች ተለይተው መታየትን ስለማይፈልጉ በሰዎች ምካከል ሲሆኑ እንግዳ ሰው አይለያቸዉም ነበር፡፡

ለሶሀቦቻቸው ከኩራት ስለመጽዳትና ራስን ዝቅ ስለማድረግ አስተምረዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ «ከኩራት በመራቅ ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ አንዳችሁ በሌላው ላይ ራሱን የበላይ ለማድረግ ትምክህት አይግባው፤ አንዳችሁ በሌላው ላይ ወሰን አይለፍ የሚል መልዕክት አላህ አውርዶልኛል» ብለው መናገራቸውን ሙስሊም በሐዲስ ቁጥር 2865 ዘግቧል፡፡

የአላህ መልዕክተኛ ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና ከአላህ ውጭ ለእርሳቸው አምልኮ እንዳይፈጸም በመስጋት ውዳሴንና ሙገሳን አይፈልጉም ነበር፡፡

« ክርስቲያኖች የመርየም ልጅ ዒሳን ከፍ ከፍ በማድረግ (ወሰን እንዳለፉት) እኔንም ከፍ በማድረግ (ወሰን አትለፉ) እኔ የአላህ ባሪያ ነኝና "የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ" ስትሉ ጥሩኝ» በማለት ተናግረዋል፡፡ ይህን ሐዲስ ቡኻሪ የሐዲስ ስብስብ ስራው ላይ በቁጥር 3445 አስፍሮት ይገኛል፡፡

. . .

## ተምሳሌታዊ የትዳር አጋር

*አላህ እንዲህ ብሏል፡- «"ሴቶችን"...በመልካምም ተኗኗሩዋቸው» ኒሳእ ፡ 19*

ለዓለማት እዝነት የተላኩት ነብይ ለትዳር አጋራቸው ተገቢውን ውዴታ፤ ክብርና እንክብካቤ የሚለግሱ ተምሳሌታዊ የትዳር አጋር ነበሩ። አጅግ የሚወዷት ውዷ ባለቤታቸው የሙዕሚኖች እናት አዒሻ ይህን ምስክርነት ሰጥታለች፡፡ «የአላህ መልዕክተኛ በቤት ውስጥ የትዳር አጋራቸውን (በስራ) ያግዙ ነበር፡፡ ልብሳቸውን ይሰፉና ጫማቸውን ይጠግኑ ነበር፡፡ እንደማንኛውም ሰው የቤት ውስጥ ስራዎችን ያከናዉኑ ነበር፡፡» አህመድ በቁጥር 25341 ዘግበውታል

ሙሐመድ ﷺሙስሊሞች ሁሉ የእርሳቸውን ፈለግ እንዲከተሉና ለትዳር አጋራቸው መልካም የህይወት ጓደኛ እንዲሆኑ ምክር ሰጥተዋል፡፡ «የተሟላ እምነት ያለው አማኝ የተሻለ ስነ ምግባር ያለውና ለትዳር አጋሩ በተሻለ ጥሩ የሆውነ ነው» አህመድ በቁጥር 24204 ዘግበውታል

## ፈለጉን ሊከተሉለት የሚገባ ድንቅ አርአያ

አላህ እንዲህ ብሏል፡- "አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ!" ሡረቱል ቀለም 4

በጥቂቱ የነብዩ ሙሐመድ ﷺን ማንነት ለመጥቀስ ተሞክሯል። ስለ ኢስላምና ሰለዚህ ታላቅ ስብዕና አንዳንድ መገናኛ ብዙሀን የሚነዙትን መሠረተ-ቢስ አሉባልታዎች መሰረት በማድረግ እይታቸውን ለገነቡ ሰዎች እነዚህ በእዝነት የተሞሉ እውነታዎች እንግዳ ሊሆኑባው ይችላሉ፡፡

ኢስላምን ለመረዳት ካሰብን የኢስላም መሠረታዊ ምንጮች የሆኑትን ቁርዓንንና እና የመልክተኛውን አስተምህሮ መሰረት ማድረግ ግድ ይለናል፡፡ ከአንዳንድ ሙሰሊሞች የተዛነፉ ተግባራት በመነሳት ኢስላም ላይ አሉታዊ አቋም መያዝ ከፍትሀዊነት የራቀ ይሆናል፡፡

> **አንድ ሰው የመልዕክተኛውን ክብር ዝቅ ለማድረግ ሞከረ። ባለቤታቸው ዐኢሻ ተቆጣች፡ እርሳቸው ግን እንድታረጋጋ መከሯት። "*ዐኢሻ ሆይ ተረጋጊ!* አላህ ሩህሩህ ነው፤ በሁሉም ነገሮች ላይ ለስላሳነትን ይወዳል" ሲሉ ገሠጿት።**

## ሙስሊም ያልሆኑት ታዋቂ ሰዎች ስለነብያችን ምን አሉ?

የህንድ ነጻነት እንቅስቃሴ የፖለቲካ መሪ ማህተመ ጋንዲ እንዲህ ብሏል፤ "መልዕክተኛው እራሱን አለማካበዱ፣ ለገባው ቃል እውነተኛነቱ፣ ለጓደኞቹና ለምዕመናን ታማኝነቱ፣ በአምላኩና በያዘው ተልዕኮ ያሳየው ሙሉ መተማመን እና መሰል ባህሪያቱ እንጂ ችግሮችን ለመወጣት የበቃው በሰይፍ አልነበረም!!"

ታዋቂው እንግሊዛዊ ደራሲ ጆርጅ በረናርድ ሾው ስለሳቸው እንዲህ ብሏል፤ «ዛሬ ላይ ዓለም ችግሮቹን የሚፈታለት እንደ ሙሐመድ ﷺአይነት ስብዕና በእጅጉ ያስፈልገዋል፡፡ በመሐከለኛው ዘመን የኖሩ የሀይማኖት አባቶች በዕውቀት ማነስ ወይም በጭፍን ጥላቻቸው ምክንያት ስለ ሙሐመድ ﷺሃይማኖት የተዛባ ጨለምተኛ ምስል ለማስቀመጥ ሞክረዋል፡፡ የክርስትና ጠላት አድርገው ስለውታል፡፡ በግሌ ስለዚህ ሰው ማንነት ባደረግኩት ጥናት የድንቅ ተዐምራዊ ስብዕና ባለቤት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በጭራሽ የክርስትና ጠላት እንዳልሆነ ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ፡፡ እንዲያውም የሠው ልጆች መድህን ተብሎ ሊሠየም ይገባዋል፡፡ በግል አስቴያየቴ ዛሬ የዓለም ጉዳዩችን ሙሐመድ ﷺቢመራቸው የሰው ልጆች የሚናፍቁትን ሠላምና ደስታ በማረጋገጥ ችግሮቻቸውን እንደሚቀረፍ አምናለሁ፡፡ የአውሮፓን ግዛት እንደ ሙሐመድ ﷺአይነት ሰው ቢመራው ከህመሞቹ ሁሉ እንደሚፈውሰው አምናለው።አዎን! ሙሐመድ ﷺየሰው ልጆች መድህን ተብሎ ሊጠራ ይገባል!»

∞∞∞∞≌≌≌≌∞∞∞∞

# ዲራያ

## ልብህን መርምር!

عن أبي هريرة رضي الله عنه قال :قال رسول الله ﷺ" :إن الله لا ينظر إلى أجسامكم، ولا إلى صوركم، ولكن ينظر إلى قلوبكم "رواه مسلم

አቡ-ሑረይራ (ረዲየላሁ ዓንሁ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል ....

***"አላህ ወደ ሰውነታቻሁና መልካቻሁ አይመለከትም። ነገር ግን የሚመለከተው ወደ ልባችሁ ነው" ሙስሊም ዘግበውታል***

በሌላ ዘገባ ላይ የመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ***"ልባችሁንና ስራችሁን ይመለከታል"*** በሚል ተላልፏል።

### የሐዲሡ አስተላላፊ አጭር ታሪክ

አቡ-ሑረይራ ሙሉ ስማቸው አብደረሕማን ኢብኑ ሰኽር ሲሆን ነቢዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መካ ሳሉ ኢስላምን ተቀብለው ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው በመመለስ ብዙ ግዜ ከቆዩ በኋላ በሒጅራ ሰባተኛው አመት ወደ መዲና መጥተው አራት አመት ያክል ከነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ጋር አሳልፈዋል። በቆይታቸውም የሰሟቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ሐዲሶች ጠብቀው በማስተላለፍ የሚታወቁ ታላቅ ሶሐቢይ ናቸው።

አቡ-ሑረይራ ከነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ህልፈት በኋላ ለአጭር ግዜ የባህሬን አስተዳዳሪ ሁነው ከመስራታቸው ውጭ ቀሪ ህይወታቸውን ያሳለፉት መዲና ውስጥ የሀፈዙትን ሐዲስ በማስተማር ነበር። አቡ-ሑረይራ ለሙስሊሞች ትልቁ ባለውለታ ሲሆኑ በተወለዱ በ78 አመታቸው ወደ አኺይራ ሄደዋል።

### ከሐዲሡ የምንማራቸው ቁም ነገሮች

1. መመልከት ከአላህ ባህሪያት አንዱ እንደሆነ።

2. ይህን የአላህ ባህሪ ልክ እንደሌሎቹ በትክክለኛ ማስረጃ የመጡ ባህርያቱ ሁሉ ያለማመሳሰል መቀበል እንደሚገባ።

3. መልክ ወይም አካላዊ ሙሉእነት አላህ ዘንድ መመዘኛ መስፈርት እንዳልሆነ።

4. ሰዎች አላህ ዘንድ ደረጃ የሚኖራቸው በልባቸው ባስቀመጡት እምነት እና ኒያ እንዲሁም በተግባራቸው መሆኑ።

5. አላህ የሰዎችን እምነት እና ኒያ የሚመለከት ውስጥ አዋቂ ጌታ መሆኑ።

6. ሰው በልቡ ባመነው እንዲሁም ባቀደው ኒያ ምንዳ እንደሚከፈለው።

7. እምነትን ማፅዳት እና ከግድፈት መጠበቅ እንደሚገባ

8. ኒያን ለአላህ ብሎ በማድረግ ኢኽላስን ማጥራት እንደሚገባ

### የሐዲሱ ዘጋቢ አጭር ታሪክ

ሐዲሱን የዘገቡት ታላቁ የሐዲስ ሊቅ ኢማም ሙስሊም ኢብን ሓጃጅ አልቁሽይሪ (ረሂመሁላህ) ሲሆኑ የዛሬዋ ኢራን በሺዓዎች ሳትሞላ በፊት በ204 ሂ. ኒይሳቡር በተባለ አካባቢ ነበር የተወለዱት።

ህይወታቸውን ሸሪዓዊ እውቀት በተለይም ሐዲስን በማጥናት ያሳለፉት እኚህ ሊቅ መምህራቸው ኢማም ቡኻሪ ካዘጋጁት ሰሒሕ አልቡኻሪ በመቀጠል ታማኝ የሆነ ትክክለኛ የሆኑ ሐዲሶችን ያሰባሰቡበት ሰሒሕ ሙስሊም የተሰኘ ኪታብ አበርክተውልናል።

አላህ ባስተላለፉልን ዕውቀት ተጠቃሚ ያድርገን እሳቸውንም ምንዳቸውን ያብዛላቸው።

∞∞∞∞≌≌≌≌∞∞∞∞

# የኑሕ መርከብ

## ውዴታን በተግባር !

ምስጋናና ውዳሴ ለአላህ ነው። አላህ በታላቁ ነብይ ላይ ሰላምና እዝነቱን እንድያወርድላቸው እንጠይቃለን። ከመሀይምነት ጽልመት ወደ ኢማን ብርሀን ያወጡን ዘንድ ለተላኩትታላቅ ነቢይ፣ ለእሳቸዉ ያለን ውዴታና አክብሮት እጅግ የላቀ ነዉ ፤በእሳቸዉ ፈለግ ላይ እንዲያፀናን አላህን እንማፀነዋለን። አዎን! የእኚህን ታላቅ መልዕክተኛ ቃል እንድናከብር፣ ፋናቸውን እንድንከተል፣ ስብናቸውን እንድንላበስለ፣ ከልጅ፣ ከእናት፣ ከአባት፣ከሰዎች በሙሉ አስበልጠን! እንድንወዳቸው በሱረቱ ተውባ ምዕራፍ፣ቁጥር 24 በአፅንኦት ተመክረናል።

﴿ قُلْ إِنْ كَانَ آبَاؤُكُمْ وَأَبْنَاؤُكُمْ وَإِخْوَانُكُمْ وَأَزْوَاجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَالٌ اقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَارَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَاكِنُ تَرْضَوْنَهَا أَحَبَّ إِلَيْكُمْ مِنَ اللَّهِ وَرَسُولِهِ وَجِهَادٍ فِي سَبِيلِهِ فَتَرَبَّصُوا حَتَّى يَأْتِيَ اللَّهُ بِأَمْرِهِ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الْفَاسِقِينَ﴾ التوبة 24

((አባቶቻቹህን ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻቹህም ፣ ሚስቶቻቹህም ፣ ዘመዶቻቹህም፣የሰበሰባኋቸው ሀብቶችም ፣መክሰርዋን የምትፈሩዋት ንግድም፣ የምትዎድዋቸው መኖርያዎችም እናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልእክተኛው፣በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እንዲሆኑ አላህ ትእዛዙን እስከምያመጣ ድረስ ተጠባበቁ በላቸው ፣አላህም አመጸኞች ሕዝቦችን አይምርም፡፡))አል-ተውባ 24

ይህ አንቀፅ ልጆቻችን ፣ ሚስቶቻችንንና፣ አባቶቻችንን ከምንወደው የበለጠ ነብዩን ﷺ መውደድ እንዳለብን ያስገነዝበናል፣ ይህም ብቻ አይደለም ፤ይህን ላላደረጉ «ተጠባበቁ!» በማለት ዝቶባቸዋል ፤አመፀኞች መሆናቸውም ገልፆልናል ።ግን የነብዩ እውነተኛ ወዳጆች እነማን ናቸው ? በእሳቸው መመርያ የፀኑት ፣ትዕዛዛቸውን የተገበሩት ፣ከፈለጋቸው ጭራሽ ያላፈነገጡት ፤ወይስ «ነብዩን በመውደድ»በሚል ሽፋን ዝንባሌያቸውን በመከተል ያማራቸውን የፈጠራ ተግባር የሚያራምዱት ?!እስኪ የእውነተኛ ውዴታን መመዘኛ አስመልክቶ የቁርኣን መመዘኛ እናስተውል፡-

﴿ قُلْ إِنْ كُنْتُمْ تُحِبُّونَ اللَّهَ فَاتَّبِعُونِي يُحْبِبْكُمُ اللَّهُ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ * ﴾ آل عمران 31-32

*((አላህን የምትወዱ ከሆናቹህ ተከተሉኝ፤አላህ ይወዳችኋልና ፤ሀጢአቶቻቹህንም ለናንተ ይምራልና ፤አላህም መሐሪ አዛኝ ነው ፡-በላቸው፡፡))(አል-ዒምራን፡ 31)*

ታዲያ ነቢዩን ( (ﷺመከተል የዉዴታችን መለኪያ እንደሆነ ከተረዳን በዲን ጉዳይ ላይ እሳቸው የሰሩትን መስራትና የተዉትንም መተው ይጠበቅብናል። ወደ ጌታችን የሚያቃርቡንን መንገዶችና የእርሱን ውዴታ እንድንጎናፀፍ የሚያስችሉንን የአምልኮ ተግባራት ያለመለኮታዊ መመሪያ በዘፈቀደ ልናውቃቸውና ልንተገብራቸዉ አንችልም! ለህዝቦቻቸው አርዓያና ተምሳሌት የሆኑ ነቢያት የመላካቸው ዋነኛ ምክንያትም ይህ ነዉ። የተከበሩት መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

*‹‹ለህዝቦቹ የሚያውቀውን መልካም ነገር መጠቆምና ከሚያውቅላቸው ከፉ ነገር ማስጠንቀቅ ግዴታ ቢሆንበት አንጂ ከእኔ በፊት (አንድም) ነቢይ አልነበረም››*

ስለዚህም ተወዳጁ ነቢያችን በዲን ጉዳይ ላይ ጠቃሚ ሆኖ ሳያስተምሩት ያለፉት ርዕስ የለም !! ወደ አላህ ውዴታ የሚያቃርቡንን የአምልኮ ተግባራት በሙሉ በጌታቸው መመሪያ መሰረት ቅንጣት ያክል ሳያጓድሉ በአግባቡ አስተላልፈዋል።

ስለሆነም በዲን ጉዳይ አዲስ የፈጠራ ተግባራት በሙሉ በተለያዩ ቁርአናዊና ሀዲሳዊ መረጃዎች መሰረት የተወገዙ ናቸው::

**ወደ ጌታችን የሚያቃርቡንን መንገዶችና የእርሱን ውዴታ እንድንጎናፀፍ የሚያስችሉንን የአምልኮ ተግባራት ያለመለኮታዊ መመሪያ በዘፈቀደ ልናውቃቸውና ልንተገብራቸዉ አንችልም!**

## የፈጠራ (የቢደዓ) ተግባር ሁለት ዐይነት ነው፤

**አንደኛው** ከነአካቴው ከሸሪዓ ምንም መሠረት የሌለው ሲሆን

**ሁለተኛው** ደግሞ ተግባሩ በጥቅሉ ሸሪዓዊ ድንጋጌ ቢኖረውም አተገባበሩ ላይ በጊዜ፣ወይም ቦታ፣ ወይም በመጠን(በቁጥር) ፣ ወይም በሰበብ፣ ወይም በሆነ የአፈጻጸም ስርዓት ያለመረጃ ሲገደብ ፤ኢሊያም ሸሪዓዊ ገደቡ ሲነሳ ነው፡፡ ሁለቱም ዓይነቶች የተወገዙ ናቸው! ፤ አላህ በተከበረው ቁርአኑ ይህንን ጠቁሞናል፤

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا [٥:٣]

*‹‹አላህ ከሂይማኖት በርሱ ያልፈቀደውን ለእነርሱ የደነገጉ ተጋሪዎች አሏቸውን?!››*

ከዚህ አንቀፅ አላህ ያልፈቀደውን ዲን መደንገግ እንደማይቻል እንመለከታለ፡፡

ረሱል ﷺእንዲህ ብለዋል፡-

*‹‹በዚህ በጉዳያችን (በዲናችን) ከእርሱ ያልሆነን ነገር የፈጠረ (ስራው) ተመላሽ ነው።››*

በሌላም ዘገባ ላይ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ትዕዛዛችን የሌለበትን ስራ የሰራ (ስራው) ተመላሽ ነው።››

እንደዚሁም በጁሙዓ ኹጥባቸው መግቢያ ላይ የሚከተለውን ይሉ እንደነበር ተዘግቧል፡-

*‹‹የንግግር ሁሉ የተሻለው የአላህ መፅሐፍ ነው፤ከመመሪያ ሁሉ በላጩ የሙሀመድ ((ﷺመመሪያ ነው፤ የነገሮች ሁሉ መጥፎ አዳዲስ ነገሮች ናቸው፤ ሁሉም የፈጠራ ተግባር ጥመት ነው...።*

ይህንንም ጉዳይ በአደራ አፅንተው ነበር ወደ አኺራ ያለፉት፤ እንዲህም አሉ ፡-

*‹‹የእኔን እና ቅን፣ የተመሩ የሆኑ ምትኮቼን ፈለግ በመከተል ላይ አደራችሁን! (ይህችን ፈለጌን) አጥብቃችሁ ያዟት! አደራችሁን! አዳዲስ ነገሮችን ተጠንቀቁ! አዲስ ነገር ሁሉም ፈጠራ ነው፤ ሁሉም ፈጠራ ደግሞ ጥመት ነው››*

በሌላም ሃዲሳቸው እንዲህ ይላሉ፡- «የርሱን ፈለግ የሚይዙና ተእዛዙን የሚከተሉ ረዳቶች ጓደኞች ከህዝቦቹ ቢኖሩት እንጂ አላህ ነብይን አልላከም ፤ከዚያም ከእነሱ በኋላ የማይሰሩትን የሚናገሩና ያልታዘዙትን የሚሰሩ ይተካሉ፡፡(እነኝህ) በእጁ የታገላቸው ሙዕሚን ነው፤በምላሱም የታገላቸው ሙዕሚን ነው፤በልቡ የታገላቸው ሙዕሚን ነው፣ከዚህ በኋላ የሰነፍጭ ፍሬ ያክል እንኳ ኢማን የለም»

ያልታዘዙትን የሚሠሩትን አስመልክቶ ***«የታገላቸው ሙዕሚን ነው»ማለታቸው ያልታዘዝነውን ነገር ጥሩ ቢመስልም ከዲናችን በመቁጠር ለመስራት መሞከራችው ተገቢ ያለመሆኑ ነው፤በ«ምናለበት»*** ፈሊጥ ራሳችንን ለአዲጋ መዳረግ አይኖርብንም !

ወደ ቀጣይ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

ይህ ዲን የሞላ ነው!! መሙላቱን በቁርዓን አውስቷል፡፡

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا [٥:٣]

***((ዛሬ ሀይማኖታቹህን ሞላሁላችሁ፤ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ ፤ለናንተም ኢሰላምን ከሀይማኖት በኩል ወደደኩ፡፡))***

ይህንን አንቀፅ አስመልክተው አልኢማሙ ማሊክ እንዲህ ይላሉ፡- «በኢስላም ውስጥ አዲስ ነገርን ፈጥሮ ጥሩ መሰላ ከታየቸው ነብዩን መልእክታቸውን አጓድለዋል ብሎ ጠርጥሯል፤ያኔ ዲን ያልነበረ ዛሬ ዲን አይሆንም!

ከዚህ አንቀፅ በኋላ የቁርአን አንቀፅ ቢወርድም ግን በጣም ውስን ነው ፡፡አንዳንድ ሰሓባዎችም የመጨረሻ ነው ይላሉ፡፡የረሱል ምርጥ ሰሀቦችና ተተኪዎቻቸው ከላይ የተጠቀሰውን ነቢያዊ ፈለግ በመከተላቸው ቢድዓን ነቅፈውና ተዋግተው ዲናቸውን ከአዳዲስ ልጣፊዎች ጠብቀው አደራቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል፡፡

ታላቁ ሰሀቢይ ሁዘይፋ አብኑል የማን እንዲህ ይላሉ፡

<<ማንኛውም የመልዕክተኛው ሰሃቦች ባልሰሩት የዒባዳ ተግባር አምልኮን አትፈፅሙ!የመጀመሪያዎቹ ለመጨረሻዎቹ ምንም አልተዉም! >>

ዓብዱላህ ኢብን ዑመር እንዲህ ይላሉ፡-

<<ሁሉም የቢድዓ ተግባር ጥመት ነው ! ሰዎች መልካም አድርገው ቢያየዩት እነኳ >> አንድ ቀን አቡ ሙሳ አል - አሽዓሪ ወደ ዓብዱላህ ኢብኑ መስኡድ ቤት ይመጡና እንዲህ ይለዋቸዋል፡- «አሁን መስጂድ ውስጥ የሚነቀፍ ነገር ተመለከትኩ።» «ምንድነው>? አሉ ኢብኑ መስዑድ አቡ ሙሳም <በሕይወት ካለህ ታየዋለህ! ሰዎች መስጊድ ውስጥ ሆነው ክብ ሰርተው ተቀምጠው ሶላትን ይጠባበቃሉ፤ ከተሰበሰቡት አንዱ በእጁ ጠጠር ይዞ፡- «አንድ መቶ ጊዜ ተክቢራ አድርጉ፣አንድ መቶ ተስቢህ፣ አንድ መቶ ተህሊል እያለ ያዝዛቸዋል። እነሱም መቶ፣ መቶ ጊዜ ይላሉ> አሉ ኢብኑ መስዑድም <ምን አልካቸው ታዲያ?>ብለዉ ይጠይቋቸዋል። አቡ ሙሳም <ምንም አላልኩም፣ የአንተን አስተያየት በመጠበቅ! > ኢብኑ መስዑድም <ታዲያ ለምን ወንጀላቸውን እንዲቆጥሩ በመንገር፣ በጎ ተግባራቸውን ግን አላህ ዘንድ እንደማያጡት ዋስ አትሆናቸውም?> ከዚያም ወደ መስጊድ ገቡ። ወደ ተሰበሰቡት ሰዎች በመምጣትም<ምንድው መሥራት የያዛችሁት? ወንጀላችሁን ቁጠሩ፣ጥሩ ሥራችሁን ግን አላህ ዘንድ እንደማታጡት ቃል እገባላችኋለሁ። የ ሙሀመድ ﷺኡመቶች! ለመጥፋት ምን አስቸኮላችሁ። የነቢዩ((ﷺ ሰሀቦች ሞልተዋል፤ የነቢዩም ﷺልብስ(ገና)አላለቀም፤ ዕቃቸው እነኳ አልተሰበረም።ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! እናንተ ከነቢዩ ﷺመንገድ የበለጠ የተመራችሁ ናችሁ ወይም የጥመት በር ከፋች ናችሁ?!>አሏቸው። ሰዎቹም<አቡ አብዱራህማን እኛ እኮ ጥሩ አስበን እንጂ ሌላ አይደለም >አሉ።<ጥሩ እያሰቡ ግብ የማይመቱ ስንቶች አሉ ? ! ነቢዩ ﷺ እንደነገሩን፡-(ሰዎች ይመጣሉ፣ቁርዓን ይቀራሉ፤ግን ከጉሮሯቸው አይወርድም!)ምናልባት ብዙዎቹ ከእናንተ ሳይሆኑ አይቀሩም። …> ከዚያ ጥለዋቸው ሄዱ ፡፡እነዚህ ጥቅሶችና መረጃዎች ከብዙ በጥቂቱ ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች የቢድዓ መጥፎነት የሚያሳዩ ምረጃዎች ሲቀርቡላቸዉ <ቢድዓ ጥሩ ነዉ!> አይሉም፡፡ግን ከነዚህ ነብያዊ ዛቻዎች ለመዉጣት ሲፍጨረጨሩ <<ሁሉም ቢድዓ ጥመት ነው!!>> የሚለውን ጥቅል ነቢያዊ መርሆ የሚፃረር ግንዛቤ ያንፀባርቃሉ፤ <<ቢድዓ ሁለት ዓይነት ነው፡- ጥሩና መጠፎ>> ይላሉ!!

ለዚህም አባባላቸው ድጋፍ ይሆናቸው ዘንድ ሁለት መረጃዎችን!?>> ይጠቅሳሉ።

**ጥሩ እያሰቡ ግብ የማይመቱ ስንቶች አሉ ? ! ነቢዩ ﷺ እንደነገሩን፡- (ሰዎች ይመጣሉ ቁርዓን ይቀራሉ ግን ከጉሮሯቸው አይወርድም ! ) ምናልባት ብዙዎቹ ከእናንተ ሳይሆኑ አይቀሩም። ...>**

## (1) የመጀመሪያዉ ማጳናገሪያ (ሹብሀ)

መልዕክተኛው <በኢስላም ውስጥ የጥሩ ፈለግ ፈር የቀደደ ለርሱ የዚህ(ስራ) እና በዚህ (እርሱ በቀደደዉ ፈር) የሚሰራ ሰው ሁሉ ምንዳ አለው።ይህም ከእነሱ ምንዳ ምንም ሳይቀነስ ነዉ፤በኢስላም ውስጥም የመጥፎ ፈለግ ፈር የቀደደ ለርሱ የዚህ(ስራ) እና በዚህ (እርሱ በቀደደዉ ፈር) የሚሰራ ሰው ሁሉ ወንጀል አለበት - ከእነሱ ወንጀል ምንም ሳይቀነስ። ብለዋል፤ ይህ ደግሞ ቢድዓ ሁለት ዓይነት እንደሆነ ይጠቁማል>> ይላሉ! የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

1ኛ፡- ነቢዩ ﷺሲናገሩ <<በኢስላም ውስጥ>> ማለታቸው እነደሚጠቁመው በንግግራችዉ የፈለጉት በዲኑ ውስጥ ተደንግገው ያሉ መልካም ተግባራትን እንጂ እያንዳንዱ ሰው ጥሩ የመሰለውን ተግባር ይስራ ለማለት አይደለም። ይህንን የሚያጎላው ደግሞ የሚቀጥለው ነጥብ ነው፡

2ኛ፡- ነቢዩ ﷺይህንን ሀዲስ የተናገሩበት ምክኒያት ሰሃቦችን ሰደቃ አንዲሰጡ ሲያነሳሷቸው አንድ ሰሃብይ ቀድሞ በመስጠት ለሌሎቹ አርዓያ በመሆኑ ነው፤ ሰደቃ ደግሞ በሸሪዓ አስቀድሞ የተደነገገ ተግባር ነው።ስለሆነም አዲስ ፈጠራ ዲኑ ውስጥ ለሚጨምሩ ሰዎች በፍፁም ማበረታቻ ሊሆን አይችልም።

## (2) ሁለተኛው ማጳናገሪያ (ሹብሀ)

<<ሰዎች የተራዊህን ሰላት ተለያይተው በሚሰግዱ ጊዜ ኸሊፋው ዑመር ተሰባስበው እንዲሰግዱ ካደረጓቸው በኋላ “ምነኛ ያማረች ፈጠራ ናት!” ብለዋል።ስለዚህ ከቢድዓም ያማረ ቢድዓ አለ ማለት ነው! ይላሉ፡፡የዚህም ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

1ኛ፡- የተራዊህ ሰላት ሱና እንጂ ቢድዓ አይደለም! ነቢዩ ﷺየተወሰኑ ቀናት ሰርተው አቁመውታል፤ ምክንያታቸውንም ተናግረዋል፡- ዋጂብ (ግዴታ) እንዳይሆንብን ፈርተው ነው፣ ግን ከአላህ የሚተላለፈዉ ወህይ ከነቢዩ ﷺበኋላ ስለማይመጣ በዑመር ጊዜ ዋጂብ እንዳይሆንብን የሚፈራበት ምክንያት አልነበረም፤ ስለሆነም ነቢዩ ﷺ የጀመሩትን ሥራ ዑመር ቀጠሉት፣ ይህን ይበልጥ የሚያብራራው የሚቀጥለው ነጥብ ይሆናል፡-

2ኛ፡- በዲናችን የተከለከለዉ ቢድዓን መስራት ነዉ እንጂ ቢድዓ የሚለውን ቃል መጠቀም አይደለም።ቢድዓ እንደሌሎች ብዙ ቃላት ሸሪአዊና የቋንቋ ትርጉም አለው።ተቋርጦ እንደ አዲስ በመጀመሩ፤ ዑመር የፈለጉት ቋንቋዊ ትርጉሙን ነው።የሰሩትም ሥራ ሱናና መሰረት ያለው እንጂ አዲስ ፈጠራ አልነበረም።

3ኛ፡- ዑመር የሠሩት ሥራ በሰሀቦች ሁሉ ስምምነት የፀደቀ የኹለፋዎች ፈለግ በመሆኑ በሸሪዓ ቢድዓ አይባልም! ታዲያ ከላይ በተጠቀሱት አስረጂዎች የተኮነነው በዲን ስም የሚተገበረው የቢድዓ ዓይነት ነው እንጂ አንዳንድ ሰዎች <አዲስ ፈጠራ ማምጣት ይቻላል!> ብለዉ ለመሞገት ሲፈልጉ የሚጠቅሷቸዉ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቶች አይደሉም።

ነቢዩ ﷺበዋነኝነት ለማስተማር የተላኩት እነዚህን ዝርዝር የዱንያ ጉዳዮች አይደለም፤ ለመዲና ገበሬዎችም ይህንን ምላሽ ሰጥተዋል፡- “ስለ ዱንያ ጉዳያችሁ እናንተ ይበልጥ ታውቃላችሁ!”፡፡

ስለዚህ ቁርዓንን በአንድ ጥራዝ ማስቀመጥ፣የእስር ቤቶችን ማዘጋጀት፣ ስፒከርን መጠቀም የመሳሰሉት በመልእክተኛው ዘመን ባይከሰቱም ወጥ የዒባዳ ተግባራት ሳይሆኑ ወደ ኢባዳ የሚያደርሱ አጋዥ መዳረሻዎች ስለሆኑ ነው። እነዚህ ደግሞ (መሳሊህ ሙርሰላ) ይባላሉ፣ ከቢድዓ ጋር በፍፁም አይገናኙም ፡፡

∞∞∞∞≌≌≌≌∞∞∞∞

# ስለ - ኢስላም አጭር ማብራሪያ

ኢስላም የአኗኗር ሥርዓትን ሁሉ የሚቀርጽ የተሟላ የህይወት ቀመር ነው። ኢስላም ማንኛውም ሠው ከፈጣሪው ጋር ያለውን ትሥሥር እንዲያጠናክርና ከፍጡራን ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲያጎለብት ያበረታታል። ኢስላማዊ አስተምህሮቶች እንደሚያስረዱን፤ የሠው ልጅ እውነተኛ ውስጣዊ ሰላምን የሚያገኘው አላህን በማወቅ እና አላህ የደነገጋቸውን መልካም ስራዎች በመተግበር ብቻ ነው። እነዚህ መልካም ተግባራት ለራስዎም ይሁን ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ጠቃሚ ናቸው።

ኢስላም በአለማችን ውስጥ ብዙ ተከታይ ካለቸው ሀይማኖቶች መካከል ይመደባል። ከአለም ህዝብ 1/5ኛው ሙስሊሞች ናቸው። የአላህን አምላክነት ማመን፣ አምልኮንም በብቸኝነት ለእርሱ ብቻ መፈጸም የህይወት ግብ እና ኢስላም የተመሰረተበት ምሰሶ ነው።

ኢስላም የአረብኛ ቃል ሲሆን ለአንዱ አምላክ አላህ እራስን ዝቅ ማድረግና እጅ መስጠት የሚሉ ትርጉሞችን ያቀፈ ነው። ለአላህ ፍላጎት በራሱ ፍቃድ ያደረ ሁሉ ሙስሊም ይሠኛል። ለአላህ እጅ ከሰጠ የቆዳ ቀለሙ፣ ጾታውና የዘር ሀረጉ የሚያሳድሩት ትጽዕኖ ሳይኖር ሙስሊም ይባላል።

ኢስላምን ከሌሎች ሀይማኖቶች ልዩና ተመራጭ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ስያሜው ከግለሰብ ወይም ከጎሣ ጋር የተቆራኘ አለመሆኑ ነው።

## ስድስቱ የእምነት መሠረቶች

### 1. በአላህ ማመን

"አላህ" የሚለው ስያሜ፤ አምልኮ የተገባው የአንድዬው እውነተኛ አምላክ የተፀውዖ ስም ነው።

"አላህ" የሚለው በአረብኛ የአንዱ ብቸኛ አምላክ ነጠላ ስያሜ ነው። አላህ አጋሮች የሉትም አቻና ባላንጣዎች፣ ወላጆችና ልጆችም የሉትም። እንደሡ ያለ ምንም የለም ። ሁሉን ሰሚ ሁሉን ተመልካች አምላክ ነው። በተሟሉት ውብ ባህሪዎቹ ማንም አይጋራውም። ያማሩ ስሞችና የላቁ ባህሪያት ባለቤት ነው። አላህ፤ ከሁሉ የበላይ የሆነ ብርቱ፣ ጥበበኛ፣ ፍትሀዊ፣ ሁሉን አዋቂ የሁሉ ደጋፊና አስተናባሪ አምላክ ነው።

የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ሲሳይንም ለጋሽ አላህ ነው። ስፍር ቁጥር የሌላቸው ፀጋዎቹን ውሎልናል። መስማትና መመልከት፣ ማሰብና ማስተዋል፣ መናገርና ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንዲሁም አምራች መሆን ሁሉ የርሱ ፀጋዎች ናቸው። ስለ ፀጋዎቹ ሁሉ ልናመሰግነው ይገባል። ትዕዛዞቹን በማክበር የከለከላቸውም በመቆጠብ እርሱን ብቻ ልናመልከው ከእርሱም ጋር ማንንም ላናጋራ ግድ ይላል።

ይህ ውስብስብ ረቂቅና የተመጣጠነ ፍጥረተ አለም ጥበበኛና ሁሉን ቻይ የሆነው ፈጣሪ አምላካችን ድንቅ ስራ መሆኑን መገንዘብ እጅግ ምክኒያታዊና ህሊናችን በተፈጥሮ የሚረዳው እውነታ ነው። ይህ ፍጥረተ ዓለም እራሱን ፈጥሯል ወይም የአጋጣሚ ውጤት ነው ብሎ ማመን ከአሳማኝ አመክነዮዎች የራቀና ፍፁም ተቀባይነት የሌለው መላምት ነው።

### 2. በመላዕክት ማመን

መላዕክት ከብርሀን የተፈጠሩ ሲሆን አላህ ያዘዛቸውን የሚፈጽሙና ትዕዛዙን የማይጥሱ ፍጥረታት ናቸው።

የአንዳንዶቹን መላዕክት ዝርዝር ሁኔታ አላህ በመለኮታዊ መልዕክቶች አማካኝነት አሳውቆናል። ለምሳሌ፤ ጂብሪል ከአላህ ወደ መልዕክተኞች የአላህን መልዕክት እንደሚያደርስ፣ የሞት-መልአክ ደግሞ ነብስን ከአካል እንደሚለይ ተነግሮናል።

**ቁርዓን የወረደው ማንበብና መጻፍ ወደ ማይችሉት ነብይ መሀመድ ከመሆኑ ጋር እጅግ ውብ ቋንቋዊ አገላለጾችን ይዟል። በአረብኛ ቋንቋዊ ውበቱ እና በአገላለጹ የምጥቀት ጫፍ ስለመድረሱ በአለም አቀፍ ደረጃ ይታወቃል።**

### 3. በመጽሀፍት ማመን

አላህ ለሠዎች እዝነትና ቅናቻን የሚያስገኙ መለኮታዊ መልዕክቶችን አውርዷል። በመጽሀፍት ማመን ለሙሳ በተወረደው ተውራት፣ ለዒሳ በተወረደው ኢንጅልና ለነብዩ ሙሀመድ በተወረደው ቁርዓን ማመንን ያካትታል። በሁሉም የአላህ መልዕክተኞች ላይ የአላህ ሠላምና እዝነት ይስፈን።

ቁርዓን ከሠማይ ወደ ምድር ከወረዱት የወህይ መልዕክቶች ሁሉ የመጨረሻው ነው። ቁርዓን የአላህ ቃል መሆኑን የሚያስረዱ ግልጽ ማስረጃዎችና ተዓምራት ብዙ ናቸው። ከነዚህም መካከል፤ ቁርአን አላህን አስመልክቶ ግልፅና ጥርት ያለ አለም አቀፋዊ መልዕክት ያዘለ ሲሆን፤ ፈጣሪን አስመልክቶ ተወራራሽ አስተሳሰቦችን እና ጥንታዊ እምነቶችን ሁሉ ይዳስሣል፤ ድክመታቸውንም ይተቻል።

ቁርዓን የወረደው ማንበብና መጻፍ ወደ ማይችሉት ነብይ መሀመድ ከመሆኑ ጋር እጅግ ውብ ቋንቋዊ አገላለጾችን ይዟል። በአረብኛ ቋንቋዊ ውበቱ እና በአገላለጹ የምጥቀት ጫፍ ስለመድረሱ በአለም አቀፍ ደረጃ ይታወቃል።

ቁርዓን ከ1400 ዓመታት በፊት የወረደ ከመሆኑ ጋር ብዙ ሳይንሳዊ እውነታዎችን ይዟል። በዚያን ግዜ እነዚህ እውነታዎች የሚታወቁ አልነበሩም። ከእውቀት መስፋፋት ጋር በቅርብ የታወቁ ናቸው።

ቁርዓን በመጀመሪያ ከወረደበት ግዜ አንስቶ በወረደበት አረብኛ ቋንቋ ቃል በቃል ተጠብቋል። ሌሎች መጽሀፍት ግን ተቀይረዋል፣ ተበርዘዋል ወይም ጠፍተዋል።

የቁርዓን ሌላኛው ተዓምር ደግሞ ከምንም አይነት ስህተት እና ግጭት የጠራ መሆኑ ነው።

ቁርዓን ልዩና ተዓምራዊ ይዘት ሊኖረው የመቻሉን ምስጢር ስናጤን፤ "ከአላህ ስለሆነ ነው" የሚለውን ሎጂካል ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን። ቁርዓን እና በትክክለኛ የዘገባ ስነድ የተላለፉ የነብዩ ንግግሮች እንዲሁም ተግባራዊ አስተምህሮዎች የኢስላማዊ እውቀቶች ምንጮች ናቸው።

### 4. በመላዕክት ማመን

ባለፉት ዘመናት አላህ ብዙ ሺ መልዕክተኛ ነብያትን እንደላከና ከየህዝቡ ቢያንስ አንድ መልዕክተኛ እንዳስነሳ ሙስሊሞች ሁሉ ያምናሉ። ሁሉም መልዕክተኞች አላህን በብቸኝነት ማምለክ እና መመሪያዎቹን መከተልን የተመለከቱ ተመሣሣይ መልዕክቶችን ይዘው መጥተዋል። ከነዚህ መልዕክተኞች መካከል ኑህ፣ ኢብራሒም፣ ሙሳ፣ ኢሳና ሙሀመድ ይገኙበታል። የነዚህ ነብያት ተልዕኮ አንድዬውን አምላክ አላህን በብቸኝነት ያመልኩ ዘንድ ሠዎችን ማንቃት ሲሆን፤ ቀጥተኛውን የስኬት መንገድ እንዲያመላክቱ እና አላህን በማምለክ ለሰዎች አርዓያ እንዲሆኑ ተልከዋል። የአላህ ስላምና እዝነት በሁሉም ነብያት ላይ ይስፍን። ከነዚህ መልዕክተኞች አንዱም ቢሆን የአላህን ብቸኛ ተመላኪነት እና ጌትነት አይቀናቀንም። ማንኛውንም አምልኮ ለነብያት መፈጸም ወይም እነርሱን በማምለክ ወደ አላህ መዳረሻ ማድረግ የእምነትን መሠረት ይንዳል። አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን በብቸኝነት የመመለክ መብትም ይቃረናል።

## የአላህ መልዕክተኛ ዒሳ

ሙስሊሞች እንደሚያምኑት ዒሳ (የአላህ ሰላምና እዝነት በእርሱ ላይ ይሁንና) አላህ ዘንድ የተከበረ ነብይ ነው። ከድንግሏ እናቱ ከመርየም ያለ አባት በአስገራሚ ተዓምር ተወልዷል። አላህም በእርሱ ፍቃድ ብዙ ድንቅ ታዓምራትን እንዲፈጽም አድርጎታል። በአላህ ፍቃድ እውሩ አይናማ እንዲሆን፣ ደንቆሮው እንዲሠማ የታመመውም ፈውስ እንዲያገኝ አድርጓል። እናቱ ላይ ወገኖቿ የሠነዘሩባትን የአሉባልታ ክሶች ውድቅ ለማድረግም በእቅፏ ጨቅላ ህጻን ሳለ ተናገሯል። ሙስሊሞች ምንም እንኳ ኢሳን ያከብሩና ያልቁ እንጂ የአላህ ልጅ ነው አይሉም። አያመልኩትም የስላሴ አካል አድርገውም አያዩትም። ለአላህ ብቻ የተገቡ መለኮታዊ ባህሪያትንም በፍጹም አይጋራም።

مَا كَانَ لِلَّهِ أَن يَتَّخِذَ مِن وَلَدٍ ۖ سُبْحَانَهُ ۚ إِذَا قَضَىٰ أَمْرًا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُ كُن فَيَكُونُ

«ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም። (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ። አንድን ነገር በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው «ኩን» ነው፤ ወዲያውም ይሆናል» መርየም 35

### ነብዩ መሀመድ ﷺ

የነብያትና የመልዕክተኞች ሁሉ መደምደሚያ ሲሆኑ ቅኑን መንገድ እና እውነተኛ ሀይማኖትን ለዓለማት ሁሉ ያስተምሩ ዘንድ ተልከዋል። አላህ ቁርዓንን አውርዶላቸዋል። ይህንን ቁርዓን የአላህ መልዕክተኛ በቃል በተግባርና በሁኔታቸው ሁሉ አብራርተዋል። አሻሚውንና ድብቁን መልዕክት ሁሉ ግልጽ አድርገዋል። የቁርዓንን ትዕዛዛትም ተግብረዋል።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . . .

*ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .*

የአላህ መልዕክተኛ በታማኝነት፣ በእዝነት፣ በእውነተኝነትና በጀግንነት መልካም አርአያ ሆነው አልፈዋል፡፡ ነገር ግን ሙስሊሞች ኢሳን እንደማያመልኩት ሁሉ ሙሀመድንም አያመልኩም፡፡

### 5. በመጨረሻው ቀን ማመን

የመጨረሻው ቀን በታላላቅ ክስተቶች የተሞላ ማምለጫና መሸሻ የሌለው የማይቀር ቀጠሮ ነው፡፡ ሁሉም ሠው በፈጣሪው ፊት ይቆምና፤ ስለ ትንሹም ስለ ትልቁም፣ ስለ መልካሙም ስለ መጥፎዉም ተግባሩ፤ ቸርነትን ባቀፈ እዝነቱ፤ ጥበብና አዋቂነቱን ባማከለ ፍትሀዊነቱ ይተሳሰበዋል።

በዚህ ታላቅ እለት አላህ ሁሉንም ነገሮች በፍትህና በጥበብ ያስተካክላል፡፡ አላህ ዘንድ አንዲትም ነፍስ ኢምንት ያክል አትበደልም። ታዛዦች መልካም ምንዳ ተከፍሏቸው ይደሠታሉ፡፡ አመፀኞች ግን ስኬትን ያጣሉ፤ ይቀጣሉም። በዚህ ቀን የፍጡራን መጨረሻ እጣፈንታቸው በአላህ ፍትህና እዝነት መካከል ነው፡፡ በእዝነቱ ወደ ጀነት ወይም ደግሞ በፊትሀዊ ፍርዱ ወደ እሣት ያመራሉ።

የፍርድ ቀን ባይኖር ኖሮ በዚህ የፈተና ዓለም ውስጥ መኖር በራሱ መበደል በሆነ ነበር። አዎን! ፈተና እና ስቃይ ሁሉ ከበስተጀርባው ምንም አይነት ጥበብና ትርጉም ባልኖረው ነበር፡፡ ታላቁና ጥበበኛው ፈጣሪ ይህንን ከማድረግ የላቀ ነው፡፡

### 6. በቀደር ማመን

አላህ ከዚህ ቀደም የተከሰተውንም ሆነ ወደፊት የሚከሰተውን ሁሉ ያውቃል፡፡ ሳይከሰት ያለፈውንም ቢሆን፤ ቢከሰት ኖሮ እንዴት ይሆን እንደነበር ያውቃል፡፡ በነገሮች ሁሉ ላይ ሀይል አለው። ከእርሱ እውቀት፣ ፍቃድና ጥበባዊ ውሳኔ በተሠወረ መልኩ በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ የሚከሠት ነገር ፈጽሞ የለም፡፡ ከስልጣኑና ከችሎታው ውጭ ምንም አይፈጸምም።

ለሁሉም ሰው አላህ ነጻ ምርጫ ሠጥቷል፡፡ ሁሉም ሰው የመልካም ሰዎችን የስኬት ጉዞ ወይም የአመፀኞችን የጥፋት እርምጃ የመምረጥ ሙሉ ነጻነት አለው፡፡ ስለ ምርጫውም ይጠየቃል፡፡ ወይ ወደ ጀነት ወይም ደግሞ ወደ እሣት ያመራል፡፡

የሠው ልጅ የመምረጥ ነጻነት አለው ሲባል፤ አላህ የነገሮችን መከሠት ቀድሞ ከማወቁና እንዲከሰቱም ከመፍቀዱ ጋር በፍጹም አይጋጭም፡፡ እንደዚሁ የአላህ ችሎታ ሁሉን ያካለለ መሆኑ የሠው ልጆች የመምረጥ ነጻነት ላይ ተጽዕኖ የለውም፡፡ በሰዎች ምርጫ ላይ የሚጥለውም ገደብ የለም፡፡ አላህ የሠዎችን ምርጫ ማወቁ በዚህ ምርጫ ላይ አስገድዷቸዋል ማለት አይደለም፡፡ እንዲከሠቱ የፈቀዳቸውን ነገሮች ሁሉ አላህ ይውዳቸዋል ማለትም አይደለም፡፡

## እምነቱ የአምልኮ መሠረቶች

## የሙስሊም ህይወት እምነቱ መሠረቶች

### 1. እምነት

በአላህ ማምንን ማረጋገጥ "ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው የለም፤ ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው" ብሎ መመስከር ነው፡፡

ይህ ምስክርነት ጥልቅ ልባዊ እምነትን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህንን ምስክርነት ማመን፣ በአንደበት መመስከርና ምስክርነትን መተግበር ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ከሌላ አላማዎች በመራቅ ለአላህ ብቻ ሲፈፀም ነው። አንድ የአላህ ባርያ ይህንን ምስክርነት ከሰጠ፤ ከአላህ ውጭ በሚመለኩ አማልክት ሁሉ ይክዳል። አላህ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ከአላህ በስተቀር የሚመለክ ሁሉ ከንቱ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንደዚሁ መልክተኛው ሙሀመድ የነብያት መደምደሚያ መሆናቸውን በመመስከርና በማረጋገጥ አንድ ሰው "ሙስሊም" ይሆናል፡፡

### 2. እምነቱ ስግደቶች

ሰላት በአንድ ሙስሊምና እና በፈጣሪ አምላኩ መካከል መንፈሳዊና ግላዊ ግንኙነትን ይፈጥራል፡፡ በአላህ ማመንና እርግጠኝነት፤ አላህን መውደድና ከእርሱ መልካምን መጠበቅ፤ አላህን ማለቅና ማወደስ የዚህ ግንኙነት አንኳር መሠረቶች ናቸው፡፡

አምስቱ ሰላቶች ከሁለቱ ምስክርነቶች ቀጥሎ እጅግ ወሳኝ የኢስላም ምሰሶዎች ሲሆኑ፤ የጧት ሰላት "ፈጅር" የእኩለቀን ሰላት "ዙህር" የቀትር ሰላት "አስር" እና የምሽት ሰላቶች "መግሪብ" እና "ኢሻእ" ተብለው ይታወቃሉ፡፡

እነዚህ ሠላቶች እጅግ አጭር የደቂቃዎች ግዜ ብቻ የሚፈልጉ ሲሆኑ፤ የቁርዓን አንቀጾችን ማንበብ፣ አላህንም ማላቅና ማወደስን ያቀፉ ናቸው፡፡ ሙስሊም ለሠላት ትኩረት በመስጠት ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል። እጆቹን፣ ፊቱንና ሌሎች አካሎቹን በመታጠብ መንፈሳዊና የውጭ ንጽህናውን በቅድሚያ ያረጋግጣል።

**የሐጅ ተጓዦች ተመሣሣይ "ኢህራም" የተባለ ልብስ ይለብሳሉ። ይህም ሀብታምና ድሀ፣ ጠንካራና ደካማ፣ ሰራተኛና አሰሪ ሁሉም እኩል የሚሆኑበትና በጋራና በእኩልነት አላህ ፊት በመቆም የሚለምኑበት ስርዓት ነው።**

### 3. ዘካ

ዘካ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ አላህ ግዴታ ካደረጋቸው አምልኮዎች መካከል ሲሆን፤ የተወሰነ መጠን የደረሠ ገንዘብ ያለው ሙስሊም ሁሉ በኢስላም በተደነገገው አፈጻጸም መሠረት መስጠትን ግዴታ የሚያደርግ ነው።

ዘካ እጅግ ትንሽ መጠን ያለውን ገንዘብ አመታዊ በሆነ መልኩ ወጪ ማድረግ ሲሆን፤ የሚሠጠውም ቁርዓን በዝርዝር ለዘረዘራቸውና መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ድሆችና ችግረኞች ነው፡፡ ዘካ ገንዘብን ንፁህ ያደርጋል፣ ያሳድገዋልም። ለሠጪውም ይሁን ለተቀባዩ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ ከጥቅሞቹ መካከል በሀብታሞችና በድሆች መካከል ያለውን ርቀት ማጥበብ ዋነኛው ሲሆን፣ እያንዳንዱ የማህበረሠብ ክፍል መሠረታዊ ፍላጎቶቹን እንዲያሟላ ያደርጋል፡፡

### 4. ጾም

ሙስሊሞች በየዓመቱ የረመዳንን ወር ከንጋቱ ጀምሮ ፀሀይ እስክትጠልቅ ድረስ ይጾማሉ፡፡ በዚህ ግዜ ከምግብና መጠጥ እንዲሁም ከጾታዊ ግንኙነት ይታቀባሉ፡፡

ጾም መንፈስን የሚያጠራ ከመሆኑ ባሻገር የትዕግስትና የቻይነትን ባህሪያት ለመላበስ ይረዳል፡፡ እንደዚሁ ብዙ ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅሞች አሉት፡፡

ረመዳን በኢስላማዊው የሒጅራ ካሌንደር ዘጠነኛው ወር ነው፡፡

### 5. ሐጅ

ማንኛውም በገንዘብና በአካላዊ ብቃት ሐጅ የማድረግ ችሎታ ያለው ሰው በእድሜው አንድ ግዜ ወደ መካ በመሄድ የሀጅን ስነ ሥርዓት መካፈል ግዴታ ይሆንበታል፡፡

ሐጅ በዙልሒጃ ወር በየዓመቱ የሚከናወን አምልኮ ሲሆን የሙስሊሞች አንድነት ግልጽ በሚሆንበት ሁኔታ የመልክ፣ የዘር ፣ የኑሮ ደረጃና የእድሜ ልዩነቶች ከመኖራቸው ጋር በጋራና በእኩልነት ለአላህ የሚደረግ ዒባዳ (አምልኮ) ነው፡፡ ይህ ታላቅ ስነስርአት ከብዙ አምልኮዎች የተዋቀረ ሲሆን መንፈሳዊ ጉዞ፣ እርድን መሰዋት፣ የተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚፈጸሙ ጸሎቶችና አምልኮዎች ይገኙበታል፡፡ ይህ ልዩ የሆነ ተሞክሮ፤ እንደ የአላህ ባሪያ መተናነስ፣ ትዕግስትና ቻይነትን የመሣሰሉ መልካም እሴቶችን ይላመድ ዘንድ ይረዳል፡፡

ሁሉም የሀጅ ተጓዦች ተመሣሣይ "ኢህራም" የተባለ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ይህም ሀብታምና ድሀ፣ ጠንካራና ደካማ፣ ሰራተኛና አሰሪ ሁሉም እኩል የሚሆኑበትና በጋራና በእኩልነት አላህ ፊት በመቆም የሚለምኑበት ስርዓት ነው፡፡

## የአምልኮ ጽንሰ ሀሳብ

ማንኛወም አላህ የሚወደው ተግባር ሁሉ አምልኮ ይባላል

በኢስላም ስለ አምልኮ ያለው ግንዛቤ ከላይ ባየናቸው አምስት የአምልኮ መሠረቶች አይገደብም፡፡ የአምልኮ ጽንስ ሀሳብ አላህ የሚወዳቸውን መልካም ስራዎች ሁሉ ያካትታል። ዕለታዊና የተለመዱ ተግባራትን ሳይቀር አንድ ሙስሊም አላማውን አጥርቶ ለአላህ ብቻ ከፈፀማቸው አምልኮ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሠላምታ፣ ፈገግታ፣ ለጎረቤት በጎ መዋል፣ ቤተሰብን መርዳት፣ እምነትን አለማጉደል ከመንገድ ላይ ጎጂ ነገሮችን ማራቅ ጭምር በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ልናስተውል የሚገባን አላህ የማንኛውንም ባሪያ አምልኮ ፈላጊና ከጃይ አይደለም፡፡ ነገር ግን በተቃራኒው አንድ ባሪያ ነብሱን ያጠራትና ከፍ ያደርጋት ዘንድ አላህን ማምለክ ያስፈልገዋል፡፡

## መደምደሚያ

የተዘረዘሩት የእምነትና የኢስላም መሠረቶች የኢስላምን አስኳል ያስገኛሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የእምነትና የኢስላም መሠረቶች ማሟላት፤ መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ፍላጎቶች ሁሉ እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ አዕምሯዊ ተቀባይነት ያለው ተግባራዊ የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር አላህ የሚወደውና የተቀበለው ብቸኛው የአኗኗር ዘይቤ፤ ለጀነት የሚያበቃውም ብቸኛው መንገድ ኢስላም ነው!

ቁርአን እንዲህ ይላል፤

مَنْ عَمِلَ صَٰلِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةً طَيِّبَةً ۖ وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ

«ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፡፡ ይሠሩትም ከነበሩትም ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን» አል ነህል ምዕራፍ 97

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ፊታዋ

## የሁለቱ የምስክርነት ቃላት ትርጉም

**ጥያቄ 12/ የተከበሩ ሸይኽ! የሁለቱ የምስክር ቃል ማለትም ላኢላሀ ኢለሏሀ ሙሐመዱ ረሱሉሏሀ ትርጉም ምንድን ነው?**

መልስ: ሁለቱ የምስክር ቃል ላኢላሀ ኢለሏሀ ሙሐመዱ ረሱሉሏሀ ወደ ኢስላም መግቢያ ቁልፍ ናቸው። አንድ ሰው ወደ እስልምና መግባት ከፈለገ እነዚህ ሁለት ምስክር ቃሎች ካልሰጠ ወደ እስልምና መግባት አይችልም። ለዚህም ሲባል የአላህ መልክተኛው ሙዓዝን ወደ የመን በላኩት ግዜ የመጀመሪያ ጥሪውን ወደ ላኢላሀኢለሏሀ ሙሐመዱ ረሱሉሏሀ እንዲያደርግ ነበር የመከሩት።

የመጀመሪያው የምስክር ቃል: ላኢላሀ ኢለሏሀ የሚለው የምስክር ቃል ሲሆን አንድ ግለሰብ በአንደበቱም ይሁን በቀልቡ ከአላህ በስተቀር የሚመለክ አምላክ እንደሌለ ማመን ይኖርበታል። "ኢላህ" ማለት የሚገዙት የሚያመልኩት ማለት ነው።

ላኢላሀ ኢለሏሀ የምትለው አ/ነገር ነፍይና ኢስባት በውስጧ ይዛለች። ነፍይ "ላ ኢላህ" የሚለው ሀረግ ውስጥ ሲሆን ኢስባት ደግሞ "ኢለ ሏሀ" የሚለው ሀረግ ውስጥ። ይህም ማለት ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚገዙት አምላክ የለም የሚለው ትርጉም ይሰጠናል። መጀመሪያ በቀልብ ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚገዙት አምላክ የለም የሚለውን ካረጋገጠ በኋላ በአንደበት መመስከር ይገባል።ይህ ደግሞ አምልኮትን ለአላህ ብቻ በማጥራት ከርሱ ውጭ ካሉ አካል ውድቅ ማድረግ በውስጡ ይይዛል። ላኢላህ ኢለሏሀ ስንል ምናልባት ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ብዙ አማልክቶች አሉ አይደል ብሎ የሚጠይቅ ሰው ምላሽ ይሆን ዘንድ "በሐቅ የሚለው" በውስጠ ታዋቂ ማስቀመጣችንም ለዚሁኑ እንለዋለን። አላህም በቁርኣኑ አማልክት በማለት ይጠራቸዋል አላህ በቁርኣኑ እንደሚለው:- ***"የአላህ ትዕዛዝም በመጣ ጊዜ እነዚያ ከአላህ ሌላ የሚገዙዋቸው አማልክቶቻቸው በምንም አላዳኗቸውም:: ከማከሰርም በቀር ምንም አልጨመሩላቸውም::"*** *[ሁድ:101]*

እንዲህም ይላል:- **"ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ አታድርግ። "** **[አልኢስራእ:39]**

እንዲህም ይላል:- **"ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ አትጣራ። "** **[አልቀሰስ:88]**

አላህ እራሱ ከርሱ ውጭ አማልክቶች መኖራቸውን እያረጋገጠ ከአላህ ውጭ የሚገዙት ሌላ አምላክ የለም እንዴት ይባላል? ከተባለ ለዚህ ምላሹ "ከአላህ ውጭ የሚገዙት ሌላ አምላክ የለም' እነዚህ ከአላህ ውጭ የሚመለኩ አማልክቶች አዎን አማልክቶች ናቸው ነገር ግን የባጢል አማልክት እንጂ የሐቅ አማልክት አይደሉም። የአምልኮት መብት አንዱም አይገባቸውምና። ይህን የሚጠቁመው ቀጣዩ የቁርኣን አንቀፅ ነው።

***"ይህ አላህ እርሱ እውነት ከእርሱም ሌላ የሚግገዙት (ጣዖት) ውሸት በመሆኑና አላህም እርሱ የበላይ ታላቅ በመሆኑ ነው::"*** *[ሉቅማን:30]*

የሚቀጥለውም አንቀፅ ይህኑ ይጠቁማል:-

***"አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም ሌላኛውን መናትን (አያችሁን? የምትግገዟቸው ኃይል አላቸውን? ለእናንተ ወንድ ለእርሱም ሴት (ልጅ) ይኖራልን? ይህቺ ይህኔ አጉዳይ ማከፋፈል ናት:: እነርሱ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸው ስሞች ብቻ እንጅ ምንም አይደሉም:: አላህ በእርሷ (መግገዛት) ምንም ማስረጃ አላወረደም:: ከጌታቸውም መምሪያ የመጣላቸው ሲኾኑ ጥርጣሬንና ነፍሶች የሚዘነበሉበትን እንጅ ሌላ አይከተሉም::"*** *[አነጅም:19_23]*

አላህ ዩሱፍ ዐለይሂሰላም የተናገረውን አላህ እንዲህ ሲል ቁርኣን ላይ አስቀምጦታል:- ***«ከእርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትገዝዙም:: አላህ በእርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም::"*** *[ዩሱፍ:40]*

ስለዚህም ላኢላህ ኢለሏሀ የሚለው ትርጉም ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም የሚለው ይሆናል።ከአላህ ውጭ ያሉ መልክተኞች፤መላኢካዎች፤ አውሊያዎች ድንጋዮች ዛፎች ፀሀይና ጨረቃ ለሎችም እነዚህ የሚያመልኩ ሰዎች አምላክ ናቸው ብለው ቢሞግቱም ትክክለኛ አምላክ ሳይሆኑ በባጢል የሚመለኩ አማልክት ናቸው። እንዲያውም ትክክለኛው የአምልኮ ተግባር ለአላህ ብቻና ብቻ ነው።

**ጥያቄ 13/ የተከበሩ ሸይኽ እስካሁን የላ ኢላህ ኢለሏሀ ትርጉም አያየን ነበር ሙሀመዱ ረሱሉላህ ማለት ደግሞ ምን ማለት ነው?**

**መልስ:** ሙህመዱ ረሱሉላህ ማለት ሙሐመድ ኢብኑ ዐብዲላህ አልቁረይሺ አልሃሺሚይ ለሰው ይሁን ለጂኖች ለፍጥረታት በሙሉ መልክተኛ መሆናቸውን በልብ ማመንንና በዐንደበት ማረጋገጥ ማለት ነው።

አላህ እንዳለው:- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ:: (እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለእርሱ ብቻ የኾነ ነው:: እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም:: ሕያው ያደርጋል:: ይገድላልም:: በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ የማያነብ ነቢይ በኾነው መልክተኛው እመኑ:: ቅንንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት::» [አልአዕራፍ:158]

እንዲህም ይላል:- "ያ ፉርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብርና ጥራት ተገባው::" [አልፉርቃን:1]

የዚህ የምስክር ቃል በተዘዋሪ ግዴታ የሚያስደርገው ነገር እነሆ:- መልክተኛው የተነገሩት እውነት ብሎ መቀበል፤ያዘዙትን መታዘዝ፤የከለከሉትን መከልከል፤በርሳቸው ሸርዓ ብቻ አምልኮትን መፈፀም። በተጨማሪም መልክተኛው አንድም የፈጣሪነት መብት አላቸው፤ አምልኮት ይገባቸው እና ፍጥረተ ዓለሙ ላይ ያስተናብራሉ ብሎ አለማመን። እንዲያውም መልክተኛው ባርያ እንጂ አይመለኩም። የማይስተባበሉ መልክተኛ ናቸው። አላህ በሻው ነገር ቢሆን እንጂ። ለራሳቸውም ሆነ ለሌላው ጥቅምን ማስገኘት ሆነ መከላከል አይችሉም።

አላህ እንዳለው:-

***«ለእናንተ የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልልም:: ሩቅንም አላውቅም:: ለእናንተም እኔ መልአክ ነኝ አልልም:: ወደእኔ የሚወርደልኝን እንጅ ሌላን አልከተልም» በላቸው:: «ዕውርና የሚያይ ይስተካከላሉ[illegible] አታስተነትኑም[illegible]» በላቸው::"*** *[አልዐንዓም:50]*

መልክተኛው የታዘዘውን የሚከተል ባሪያ ነው። ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል

***«እኔ ለእናንተ ጉዳትንም ሆነ ጥቅምን አልችልም» በላቸው::ከአላህ (ቅጣት) አንድም አያድነኝም:: ከእርሱም ሌላ መጠጊያን አላገኝም» በላቸው::"*** *[አልጂን:21_22]*

እንዲህም ይላል:- «አላህ የሻውን በስተቀር ለእራሴ ጥቅምንም ጉዳትንም ማምጣት አልችልም:: ሩቅንም (ምስጢር) የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ ነበር:: እኔ ለሚያምኑ ሕዝቦች አስፈራሪና አብሳሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም» በላቸው::" [አልአዕራፍ:188]

ይህ ነው የላ ኢላህ ኢለሏሀ ሙሐመደ ረሱሉሏሀ መልክት። ከዚህም መልክት የምንረዳው መልክተኛውም ይሁን ከሳቸው በታች ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ፍጥረታት ከአምልኮ ዘርፎች አንዱም አይገባቸውም። አምልኮ ለአላህ እንጂ ለሌላ የማንም መብት አይደለምና። የመልክተኛው መብት ደግሞ አላህ የሰጣቸው ደረጃ ላይ ማስቀመጥ ብቻ ነው። እርሱም የአላህ ባሪያና መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር።

ምንጭ:-ነሲሐ የፊትዋ ማዕድ ድረገፅ ጥያቄ የሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል ኡሰይሚን ፊትዋዎች ቁ.12 እና 13

*http://www.nesiha.info*

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

*ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል ..........*

ካለፈው ገጽ የቀጠለ .........

**ጥያቄ / የተከበሩ ሸይኽ! ሙስሊሞ የመርየም ልጅ ዒሳን አስመልክቶ ያላቸው ዐቂዳ (እምነት) ምንድነው? ተገድሏል ተሰቅሏል ማለትስ በሸሪዓው ያለው ብይን ምንድነው?**

መልስ፡ ሙስሊሞች የመርየም ልጅ የሆነው ዒሳን አስመልክቶ ያላቸው እምነት፤ ባለሟል ከሆኑ መልክተኞች አንዱ ነው እንዲያውም ኡሉል ዐዝም (መካራን እና ችግርን በትግስት ተወጡ) ከሚባሉት አምስት ምርጥ ነብያት መካከል አንዱ ነው። አላህ በቁርኣኑ ሁለት ቦታዎች ላይ ጠቅሷቸዋል። ሱረቱ አሕዛብ ላይ እንዲህ ይላል፡-

***"ከነቢዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን ከአንተም፣ ከኑሕም፣ ከኢብራሒምም፣ ከሙሳም ከመርየም ልጅ ዒሳም በያዝን ጊዜ (አስታወስ)። ከእነርሱም የከበደን ቃል ኪዳን ያዝን።" [አል አሕዛብ፡7]***

ሱረቱ አሹራ ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል።

***"ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን በእርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ። ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በእርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በእርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገግን)።" [አሹራ፡13]***

ዒሳ ያለ አባት ከእናት ብቻ የተፈጠረ የአደም ልጅ እና ሰብዓዊ ፍጡር ነው። እርሱም የአላህ ባሪያና መልክተኛ ነው። የማይመለክ ባሪያ ሲሆን ሊያስተባብሉት የማይገባ ነብይ ነው። የፈጣሪነትና የጌትነት መለያ አንዱም የለውም። እንዲያውም እርሱ አላህ እንዳለው ነው፡- "እርሱ(ኢሳ) በርሱ ላይ የለገስንለት ለእስራኤለም ልጆች ተዓምር ያደረግነው የኾነ ባሪያ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡" [አዙኽሩፍ፡59]

እርሱንም ሆነ እናቱን ከአላህ ውጭ ያሉ አምላኮች አድርገው እንዲይዙ ህዝቦቹን አላዘዘም። አላህ ያወደረለትን ብቻ ነው ያዘዛቸው። **«በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም፡፡" አልማኢዳ፡**117]

ዒሳ የተፈጠረው ሁን በሚለው የአላህ ቃል ትዕዛዝ ነው። አላህ እንዳለው፡- **"አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አደም ብጤ ነው። ከዐፈር ፈጠረው። ከዚያም ለርሱ (ሰው) «ኹን» አለው፤ ኾነም።" [አልዒምራን፡59]**

በኢሳና በመልክተኛው ሙሐመድ ﷺ መካከል የተላከ መልክተኛ የለም። አላህ እንዳለው ፡- "የመርየም ልጅ ዒሳም፡- **«የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» ባለ ጊዜ (አስታውስ)። በግልጽ ተዓምራቶች በመጣቸውም ጊዜ «ይህ ግልጽ ድግምት ነው» አሉ።" [አሰፍ፡6]**

ዒሳ የአላህ ባሪያና መልክተኛው መሆኑ ሳያምን አንድ አማኝ እምነቱ የተሟላ ሊሆን አይችልም። እርሱ የሁዳዎች ዒሳን ከገለፁ አስፀያፊ ማንነት የፀዳ ነው። የሁዳዎች፡- እርሱ የዝሙተኛ ልጅ ነው አሉ።አላህ ይጠብቀንናእርሱ ከዝሙት ነው የተገኘው አሉ። አላህ ከዚህ ነጻ መሆኑን መስክሮለታል፤ሙስሊሞች እንዲሁ ክርስቲያኖች ከሚጋዙበት መንገድ የጠሩ ናቸው። እርሱና እናቱ ከአላህ ውጭ አምላክ አድርገው ስለያዙት። አንዳንዶቹ ደግሞ ፡- የአላህ ልጅ ነ ው በማለታቸው፤ ሌሎች ደግሞ የአላህ አንድ ሶስተኛው ነው (ስላሴን በማመናቸው) ክርስቲያኖች የመርየም ልጅ የሆነው ዒሳ ማንነት አስመልክቶ ግንዛቤያቸው የተሳሳተ ነው። ዒሳ ተገድሏል ወይም ተሰቅሏል የሚለውን አስመልክቶ አላህ በቁርኣኑ ይህ እንዳልተከሰተ በግልጽ እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፡-

***«እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን» በማለታቸውም (ረገምናቸው)። አልገደሉትም አልሰቀሉትምም። ግን ለእነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ። እነዚያም በእርሱ ነገር የተለያዩት ከእርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም። በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንስ አላህ (ኢሳን) ወደርሱ አነሳው። አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው። ከመጽሐፉም ሰዎች ከመሞቱ በፊት (እዚህ ምድር ሳለ) በእርሱ (በዒሳ) በእርግጥ የሚያምን እንጅ (አንድም) የለም። በትንሣኤም ቀን በነሱ ላይ መስካሪ ይኾናል።" [አኒሳእ፡157-159]***

**ዒሳ ያለ አባት ከእናት ብቻ የተፈጠረ የአደም ልጅ እና ሰብዓዊ ፍጡር ነው። እርሱም የአላህ ባሪያና መልክተኛ ነው።**

ዒሳ ተገድሏል ወይም ተሰቅሏል የሚል እምነት ያለው ቁርኣን በርግጥ አስተባብሏል። ቁርኣን ያስተባበለ ደግሞ ካፊር ነው። ዒሳ አልተገደለም አልተሰቀለም ስንል እናምናለን። ነገርግን የሁዳዎች ተገድሏል ተሰቅሏል የሚለውን ውሸት በማራገባቸው የተነሳ ወንጀሉ እነሱ ተሸክሙት እንላለን። እርሱን ገደልነው ይላሉ እውነታው ግን አልገደሉትም አልሰቀሉትም። ነገርግን አምሳያውን ይዘው ገደሉት።ከነርሱ መካከልም የዒሳን መልክ አለበሰውና እርሱ መስሏቸው ይዘውት ሰቀሉት ገደሉትም። እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን አሉ። ስለዚህም በአንደበታቸውም ሰቅለነዋል ገድለነዋል ብለው በማረጋገጣቸው የተነሳ ወንጀሉን የሁዳዎች ይሸከሚታል። ዒሳ ግን ከተባለው ነገር በሙሉ አላህ ነጻ አድርጎታል ከየሁዳዎች ሴራም ጠብቆ ወደ ሰማይ አሳርጎታል። የመጨረሻው ቀንም ሲቃረብ ወደ ምድር በመውረድ በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ሸሪዓ (ህግ) ያስተዳድራል ከዚያም የተወሰነለትን ሞትን አይቀርለትምና ይሞታል፤መሬት ውስጥ ይቀበራል። ሌሎች የሰው ልጆች ከቀብራቸው እንደሚቀሰቀሱት እሱም ዳግም ይቀሰቀሳል። አላህ እንዳለው፡-

**"ከእርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ። በእርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን። ከእርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን።" [**ጧሀ፡55]

እንዲህ ብሏል፡- ***«በእርሷ ላይ ትኖራላችሁ። በእርሷም ላይ ትሞታላችሁ። ከእርሷም ውስጥ ትወጣላችሁ» አላቸው። [አል አዕራፍ፡25]***

ምንጭ፡-ነሲሐ የፈትዋ ማዕድ ድረገፅ ጥያቄ የሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል ኡሰይሚን ፈትዋዎች ቁ.56

*http://www.nesiha.info*

# ፀረ ኢስላም ሳይቶችን ከማገዝ ተጠንቀቁ!!

ፀረ ኢስላም ዌብሳይቶችን ተጠንቀቁ፣ መልእክተኛውን የሚሳደቡ ዌብሳይቶችን ተጠንቀቁ...ወዘተ እየተባሉ የሚለቀቁ ማስታወቂያዎችን የሚያሰራጩት ባብዛኛው ባለ ዌብሳይቶቹ ናቸው። ለጉግል እና መሰል ድርጅቶች ለማስታወቂያ ከሚያወጡት ወጪ ይላቀቃሉ። አላህና መልእክተኛው ላይ ዘለፋዎችን እንዲሁም ቅጥፈቶችን በነፃ ማሰራጨት ይችላሉ። እስቲ ቆም ብለን እናስበው፤ ኢስላምን የሚሳደብ አንድ መፅሄት ቢወጣ ያንን መፅሄት እንዳይሰራጭ እንፈልጋለን ወይስ በብዛት ገዝተን ተጠንቀቁት እያልን እንበትናለን??

በግል ህይወታችን ከሰዎች ጋር ባለን አለመግባባት ስለኛ መጥፎ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛ እናሰራጨው ነበርን? አሁን አሁንማ መልእክተኛውን የሚሳደቡ ስእሎችን እና ቪዲዮዎችን እያሰራጩ፣ ላይክ ወይም ዲስላይክ እያደረገ "ተመልከቱ ሲያሾፉብን" የሚሉ ቀልደኞች በዝተዋል። እያንዳነዱን መልእክት ስናስተላልፍ ከበስተጀርባው ላለው ቅናቻ ወይም ጥመት አስተዋፅኦ **እያበረከትን** መሆኑን እናስተውል። መልካም ስራዎች አናሳ በሆኑበት ዘመን፤ ከሞትን በኃላ የመልካም ስራ ምንዳችን እንዳይቋረጥ የሚያደርጉ ቀጣይ ስራዎችን ትተን ለማለፍ መጣር ግድ ነበር። ይህ ተግባር ግን በቋሚነት ወንጀል እንዲፃፍብን የሚያደርግ ጥፋት ነው። አላህ ማስተዋልን ይለግሰን!!

## ✍ እራስን ማጥራት ግዴታ ነው!

በሳንባ በሽተኞች መካከል፤ በተበከለ አየር ውስጥ ካለመከላከያ የሚኖር ሰው ስለጤንነቱ እጨነቃለው ቢለን አትቀልድ እንለዋለን።

ለፀረ ኢስላም አቡጃህሎች ጆሮውን ያዋሰ ሁሉ ሊነቃ ይገባዋል። ግሩፓቻቸውን ያሞቁ ፔጆቻቸውን በላይክ ያደመቁ ሁሉ ሊያስቡበት ይገባል። ለአላህና ለመልእክተኛው ያላቸውን ክብር፤ ለኢስላም ያላቸውን ቁርጠኛ እምነትና ውዴታ ካስተዋሉ ከከሀዲያን ጋር ለመቀመጥ ትእግስቱ አይኖራቸውም። አራስን ማፅዳትም ተቀዳሚ ተግባራቸው ይሆናል።

وَقَدْ نَزَّلَ عَلَيْكُمْ فِي الْكِتَابِ أَنْ إِذَا سَمِعْتُمْ آَيَاتِ اللَّهِ يُكْفَرُ بِهَا وَيُسْتَهْزَأُ بِهَا فَلَا تَقْعُدُوا مَعَهُمْ حَتَّى يَخُوضُوا فِي حَدِيثٍ غَيْرِهِ إِنَّكُمْ إِذًا مِثْلُهُمْ النساء. 140/

*«በእናንተም ላይ በመጽሐፉ ውስጥ፤ የአላህን አንቀጾች በርሷ ሲካድባትና በርሷም ሲላገጥባት በሰማችሁ ጊዜ፣ በሌላ ወሬ ውስጥ እስከሚገቡ ድረስ ከነርሱ ጋር አትቀመጡ ማለትን በእርግጥ አወረደ፤ እናንተ ያን ጊዜ ቢጤያቸው ናችሁና፤ አላህ መናፍቃንን እና ከሐዲዎችን በሙሉ በገሀነም ውስጥ ሰብሳቢ ነውና» ኒሳእ 140*

የአላህን ውዴታና ፍቅር ከፈለግን ኢስላማዊ እውቀትን ከትክክለኛ ምንጮች እናጣጥም።

ኢስላምን ንፁህ ከሆነው ምንጩ ከተማርነው፤ አላህን በመፍራት፣ ልባችንን በማንፃት፤ እራስን በእውቀት በማበልፀግና በአላህ በመታገዝ ከማንኛውንም አይነት መደናገርና የቀልብ በሽታ እራስን መከላከል ይቻላል። ኢስላምን ባወቅን ቁጥር ብርሀን እንደሆነና ጨለማን እንደሚገላልጥ እንረዳለን።

አዎ! ኢስላምን ከምንጩ እንረዳው፤ ያን ግዜ ለሚነሱ ሹቡሀቶች ሁሉ የኢስላም ሊቃውንት ምን ያክል የማያዳግሙ ምላሾችን እንደሰጡ በዝርዝር ማወቅ እንችላለን። እነዚህ ግሳንግስ ማወናበጃዎች ሁሉ በቁርአናዊ አስተምህሮ እንደሸረሪት ድር ሲበጣጠሱ እናስተውላለን።

ኢስላምን ስንኖረው ጉዞአችን መሰናክሎች የተደረደሩበት ነው። ስሜታችንን ተከትለን ለዱንያ እጅ ሰጥተን ከመስመር እንድንወጣ፤ አለያም ውዥንብሮችን በመስማት መደናገር ውስጥ እንድንገባ ሌት ተቀን የሚለፉ የሸይጣን ወታደሮች ብዙ ናቸው። ከኛ የሚጠበቀው፤ ጥሩ የጉዞ ጓደኞችን መቅረብና ጉዞአችንን የሚያሰናክሉ ሸፍቶችን መራቅ ነው።

አላማ ያለው ሰው ለስኬት የሚያበቁትን እርምጃዎች መሳት የለበትም፤ መርከብ በየብስ አይጓዝምና!!

**✍ አቡጁነይድ ሳላሕ አሕመድ**

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ነሲሓ
# ቤተሰብ



- ጠቃሚ ነጥቦች ለባለትዳሮች
- የምዕመናን እናቶች
- የልጆችህ ጓደኞች እነማን ናቸው?
- በመጀመሪያው ቀን ትውውቅ እንዴት ልገመግመው?
- ሸይኽ ባሲጢ ሲዘከሩ
- የእናት ጡት . . .



# ኢስላማዊ ቤተሰብ

## ጠቃሚ ነጥቦች

### ለባለትዳሮች!

ሁልግዜም ቢሆን በትዳር ውስጥ ችግሮች መፈጠራቸው አይቀርም። አልፎ አልፎ በባልና በሚስት መካከል መጨቃጨቆች ሊፈጠሩ ይችላል። እነዚህ ሁኔታዎች በሁሉም ትዳር ውስጥ የሚከሠቱ እና የሚጠበቁ ነገሮች ናቸው።

በመነሻ ላይ ብዙም ጉዳት ላይኖራቸው ይችላል። እየተደራረቡ ስሄዱ ግን የትዳሩን ህልውና የሚፈታተን ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላሉ። በትዳር ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

በዚህ ወቅት ባልና ሚስት የትዳራቸውን ህልውና ለመታደግ እና መሠላቻቸትን ለማስቀረት የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሠድ ይኖርባቸዋል። የሚከተሉት ምክረ-ሐሳቦች ትዳር ሁልግዜም ጣፋጭ ሆኖ እንዲቀጥል ይጠቅማሉ።

1 ፍፁም እና እንከን የለሽ ትዳር የለም። ባልና ሚስት ይህን ማወቅ አለባቸው። የሁሉም ሠው ትዳር ሠላማዊና ጭቅጭቅ አልባ የነርሱ ትዳር ብቻ በጭቅጭቅ የተዋጠ እንዲሆን ማሠብ አይኖርባቸውም። አልፎ አልፎ የሚከሠቱ ጭቅጭቆችና አለመግባባቶች በየትኛውም ትዳር ውስጥ ሊኖር የሚችል የትዳር ህይወት አንድ ገጽታ ነው። ይህ መገንዘብ ይጠቅማል።

2 አለመግባባቶች ሲከሰቱ ወደ ከረረ ጭቅጭቅ ቁመት ከመጨመራቸው በፊት ገለል ማለት በጣም ጠቃሚ ነው። ነገሮች ረጋ ብሎ በሠከነ መንፈስ ለማሰብ እና ልዩነቶችን ለማብረድ ይረዳል።

3 ባልና ሚስት በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ለራስ ጠበቃ የመቆም ዝንባሌ ማስወገድ ይኖርባቸዋል። ስህተቱን ማመን እና በስህተቱ የተፈጠረውን ችግር ኃላፊነት ችግር መቀበል እንዲሁም ጭቅጭቆችን ማለሥለስ ፣ በጭቅጭቅ ወቅት ለትዳር አጋር ፍቅር ለማሳየት መሞከር ፈተናዎችን ለመሻገር ይረዳል፤ ትዳርንም ጣፋጭ ያደርጋል።

4 ህይወትን በቁም ነገር ኮምጣጥ ባለ ነገሮች ብቻ እንድትቀጥል ማድረግ ያስቸግራል። ስለሆነም ከሐራም በራቀ ሁኔታ በቤት ውስጥ የተፍታታ እና ቀለል ያለ የሚያዝናና ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል። ባልና ሚስት በየግዜው በጋራ ዘና የሚሉበት ፕሮግራም ሊኖራቸው ያስፈልጋል።

5 ባልና ሚስት ሁሌም ሊነጋገሩ ይገባል። በግልፅና በመደማመጥ የመነጋገር ባህል ማዳበር አለባቸው፤ ይህ ባህል በሠላምና በፍቅር ግዜ ብቻ ሳይሆን ፣ በአለመግባባትና በጭቅጭቅ ግዜም ሊታይ ይገባል። መነጋገር የማይችሉ ባለትዳሮች ደስታ አኖራቸውም፤ የትዳር ዕድሜው አጭር ይሆናል።

6 ባለትዳሮች አንዳንድ ነገሮች በጋር የማድረግ ወይም የማዘውተር ልምድ ማዳበር እጅጉም ይጠቅማቸዋል። አብሮ ቁርዓን (ማዳመጥ)፣ አብረው ጉዞ ማድረግ፣ አብረው ገባያ መውጣት፣ አብረው መመገብ.....

7 ስህተቶችን ሁሉ በትዳር አጋር ትካሻ ላይ ማሳረፍ ጭቅጭቆች እንዲዳብሩ ስለሚያደርግ ከዚህ መራቅ ያስፈልጋል።የትዳር አጋር ራሱን ማስረዳት እንዲችል ዕድል ሊሠጠው /ሊሰጣት ይገባል።

8 ባለትዳሮች ለትዳራቸው በቂ ትኩረት መስጠት አለባቸው፤ ትዳራቸውን እንደ ህይወት ሊመለከቱት ይገባል። ብዙ ግዜ የባል ወይም የሚስት ትኩረት ትዳር ላይ መሆኑ ቀርቶ ስራቸው ወይንም ትምህርታቸው ላይ ሲሆን ችግሮች መፈጠር ይጀምራሉ። ይህ እንዲሆን መፍቀድ የለበትም። ስራ ወይንም ትምህርት ሊሠጣቸው ይገባል። ነገር ግን ትዳርን እና የትዳር አጋርን ወደ ማስረሳት ደረጃ ከፍ ሊሉ አይገባም። የትዳር አጋር በቂ ትኩረትና ግዜ ሊያገኝ የግድ ይላል።

9 በትዳር ውስጥ በሁሉም ጉደይ ላይ ስሞታ ማቅረብ መሠላቸትን ይፈጥራል፤ ለትዳር ጠቃሚ አይደለም። ማሳለፍ ባህል መሆን አለበት።

10 የትዳር አጋራችን ራሱን እንዲሆን መፍቀድ መቻል አለብን፤ የትዳር አጋራችን በሁሉ ነገር የእኛን ፍላጎት እንዲከተል እና ማንነቱን እንዲቀይር ማስገደድ የለብንም።

11 አክብሮት መለዋወጥ ለባለትዳሮች መሠረታዊ ነገር ነው። ፀያፍ ቁስል የሚፈጥሩ ቃላቶችን በትዳር አጋር ላይ ከመሠንዘር መቆጠብ ያስፈልጋል። በተለይ ይህ ነጥብ በንዴት እና በጭቅጭቅ ወቅቶች ሊተኮርበት ይገባል።

وَقُل لِّعِبَادِي يَقُولُوا الَّتِي هِيَ أَحْسَنُ ۚ إِنَّ الشَّيْطَانَ يَنزَغُ بَيْنَهُمْ ۚ إِنَّ الشَّيْطَانَ كَانَ لِلْإِنسَانِ عَدُوًّا مُّبِينًا [١٧:٥٣]

*‹‹ለባሮቼም በላቸው፦ ያችን እርሷ መልካም የኾነችውን (ቃል) ይናገሩ፡፡ ሰይጣን በመካከላቸው ያበላሻልና፡፡ ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና፡፡ ›› /ኢስራእ 53/*

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# የምዕመናን እናቶች ታሪክ

## ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ

በአረቡ ባህረ ሰላጤ ምድረ በዳ ላይ በነብዩ ( ﷺ)ላይ አንድ ነገር ተከሰተ። ነገሩ እንዲህ ነው። የአላህ መልክተኛ ከመላካቸው በፊት ወደ "ጋር ሄራ" የተባለ ዋሻ እየሄዱ ስለ አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) ያስተነትኑ ነበር። ታዲያ ከዕለታት አንድ ቀን በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ ጅብሪል (ዐለይሂ ሰላም) ከተፍ አለ። ነብዩንም ( ﷺ)ጭምቅ በማድረግ አንብብ አላቸው። እርሳቸውም ማንበብ እንደማይችሉ ነገሩት። እርሱ ግን ሶስት ግዜ በዚህ መልኩ ካደረጋቸው በኋላ የምእራፍ "አል-ዐለቅን" የመጀመሪያዎቹ አምስት አንቀጾችን አነበበላቸው።

" اقرأ باسم ربك الذي خلق1 خلق الإنسان من علق2 اقرأ وربك الأكرم3 الذي علم بالقلم4 علم الإنسان ما لم يعلم5"

*"አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፣ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)2 አንብብ ጌታህ በእጅጉ ቸር ነው3 ያ በብእር ያስተማረ4 ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ነው5" (አል ዓለቅ 1-5)*

ነብዩ ( ﷺ)በሁኔታው እጅግ በጣም ተደናገጡ። ወደ ውዲቷ ባለቤታቸውም እየገሰገሱ በመምጣት ደርቡልኝ ደርቡልኝ በማለት አረፍ አሉ ::ከአፍታ ቆይታ በውኃላ ገጠመኛቸውን አንድ በአንድ ተረኩላት ::ለህይወታቸውም እንደፈሩ ገለጹላት:: ነገር ግን ብሩህን ተስፋ አቀንቃኝ የነበረችው ውዲቷ ባለቤታቸው እንዲህ በማለት አፅናናቻቸው ::

*"ፍጹም አይዞህ ምንም አይገጥምህም። በአላህ ይሁንብኝ አላህ አያዋርድህም። አንት ዝምድናን ቀጣይ፣እንግዳን አክባሪ፣የተቸገረን ደጓሚ፣የታረዘን አልባሽ፣የተራበን አጉራሽ ነህና።"*

በዚህም አላቆመችም። ነብዩን ( ﷺ)ይዛ የአጎቷ ልጅ ወደሆነው ወረቃ ቢን ነውፈል ዘንድ ገሰገሰች። እርሱም ክርስቲያን የሆነና ኢንጅልን የሚያውቅ ነበር። ነገሩን የአላህ መልክተኛ ( ﷺ)አጫወቱት እርሱም:-"ይህ በሙሳ ላይ የወረደው ነው"፡፤በማለት ገለፀላቸው። በመቀጠልም እንዲህ አለ። "ህዝቦችህ ከአገርህ በሚያሶጡህ ሰአት ብኖር ኖሮ እረዳህ ነበር"፡፡ በዚህ ጊዜ የነብዩ ( ﷺ)ድንጋጤ ጨመረ። እንዲህም አሉት። "እነርሱ እኔን ያስወጡኛል?" ወረቃም ይህን መልስ ሰጣቸው:- "አዎ አንተ በመጣህበት የመጣ ሁሉ ጠላት ተደርጐ ይያዛል"። ከዚህ በኃላ ነብዩና ኸዲጃ ወረቃን ተሰናብተው ወጡ። በዚህን ጊዜ ይህች ውድ እንስት የእረፍት ጊዜ እንዳበቃ ተገነዘበች። ከዚህ በኃላ የፈተናዎች አይነት ከሚወርድበት ባል ጋር መተሳሰሯን አረጋገጠች ፡፡ እናም እርሷም ልጆችዋም ፈተናውን በሰፊው ተቋዳሽ እንደሚሆኑ አመነችበት። ለዚህም እራሷን አዘጋጀች። ግን ይህች እንቁ ሴት መጀመሪያ ማን ነበረች??? አዎ! እርሷ ማለት በምቾትና በእንክብካቤ በክብር ያሳለፈች ነበረች። ነገር ግን ይህ ምቾትና ቅንጦት ከባሏ ጐን ተሰልፋ ሽርክን የማርከስ፣ ጣኦትን የመገርሰስ፣ ተውሒድን የማንገስ ትግል ላይ ከመቆም አላቀባትም። ይልቁንም በጌታዋ አመነች። ነብዩንም ተከተለች። የመጀመሪያዋ ኢስላምን ተቀባይ የሆነች እንስት ለመሆንም በቃች። በራሷም፣በገንዘቧም ፣በንብረቷም ከውዱ ባለቤቷ ( ﷺ)ጐን በመቆም ታሪክን አድምቃ አለፈች (ረድየላሁ አንሀ)፡፡ ነብዩም ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ይሉ ነበር። " وأين مثل خديجة صدقتني حين كذبني الناس.."[ማን እንደኸዲጃ አይነት ።ሰዎች ባስተባበሉኝ ጊዜ ያመነችኝ ነበረች] ።

ሙስሊም የዘገቡት ሃዲስ ላይ ደግሞ ጅብሪል (ዐለይሂሰላም) ወደ ነብዩ ( ﷺ) በመምጣት እንዲህ ብሏል :-

"አንተ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይህች ኸዲጃ ነች። ወደ አንተ መጥታለች። ከእርሷ ጋርም ሳህን ይዛለች። በውስጡም ወጥ ወይም ምግብ ወይም መጠጥ አለ።ልክ ስትመጣ ከጌታዋ ከእኔም የሆነን ሰላምታ አቅርብላት።ጀነት ውስጥ ከሸንበቆ የሆነን በውስጡ ጩኸትም ሆነ ድካም በሌለው ቤትም አበስራት።"'

*ታዲያ እህቴ ሆይ! እኔና አንቺ የአማኞች እናት የሆነችውን ኸዲጃን ምን ያህል አርአያ አድርገናታል??? ምንም ቢመጣ ቢከሰት በኢማንና ዳእዋ ላይ ጸንተናል ??? ትክክለኛ*

እምነት (ዓቂዳን) እና የነብዩን ( ﷺ)ፈለግ (መንሀጅ)ን ይዘው በመጓዝ ሌላውን ወደዚህ ብሩህ ጐዳና የሚጠሩ ወንድሞች ጐን ተሰልፈናል?? ባለንና በምንችለው ከጐናቸው ቆመናል?? መልሱን ለአንቺ ትቼዋለሁ::

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

## ዓኢሻ ቢንት ሲዲቅ

ዓኢሻ ቢንት ሲዲቅ የእውቀት ተምሳሌት :-

በኢስላም ታሪክ ውስጥ ሙስሊሟ ሴት ከወንዱ ጐን ቆማ እውቀትን ትቀስም ነበር። ምንም ነገር ሳያግዳቸው በእውቀት መሰላል የበላይነትን ኮርቻ የተቆናጠጡ እንስቶች ጥቂት የሚባሉ አልነበሩም:: ዳሩ የሚደንቅ አይደለም።

ነብያቸው ( ( ﷺ)እንዲህ ሲል መሰረትን ጥሎላቸዋልና

" طلب العلم فريضة على كل مسلم"

*«ዕውቀትን መገብየት (መፈለግ) በማንኛውም ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው፡፡ (ኢብኑ ማጃህ ኪታብ ሱና224)*

ታዲያ ከእነዚህ ውዶች መካከል እናታችንና የነብዩ ( ( ﷺ)ተወዳጅ ባለቤታቸው የነበረችው አዒሻ ቢንት አሲዲቅ በቀዳሚነት ትጠቀሳለች፡፡ እጅግ በጣም ሰፊ እውቀትና ጥልቅ ግንዛቤ የነበራት ሴት ነበረች። እድሜዋ በአስራ ስምንትና በአስራ ዘጠኝ አካባቢ እያለ ነበር ይህን የእውቀት ሀብት ያካበተችው። አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ከሰባት ሰማያት ላይ ንፅህናዋት ያወጀላት እንቁ እንስት ናት። ዓምር ኢብኑል ዓስ ረዲየላሁ ዓንሁ ነብዩ አንድ ጦር ሜዳ ላይ በላኩት ጊዜ የተከሰተውን እንዲህ ሲል ተናግሯል።

ወደ እርሳቸው መጥቼ አንተ ዘንድ በጣም የሚወደደው ሰው ማነው? አልኳቸው። እርሳቸውም {ዓኢሻ} አሉኝ። ከወንዶችስ? አልኳቸው።{አባቷ} አሉኝ። ከዚያስ ማነው? አልኳቸው። {ዑመር ኢብኑል ኸጣብ} አሉኝና ሌሎችንም ወንዶች ቆጠሩ። (ቡኻሪና ሙስሊም )

ስለ አዒሻ (ረድየላሁ አንሀ) ሲናገሩ አል ኢማሙ ዙህሪ እንዲህ ብለዋል :-

*«የአዒሻ ዕውቀት ተሰብስቦ ከሁሉም የነብዩ ባለቤቶችና ወደ ሁሉም ሴቶች ዕውቀት ጋር ቢወዳደር የአዒሻ ዕውቀት ይበልጥ ነበር ፡ ፡ (አል ኢስቲዓብ 4/1883 አል ኢሳባ 8/140)*

አዎ! ስንትና ስንት ታላላቅ ሰሃባዎች ናቸው የተለያዩ የእውቀት ዘርፎችን እንድታብራራላቸው ወደ አዒሻ ይመጡ የነበሩት። ኡርዐት ኢብኑ ዙበይር (ረድየላሁ አንሁ) እንዲህ ብሏል :-

*«በፊቅህም ይሁን በህክምና እንዲሁም በግጥም ከአዒሻ የበለጠ አዋቂ አንድንም አላየሁም» (ታሪኽ አጠበሪ ሃዋዲሱ ሰና 58)*

ሱብሃነላህ! ምን ያላት ታላቅ ሴት ነበረች! አላህ ስራዋን ይውደድላት። አማኟ ሴት ከዚህ ብዙ ትማራለች። ምክንያቱም ኢስላም ያጸደቀላትን መብት ተቋዳሽ የምትሆነው ስታውቅና ሥታውቅ ብቻ ነው። እውቀት ከሌለ ግን የራሷንም ይሁን የሌሎችን መብትና ግዴታ ልታውቅ አትችልም። እናም ውዲቷ እህቴ በተለይ ያላገባሽና ያልወለድሽ ከሆነ ይህንን እድል አላህ እስኪያድልሽ እራስሽን በትክክለኛ እውቀት ከትክክለኛ ሰዎች በመውሰድ ልትገነቢው ይገባል። ነገ እንዳይፀፀትሽ ዛሬውኑ ተጠቀሚበት አላህ የጣሩትን ሊረዳ ቃል ገብቷልና :-

وَالَّذِينَ جَاهَدُوا فِينَا لَنَهْدِيَنَّهُمْ سُبُلَنَا ۚ وَإِنَّ اللَّهَ لَمَعَ الْمُحْسِنِينَ [٢٩:٦٩]

***«እነዚያም በእኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን፡፡ አላህም በእርግጥ ከበጐ ሠሪዎች ጋር ነው፡፡» (አል አንከቡት 69)***

እንግዲህ የእንቁዎችን ማህደር እንዲህ በቀላሉ ዳሰን የምንጨርሰው አይደለም። ነገር ግን ከባህር ላይ መጭለፍም ቢሆን እንኳ ማስታወሱ አማኟ ሴት ከነጠረ ታሪኳ ብዙ እጅግ ብዙ ትማርበታለች።

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ልጄ ሆይ

## የልጆችህ ጓደኞች እነማን ናቸው?

- የልጆችህ ጓደኞች እነማን ናቸው ?
- ከልጆችህ ጓደኞች ጋር ተዋወቀህ ወይንም ቢያንስ እንኳ ተገናኝተህ ታውቃለህ?
- ልጆችህ ከውጭ ወደ ቤት ሲመጡ ምን ይዘው ይገባሉ?
- በልጆችህ ቦርሳ ውስጥ አሊያም በክፍላቸው ውስጥ ምን አለ?

ብዙ አባቶች የነዚህን ጥያቄዎች መልሶች አያውቁም። በቂ መልስ ማቅረብ አይችሉም። በጥያቄው አስፈላጊነት ላይም ጥያቄ ሊያነሡ ይችላሉ። ይህ ስህተት ነው። ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ጓደኞች ማንነት ስለ ልጆቻቸው ዝንባሌ ፣ ስለ ልጆቻቸው ውሎ ፣ ሙሉና በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይገባል። ልጆቻቸው በባህሪና በአካሄድ በዝርዝር ማወቅ አለባቸው። ኃላፊነትም አለባቸው። ነሳኢ በሐዲስ ስብስብ ውስጥ ባካተተው ነብያዊ ሀዲስ ረሱል (ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) « አላህ ኃላፊነት ያለበትን እያንዳንዱን ሠው ኃላፊነቱን በአግባቡ ተወጥቶም ይሁን ኃላፊነቱን ስቶ እንደሆነ ስለተሰጠው ኃላፊነት ይጠየቃል፣(አባት) (ወንድ) ስለ ቤተሰቦቹ (ስለተሰጠው ኃላፊነት) ይጠየቃል» በማለት ተናግረዋል።

ልጆችን የመቆጣጠር ኃላፊነት በመወጣት ዙሪያ አምስት ነገሮችን ማስተዋል ያስፈልጋል።

1. በቁጥጥር ስም የሽብር ድባብ ልጆች ላይ መፍጠር አያስፈልግም። ልጆችን መቆጣጠር ልጆችን ማሸበር ሁለት የተለያየ ነገሮች ናቸው።

2. አንዳንድ የቁጥጥር መንገዶች ድብቅ እና ልጆች በቀጥታ የማያውቋቸው ሊሆኑ ይገባል። ፊት ለፊት ዓይኑን ያፈጠጠ የቁጥጥር ዘዴ መሆን የለባቸውም።

3. ልጆች በራሳቸው ላይ እምነት እንዲያጡ ከማድረግ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በቤተሠብ ውስጥ ያላቸው ታማኝነትም መከበር አለበት። በወላጆችና በልጆች መካከል ያለው ግንኙነት በመተማመንና በግልጽነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። የልጆች ቁጥጥር መስመር መጠበቅ አለበት።

4. በልጆች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር እንዲሁም በጠቅላላው የልጆች አስተዳደግ ላይ የልጆችን የእድሜ ደረጃ የአስተሳሰብ መጠን ግንዛቤ ውስጥ መክተት ያስፈልጋል። የቁጥጥሩ መጠንና ዓይነት እንዚህን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

5. የወላጆች ቁጥጥር የልጆችን ትንፋሽ እስከመቁጠር ድረስ ከፍ ያለ እና መድረሻ የሚያሳጣ ዓይነት መሆን የለበትም። እንዲህ አይነት ቁጥጥር አሉታዊ ነው። የሚያስገኘውም ውጤት አፍራሽ ነው። ልጆች እስረኛ የሆኑ አይነት ስሜት ይፈጥርባቸዋል። በራስ መተማመናቸውንም ይንደዋል። ከዚህም በላይ ለቤተሰባቸው ፍቅር እንዲያጡ ያደርጋል።

በጠቅላላው ማንኛውም የልጆች ቁጥጥር ኢስላም ካስተማረው የልጆች ስርዓትና መርህ መውጣት የለበትም። ረሡል/ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን? ከልጆች ጋር ያላቸው የግንኙነት አካሄድ አጥብቆ እንዲከተል ያስፈልጋል። ውጤቱም ተደናቂ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

## ታዳጊነትና ክና ወላጆች

የታዳጊነት ግዜ እጅግ በጣም ወሳኝ የእድሜ ምዕራፍ ነው። ልጆች ሞግዚትነት እና ዕቅፍ ወጥተው የራስን ወሳኔ ወደ መስጠት የሚራመዱበት የሽግግር ምዕራፍ ነው። በታዳጊነት የእድሜ ክልል በሚከሠቱት በርካታ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ለውጦች ምክንያት ልጆች የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ወላጆች በዚህ ክልል ላይ የተለያየ እንክብካቤና ትኩረት ለልጆቻው መስጠትና አለባቸው። አላህ የጣለባቸውን ታላቅ ኃላፊነት መወጣት አለባቸው። በዚህ ወሳኝ የእድሜ ምዕራፍ ላይ ለልጆቻቸው የሚሠጡት ትኩረት በአላህ ፍቃድ በልጆቻቸው የወደፊት ህይወት ላይ ከባድ ሚና ይኖረዋል።

## በታዳጊዎች ላይ የሚከሠቱ የስነ - ልቦና ሁኔታዎች

### 1 የስሜት መለዋወጥና ቶሎ መቆጣት

ታዳጊዎች በአንድ አጭር ቆይታ ውስጥ በተለያዩ የስሜት ሁኔታ ውስጥ ይለዋወጣሉ። አዲስና ትኩረት የሚስቡ ነገሮች ይማርካቸዋል። እዚህ ግባ በማይባል ቀላል ምክንያት ደግሞ በቶሎ ይቆጣሉ። ራሳቸውን መቆጣጠር አይችሉም። ወላጆች እነዚህን ሁኔታዎች ማወቅና በምላሹ የሚያስፈልገውን አያያዝ በደንብ መረዳት አለባቸው።

### 2 ራስን መሆን / መቻል

ታዳጊዎች ራሱን እንደሚያውቅ ትልቅ ሠው እንዲታዩ ይፈልጋሉ። ከቁጥጥር እንዳልወጡ ህጻናት መታየታቸውን አይፈልጉም። በዚህ ምክንያት ከዕድሜያቸው በላይ በሆነ ትላልቅ ጉዳዮች ውስጥ ራሳቸውን ለመክተት ሲሞክሩ ይታያል። ወላጆች ይህን ስሜት መረዳትና ለስሜቱ የሚመጥን ተገቢ የአያያዝ መንገድ መፈለግ አለባቸው።

ታዳጊዎች በትክክል ለመያዝና ተገቢውን ቤተሠባዊ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ነገሮች።

### 1 ውዴታ

ታዳጊዎች ከላይ ሲታዩ ግልፍተኞችና በቶሎ ስሜታቸውን የሚቀይር ቢሆንም ውስጣቸው የህይወት ተሞክሮና ክፋት ያልበረዘው ንጹህ በጣም ስስ ናቸው። ፍቅርና ውዴታን ማግኘት ይፈልጋል። ወላጆች ይህን የውዴታ ጥማት በቤተሠባዊ ፍቅር ሚሟላት አለባቸው። አለበለዚያ ታዳጊው በመጥፎ መንገድ ይህን ክፍተት ለመሙላት ይሞክራል። ካለፈ በኋላ መጸጸት ዋጋ ስለማይኖረው ቤተሠብ ለታዳጊው ልጁ በዚህ ወቅት ስለሚሠጠው ፍቅርና ወዴታ ጠንቅቆ ማሠብ አለበት።

### 2 ክዝነት

ታዳጊዎች የቤተሠባቸውን በተለይ ደግሞ የእናታቸውን እዝነት ይፈልጋሉ። ከቤተሠባቸው የሚያገኙት እዝነት ውስጣቸው የሚኖረውን ሐዘን የሚያቀልህ ደማቅ ጸሀይ ይሆንላቸዋል። እርጋታን ይሠጣቸዋል። ስለ ወደፊቱ ብሩህ እንዲስቡ ያደርጋቸዋል። ስለዚህም በተስፋ መቁረጥና በታዳጊነት የሐዘን ስሜት ሊዘፈቁባቸው ከሚችሉ ብዙ ችግሮች ራሳቸውን ያርቃሉ።

### 3 ጥበብ

ወላጆች ብዙ የህይወት ተሞክሮዎችን ያሳለፉ እንደመሆናቸው ወደ ህይወት አዲስ እየገቡ ለሚገኙ ልጆቻቸው የሚሠጡት አያያዝና ጥበብና ብስለት የተሞላበት መሆን አለበት። ከታዳጊዎች ጋር የቀጥታ ግጭት ውስጥ መግባት እና ጉዳዩቻቸውን በእልህ መያዝ አያስፈልግም። ጥፋት ሲፈጽሙም ስሜት በሚጎዱ ቃላቶች ምክር መስጠት የለባቸውም። ለምሳሌ:- አንተ ጎረመስክ ማለት ነው። የመሣሠሉትን ቃላቶች መጠቀም ጥሩ አይደለም።

### 4 ውይይት

ታዳጊዎች የሚፈጽሙትን ስህተት ለመፍታት በአላህ ፈቃድ ጠቃሚውና ውጤት የሚያስገኘው የተሻለው አማራጭ ውይይት ነው። ታዳጊዎች ቀጥተኛ ትዕዛዝ ይልቅ በውይይት መልክ በአሳማኝ ሁኔታ የሚሰጣቸውን ምክር ይቀበላሉ። ወላጆች በዚህ ውይይት ወቅት መልዕክት ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ከታዳጊ ልጆቻቸው የሚመጡ መልዕክቶችንም መቀበል አለባቸው።

### 5 ትዕግስት / ሆደ ሠፊነት /

የልጆች አስተዳደግ ረዥም ትንፋሽ ይፈልጋል። ወላጆች በቶሎ መጠበቅ የለባቸውም። ታዳጊ ልጆች ከሌላው ግዜ በበለጠ በሆደ ሠፊነትና ቻይነት የሚንከባከባቸው የወላጆች ትኩረት ይፈልጋል። ሆደ ሰፊነት /ቻይነት/ ኢስላም ክብር የሚሠጠው መልካም ስነ - ምግባር ነው። ረሡል / ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን / ለአንድ ሰሀባ አላህ ከአንተ የሚወዳቸው ሁለት መገለጫ ባህሪያት አሉህ፤ ሆደ ሠፊነት እና እርጋታ ናቸው በማለት ተናግረዋል። ይህ መልካም የቻይነት ስነ-ምግባር በተለይ በታዳጊ ልጆች አያያዝ ላይ ጥቅም መስጠት አለበት።

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ካውንስሊንግ

## በመጀመሪያው ቀን ትውውቅ እንዴት ልገመግመው?

ዕድሜዬ 22 ነው፤ የመጨረሻ ዓመት የዩንቨርስቲ ተማሪ ነኝ፡፡ ከአንድ ወጣት በቤተሰቦቹ በኩል የትዳር ጥያቄ ቀረበልኝ። እናቱ ወደደችኝ እና ለእናቴ ጥያቄዎን አቀረበች፤ አባቱ እና አባቴ ተነጋግረው የሁለታችንም ቤተሰቦች በተገኙበት እንድንተያይ እና እንድንተዋወቅ ቀጠሮ ያዙልን ።

ከልጁ ጋር ምንም የቀደመ ትዉዉቅ የለንም፤ ተያይተን አናውቅም፡፡ ምናልባት ስንተያይ የምርጫውን አይነት ሴት እንዳልሆን ወይንም እርሱ እኔ የማልወደው ዐይነት ወንድ እንዳይሆን ፍርሃት አለኝ። ቤተሰቦቼ ቀጠሮው ለመተዋወቅ ያህል ብቻ እንደሆነ እና ሌሎች እርምጃዎች የሚኖሩት በሁለታችንም በኩል ሙሉ መፈ ቃቀድ ሲኖር ብቻ እንደሆነ አስረድተውኛል።

ጥያቄዬ የሚከተለው ነው ፤

በመጀመሪያ ትውውቅ የምርጫዬን ዓይነት እንደሆነ እንዴት ልገመግመው እችላለሁ?

ስብዕናውን ለመረዳት እና አስተሳሰቡን ለማወቅስ ምን መጠየቅ ወይም መናገር አለብኝ?

የተሳሳተ ምርጫ ላይ ወድቄ የስሜት ጉዳት እንዳይደርስብኝ መጠንቀቅ እፈልጋለውና እባካችሁ ምክር ለግሱኝ።

::::::::::::::

ምላሽ:– ከሁሉም በፊት ከአላህ ጋር ያለሽ ትስስር በጣም ጠንካራ ይሁን፤ ከአላህጋር ያለሽ ትስስር ጠንካራ ከሆነ እና ዘወትር ዱዓ ካልተለየሽ የጉዳዬችሽ ፍጻሜ ሁሉ ያማረ እንደሚሆን አያጠራጥርም። አላህ እርሱን ታዛዦችን ወደ መልካም መንገዶች ይመራል፡፡

وَمَن يَتَّقِ اللَّهَ يَجْعَل لَّهُ مِنْ أَمْرِهِ يُسْرًا

«አላህንም የሚፈራ ሰው ከነገሩ ሁሉ ለርሱ መግራትን ያደርግለታል» ጦላቅ 4

### ውዷ እህታችን!

በጥያቄሽ ላይ እንደቀረበው አይነት የህይወት መንገድን የሚያስቀይሩ መንታ መንገዶች ሲገጥሙን ምርጫን ወደ አላህ ማስጠጋት መልካም መሸሸጊያ ነው፡፡ ፍርሃትና ስጋትን ሁሉ ያጠፋል፡፡ አላህ ትክክለኛውን ምርጫ እንዲያሳይሽ ከብዙ እና ብርቱ ዱዓ ጋር ደጋግመሽ [እስቲኻራ] አድርጊ፡፡

ትዳር ላሠቡ ሁለት ጥንዶች የመጀመሪያ ትውውቅ እና መተያየት በመሀላቸው መፈ ቃቀድ እና ተቀራራቢ የነፍስ ፍሰት መኖሩን ለመፈተሽ ወይም ለማወቅ የሚጠቅም ነው፡፡ በዚህ ሂደት ዐይን በሚያየው አካላዊ ገፅታ አሊያም በንግግርና በውይይት መጣጣምና መፈ ቃቀድ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በዚህ የመጀመሪያ ትውውቅ ወቅት አላህ ከአንቺ ጋር ሁሌም እንደሆነ አስቢ፤ ራስሽን ብቻ ሁኚ፤ ምን መናገር ወይም መጠየቅ እንዳለብሽ በማሰብ ስሜትሽን አትረብሺ፡፡ እነዚህ ነጥቦች ወደ ለትክክለኛው ምርጫ ያግዙሻል፡፡

ነገር ግን ይህ ሰው ትክክለኛ ምርጫ መሆኑን ለማረጋገጥ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ባልሆኑ መንገዶች መሠረታዊ የሆኑ በርካታ ወሳኝ ነጥቦችን መመርመር እና ማጣራት ያስፈልግሻል፡፡

1) ለእምነቱ ያለው ትኩረት ምን ያህል ነው? ሰላት በህይወቱ ውስጥ ምን ቦታ አለው?



ከሰዓት ከመዘውተር እና ከሁኔታ አንፃር በትክክል ሰላቱን ይጠብቃል?

ትክክለኛውን የትዳር አጋር ለማግኘት እነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ማግኘት አለባቸው፡፡ ሰላቱን የሚጠብቅ ሰው ከአላህ ጋር ዘወትር የተሳሰረ ነው ፤ ከአላህገር የተሣሠረ ሰው አብሮ ከሚኖረው ሰው ጋር መልካም ግንኙነት እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

2) ለወላጆቹ ምን ያህል መልካም ነው? ለወላጆቹስ በጎ ነውን? ይህን ጥያቄ ቀጥሎ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

ለወላጆቹ መልካም ከሆነ አላህን የሚፈራ እና የአላህን ውዴታ የሚፈልግ ሰው ለመሆኑ አንድ ማስረጃ ነው፡፡

፨ ከነዚህ ምላሾች በመነሣት ከዚህ ሰው ጋር የህይወት ጥምረት መፍጠር እምነት የሚጣልበት መሆኑን እና አለመሆኑን መገምገም ይቻላል፡፡

3) ከወንድሞቹ ፣ ከእህቶቹ ፣ ከጓደኞቹ፣ ከስራ ባልደረቦቹ እንዲሁም በዙሪያው ከሚገኙ ሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ተወዳጅ ሰው ነው? ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማ እና ያልተረበሸ ነው? ለሰዎች ያለው አቀራረብ ለዛ አለው?

፨ የእነዚህ ጥያቄዎች ምላሾች ደግሞ የማህበራዊ ግንኙነቱን ስኬታማነት ያሳያሉ፡፡

4) የህይወት ታሪኩ ምን ይመስላል? ቢያንስ ስለዚህ አጭር ነገር ማወቅ የኀላ ማንነቱን ለማወቅ ጠቃሚ ነው። ዕውቀት በመፈለግ ባሳለፈባቸው ትምህርት ቤቶች ፣ ሪዝቅ በመፈለግ ባሳለፈባቸው የስራ ቦታዎች እንዲሁም ኑሮውን ባሳለፈበት መንደር ትቶት ያለፈውን የህይወት ጠረን ጥሩ ይሁን መጥፎ ማሽተት ያስፈልጋል፡፡

፨ መልካም ሽታ የመልካም ስነምግባር ውጤት ሲሆን መጥፎ ሽታ የመጥፎ ስነምግባር ውጤት ነው፡፡

5) ተቀዳሚ ምልከታሽ ዲን ይሁን ፤ ገንዘብን ወይንም ማህበራዊ ክብርን ከዲን አታስቀድሚ፤ የነብዩ /የአላህ ሠላም እና ሰላት በእርሳቸው ላይ ይሁን/ የምክር ቃል ይህን ይላል:-

قال النبي صلى الله عليه وسلم: إذا أتاكم من ترضون دينه وخلقه فانكحوه

«እምነቱን እና ስነምግባሩን የወደዳችሁት ሰው የትዳር ጥያቄ ሲያቀርብ ተቀበሉት»

አደራ የምንልሽ ቤተሰቦችሽ የትዳር ጥያቄ ያቀረበውን ሰው አስመልክቶ የሚሰጡትን አስተያየት ቦታ እንዳትነፍጊው ነው። አስተያየታቸው በህይወት ተሞክሮዎች የተፈተሸ በመሆኑ ጠቃሚነቱ አያጠራጥርም፡፡

የምታማክሪዉን ሰው ልታውቂ ይገባል። በእድሜ ላንቺ እኩያ ወይም ካንቺ ያነሱ ያልበሰሉ ወጣቶችን ካማከርሽ፤ ቁሳዊ መመዘኛን ተጠቅመው ወይም ከቅናት ስሜት በመነሳት የማይበጅሽን ሀሳብ ሊለግሱሽ ስለሚችሉ ተጠንቀቂ።

ሁልጊዜም ለአላህ ትእዛዛትና ገደቦች ጥንቁቅ ሁኚ፡፡ አላህን መፍራት ያማረ ፍፃሜ የሚገኝበት ብቸኛ መንገድ ነው።

وَالْعَاقِبَةُ لِلتَّقْوَىٰ

«መልካም መጨረሻም ለጥንቁቆቹ ናት!» ጣሀ 132

©ተንቢሀት

www.facebook.com/tenbihat

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# አርዓያዎቻችን

## ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በመማር ማስተማር የተጉ ድንቅ የሀገራችን ዐሊም

ዑለሞቻችን ሲዘከሩ... የአንድ ሰዉ ስም ከተጠራ ለኢትዩጵያ ሙስሊም ከፍተኛ አስተዎጾ ማበርከታቸዉ ብዙ ባይነገርም ብዙዎች ግን "ተምሬባቸዋለሁ" ይላሉ። እኚህ ሰዉ ተዉሒድን በማስተማር ለአስርት አመታት ታግለዋል። ሚሊየኖች የሚታደሙበት የመረጃ መረቦችና የሀርድ ኮፒ ሲዲዎች ሳይኖሩ በፊት፤ ከደሴው አረብ ገንዳ እስከ አንዋርና ሀሺም መስጂዶች ለረጅም አመታት በሰጧቸዉ የተዉሒድ፣ የሀዲስና የተፍሲር ትምህርቶች ለብዙ ኢትዬጵያውያን ሙስሊሞች መድረስ የቻሉ የኢትዮጵያ ሙስሊም ባለውለታ ናቸው።

ለመሆኑ እኚህ ሸይኽ ማናቸዉ???

ሸይኽ መሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ ይባላሉ።

## ዉልደት

ሸይኽ ሙሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ በወሎ ከተማ ምዕራብ ደሴ የባሲጥ እጅ መንደር በ1938 እ•ኢ•አ በ1945 እ•ኤ•አ ከተከበረ ሙስሊም ቤተሰብ ተወለዱ። የአባታቸዉ ስም አሕመድ ዑመር የእናታቸዉ ስም ዘይነቡ ሽፋ ይባላል። የሸይኽ አልባሲጢይ አባት አሕመድ ዑመር የዘመነ መሳፍንት ባላባት ናቸው። እናታቸው ዘይነቡ ሽፋ የሸይኽ ልጅ ናቸው።

## የ22 ዓመታት የትምህርት ጉዞ

ሸይኽ መሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ የልጅነታቸውን ጊዜ በጥሩ ኢስላማዊ አስተዳደግ ያሳለፉት።ገና በልጅነታቸው በባሲጥ የጁ መንደር ውስጥ ቁርዐንና ሌሎች ተዛማጅ የሸሪዐ ትምህርቶችን ቀስመዋል። በጭንቅላነታቸዉ ቁርዐንን ከእናታቸዉ ዘመድ ከሸኽ አሊ ቡሩ ቀሩ።

- ለ9 አመታት በለገሂዳ መንደር ሸይኽ አሊ አደም ዘንድ የፊቅህ እውቀትን አዳርሰው ቀስመዋል። እኚህ ሸይኽ የታዋቂዉ የመካ አሊም ሸይኽ ሙሐመድ አሊ አደም አል–ወሎዊ አባት ናቸው።
- በመቀጠል ወደ ቃሉ ወረዳ አጋምሳ መንደር ሸህ ተማም ዘንድ በመሄድ ለ 6 አመታት ነህውና ሰርፍ ተምረዋል።
- ከቃሉ ሳይወጡ በቦሩ መንደር ሀጅ ቡሰይር ዘንድ ለአንድ አመት ተኩል ተፍሲር ቀርተዋል።
- ወቅቱ ታላቁ አሊም አል ሐጅ ራፊዕ ወደ ከረጅም አመታት ቆይታ በኃላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ማስተማር የጀመሩበት ወቅት ስለነበር ቀጣጤ መንደር በመዘዋወር ለሁለት አመታት ቡኻሪና ሙስሊምን ቀርተውባቸዋል። ከሸይኹ ጋር የነበራቸው ቆይታ ይህ ብቻ አልነበረም። ሸይኹ የኃላ ኃላ ወደ አዲስ አበባ ሲገቡም ተከትለው በመምጣት ለተከታታይ ሶስት አመታት ከኩቱቡ ሲታ ያልተማሯቸውን አራቱን ሱነኖች አንጥረው ቀርተዋል።በጥቅሉ ወደ ዳዕዋ መንደር ሳይገቡ ለ22 አመታት የሸሪዕ ዕውቀትን ቀስመዋል።

> **ሐጅ ራፊእ በታላቁ አንዋር መስጂድ በራሳቸው ቦታ ላይ ቡኻሪና ሙስሊም እንዲሁም ተፍሲር እንዲያስቀሩ አድርገዋቸው ነበር። ሐጂ ሣኒን ተክተው በአንዋር ትልቁ መስጂድ ውስጥ የተፍሲር ትምህርት መስጠታቸው ይታወሳል።**

## የታላላቅ ዑለማዎች ማእድ

ሸይኽ ሙሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የከተማ ዳዕዋና የመማር ማስተማር ህይወትን አሀዱ ብለዉ የጀመሩት በ1970ዎቹ እ•ኢ•አ ነው። በአዲስ አበባ ከሀጅ ሙሐመድ ሳኒ ሀቢብ ዘንድ ብዙ የተማሩ ሲሆን ሀዲስን በተመለከተም ከሸይኽ ሙሐመድ ራፊዕ ብዙ ተምረዋል።

ከታላላቅ ኡለማዎች በቀሰሙት ጥልቅ እውቀት ለማስተማር የብቃት ማረጋገጫ ኢጃዛ የተሰጣቸው ኢጃዛ በእጃቸው ይገኛል። ከዚህም መካከል የሀዲስ ሊቁ አል ሐጅ ራፊዕ እና የሸይኽ ሙሐመድ ሳኒ ሀቢብ ኢጃዛ ይገኙበታል።

ሸይኽ ሙሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ በሸይኾቻቸው ዘንድ ተወዳጅና ተመራጭ ነበሩ። ሐጅ ራፊእ በታላቁ አንዋር መስጂድ በራሳቸው ቦታ ላይ ቡኻሪና ሙስሊም እንዲሁም ተፍሲር እንዲያስቀሩ አድርገዋቸው ነበር። እንደዚሁ ሀጂ ሳኒንን ተክተው በአንዋር ትልቁ መስጂድ ውስጥ የተፍሲር ትምህርት መስጠታቸው ይታወሳል።

ከዘመናችን ታላቅ ዐሊም ሸይኽ አብዱልዓዚዝ ኢብኑ ባዝ ጋር ጥሩ ወዳጅነት የነበራቸው ሲሆን፤ ሸይኹ ለዳእዋ እንዳበረታቷቸው እና የዒልም ብቃት ፈተናዎችን ካለፉ በኃላ ብዙ መልካም ውለታዎችን እንደዋሉላቸው ይጠቅሳሉ።

ሸይኽ ሙሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ በዘመናችን የፊቅህ ፈርጥ የሆኑትን ሸይኽ ኢብን ዑሰይሚን ብዙ የሚያደንቁና በእጅጉ የሚወዱ ከመሆናቸው ባሻገር ከኪታቦቻቸውም ብዙ ተምረዋል። የአላህ ፍቃድ ሆኖም በመካ ለአስር ቀናት የቆየ የኢልም ኮርስ ታድመዋል። ያዩትን የሸይኽ ኡሰይሚን ትህትና፣ ጥልቅ እውቀትና ግርማ ሞገስ ሲያወጉ በሰፊው ነው።

### ረጅሙ የዳዕዋና የማስተማር ስራ

ሸይኽ ሙሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ በአዲስ አበባ ከተማ ከ38 አመታት በመማር ማስተማር እና በዳዕዋ ላይ የታገሉ፤ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሙስሊሙን በማገልገል ላይ የነበሩ ታላቅ ዐሊም ናቸው። ባለፉት ሶስት አስርት አመታት የሸኹ የተፍሲር ደርሶች ብዙ መስጂዶችን ያስዋቡ ነበሩ። በተለይም አንዋር፣ ሀሸም እና አባቦራ መስጂዶች በሸይኹ የኢልም መጅሊሶች የደመቁ ሆነው ቆይተዋል።

ሸይኽ ሙሐመድ አሕመድ ዑመር አልባሲጢይ ሀቅን ለመናገር ባላቸው ጀግንነት ጥንካሬና ለኢስላም የመቆርቆር ስሜት ይታወቃሉ። ኑር መስጂድ አጠገብ በነበረው ፈትህ መስጂድ ለ22 አመታት ያስተማሩ ሲሆን ከመድረኮቻቸው በአላህ ፍቃድ አያሌ ተማሪዎችን አፍርተዋል። ብዙዎችም የሳቸውን ፈለግ በመከተል በኢልምና በዳዕዋ ሙስሊሙን ማህበረሰብ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በአሜሪካ አትላንታና ዲሲ የነበራቸው የዳእዋ ቆይታ ፍሬያማ የነበረ ሲሆን በሳውዲም በተለያዩ አጋጣሚዎች የዳእዋ ስራዎች ላይ ተሳትፈዋል።

## የሸይኹ ድርሳናት

ሸይኽ አልባሲጢይ በአረብኛ አያሌ መፅሀፍትን የደረሱ ሲሆን በተለይም በቅርቡ ጠንካራ ጥናቶችና ጠቃሚ መልእክቶችን ለንባብ አብቅተዋል። ከነዚህም መካከል፤

1) ኑሩሽምዓህ ፊ መሳኢሊ የውሚል ጁምዓህ

2) ተፍሲሩ ጁዝ ዓምመ

3) ሪሳላህ ፊል ኢማን ቢላህ

4) መዛየል ኢስላም

5) አል መርአቱ ፊል ኢስላም

እና ሌሎችም ይገኙበታል።

## ህልፈታቸው

ሸህ ባሲጥ በደረሰባቸው የጤና መታወክ ህንድ ሀገር የህክምና እርዳታ ሲደረግላቸው ቆይተው ቅዳሜ ነሐሴ 12/2010 ዓ.ል ህይወታቸው አልፏል።

የቀብር ስነስርአታቸው እሁድ ነሀሴ 13/2010 በኮልፌ መካነ መቃብር ተፈፅሟል። ለቤተሰባቸው፣ ለተማሪዎቻቸው እና ለወዳጆቻቸው በሙሉ መፅናናትን እንመኛለን። አላህ ይማራቸው፣ ስራቸውን ይቀበላቸው፣ ትተውት ያለፉትን የእውቀት አሻራ ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ጠቃሚ ያደርግላቸው!

አሚን!!

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# አል ዐፊያ

✍ ዶ/ር ዐብዱልከሪም ግርማ

## የእናት ጡት . . . የጤና ስንቅ !

የእናት ጡት ወተት ለህፃናት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ በተደጋጋሚ ይነሳል። ቢሆንም ለጉዳዩ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት ህፃናት በተገቢው ማንገድ የጠት ወተት ሲያገኙ አይታይም። እናት ለልጇ ጡት በማጥባቷ ሕፃኑ ብቻ ሳይሆን እናትየውም ጭምር በሌላ መንገድ የማይገኙ ፋይዳዎችን ታገኛለች። የእናት ጡት ወተት ጥቅም ከሌላ የማይገኝ እና በአጭርም ሆነ በረጅም ግዜ ለህፃኑም ሆነ ለእናቱ ጤና የማይተካ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ነው።

የእናት ጡት ወተት የሚባለው እናት ልጇን ከተገላገለች ከመጀመሪያው ጥቢ ጀምሮ ጡት እስከሊጥል ድረስ ከእናቱ ጡት የሚያገኘው ወተት ነው። የጡት ወተትን ጥቅሞች ዘርዘር አድርገን ማየት እንድንችል በቅድሚያ ለህፃኑ የሚሰጠውን ፋይዳ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ/በረዥም ግዜ የሚታይ በማለት ከፍለን እንመልከት።

**A. ህፃኑ የእናት ጡት ወተት ብቻን እስከ ስድስት ወር በመጥባቱ የሚያገኛቸውን ባአጭር ግዜ የሚታዩ ፈጣን ጥቅሞች . . .**

ሀ. ህፃኑ ልጅ ማህፀን ውስጥ እያለም ሆነ ከተወለደ በኋላ ከምግብ መፈጨት ጋር በተያያዘ የሚጠቅሙት የሰውነቱ አካላት (የምግብ ቱቦ፣ ጨጓራ፣ አንጀት ...) እድገታቸውን እንዲያጠናቅቁ እንዲሁም ስራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ያደርግለታል።

ለ. የጡት ወተት ህፃኑም ልጅ ከሆድ ድርቀት ይከላከልለታል።

መ. የጡት ወተት ያለግዜያቸው የተወለዱ ህፃናት ካለግዜ ከመወለዳቸው ጋር በተያያዘ የሚያጋጥማቸውን የአንጀት ችግር ይከላከልላቸዋል።

ሠ. የጡት ወተት ለህፃኑ የበሽታ መከላከል አቅምን ያሳድግለታል። ይህም ከእናቱ ወደልጁ በሚተላለፉ በሽታ ተከላካይ ህዋሶችና ንጥረነገሮች አማካኝነት የጡት ወተት ህፃኑን ከተለያዩ በሽታዎች ይታደጋል። በተለይ ከአንጀት ቱቦ ኢንፌክሽን፣ ከመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽን እንዲሁም ከሽንት ቱቦ ኢንፌክሽኖች ህፃኑን የመከላከል አቅም ይፈጥርለታል።

ከላይ ያወሳናቸውም ሆነ በቀጣይነት የምናነሳቸው የጡት ወተት ጥቅሞች ከዱቄት ወተትም ይሁን ከላም ወተት ውስጥ የማይገኙ ናቸው።

**B. ህፃኑ በተዘዋዋሪ መንገድ በረጅም ግዜ ከሚያገኛቸው ጥቅሞች መካከል**

እነዚህ የረዥም ግዜ ጥቅሞች ምንም እንኳ ሳይንስ ሙሉ ለሙሉ ለማረጋገጥ ባይቻለውም የተለያዩ ጥናቶች የተጠቆሙ ናቸው። እነዚህ በረጅም ግዜ የሚገኙ ጥቅሞች የሚሰጡት ፋይዳ ህፃኑ ባጠባበት የግዜ ርዝመት ላይ ይመሰረታሉ። ከእነኝህ ጥቅሞች መካከል ...

ሀ. የእናት ጡት ወተትን በበቂ መጠን ማግኘት ከመጠን ያለፈ ክብደትን/ውፍረት ለመከላከል፣ የካንሰር ህመሞችን ለመከላከል፣ ከእድሜ መግፋት ጋር በተያያዘ ከሚመጣ የልብ ህመምና የተለያዩ አለርጂዎች ለመከላከል፣ ታይፐ 1 ከሚባለው የስኳር በሽታን እንዲሁም የአንጀት ኢንፍላማቶሪ ቦውል በሽታ ለመከላከል እጅጉን ይጠቅማል።

ለ. የጡት ወተት ህፃኑ የእይታውን ብቃት እና የአእምሮ እድገቱን ለመጨመር፣ የዱቄት እና የላም ወተት ከሚጠጡ ህፃናት አንፃር የተሻለ መልካም ባህሪ እንዲኖረው እና በእናትና ልጅ መካከል ያለው ጥምረት እንዲጠናከር ያደርጋል።

መ. የጡት ወተት ልጁ ከኑሮ-ከባቢ ለሚመጡበት ስነልቦናዊም ሆነ የአካላዊ ህመም ተፅእኖዎች ለመቋቋም ይረዳዋል።

እስካሁን ያየናቸው ህፃኑ ልጅ ከተወለደ በኋላ በአጭር ግዜ ውስጥም ሆነ ካደገ እና ከጎለመሰ በኋላ በረጅም ግዜ ሂደት ውስጥ የእናቱን ጡት በመጥባቱ የሚያገኛቸውን ጥቅሞች ነው። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ጡት ማጥባት ለእናት የሚሰጠውን ጥቅም እንመለከታለን። ጡት ማጥባት ለህፃን ልጅ የአጭርና የረዥም ግዜ ፋይዳዎችን እንደሚሰጠው ሁሉ ለእናትም ወዲያው የሚታይም ሆነ ከግዜ በኋላ የሚመጡ ጥቅሞች አሉ።

A. የወዲያው (Immidiate) **ጥቅሞች . . . .**

ሀ. ጡት ማጥባት እናት ልጇን ከተገላገለች በኋላ ከማህፀን የሚፈሰው ደም እንዳይበዛ ለማድረግ እና በእመጫትነት ወቅት ከልክ ያለፈ የክብደት መጨመር እንዳይከሰት ይረዳል።

ለ. ሌላው እናት ከወለደች በኋላ በእርግዝናዋ ምክንያት ወይም በምጥ ምክንያት ከመጡ ተፈጥሮአዊ ለውጦች ቶሎ እንድታገግምና ወደ ቀድሞ አቋሟ እንድትመለስ ይረዳታል። ይህ የሚሆነው ህፃኑ ልጅ ጡት ለመጥባት ከሰውነቷ ጋር በሚያደርገው ንክኪ ምክንያት በአእምሮ ውስጥ በሚመነጭ ኦክሲቶሲን በሚባል ሆርሞን አማካኝነት ነው።

መ. እናት ጡት ማጥባቷ ሌላው ጥቅም ከስነልቦናዊ ጫናዎች እንድትላቀቅ እና ባለማጥባት ከሚመጣ ጭንቀት እንዲሁም ድብርት ለመከላከል መርዳቱ ነው።



B. ጡት ማጥባት ለእናት የሚሰጣቸው የረጅም ግዜ ጥቅሞች ደግሞ ...

ሀ. ጡት ማጥባት ለጡት ካንሰር እና የዘር ፍሬ ካንሰር የመጋለጥ እድልን ይቀንሳል።

ለ. ጡት ማጥባት ለአጥንት መሳሳት ከመጋለጥ ይቀንሳል

መ. ጡት ማጥባት እንዲሁ ከመጠን ያለፈ ውፍረት እና የልብ በሽታን እንደሚከላከልላት በአንዳንድ ጥናቶች ተረጋግጧል።

ከዚህ በተረፈ ህፃን ልጅን ጡት ማጥባት ቤተሰቡ ለወተት ግዢ ከሚያወጣው ወጪ ሲታደግ ይህን ተከትሎ ከሚመጣው የጤና መታወክ እና የህክምና ወጪም ያድናል።

ጡት ማጥባትን በተመለከት ማየት ያለብን ሌሎች ጉዳዮች አሉ። በቅድሚያ ህፃኑ እንደተወለደ ከጡት የሚወጣው የመጀመሪያው ወተት (እንገር) ለህፃኑ ልጅ እጅግ አስፈላጊ እና ሊያልፈው የማይገባ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ህፃኑ ከተወለደ እስከ ሶስት እና አራት ቀን ድረስ የጡት ወተት እጥረት ቢኖርም ጡቱ ወተት የሚያመነጨው ልጁ በጠባው ልክ በመሆኑ የለውም ብላ ከማጥባት ማቆም የለባትም። ምናልባት ወተት የሚያንሰው ከሆነ ግን የሚያደክማትን ስራ መቀነስ፣ ሀሳብ ወይም ጭንቀት ካለ ማስወገድ እንዲሁም ምግብ እና ፈሳሾችን በደንብ መውሰድ ይኖርባታል። መድሀኒት እየወሰደች ከሆነም መድሀኒቱ ወተቱን ሊቀንሰው ስለሚችል ሐኪሟን ማማከር አለባት።

አንድ ህፃን በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንቶች ከስምንት እስከ አስራ ሁለት ግዜ ጡት መጥባት እንዳለበት ይመከራል። ከዛ በኋላ ግን እንደልጁ ሁኔታ የሚጠባበትን ጉዜና ድግግሞሽ ማስተካከል ይቻላል። የሚጠባው ህፃን እንቅልፍ ማጣት ወይም ቶሎ ቶሎ መባነን፣ ጭንቅላቱን ጡት ፍለጋ ማንቀሳቀስ፣ እጁን ወይም ሌላ ነገር መጥባት የሚታይበት ከሆነ ይህን የሚያደርገው ርቦት ስለሆነ እስኪያለቅስ መጠበቅ የለበትም ጡት ሊሰጠው ይገባል። ሌላው አንድ እናት ጡት ስታጠባ ህፃኑ አንደኛውን ጠብቶ እስኪጨርስ ወደ ሌላው ማዞር የለባትም ይህ አንድ ልጅ በቂ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ሙሉ በሙሉ እንዲያገኝ ሲያደርገው ጡቱ ደግሞ ሙሉውን ሲጠባ ለቀጣይ እንዲያመርት ያደርገዋል።

እናት ልጇን ለሁለት አመት ያክል እንድታጠባ ይመከራል ጌታችን አላህ (ሱ.ወ) ያለውም ይኸው ነው።

﴿وَالوالِداتُ يُرضِعنَ أَولادَهُنَّ حَولَينِ كامِلَينِ لِمَن أَرادَ أَن يُتِمَّ الرَّضاعَةَ﴾

*"እናቶችም ልጆቻቸውን ሙሉ የኾኑን ሁለት ዓመታት ያጥቡ፡፡ (ይህም) ማጥባትን መሙላት ለሻ ሰው ነው" አልበቀራ 233*

ህፃን ልጅ ጡት በመጥባቱ ቶሎ በሚታዩ የአጭር ጊዜም ሆነ የረጅም ግዜ ጥቅሞችን ያገኝበታል። በአጭሩ አንድ ልጅ በቂ የጡት ወተት ማግኘቱ ለቀሪ ህይወቱ የጤና ስንቅ ይሆነዋል።

እናት ልጇን ጡት ማስጣል ስትፈልግ በአንድ ግዜ ማስቆም አይመከርም። ምክንያቱም ጡት የሚጥለው ህፃን ከእናቱ በጡት የሚያገኛቸውን ጥቅሞች ሙሉ በሙሉ ከምግብ እንዲወስድ ማላመድ ያስፈልጋል። ስለሆነም በእያንዳንዱ ግዜ የሚጠባውን የጊዜ ርዝመት በመቀናነስ ቀጥሎም በቀን የሚጠባበትን ድግግሞሽ በመቀነስ ቀስ በቀስ ማስጣል ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ድንገተኛ ጡት መጣሉ ህፃኑ ላይ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳት ሊያደርስበት ይችላል።

የጡት ወተት የሚያንሳቸው እናቶች የላም ወተት ከአንድ አመት በታች ለሆኑ ህፃናት እንዲሰጡ አይመከርም። የላም ወተት ህፃኑ ላይ አለርጂዎችንና የደም ማነስን ሊያስከትልበት ይችላል። ሌላው የላም ወተት አንዳንድ በጡት ወተት ከሚገኙ በቂ ንጥረነገሮች በላይ ስለሚይዝ የህፃኑ ሰውነት እነዚህን አላስፈላጊ ንጥረ ነገሮች ለማስወገድ ሲል ኩላሊቱ ላይ ጫና ሊበዛበት ይችላል። ምናልባት የላም ወተት ተሻሽሎና ንጥረነገሮቹ ተቃልለው ከቀረቡ ከስድስት ወር በላይ ላሉ ህፃናት ልንጠቀመው እንችላለን።

የዱቄት ወተትም ቢሆን በየእድሜ ክልሉ የተዘጋጀ ካልሆነ ለላም ወተት የጠቀስናቸውንና ሌሎችም ጉዳት ሊኖረው ይችላል። ለጨቅላ ህፃናት ተመጥኖ የሚዘጋጀው ግን የእናት ጡት በቂ ወተት ማምረት ሲሳነው ልንጠቀመው እንችላለን። ሆኖም ከእናት ጡት የሚገኙ ጥቅሞች ከዚህ አይነቱ ወተት አይገኝም።

በመጨረሻም ጡት ማጥባት የማይመከሩ እናቶችን እንመልከት። እነዚህ እናቶች ወደ ህፃናት ሊተላለፉ የሚችሉ በሽታዎች ያሉባት እናት፣ መቋረጥ የሌለበት ህፃኑን ሊጎዳ የሚችል መድሀኒት የምትወስድ እናት እንዲሁም የጡት ካንሰር ያለባት እናትና በአንዳንድ ኢንፌክሽኖች ጡቷ የተጠቃ እናት በበሽታው ከተጠቃው ጡት ማጥባት የለባትም።

እንደ ኤች አይቪ ባለ በሽታ የተጠቃች እናት ለህፃን ልጇ እስከመጨረሻው የዱቄት ወተት መግዛት የምትችል ከሆነ ባታጠባ ይመከራል። ያ ካልሆነ ግን የመከላከያ ሕክምናውን እየወሰደች ማጥባት ይኖርባታል ሆኖም ጡት እያጠባች ለልጇ የዱቄት ወተት መስጠት የለባትም። ምክንያቱም የዱቄት ወተቱ ህፃኑን ለቫይረሱ ተጋላጭ ሊያደርገው ስለሚችል ነው።

በዚህ ፅሁፍ ለመጥቀስ የሞከርነው የእናት ጡት ወተት አስፈላጊነት እና ተጓዳኝ ነጥቦችን ነው በቀጣይ በአላህ ፈቃድ ሌሎች ጠቃሚ ርዕሶችን እንዳስሳለን።

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ነሲሓ

# ብዕር



- ለምን ተፈጠርኩ
- የአል ኡሱሉ ሠላሣህ ጭብጦች
- ፍትህን እንጠብቅ
- ለሌሎች ምን አበርክተሃል?
- ክብር ለሰሓቦች
- ቁርኣን የአላህ ንግግር
- የምርጦች ምርጥ
- አደብን ተማር
- የመልካም መክፈቻ ሁን!



# ለምን ተፈጠርክ?

ከ

ለምን?

ለምን ወደዚህ ዓለም መጣህ? ለምን ተገኘህ? ለምን ተወለድክ? ለምን ተፈጠርክ?

ለምን? ራስህን ጠይቀው እስኪ?

ለምን እዚህ ምድር? ምን ላደርግ? ምን ልፈይድ መጣሁ?

"ለምግብ ለመጠጥ? ወይስ ላገባ ልወልድ? ነው ወይ ሀብት ንብረት ላከማች? ወይንስ ስልጣን ዙፋን ልይዝ? አሊያ ታዋቂ ተደናቂ ልሆን?"

አስተውል! ይህን ጥያቄ አንተም ሆንክ ሌላ - ማንም አይመልሰውም! ከፈጠረህ ጌታ በስተቀር!

እርሱ ግን ለምን እንደፈጠረህ ያውቃል፣ እርሱው ይነግርሀል? ...

*["ጋኔንንና ሰውን ሊገዙኝ (ሊያመልኩኝ) እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም ❁ ከነሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፤ ሊመግቡኝም አልሻም"] ሱረቱ 'ዛሪያት 56 -57*

የተፈጠርከው ለዚህ ነው!

ፈጣሪህን ጌታህን አላህን፡- ልታውቀው ልታልቀው ልታከብረው ልትወደው፤ ያለ ተጋሪ በብቸኝነት ልታመልከው - ልትገዛው ነው!

ከእርሱ ሌላ ካለ የሀሰት ተመላኪ ልትርቅ ነው። ወደ እርሱ ልትመለስ፣ ልትሰግድ፣ ልትፆም ... ልትታዘዘው ነው!

እየውልህ! ተድላህ፣ ሀዘንህ፣ ኑሮህ፣ ሞትህ ለዛው ለፈጠረህ አላህ ለተፈጠርክበት አላማ ነው። ሌላ ግብ የለህም! ...

*["«ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል ❁ «ለእርሱ ተጋሪ የለውም፡፡ በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ ... » (በል)"] አል - አንዓም 162-163*

የምትኖረውም የምትሞተውም ለአምልኮ ነው! አላህን ብቻ እና ብቻ ለማምለክ!

ዓለማህ ላይ በስኬት ከተገኘህ ታላቅ ሽልማት አለህ። በዚህ ጭንቀት ሐሳብ ሩጫ ልፋት በማያቋርጥበት ዓለም፡- አንተ መልካም አስደሳችና ሰላማዊ ህይወትን ታጣጥማለህ።

በዛ ደግሞ ሰዎች እንደ ወንጀላቸው ወደ ገሀነም በሚነዱበት ዓለም ላንተ የማይሰፈር የማይመዘን፤ ያላየኸው ያልሰማኸው፣ በልብህም ውል ብሎብህ እንኳ የማያውቅ የፀጋ የተድላ የምቾት ሀገር ይጠብቅሀል። እንዳሻህ የምትምነሸነሽበት የጀነት ዓለም!

*["ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሠራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ ይሠሩትም በነበሩት ነገር (በቀጣዩ ዓለም) ምንዳቸውን በተሻለ እንመነዳቸዋለን"] አል-ነህል 97*

የምትኖርበት ዕድሜ ምንም አጭር ቢሆንም የተፈጠርክበትን አላማ ለማሳካት ከበቂ በላይ ነው። ግና መንገዱን ማወቅ አለብህ! ለዚህ ደግሞ አላህ አንተን ፈጥሮ አልተወህምና ይህን የሚያስተምሩህ አዛኝ እና ሩህሩህ ነብይ ልኮልሀል። መከተል ያንተ ፋንታ ነው!

*["ከናንተው የሆነ ችግራችሁ በርሱ ላይ ጥኑ የሆነ፣ በናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእምናን ላይ ርኅሩህ አዛኝ የሆነ መልክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ"] ሱረቱ ተውባ 128*

አስተውል! አላማህን መለየት ትልቅ ነገር ነው፤ እርሱን አሳክተህ ደግሞ ለተደገሰልህ ሽልማት መጓጓት ተገቢ ነው። ሆኖም አንድ ጥያቄ ሊኖርህ ይገባል፤ እንዴት አድርጌ ላሳካው? እንዴት አድርጌ አላህን ልገዛው?

> **"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ኢስላም ጥቅልል ብላችሁ ግቡ። የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ፤ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና" አል-በቀራ 208**

ያዝ!

ከምንም ነገር እውቀት ይቀድማል። በቅድሚያ ፈጣሪህን፣ የምትገዛውን አላህን ፈጣሪነቱን፣ ንግስናውን፣ አስተናባሪነቱን ሌላውንም የጌትነት ስልጣኑን ልታውቅ! እንዲሁም በብቸኛ ተመላኪነቱ እሱን ብቻ ልትለምነው፣ ልትታገዝበት፣ ልትጠበቅበት፣ ለጭንቅህ ደራሽህ ልታደርገው የሚገባ መሆኑን ልትረዳ! በተጨማሪም የእርሱን መልካም ስምና ባህርያቱን አጥንተህ የጌታህን ብቸኛ ተመላኪነት (ተውሒድ) በትክክለኛው መልኩ ማወቅና ማመን ይጠበቅብሀል።

["እነሆ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን ዕወቅ ..."] ሙሐመድ 19

እንዲሁም እርሱ ወዳንተ የላከውን ነቢይ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ማንነት፣ ታሪክ፣ አስተምህሮ፣ የሳቸውንና እና የሶሐቦቻቸውን ፈለግ(ሱና) ልታውቅ ልትማር ይገባሀል።

በሌላ በኩል እንድትገዛው የፈጠረህ አላህ እርሱን በምን መልኩ መገዛት እንዳለብህ ያወረደውን የተሟላ እና ገር የሆነውን እስልምና ከመሰረቱ ጀምረህ ልትማር ይገባሀል።

ይህ የተፈጠርክበትን አላማ አሳክተህ ዘላለማዊ ደስታን የምትጎናፀፍበትን መንገድ የምታውቅበት ሂደት ነውና ከምንም ነገር በላይ ትኩረት ሰጥተህ መወጣት አለብህ!

ይህን የተማርከውን ያወቅከውን ደግሞ ወደ ተግባር በማምጣት የስኬት መንገድህን ለመጀመር የምታባክነው ግዜ ሊኖር አይገባም። ጠላትህ ከአላማህ አዘናግቶ በአላፊ ማታለያ ሊያደናቅፍህ ከመንገድህ ተሰይሟልና ለሸይጧን እድል መስጠት የለብህም!

*["እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ኢስላም ጥቅልል ብላችሁ ግቡ፡፡ የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ፤ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና"] አል-በቀራ 208*

ያወቅከውን እና በቻልከው ልክ በተግባር ላይ የምታውለውን የፅድቅ መንገድ ታዲያ ለሌላውም በማጋራት ያ ሰው ቅኑን መንገድ ቢከተል የሚያገኘውን ምንዳ ከርሱ ሳይቀነስ መቋደስን አትርሳ። ያወቅከውን ማሳወቅ ግዴታህም ጭምር ነውና በጥሩ ሁኔታ ማድረሱን አትዘንጋ!

ይሁንና የስኬት ጎዳና አልጋ ባልጋ አይደለም። ዘላለማዊ ደስታ ያለፈተና አይገኝም። በዚህች ምድር እስካለህ በተለያየ አቅጣጫ አቋምህን የሚፈታተን ተግዳሮት ይመጣብሀል፤ ይህኔ የትእግስትን ጋሻ አንግበህ ወደ ፊት መቀጠል እንጂ ፍፁም ወደኋላ ማለት የለብህም፤ ዓላማህን ጥለህ ወዴት ትመለሳለህ? ወደ ጀሀነም?

*["ሰዎቹ አምነናል በማለታቸው ብቻ እነሱ ሳይፈተኑ የሚተዉ መሆናቸውን ጠረጠሩን? ❁ እነዚያንም ከነሱ በፊት የነበሩትን በእርግጥ ፈተንናል፤ እነዚያንም እውነተኞቹን አላህ በእርግጥ ያውቃል፤ ውሸታሞችንም ያውቃል"] አል-ዓንከቡት2-3*

በዓላማህ ፀንተህ ስትጓዝ አለማዊ ጥቅሞችህን ትተዋለህ ማለት አይደለም። ከዚህ መብቃቃት አይቻልህም! ይሁንና ለመኖር ስትል መብላት ይኖርብሀል እንጂ ለመብላት ስትል አትኖርም። ፈተናው እዚህ ላይ ነው፤ ጠላትህ ግን ተቃራኒውን ይሰብክሀል። እንዳትሸነፍ!

አላማህን በማሳካት ከዛ አስፈሪ ቅጣት ለመዳን እና ያንን የሚያስጎመዥ ሽልማት ለማግኘት መንገዱን ዛሬ ነገ ሳትል ጀምረው። ሞት መች መጥቶ እንደሚቀድምህ አታውቅምና!

*["ከጌታችሁ ወደ ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ሆነች ገነት፥ አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትሆን ተቻኮሉ"] አሉ-ዒምራን 133*

አላህ ባነበብነው የምንጠቀም ያድርገን!!

✍ አቡ ኢብራሂም ሙሐመድ ኢብራሂም

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# የአል–ኡሱሉ ሰላሳህ ኪታብ ጭብጦች እና የተደራጀው የማጠልሸት ፕሮፓጋንዳ!

አል ኡሱሉ ሰላህ (ሶስቱ መሰረተሰዊ መርሆዎ ኪታብ) ወሳኝ የአኼራ ጥያቄዎችን በማስታወስ ቁርአንና ሀዲስን መሰረት አድርጎ ለጀማሪ ተማሪዎች የተዘጋጀ ምርጥ ትምህርት ነው። ቁርአንና ሱናን መሰረት አድርጎ የተከተበው ይህ መፅሐፍ፤ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ዘርፈ ብዙ የማጠልሸት ፕሮፓጋንዳዎች ኢላማ አድርገውታል። በበርካታ ሀዲሶች የተብራሩ ግልፅ መሰረቶችን የሚያብራራውን ድንቅ መልእክት ሲያጠለሹ፤ የኩፍር መፅሐፍ፣ መፅሀፈ ስላሴ፣ የወሓቢያ ካሪኩለም ወዘተ... በማለት ተማሪዎችን ለማሸማቀቅ ይሞክራሉ። በተለይ አንዳንድ አደብ ያጡ ኹራፊዮች የነጃሳ መሰረቶች "ኡሱሉ ነጃሳ" ይሉታል። ለመሆኑ ተውሂድ የማይመቻቸውን ወገኖች እንቅልፍ ያሳጣው አል ኡሱል አሰላሳህ የሚዳስሳቸው ቁምነገሮች ምን ምን ናቸው?

በሸይኽ ሙሀመድ ኢብኑ አብድልወሀብ የተዘጋጀው ይህ መፅሀፍ አንድ ሰው ጌታውን ነብዩን እና ዲኑን መገንዘብ እንዳለበት ይመክራል። መፅሀፉ አንድን ቁምነገር ለማስተላለፍ መረጃን ብቻ በመጥቀስ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከፍተኛ ተቀባይነትን አትርፏል።

በመፅሀፉ በዋናነት የተዳሰሱት ሶስቱ መሰረታዊ ጉዳዮች በሀዲስ ላይ በቀጥታ የቀብር ጥያቄ መሆናቸው ተዘክሯል።

ሁለቱ መላእክቶች እነዚህን ጥያቄዎች እንደሚጠይቁ የሚገልፀው ሀዲስ በኢማሙ አህመድ የተዘገበ ሀዲስ የታወቀ ሲሆን፤ ሌላም ሀዲሶች እነዚህን መሰረታዊ አጀንዳዎች አንስተዋቸዋል። ከአል ዓባስ ኢብኑ አብደልሙጠሊብ የተዘገበው ሀዲስ እንዲህ ይነበባል።

عن العباس بن عبد المطلب في صحيح مسلم أنَّه سمع رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول "ذاق طعم الإيمانِ مَن رضي بالله ربًّا، وبالإسلام ديناً، وبمحمد رسولاً "رواه مسلم

«አላህን በጌትነት፣ ኢስላምን በሀይማኖትነት ሙሀመድን በመልእክተኝነት ወዶ የተቀበለ የኢማንን ጣዕም አጊኝቷል» ሙስሊም ዘግበውታል ተመሳሳይ መልእክት ያለውን የአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ ሀዲስም ኢማሙ ሙስሊም ዘግበውታል።

በማጠልሸት ፕሮፓጋንዳ ተጠቅተው ሳያውቁት ሀሰትን ለሚያራግቡ ሁሉ መፅሀፉን እንዲማሩት እየመከርን ለተዛላፊዎቹ አላህ ልብ የሰጣቸው ዘንድ ፀሀፊውንም አላህ ይምራቸው ዘንድ እንለምነዋለን።

ባለፉት አመታት የተውሂድ ተጣሪዎች ላይ ወሓቢያ የሚል ስያሜ በመለጠፍ ከፍተኛ የማጥላላት ዘመቻዎች መካሄዳቸው ግልፅ ነው።

## ለመሆኑ ሰዎች ወሓቢያ ተብለው የሚፈረጁበት መስፈርት ምን ይሆን?

ሸህ ሙሀመድ ቢን አብድልወሀብ ከኖሩባቸው አካባቢዎች በራቁት እንደ ህንድ ባሉ አገሮች ከቁርአን እና ከሱና እንዲሁም ከቀደምት አበዎች የተወረሱ አስተምህሮቶች ከእሳቸው ዳእዋ በብዙ ምእተአመታት ቀድመው የተስፋፉ የአህሉልሀዲስ ዳእዋዎች ይታወቃሉ። በሰሜናዊው አፍሪካ በየመን እና በብዙ አረብ አገራትም ሸይኹን ሳያውቁ ነገር ግን ተመሳሳይ ግንዛቤና ጥሪ የነበራቸው ብዙ ናቸው።

**መፅሀፉ አንድን ቁምነገር ለማስተላለፍ መረጃን ብቻ በመጥቀስ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከፍተኛ ተቀባይነትን አትርፏል።**

ከተላላቅ የአልጄሪያ ኡለማዎች መካከል እ.ኤ.አ 1960 ያለፉት ሸይኽ ጠይብ አል–ዑቅቢ "እንዲህ ቢሉኝ እንዲህ አልኳቸው" በሚል ርእስ ባሰፈሩት ወግ ላይ ይህንን ብለዋል፤ « ሰዎች 'ያንተ እምነት የወሓብዮች አይነት ነው' ሲሉኝ፤ "ይህ ከሆነማ ወሀብዮች ማለት የአላህን አንድነት የሚያረጋግጡ (ሙወሂዶች) ናቸው ማለት ነው" በማለት እመልስ ነበር» ሲሉ ፅፈዋል።»

ምንጭ፡- ሺሀብ ጋዜጣ ኦክቶበር 27/1927

በሌላም ፅሁፋቸውም፤

«በዳእዋ ስራ ህዝባችንን ግንዛቤ ማስጨበጥና በትክክለኛው ኢስላማዊ አስተምህሮ ማነፅ እንፈልጋለን። ይህንንም በሁለት ነጥቦች ማስቀመጥ ይቻላል።

1) ከአላህ በስተቀር ማንንም አለማምለክ፤

2) አላህን የምናመልከው እርሱ በደነገገውና ከሱ ዘንድ በመጣው መመሪያ መሆን አለበት።

ወሓብያ ማለት፤ አላህ ለባሮቹ በደነገገው መልኩ እርሱን በብቸኝነት ማምለክ ከሆነ፤ ይህ አላህን የምናመልክበት ዲናችን፣ መዝሃባችንም ነው። ገር የሆነው መንገዳችን እሱ ነው። በዚህ ላይ ኖረን በዚሁ አቋም ላይ እንሞታለን። በአላህ ፍቃድም ከሚድኑት ሆነን እንቀሰቀሳለን።»

**ምንጭ፡- ሱና ጋዜጣ አፕሪል 22 1933 እትም ካቀረበው ፅሁፋቸው**

እውነት ነው! ባሁኑ ጊዜ፤ የኢስላምን ብርሐን ከጃሂሊያ ፅልመት የለየ፤ አላህን በብቸኝነት አምልኩ፤ ከቀብር አምልኮ፣ ቅዱሳንን ከመማፀን እንዲሁም ከማንኛውም የባእድ አምልኮ ተግባር እንራቅ... ያለ ሁሉ ወሀብይ ይባላል። በተለይም ባሁኑ ዘመን የጃሂሊያን ሽርክ ለማንገስ የሚሯሯጡ አካላት ዘንድ ወሀቢያ የሚለው ታፔላ የጧት ማታ መዝሙር ሆኗል።ሀቁ ግን፤ ከሸይኽ ሙሀመድ አብዱልወሀብ ዳእዋ በፊትም ይሁን በኃላ፤ እራሱን ከተፅእኖ አላቆ ላስተዋለ ሁሉ፤ ቅዱሳንን ማምለክ ከኢስላማዊ አስተምህሮ ጋር ፍፁም የሚጋጭ የሽርክ ተግባርና የጃሂሊያ ቅሪት መሆኑን አያጣውም! ኢስላም ማለት የአላህን አንድነት በማረጋገጥ ለርሱ ትእዛዛት ማደር መሆኑ ያጠራጥራልን?

አላህ ሆይ! ከኛ መካከል በጃሂሊያ የሽርክ ጥሪ የተሸነገሉን ሁሉ የተውሂድን ብርሀን አሳያቸው! ባጢል ልቦናቸውን ሰውሮታልና በጥበብህ ወደ ተፈጥሯዊ ምልከታቸው መልሳቸው! አሚን!

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

✍ አቡ ጁነይድ ሳላሕ አሕመድ



# ፍትህን እንጠብቅ!

## ለእውነት ከመቀርቀር ጋር ፍትህን እንጠብቅ!

እውነት መቆርቆር በመሰረቱ የሁሉም ግዴታ ቢሆንም ወደ ጭፍን ስሜታዊነት ተሻግሮ ለከት እንዳይጥስ ሸሪዓዊ ልጓም ሊታሰርለት ያሻል። በዚህ ረገድ ብዙዎች ዘንድ ከሚስተዋሉ እንከኖች አንዱ ባመኑበት ጉዳይ ላይ በሚኖራቸው የጋለ ወኔ የተነሳ የተቃረኗቸው ግለሰቦች ማንነትና ክብር ላይ ያለ ፍትህ መፍረዳቸው ሲሆን ይህም ከሚንፀባረቅባቸው የግድፈት መስኮች አንዱ ስለሌሎቹ ውስጣዊ አላማና እቅድ ያለ በቂ አስረጅ መደምደምና እነርሱንም በአድርባይነት መፈረጅ ነው። ሙስሊሞች ሆይ! «ሙናፊቅ፣ የአይሁድ ቅጥረኛ፣ የመንግስት ካድሬ...» ወይም «ስልጣን ፈላጊ፣ በሙስሊሙ ስም የሚነግድ አስመሳይ፣የተውሒድ ጠላት...» እና መሰል የቃላት ጥቃቶች እንደ ቀትር ፀሐይ ፍንትው ያለ ማስረጃ እስካልደገደፉቸው ድረስ እጅጉን የከበዱ መዘዞችን ያስከትላሉ! ወንድሞችና እህቶች ሆይ! ይህ እኮ በግንፍልተኝነት የሚዳፈሩት ተራ ዘለፋ አይደለም።

(( سَتُكْتَبُ شَهَادَتُهُمْ وَيُسْأَلُونَ ))

=«ምስካሬያቸው ይፃፍና ይጠየቃሉ!» [አዝ-ዙኽሩፍ 19]

የሚከተሉትን ሁለት መዘዞች አብረን እናስተውል፡-

*** አንደኛ፡-**

የአንድን ሙስሊም ክብር ያለ አግባብ ማጉደፍ ጉዳዩን የተመለከቱ ሸሪዓዊ ትዕዛዛትን መጣስ ከመሆኑ ባሻገር ለከፋ ቅጣትም ያጋልጣል።

"عن ابن عمر، عن النبي -صلى الله عليه وسلم - أنه قال : مَن قَالَ فِي مُؤْمِنٍ مَا لَيْسَ فِيهِ، أَسْكَنَهُ اللّهُ رَدْغَةَ الْخَبَالِ حَتّى يَخْرُجَ مِمّا قَالَ ..."

ኢብኑ ዑመር ባስተላለፉት ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«በአንድ አማኝ ላይ የሌለበትን የተናገረ ከንግግሩ ጣጣ እስኪወጣ ድረስ አላህ የ"ጥፋት ማጥ" ውስጥ ያኖረዋል!»

[አሕመድ (ቁ. 5385)፣ አቡ ዳዉድ (ቁ. 3597) እና ሌሎችም የዘገቡት ትክክለኛ ሐዲሥ ነው፤ "ሲልሲለቱ'ል - አሓዲሥ አስ-ሰሒሓህ" (ቁ.437) ይመልከቱ።]

በሌላ አጋጣሚ ሰሓቦች «የ"ጥፋት ማጥ" ( رَدْغَةَ الْخَبَالِ ) ምንድነው?» ብለው ሲጠይቁ ነብያችንም «የእሳት ነዋሪዎች እዥ!» ብለው መልሰዋል። [ኢብኑ ማጃህ (ቁ.3377)]

- «ሙስሊምን መሳደብ አመፅ ነው!» የሚለው የነብያችን ንግግር [አል-ቡኻሪይ (ቁ. 46)፣ ሙስሊም (ቁ. 64)]

ማንኛውንም አግባብ-የለሽ ስድብ የተመለከተ ከሆነ ጭራሽ እምነት ላይ የሚያነጣጥር ዘለፋ ደግሞ ከዚህ የከፋ መዘዝ እንደሚኖትት ግልፅ ነው። ይህንን የሚያጠናክረው ሁለተኛው ነጥብ ነው፡-

**ሁለተኛ፡-**

አንድ ሙስሊምን ያለ አግባብ "ከሃዲ፣ የአላህ ጠላት፣ ሙናፊቅ.." ብሎ መጥራት እምነትን ለአደጋ የሚያጋልጥ አደገኛ ጠንቅ ነው።

"عن ابْنَ عُمَرَ، قَالَ رَسُولُ اللهِ -صَلّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلّمَ :- أَيُّمَا امْرِئٍ قَالَ لِأَخِيهِ : يَا كَافِرُ، فَقَدْ بَاءَ بِهَا أَحَدُهُمَا، إِنْ كَانَ كَمَا قَالَ، وَإِلّا رَجَعَتْ عَلَيْهِ "

ኢብኑ ዑመር ባስተላለፉት ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

***«ወንድሙን "አንተ ከሃዲ" ያለ ማንኛውም ግለሰብ ከሁለቱ አንዳቸው ይህን ተሸክሞ ይመለሳል፤ እርሱ እንዳለው ካልሆነ በስተቀር (ፍርዱ ወይም መዘዙ) ወደ ራሱ ይመለሳል!»***

[አል-ቡኻሪይ (ቁ.6104)፣ ሙስሊም (ቁ. 60)]

**«በአንድ አማኝ ላይ የሌለበትን የተናገረ ከንግግሩ ጣጣ እስኪወጣ ድረስ አላህ የ"ጥፋት ማጥ" ውስጥ ያኖረዋል!»**

- አቡ ዘር ባስተላለፉት ሌላ ዘገባ ላይ ደግሞ፡-

"..وَمَنْ دَعَا رَجُلًا بِالْكُفْرِ، أَوْ قَالَ : عَدُوُّ اللهِ وَلَيْسَ كَذَلِكَ إِلّا حَارَ عَلَيْهِ "

= «. . .አንድን ሰው በከሃዲነት የፈረጀ ወይም "አንተ የአላህ ጠላት!" ብሎ የጠራው እርሱ እንዳለው ካልሆነ (ፍርዱ ወይም መዘዙ) ወደራሱ መመለሱ አይቀርም!» ብለዋል።

[አል-ቡኻሪይ (ቁ.6045)፣ ሙስሊም (ቁ. 61)]

- ሣቢት ኢብኑ አድ-ዶሕ-ሓክ በሚያስተላልፉት ሐዲሥ ደግሞ፡-

وَمَنْ رَمَى مُؤْمِنًا بِكُفْرٍ فَهُوَ كَقَتْلِهِ ...»

= «አንድን አማኝ በከሃዲነት መወንጀል እርሱን እንደ መግደል ነው!» ብለዋል።[አል-ቡኻሪይ (ቁ.6105)]

ለዚህ ታላቅ ጥፋት ሊያበቁ የሚችሉ አንዳንድ ግርድፍ ግንዛቤዎችን ለማረም የሚከተሉት ሶስት ቁም ነገሮችን እንተዋወስ፡-

(1) ሰዎች በግልፅ ከሚያንፀባርቁት እምነትና አላማ ውጭ ከነርሱ ራሳቸው በቀር አላህ እንጂ ማንም ሊያውቀው ስለማይችለው የሆዳቸው ሚስጥር መላ መምታት ጥፋት እንጂ ብልሃት አይደለም። በመለኮታዊ ወሕይ በቀጥታ ይታገዙ የነበሩት ታላቁ መልዕክተኛ እንኳ በአንድ አጋጣሚ ለሰዎች ንብረት ሲያከፋፍሉ አክብሮት በጎደለው ቃና ፍርዳቸውን በቀጥታ የተፃረረውን ግለሰብ አስመልክቶ ኻሊድ ኢብኑ'ል ወሊድ «አንገቱን (በሰይፍ) ልበለው?» ብሎ ሲጠይቃቸው እርሳቸውም «አይ! ምናልባት የሚሰግድ ሊሆን ይችላል!» አሉት። ኻሊድም መልሶ «ስንት በልቡ የሌለውን በምላሱ የሚናገር አለ!» ሲላቸው እንዲህ ብለው መለሱለት፡-

«إِنِّي لَمْ أُومَرْ أَنْ أَنْقُبَ عَنْ قُلُوبِ النّاسِ، وَلَا أَشُقّ بُطُونَهُمْ »

***«እኔ ወደ ሰዎች ውስጠ-ልቦና እንድቦረቡር ወይም ሆዳቸውን እንድሰነጥቅ አልታዘዝኩም!»*** *[ሙስሊም (ቁጥር 1064)]*

(2) ከአንድ ሰው ንግግር በተዘዋዋሪ የተረዳነውን ተጓዳኝ ሐሳብ ከአንደበቱ እንደወጣ ቀጥተኛ ንግግር ወይም አቋም መቁጠርና በዚህም ላይ ተንተርሶ ፍርድ መስጠት ከፍትህ የራቀ የችኮላ መስመር መሆኑ የኢስላም ሊቃውንት ዘንድ ያለቀለት ጉዳይ ነው። [ለምሳሌ፡- "መጅሙዑ'ል-ፈታዋ" (20/217) ይመልከቱ!]

ጭራሹኑ ተያያዥነት የሌላቸውን ሐሳቦች ያለ አግባብ በማስተሳሰር ሰዎችን በአድርባይነት ወይም በከሃዲነት መወንጀል ደግሞ ይበልጥ አስከፊና የንትርክ ቀዳዳን የሚያሰፉ የአላዋቂዎች መገለጫ ነው። ኢብኑ ሐዝም ይህን አስመልክተው እንዲህ ይላሉ፡-

"وَأما من كفّر النّاس بِمَا تؤول إِلَيْهِ أَقْوَالهم فخطأ؛ لِأَنّهُ كذب على الْخصم وتقويل لَهُ مَا لم يقل بِهِ! وَإِن لزمَه فَلم يحصل على غير التّنَاقُض فَقَط، والتناقض لَيْسَ كفرا، بل قد أحسن إِذْ فر من الْكفْر !"

«የሰዎችን ንግግር ተዘዋዋሪ መመለሻ በማየት እነርሱን በከሀዲነት የሚፈርጅ ሰው ስህተትን ፈፅሟል፤ ምክንያቱም ይህ በተቃራኒ ወገን ላይ መዋሸትና ያላለውን እንዳለ መናገር ነውና! ንግግሩ በተዘዋዋሪ ወደዚያ ቢያመራ እንኳ (እስካልተቀበለው ድረስ) ከአቋም መጣረስ ያለፈ መዘዝ ላይ አልደረሰም! የአቋም መጣረስ ደግሞ ክህደት አይደለም፤ እንዲያውም ከክህደት በመሸሹ መልካም ሰርቷል!»

["አል-ፊሰል ፊ'ል-ሚለሊ ወ'ል-አህዋኢ ወን- ኒሐል" (3/139)]

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

(3) በደካማ መነሻዎች ወይም አጠራጣሪ መረጃዎች ላይ ተመርኩዞ ለድምዳሜ መቻኮል ለአደጋ ይዳርጋል። በእርግጠኝነት የፀደቀውን የሰዎች አማኝነት ደግሞ በተራ መላምት ቀርቶ በአመዛኝ ጥርጣሬ እንኳ ማስተባበል አይቻልም! ነብያችን መካን ለመቆጣጠር ለዘመቻ በተነሳሱበት ወሳኝ ወቅት ሓጢብ ኢብኑ አቢ በልተዓህ የተባለው ሰሓቢይ በሚስጥር የተያዘውን የሙስሊሞች የጦር እቅድ ለቁረይሽ መኳንንት አሳልፎ ለመስጠት ደብዳቤ ፅፎ ነበር። ሆኖም ጉዳዩን አላህ ለመልዕክተኛው በወሕይ ስለገለጠላቸው በርሳቸው ትእዛዝ ደብዳቤው ከመንገድ ተይዞ እጃቸው እንዲገባ ሆነ። ያኔ እርሳቸው በሓጢብ ላይ በቀጥታ ብይን አላስተላለፉም! አስጠርተው «ይህን ለመስራት ያበቃህ ምንድነው?» ነበር ያሉት! እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው:- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እንዳይቸኩሉብኝ! እኔ ከቁረይሾች ጋር ተቀላቅዬ የምኖር ነበርኩ እንጂ የነርሱ ጎሳ አባል አልነበርኩም፤ ከእርሶ ጋር ያሉት ሙሃጂሮች ግን (በመካ ያሉ) ቤተሰቦቻቸውን (ከከሃዲያኑ ጥቃት) የሚያስጠብቁበት ዝምድና አላቸው፤ ከነርሱ ጋር በዘር ግንድ ለመተሳሰር ያልታደልኩ ከመሆኔ አኳያ ቤተሰቦቼን (ከጥቃታቸው) የምከላከልበት ውለታ እነርሱ ዘንድ እንዲኖረኝ አስቤ ነው፤ ዳግም ወደ ክህደት ተመልሼ ወይም ከኢስላም በኋላ ክህደትን መርጬ አይደለም!» እርሳቸውም:- «እውነቱን ተናግሯል!» አሉ። ያን ጊዜ ታላቁ ሰሓቢይ ዑመር ኢብኑ'ል-ኸጥ-ጧብ «ይህን ሙናፊቅ አንገቱን እንድለው ተዉኝ!» ብሏቸው ነበር። እዚህ ላይ ልብ ሊሉ የሚገባው ዑመር ይህንን እንዲል ያነሳሳው ደካማ መረጃ ወይም የተድበሰበሰ ፍንጭ አይደለም፤ ሓጢብ ለጠላት እገዛ ማድረጉ ግልፅ ነው። ይህ ከመሆኑ ጋር ግን ነብያችን እንዲህ አሉት:-

«እርሱ በበድር ዘመቻ ላይ ተሳትፏል፤ አላህ ለበድር ዘማቾች "ያሻችሁን ብትሰሩ እኔ ምሬያችኋለሁ!" ብሏቸው እንደሆነ ምን ታውቃለህ?!» [አል-ቡኻሪይ (ቁ.4274፣ 6939...)፣ ሙስሊም (ቁ. 2494)]

ልብ ይበሉ! ሓጢብ በክህደት ያልተፈረጀው ባቀረበው ምክንያት የተነሳ እንጂ የበድር ዘማች ስለሆነ አይደለም፤ ሆኖም አላህ የበድር ዘማቾች ባስመዘገቡት ታላቅ ገድልና መስዋትነት ምክንያት ወደፊት ቢሳሳቱ እንኳ ክህደትን የመሰለ አፀያፊ ጥፋት ውስጥ እንደማይወድቁ ቀድሞውኑ ስለሚያውቅ ሁሉንም ነገር ይቅር ብሏቸዋል። ተግባሩ ራሱ አስደንጋጭ ጥፋት ቢሆንም መነሻው ግን የትልቁ ክህደት እርከን ላይ አያደርስም። እናም ይህንን አስመልክቶ አላህ ያወረደው ምዕራፍ (ሱረቱ'ል-ሙምተሒናህ) የሚጀምረው «እናንተ ያመናችሁ ሆይ!..» በሚል ጥሪ መሆኑ ይህንን እንደሚያፀና ዑለማዎች ያስረዳሉ።

አደራ!!

 ጥርጣሬ ቢያይልብህ እንኳ የማይገባውን ሰው በስህተት ከመወንጀል ይልቅ ምናልባት የሚገባውን በዝምታ ማለፍ እንደሚሻልና ይህም አጉል የዋህነት ሳይሆን ተገቢ ጥንቃቄ መሆኑን አውቀህ እንደበትህን ቆጥብ!

عَنْ بِلَالِ بْنِ الْحَارِثِ الْمُزَنِيِّ، قَالَ : قَالَ رَسُولُ اللهِ— (ﷺ) إِنَّ الرَّجُلَ لَيَتَكَلَّمُ بِالْكَلِمَةِ مِنْ رِضْوَانِ اللهِ عَزَّ وَجَلَّ، مَا يَظُنُّ أَنْ تَبْلُغَ مَا بَلَغَتْ، يَكْتُبُ اللهُ عَزَّ وَجَلَّ لَهُ بِهَا رِضْوَانَهُ إِلَى يَوْمِ الْقِيَامَةِ، وَإِنَّ الرَّجُلَ لَيَتَكَلَّمُ بِالْكَلِمَةِ مِنْ سَخَطِ اللهِ عَزَّ وَجَلَّ، مَا يَظُنُّ أَنْ تَبْلُغَ مَا بَلَغَتْ، يَكْتُبُ اللهُ عَزَّ وَجَلَّ بِهَا عَلَيْهِ سَخَطَهُ إِلَى يَوْمِ الْقِيَامَةِ فَكَانَ عَلْقَمَةُ يَقُولُ : " كَمْ مِنْ كَلَامٍ قَدْ مَنَعَنِيهِ حَدِيثُ بِلَالِ بْنِ الْحَارِثِ !"

ቢላል ኢብኑ'ል-ሓሪሥ አል-ሙዘኒይ እንደሚያተላልፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል:-

= «አንዳችሁ የአላህን ወዴታና ደስታ የሚያጎናፅፍ ቃልን እዚህ ደረጃ እንደሚደርስ ሳይገምት ተናግሮ በዚሁ ምክንያት አላህ ውዴታውን እስከ እለተ-ትንሳኤ ድረስ ይፅፍለታል! እንዲሁም አንዳችሁ የአላህን ቁጣ የሚያተርፍ ቃልን እዚህ ደረጃ እንደሚደርስ ሳይገምት ተናግሮ በዚሁ የተነሳ አላህ ቁጣውን እስከ እለተ-ትንሳኤ ድረስ ይፅፍበታል!» (ከዚህ ሐዲሥ አስተላላፊዎች አንዱ የሆኑት ታዋቂው ታቢዒይ) ዐልቀማህ እንዲህ ይሉ ነበር:- «የቢላል ኢብኑ'ል-ሓሪሥ ሐዲሥ ከስንት ንግግር አቅቦኛል!» [አሕመድ (ቁ. 15852)፣ አት-ቲርሚዚይ (ቁ. 2319) እና ሌሎችም የዘገቡት ሲሆን ተቀራራቢ መልዕክት ያዘሉ ከአቡ ሁረይራህ የተላለፉ ሐዲሦች አል-ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘንድ ተዘግበው ይገኛሉ።]

**በአሉባልታ ተመርተህ ጭፍን ጥላቻን አታመርቅዝ፤ የአንዱን ጥፋትም በሌሎች ላይ አትለጥፍ! የበደል ገፈት መራራ ነውና ከምትጠላውም ሰው ጋር ቢሆን ሁል ጊዜ ፍትሃዊ ሁን!**

 ሰዎች በቁጣ መንፈስ ሲናገሩ ፍትህን የማጓደል ዝንባሌ ይኖራቸዋልና በንዴት ግለት ላይ እያለህ ቃላትን ከመሰንዘር ተቆጠብ፤ ነብያችን አላህን ሲማፀኑ:-

«በደስታም ይሁን በቁጣ ጊዜ የእውነት ንግግርን» እንዲለግሳቸው መጠየቃቸው ይህንን ያጎላል። [ሱነኑ'ን-ነሳኢይ (ቁ. 1305)]

በሌላ ሐዲሥ እንዲህ ብለዋል:-

«لا يَحكم أحدٌ بين اثنين وهو غَضبان »

= «አንድም ሰው በሁለት ሰዎች መካከል በቁጣ ተሞልቶ እያለ እንዳይፈርድ!»

[አል-ቡኻሪይ (ቁ. 7158)፣ ሙስሊም (ቁ. 1717)]

 በአሉባልታ ተመርተህ ጭፍን ጥላቻን አታመርቅዝ፤ የአንዱን ጥፋትም በሌሎች ላይ አትለጥፍ! የበደል ገፈት መራራ ነውና ከምትጠላውም ሰው ጋር ቢሆን ሁል ጊዜ ፍትሃዊ ሁን! የሚከተለውንም የአላህ ቃል ዘውትር አስታውስ:-

《 يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُونُوا قَوَّامِينَ لِلَّهِ شُهَدَاءَ بِالْقِسْطِ ۖ وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَآنُ قَوْمٍ عَلَىٰ أَلَّا تَعْدِلُوا ۚ اعْدِلُوا هُوَ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ ۖ وَاتَّقُوا اللَّهَ ۚ إِنَّ اللَّهَ خَبِيرٌ بِمَا تَعْمَلُونَ [٥:٨] 》

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በፍትህ መስካሪዎች ሆናችሁ ለአላህ የምትቆሙ ሁኑ፤ የሰዎችም ጥላቻ ፍትህን እንዳትፈፅሙ እንዳይገፋፋችሁ፤ ፍትህን ተግብሩ፤ ይህ ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው፤ አላህንም (ህግጋቱን በማክበር) ተጠንቀቁት፤ አላህ ስለምትሰሩት ሁሉ ወስጠ- አዋቂ ነውና!» [አል-ማኢዳህ 8]

አላህ ለፍትህ የምንቆም ያድርገን!

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

✍ ሸይኽ አቡ ሑነይፍ ኢልያስ አህመድ

# ከሌሎች ምን አበርክተሃል?

ኢስላም ከመሰረቱ ያለው አስተምህሮት ራስን፣ ቤተሰብን፣ ጎረቤትንና ዘመዶችን አልፎም ጓደኛንና ማህበረሰቡን እያለ የሰው ልጅን ሆነ ሌሎች ፍጡራንን በሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ መሰማራትን በማስተማር ነው የመጣው። በዚህም አስተምህሮት ራስን ከጎጂ ነገር ከመከላከል ጀምሮ የሰዎችን ችግር በማቅለሉ ረገድ የቅርብ የቅርብ እያለ እየሰፋ ይሄድና በተለይ ፍላጎታችን የአላህን ውዴታ ለማግኘትና የምንችለውን ያህል መልካም አስተዋፅኦ ለሙስሊም ወገናችን ካበረከትን ለከፍተኛ ክብር ያደርሰናል። ያለበለዚያ ለብቻችንም ሆነ ከሌሎች ጋር ተሰባስበን የምናሰላው፣ የምንወያየው፣ የምንጨዋወተውና የምንመካከረው ጉዳይ ሁሉ ጥቅሙ አይታይም። ምክንያቱም ለራሱም ለሌሎችም በማይፈይድ ነገር ግዜና አቅልን እንዲሁም ገንዘብና ጉልበትን ማባከን ምንም ኸይር የለውምና።ይህንንና ሌሎች ነጥቦችን በሚገልፅ መልኩ አላሁ ሱብሀነሁ ወተዓላ በተከበረው ቃሉ:-

لَا خَيْرَ فِي كَثِيرٍ مِنْ نَجْوَاهُمْ إِلَّا مَنْ أَمَرَ بِصَدَقَةٍ أَوْ مَعْرُوفٍ أَوْ إِصْلَاحٍ بَيْنَ النَّاسِ ۚ وَمَنْ يَفْعَلْ ذَٰلِكَ ابْتِغَاءَ مَرْضَاتِ اللَّهِ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا). [سورة النساء : ١١٤ ].

«ከውይይታቸው በምጽዋት ወይም በበጎ ሥራ ወይም በሰዎች መካከል በማስታረቅ ከሚያዝዙ ሰዎች ውይይት በስተቀር በበርካታው (ውይይታቸው) ውስጥ ደግ ነገር የለበትም:: ይኸንንም (ጠቃሚ ውይይት) የአላህን ውዴታ በመፈለግ ለሚሠራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን::» ይላል [አን-ኒሳእ: 114]

ለዚህም ተጨማሪ ማብራርያ የሚሆነንን አላህ ስራውን ይውደድለትና በጃቢር ቢን አብደላህ ሀዲስ እንደተገለፀው የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ስለ ምርጥ ሰዎች ሲያወሱ:-

«ከሰዎች መሃል በላጩ ሰውን የሚጠቅም ነው።"ብለዋል።»
(ጦበራኒ ዘግበውታል... አልባኒም ደህና ዘገባ ነው ብለውታል።)

በሌላኛው ከአቡሁረይራ ረዲየላሁ አንሁ በተወራው ሀዲሳቸው የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ሰዎች እርስ ለርሳቸው እንዲተዛዘኑና እንዲረዳዱ፣ ሙስሊሙ የወንድሙ ጭንቀት እንዲሰማውና የራሴ ጉዳይ ነው ብሎ ያን ችግሩን ለመቅረፍ እንዲሯሯጥ ለማነሳሳት በዚህም የሚያገኘውን ሽልማት በማውሳት:-

«ከዱንያ ላይ ጭንቀቶች መካከል የሆነ ጭንቀትን ከሙእሚን ላይ ለገላገለ ሰው አላህም ከትንሳኤው ቀን ጭንቀቶች መካከል እንዲሁ ከጭንቀ ይገላግለዋል። ከተቸገረ ሰውም ችግሩን ላቀለለት አላህም ዱንያውንና አኺራውን ያቀልለታል። ...

ወደ ቀጣ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

. . . የሙእሚኑን ነውር ለሸፈነለትም አላህ በዱንያም በአኺራም ከከፉ ነገር ይሸፍነዋል። አንድ ባሪያ ወንድሙን በመርዳት ላይ እስካለ ድረስ አላህም ባሪያውን በመርዳት ላይ ይገኛል..." ብለዋል። 【ሙስሊም ዘግበውታል።】

ይህንን ሀዲስ ኢማም አን-ነወዊ አላህ ይዘንላቸውና ሲያብራሩት :-

« ይህ ሐዲስ ሙስሊሞችን በስልጣኑ፣ በገንዘቡና በእገዛው የመርዳት፣ ከችግራቸው እንዲላቀቁ የማገዝ፣ ስህተቶቻቸውን የማለፍ ትሩፋትን ያመላክታል። እንዲሁም ሀዲሱ እንደሚያሳየው [የቸገረው መፍትሄ እንዲያገኝ] በሚሰጠው ጥቆማው፣ በሚያቀርብለት አስተያየትና በሚያመላክተው አቅጣጫ ችግርን ያስወገደ ሰው ትሩፋቱን ከሚያገኙት ይካተታል።»

ሽርሕ ሰሂህ ሙስሊም: 16/135

## ከራሱም ከሌሎችም በማይፈይድ ነገር ግዜና አቅልን እንዲሁም ገንዘብና ጉልበትን ማባከን ምንም ኺይር የለውም።

አላህ በእዝነቱ የጠበቀው ሰው ሲቀር አብዛኛው የዘመናችን ሰው እንኳንስ የሙስሊሞችን ችግር ለመቅረፍ ሊንቀሳቀስ ቀርቶ ራሱን ውጥረት ውስጥ ከመዝፈቅ ጀምሮ የትዳር አጋሩንና ልጆቹን በማማረር፣ ቤተሰቦቹን በማወክ፣ ጎረቤቶቹን ሰላም በመንሳት፣ ጓደኞቹን በመመቅኘትና የሌላውንም ሰው መብት በመተላለፍ የተፈተነ ነው።

የኢስላም ዕንቁዎቹ ትውልዶችና እነሱን በዓርዓያነት የተከተሉት ግን ከአላህ ምንዳን በመፈለግ የሙስሊሞችን ችግር መቅረፍ ከተጨማሪ የግል ዒባዳቸው ይልቅ እነሱ ዘንድ ተወዳጅ ተግባር እንደሆነ ከሰሃቦች የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ። እንደምሳሌነትም በርካታ የሚጠቀሱ ተምሳሌቶች ይኖራሉ አላህ ተግባሮቻቸውን ይውደድላቸው።

በአጠቃላይ ሙስሊም ለሙስሊም እንደ አንድ አካል እንደመሆኑ አንዳችን ያንዳችን ህመም ሊሰማን ይገባል። በተለይ በቤተሰቦቻችን፣ በዘመዶቻችን፣ በጎረቤቶቻችንና በጓደኞቻችን ላይ የሚደርሱ አስጨናቂና አሳሳቢ ጉዳዮች ከእይታችንም ሆነ ከመስሚያችን የተሰወረ ባለመሆኑ እንዳላወቀ፣ እንደማይመለከተውና እንደማይችል ሰው ሆነን ችላ ልንለው አይገባም።

በዚህ ድጋፋችን ከምናገኘው መልካም ትሩፋት ባሻገር ተጠያቂነትም ስላለብን በጉልበታችን፣ በእውቀታችን፣ በገንዘባችንና በግዜያችን ብሎም ባለን ተሰጥኦና ተሰሚነታችን ልክ ወገንን ለመርዳት እንንቀሳቀስ ።

አላህ ከችግር ያውጣን። ለሌሎችም ደራሽ ያድርገን።

∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞

✍ አቡ ሀምዛ ጀማል ያሲን ራጁኡ

# "የምርጦች ምርጥ"



ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ አላህ የነቢያት መደምደሚያ ለማድረግ አጪቸው በዚህም የትልቅ መልእክትና አደራ ተሸካሚ አደረጋቸው ። የሰውልጆች ከጨለማ ወደ ብርሃን ከመሀይምነት ወደ ዕውቀት እንዲወጡ ነቢዩ ሙሀመድን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በስጦታነት አበረከተላቸው።

የተላኩለት ዓለማም ይሳካ ዘንድም አላህ ነቢዩን ረዳ! ሰዎች እንዲቀበሏቸውም ባማሩ ስነምግባሮች አስዋባቸው በአደብም አነጻቸው ምንም እንኳ ወላጅ አልባ ሆነው ቢያድጉም! የእናትን ፍቅር ቢያጡም! የአባትን ርህራሄና ክብካቤ ባያገኙም ሁሉ በእጁ የሆነው ጌታ በሁለት ወላጆቹ መሀል ካደገ ጅል የተሻለን ጥበቃ አደረገላቸው! ወላጆች ልጆቻቸውን አደብና ስርአትን ከሚያስተምሩት በላቀ መልኩም አላህ ቀረጻቸው!

በዚህም በጊዜያቸው ከነበሩ የባለባት ልጆች ሁሉ ተሽለው ተገኙ ሁሉም ወደዳቸው፣ ሁሉም አቀረባቸው፣ ሁሉም አዘነላቸው፣አቀፋቸውም እንደ ትልቅ ሰውም አከበራቸው ፣አደገው ከትልልቅ ሰዎች ተርታ መሰለፍ ሲጀምሩም ለሀገራቸውና ህዝባቸው ትልቅን ነገር የሚያደርጉ ሰው እንደሚሆኑ በማመን ልዩ ትኩረት ሰጧቸው አብሯቸው ያደገውን መልካም ስነምግባር የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠሉን በማየታቸውም

"አሷዲቁል አሚን" ብለው ሰየሟቸው (ፍጹም እውነተኛውና ታማኙ ) ማለታቸው ነው ይህንን ስያሜና ከፍተኛ ማዕረግ ያሰጣቸው ሁሉም የሚወደውና የሚመኘውን ግን ጥቂቶች እንጂ የማይታደሉትን አላህ የሚወደውን ኢስላማዊ ባህሪይ በመላበሳቸው ነበር፣ ሲናገሩ አይዋሹም፣ ቃላቸውን አያፈርሱም፣ እንግዳንያከብራሉ፣ ዝምድናን ይቀጥላሉ፣ አቅመ ደካማን በሚችሉት ሁሉ ይረዳሉ፣የተጣላን ያስታርቃሉ፣ ታላቃቸውን ያከብራሉ፣ በዕድሜ ለሚያንሳቸው ይራራሉ፣ ውለታን ይመልሳሉ፣ ጉረቤትን ይንከባከባሉ፣ ከኩራት የፀዱ ናቸው፣ የግልም ይሁን ያከባቢ ንፅህናን መጠበቅ ይወዳሉ፣ ሽቶ ያዘወትራሉ፣ የጥርስ መፋቂያ አይለያቸውም፣ነጭ ልብስን እንደሚወዱትና እንደሚጠቀሙት ሁሉ ፡- ልባቸውም ነጭ ፣ንፁህ ነው ።

### የንፁህ ልብ ባለቤቶችንም ይወዳሉ፣

ከጌታቸው በቀር ማንንም አይፈሩም!ከመሆኑም ጋር ለወገናቸው ይተናነሳሉ፣ ማንንም አይበድሉም፣ የጌታቸው ድንበር ካልተጣሰ በስተቀር ለራሳቸው ክብር ብለው አይቆጡም! በአላህ መንገድ እየተፋለሙ ካልሆነ በስተቀር በእጃቸው ማንንም መተው አያውቁም፣ ፍትህን ይጠብቃሉ በዚህም እንደ ሁኔታው እራሳቸውም ላይ ይፈርዳሉ!

ሀቅን ከመናገር ማንንም ምንንም ፈርተው ወደ ኋላ አይሉም፣ ሰውን የሚያስቀይምና ትርፍ ንግግርን አይናገሩም፣ ንግግራቸውም አጠር ያለና ግልጽ ነው፣ ከሰዎች ጋር ሲገናኙ እንደ ደረጃቸውና እንደ ሁኔታቸው ሳይበዛ ቀልድን ይጠቀማሉ ሆኖም ግን ለቀልድ ብለው አይዋሹም! ሲስቁም የሳቃቸው ድምጽ አይሰማም፣ ለመላው ፍጡር ያዝናሉ፣ አንዲት እርግብ ካጠገባቸው ዝቅ ብላ ከንፏን እያርገበገበች ስትሽከረከር ማነው ልጇን የወሰደባት? ብለው ሲጠይቁ አብረዋቸው ከነበሩ ሰሃቦች መሀል አንዱ እኔ ነኝ ብሏቸው እንዲመልስላት አዘዋል።

ህጻን ልጅ ሲስሙ ያየ አንድ ግለሰብም፥ እኔ 9 ልጆች አሉኝ ከነሱ መሀል እስከ ዛሬ የትኛውንም ስሜ አላውቅም ሲላቸው "እዝነት ከልብህ ወጥታ ከሄደች እኔ ምን ላደርግልህ እችላለሁ?!" በማለት ተችተዋል፣ ለአረጋዊያንና ጠዋሪ ለሌላቸው ሴቶች በተለየ መልኩ ያዝናሉ፣ ከሁሉም በላይ የጌታቸውን መመሪያ ለሚያከብሩ የአላህ ባሪያዎች ጌታቸው ባዘዛቸው መሰረት ልዩ እዝነትና ርህራሄ አላቸው፣

ለሁሉም የሚገባውን ክብር ይሰጣሉ፣ የታመመን ይጠይቃሉ፣ የሞተን ይቀብራሉ፣ ሞተው የተቀበሩ ወንድምና እህታቸውን ቀብር በየግዜው ሄደው እየዘየሩ ምህርት ይጠይቁላቸዋል፣ መስጅድ ታጸዳ የነበረች ሴት ሞታ እሳቸው ሳያውቁ ሰሃቦች ቀብረዋት በኋላ ሲሰሙ" ለምን ሳትነግሩኝ?! በማለት "ቀብሯን አሳዩኝ" በማለት ሄደው ሰግደውባት ዱኣ አድርገዋል፣ ከሰዎች የተበረከተላቸውን ስጦታ ትንሽም ቢሆን ይቀበላሉ፣ ሲመልሱ ግን በተሻለ መልኩ ይመልሳሉ፣ ምንም የሌለው ደሃ እንኳ ቢሆን ጥሪን አክብረው ይሄዳሉ፣

ሰውን ስያገኙ ቀድመው ሰላም ይላሉ፣ ሀብታሙንም ደሃውንም ይጨብጣሉ፣ ህጻናትን ያጫውታሉ።ታፋቸው ላይ በማስቀመጥም ያቅፋሉ፣ ከሰሃቦቻቸው ጋር በመሆንም እነሱ የሚሰሩትን ስራ አብረው ይሰራሉ፣ ምግብም አብረዋቸው ይበላሉ።

ከእለታት አንድ ቀን አይቷቸው የማያውቅ ግለሰብ ወዳሉበት ደርሶ ከቅርበት ሲያያቸው ከነበራቸው ግርማ ሞገስ የተነሳ ሰውነቱ ሲንቀጠቀጥ አይተው " እራስህን አረጋጋ እኔ እኮ የአንዲት ስጋን አድርቃ እያቆየች ትበላ ከነበረች ሴት የተወለድኩ ሰው ነኝ"በማለት አረጋግተውታል፣ ከሰሃቦቻቸው ጋር ጉዞ ላይ ሳሉ በግ ማረድ ፈልገው ከነሱ መሀል አንዱ፥ እኔ አርዳለሁ ሲል ሌላኛው እኔ እገፈለሁ እያለ ሌላኛው ደግሞ እኔ አበስላለሁ በሚልበት ሰአት ታላቁ ሰው (ነቢዩ ሙሐመድ ሰለላሁ ዐለይሂወሰለም) እኔ ደግሞ እንጨት ለቅሜ አመጣለሁ ብለው እራሳቸውን ዝቅ አድርገዋል!!

ስለዚህም አላህ ዘንድ ከፍ ብለዋል አማኞች ልብ ላይም ውዴታቸውን ዘርተዋል !

የሰው ልጆች ምርጥ እንደሆኑ፥ የሩቁም የቅርቡም፣ወዳጅ ዘመዱም መስክሯል! እነሆ እኚህ ናቸው ነቢያችን እንወዳቸዋለን! እናከብራቸዋለን! የሙስሊሞች አርኣያና ተምሳሌትም እሳቸው ናቸው !

አላህ ሆይ፥ በፈጠርካቸው ነገሮች ልክ ነቢዩ ሙሀመድ ላይ ሰላትና ሰላምን አስፍን!

∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞

✍ አቡ ዐብዲላህ አሕመድ ኣደም

# ቁርኣን የአላህ ንግግር

ከ

## ቁርኣን ጋር እንኑር ...

## ቁርኣን የአላህ ንግግር መሆኑ የማያጠራጥር እውነታ ነው !

قال الله تعالى" :إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ "

[الحجر: 9]

«ቁርኣንን እኛ አወረድነው። ጠባቂውም እኛው ነን።»

"قرر تعالى أنه هو الذي أنزل الذكر ، وهو القرآن، وهو الحافظ له من التغيير والتبديل".

«ክብሩ የላቀው አላህ ይህን ዚክር ማውረዱን አፅንኦት ሰጥቶታል። እሱም ቁርኣን ነው። ከመለወጥና ከመቀየርም ጠባቂው እሱ ነው።» [ኢብኑ ከሲር]

በነቢዩﷺ መስጂድ ውስጥ በቋሚነት ዒልምን ከሚያሰራጩ እውቅ መሻኢኾች አንዱ የሆኑት ሸይኽ ዶ/ር ሷሊህ አስሲንዲ ሀፊዘሁላህ፤ ቁርኣን የአላህ ንግግር መሆኑ የማያጠራጥር እውነታ ለመሆኑ የሚቀርቡ መረጃዎችና ማስረጃዎችን ሲያወሱ ቀጣዮቹን ጠቃቅሰዋል።

1ኛ በሁሉ ነገሩ ቁርኣኑን የመሰለ የተዋጣለት ነገር ኣምጡ በማለት ጂኖችን ሆነ የሰው ልጅን መፈታተኑ፤ ሙሉውን ካልቻሉ አንዷት ምዕራፍ እንኳ አቅርቡ ብሏቸው ኣለመቻላቸው፤

2ኛ ከመቀየርና ከመለወጥ ለመጠበቅ የጥበቃ ሃላፊነቱን አላህ ራሱ መውሰዱ፤

3ኛ ከቅነሳ ወይም ከስህተት ወይም ከተቃርኖ ወይም ከግጭት ነፃ መሆኑ፤

4ኛ አሁን አሁን በቅርቡ የደረሰበት ቢሆን እንጂ ቀድሞ የሰው ልጅ የማያውቀውን የስነ ተፈጥሮና የስነ ህይወት ሳይንስን የሚጠቁሙ አንቀፆችን ያቀፈ መሆኑ፤

5ኛ ወደፊት እንደሚከሰቱ የተነበያቸው ሚስጥሮች በተናገረው መሰረት መከሰታቸው፤

6ኛ አንዳንድ ጉዳዮችን የሰው ልጅ ከህሊናዊ ግምቱ አንፃር ሊከሰት እንደሚችል ቢገምትም ቁርኣን ግን ለወደፊት አይከሰትም ብሎ መናገሩና እስካሁንም ኣለመከሰቱ፤

7ኛ የህግጋቱ ልቅናና ሁሉንም የህይወት ዘርፍ ያጠቃለለ መሆን፤

8ኛ ከጤናማ አዕምሮና ከተፈጥሮ ጋር የተስማማ መሆኑ፤

9ኛ ልቦናዎች ላይ አስገራሚ ተፅዕኖ መፍጠሩ፤

10ኛ ለመታወስ ሆነ ለመሸምደድ የተገራና የተመቻቸ መሆኑ በማለት አስር ነጥቦችን ጠቅሰዋል።

ይህም ዐቂደቱ አህሉሱንና ወልጀማዓ የተሰኘውን የሸይኽ ኢብኑ ዑሰይሚንን ረሂመሁላህ ኪታብ ሲያብራሩ ከጠቃቀሱት የተወሰደ ነው።

### ካቀረቡት መረጃ እንደምንረዳው

- እስካሁን ድረስ ያሉ የቋንቋ፣ የስነ ፅሁፍ፣ የፍልስፍና ሆኑ የየትኛውም ዘርፍ ሊቅ ናቸው የሚባሉት ሁሉ ሰዎች ብቻም ይሁኑ ከጋኔን ጋር ተደምረው ምንም ማምጣት ኣለመቻላቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ሆኗል።

ቅንጣት ታክል እንኳ ማምጣት ቢችሉ ኖሮ ሙስሊሙን ዓለም ለማወክ ከባድ መሳርያ ስለሚሆናቸው እነሆ ባሉ ነበር። ማድረግ እየቻሉ ማስተዛዘኛ ብለው የሚተዉልን ነገር እንደሌለም ልብ በሉት።

- አላህ አዝዘ ወጀልለ ለንግግሩ ባደረገው ጥበቃ መሰረት እስካሁንም በምንም ጎኑ ሳይቀየርና ሳይለወጥ ቆይቷል። ወደ ፊትም በዚሁ መልኩ ይቀጥላል።

- እስከዛሬዋ እለት ፀረ ኢስላም ሀይሎች አለን የሚሉትን መላምትና ማደናገርያ ብሎም የፈጠጠ ቅጥፈታቸውን ለጣጥፈው ቁርኣን እርስ ለርሱ ይጋጫል ብለው የሆነች ስህተት ፈብርከው ለማምጣት ቢጥሩም ተረታቸው ውኸ'ንብር ከመሆንና ራሳቸውን ከማሳፈር አላለፈችላቸውም። ፍጡር ፈጣሪውን አያሸንፍምና።

**ፊደልን ከፊደል፣ ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ፣ አንቀፅን ከአንቀፅ፣ ምዕራፍን ከምዕራፍ ሳያዛንፍና ሳያዛባ የሚሸመድድ ኣለን?**

□ ቁርኣን የሰው ልጅ ዛሬ ዛሬ ተመራምሮ በጥቂቱ የደረሰበትን የስነ ከዋክብት፣ የስነ እፀዋት፣ የስነ ተዋልዶ፣ የሂሳብ፣ የጂኦግራፊ፣ የፖለቲካል ሳይንስ፣ የንግድ ሳይንስና ህግጋት፣ በሶሻል ላይፍ ሳይንስ፣ የግዜ ቀመር እና በሌሎችም የተለያዩ የስነ ምናምን ዘርፎች ለዛሬው ግኝት ፈር የቀደዱ እውቀቶችን ቀደም ብሎ ጠቃቅሷል።

□ ሌላው እንኳ ቢቀር ከሃዲያኑ የአላህ ብርሃን የሆነውን እስልምናን ቢችሉ በትችት፣ በማንቋሸሽ፣ በማስተባበልና በሀሰት ሰበካ በአንደበታቸው ብቻ ያጠፉት ነበር። በዚህ ካልቻሉ ደግሞ ያለ የሌለ ጫናቸውን ተጠቅመው ሊያጠፉት እንደሚፈልጉ እዚያው ቁርኣን ላይ ሰፍሯል። አላህ ደግሞ ይህን ብርሃኑን የተሟላና ለሁሉም እንዲታይ የበላይ ያደርገዋል በማለት አስከትሎ ጠቁሟል፣ ቃል ገብቷል። እየሆነ ያለውም ይኸው ነው።

እንዲያው በዚህ ዓለም ላይ ከሚገኙ ሰዎች ከቁርኣን ውጭ ህፃኑ ሆነ አዋቂው፣ ሊቁ ሆነ ተራው ሰው፣ አረቡ ይሁን ሌላው ይህን ከ600 ገፅ በላይ የሆነን ኪታብ በቀላሉ ፊደልን ከፊደል፣ ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ፣ አንቀፅን ከአንቀፅ፣ ምዕራፍን ከምዕራፍ ሳያዛንፍና ሳያዛባ የሚሸመድድ ኣለን? የለም። አልተሰማምም። መልእክቱስ እንዲሁ በቀላሉ ይያዛልን? ዘበት ነው። ቁርኣን ግን ለሁሉም የተገራ ነው። አልሀምዱ ሊላህ።

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

✍ **አቡ ፈውዛን አሕመድ ሙሐመድ**

## ጠቃሚ ነጥቦች ከፈትዋ ጠያቂዎች



1.በትምህርቶች ላይ የተብራሩ ነጥቦችን ከደርሱ ላይ ማዳመጥ እየተቻለ ደግመን ከመጠየቅ መቆጠብ ይገባናል።

2.ስንጠይቅ ለተግባር ሊሆን ይገባዋል። እድሉን ስላገኘን ብቻ መጠየቅ የለብንም። የግዴታ የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንጠይቅ ፤ የሌሎችን ሰዎች እድል ካለመዝጋት አንፃር የምናውቀውን ባንጠይቅ መልካም ነው።

3.የሚጠየቁት ጥያቄዎች የተከሰቱ መሆን አለባቸው ፤ በአዕምሯችን ውል ያለውን ነገር በሙሉ እና እንዲህ ቢሆንስ እያልን እየተመራመርን እየተፈላሰፍን ያልተከሰተን ነገር መጠየቅ የለብንም ፤ ይህም የቀደምት ዑለማዎች መንገድ ነው። በሚጥጠየቁ ሰአት ይህ ነገር ተከስቷል ወይ? ብለውም ይጠይቁ እንደነበር ተነግሯል።

4.ፈትና ለመፍጠር ብለን መጠየቅ ተገቢ አይደለም ፤ የአንዱን ዓሊም ፈትዋ ከሌላው ዓሊም ፈትዋ ጋር ለማጋጫት ብለን መጠየቅ የለብንም። መጀመሪያ አላህን ይፈራል ብለን አምነንበት የጠየቅነውን ሰው የሰጠንን ፈትዋ ከስሜታችን ጋር ሳላልተመቸን በመተው እና ሌላ ገር ነገርን ለመፈለግ እንደገና ከመጠየቅ መቆጠብ ይገባናል።

5.በፊቅህ ጉዳዮች ላይ ብዙ የልዩነት ርእሶች ስላሉ ፈትዋ ሰጪው አንዳንዴ ከማስረጃ አንፃር የተሻለውን አቋም ብቻ አስቀምጦ ሊሄድ ይችላል ፤ አንዳንዴ ደግሞ ኺላፎቹን ሊያብራራ እና የተሻለውን ሊያስቀምጥ ይችላል። በዚህም የተነሳ ጅምር ላይ ያለ ሰው የፊቅህ ጉዳዮችን ከዛም ከዚም መስማት አይገባውም ፤ ፈትዋዎች ተጋጭቶ ቢያገኝም እንዴትስ ሊጋጭ ይችላል ብሎ ሊወዛገብ አይገባውም። ምክንያቱም ርእሱ የፊቅህ ጉዳይ ነውና።

6.ከጥያቄው ላይ ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች እና መልሱ ላይ ጫና የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ብቻ በማንሳት አጠር ባለ መልኩ ጥያቄን መጠየቅ ያስፈልጋል። በመሆኑም በጣም አስፈላጊ ነገር ካልሆነ በስተቀር አንድ ጥያቄ ለመጠየቅ ብለን የሕይወት ታሪካችንን በሙሉ ልንዘረዘር አይገባም።

7.አንዳንዴ የፈትዋው ጥያቄ እና የሚሰጠው መልስ ሊለያይ ይችላል ፤ ይህም የሚሆነው ከጠያቂው የጥያቄ አጠያየቅ የተነሳ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ፈትዋ ሰጪው መልስ የሚሰጠው ጥያቄውን በተረዳው መሰረት ስለሆነ ማለት ነው።

8.በጣም አስገዳጅ ምክንያት ካልተፈጠረ በስተቀር እያንዳንዱ ሰው በራሱ መጠየቅ ተገቢ ነው። ሌላ ሰው ሲጠይቅ ራሱ እንደተረዳው አድርጎ ሊያስተላልፍ እና እንደዚሁም ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን ከፈትዋ ሰጪው አካል በሚጥጠየቅበት ሰአት በራሱ ገለፃ ሊገልፅ ስለሚችል እና ለሌሎችም ምክንያቶች ሲባል በራስ መጠየቁ የተሻለ ነው።

9.የትዳር እና የፍቺ ጉዳዮች ላይ ከጠያቂዎቹ አካል የሚፈለጉ ሰፋ ያሉ ማብራሪያዎች እና ዝርዝር ሁኔታዎች ስለሚኖሩ እንደዚሁም ከጉዳዩ ክብደት አንፃር በፅሑፍ መላክ ሳይሆን በአካል ዓሊሙ ጋር ቀርቦ መጠየቅ ያስፈልጋል። ካልተቻለ በቀጥታ ስልክ ቁጥር ደውሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜም ሁለቱም ባለትዳሮች ቀርበው መናገር የሚገባቸው ርእሶችም ስለሚኖሩ በአካል በቀጥታ መጠየቅ ያስፈልጋል። ነገር ግን ከኒካሕበፊት ያሉ ጉዳዮችን ለምሳሌ የኒካሕ መስፈርቶችን ፣ ኒካሕ የሚያበላሹትን ነገሮች መጠየቁ ችግር የለውም።

10.በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ምላሽ በተመሳሳይ ጉዳይ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ ሊሆን ከመቻሉ ጋር አንዳንድ ጊዜ በጉዳዮች መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል። ነገር ግን የየግለሰቡ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት ላይኖረው እና ሊለያይ ስለሚችል የአንዱን ጥያቄ ምላሽ ለሌላው አድርጎ መወሰድ የለበትም። በመሆኑም የአንድን ጥያቄ ምላሽ ለሌላው ከመጠቀማችን በፊት ጥያቄዎቹ ግልጽ እና ተመሳሳይነት አላቸው የላቸውም የሚለውን ማጣራት ያስፈልጋል።

11.ብዙ ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎችን ፣ በየአመቱ የሚደጋገሙ ጥያቄዎችን ፣ መደጋገም አያስፈልግም ለምሳሌ የዛሬ አመት ስለረመዷን የተጠየቀ ጥያቄ ካለ ያንን ማየት እና ማጥናት ያስፈልጋል እንጂ ደግሞ መጠየቅ አያስፈልግም።

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

✍ **የኡስታዝ አሕመድ ኣደምን ድምጽ ወደ ጽሁፍ የገለበጠው :-**

**አሕመድ ያሕያ**

# አደብን ተማር

ምስጋና ለአላህ ብቻ ነው፤ እርሱን ብቻ እናመሰግናለን ሙሐመድም የአላህ ቅን ባሪያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመስክራለሁ፡፡ በጣም እውተኛው ቃል የአላህ መጽሐፍ (ቁርዓን) ነው፤ ከፈለጎች ሁሉ በላጩ የሙሐመድ ፈለግ ነው፡፡

አላህ ለሰው ልጅ ከሰጠው ታላላቅ ፀጋዎች መካከል ካልነበረበት ማስገኘቱ (መፍጠሩ) እና የዕውቀት ባለቤት ማድረጉ ነው፡፡

ይህንንም አስመልክቶ አላህ ለመጀመሪያ ጊዜ ባወረዳቸው አምስት አንቀጾች ሡረቱል ዐለቅ ላይ ገልጾታል፡፡ አላህ የሰው ልጅን ሲፈጥር፤ በዕውቀት ከመላኢካዎች እንዳስበለጠውና ለዚሁም ክብር ሲባል ለአደም እንዲሰግዱ መታዘዛቸውን በሡረቱል በቀራ ገልጾታል፡፡ አላህ ሙእሚኖችን (አማኞችን) በአንድ ደረጃ ከፍ ሲያደርጋቸው የዕውቀት ባለቤቶችን ግን በብዙ ደረጃዎች ከፍ ያደረጋቸው መሆኑን ሲናገር ኢብኑ አባስ የአሊሞች ደረጃ ከአማኞች በሳባ ደረጃ እንደሚበልጥ አስቀምጠዋል ፡፡

የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹አላህ መልካምን የሻለትን ሰው ሃይማኖቱን ጠልቆ እንዲረዳ ያደርገዋል (ዲኑን ያስገነዝበዋል)›

ከአቡደርዳ በተነገረው ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ ‹‹ ዑለማዎች የነቢያት ወራሾች ናቸው›› ነቢያት ዲናርም ሆነ ዲርሐምን (የገንዘብ ሀብትን) አላ ወርሱም ያወርሱት ዕውቀትን ብቻ ነው፡፡ አቡዳውድ፣ቲርሚዚና ኢብኑማጀህ ዘግበውታል፡

ከዚህ የምንረዳው ሸሪዓዊ ውርስ በዝምድና ትስስር ስለሆነ ነቢያትና ዑለማዎችን የሚያስተሳስራቸው የዘር ሐረግ (ዝምድና ) ዕውቀት መሆኑን ነው፡፡

አሊይ ቢን አቢ ጧሊብ እንደተናገሩት፡- የዕውቀት ክብር መገለጫው ይህ ብቻ ይበቃል አዋቂ ያልሆነው (ዕውቀት የሌለው ሰው) አዋቂነኝ ብሎ መሞገቱ የማያውቀው መሃይም (አላዋቂ) መባሉን መጥላቱ፡፡

የዕውቀት ደረጃና ትሩፋቱን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በርከታ ናቸው፡፡ ስለዕውቀት በከፈሉት መስዋዕትነት የተነሳ ከታላላቅና አንጋፋዎች ተርታ በመጀመሪያው እርከን የተሠለፉት ከሠለፎች (ሰሃቦችና ተከታታይ ትውልድ) እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ከከፈሉት መስዋዕትነት የተነሳ ያበረከቱት አስተዋጽኦ እንዲሁ በዘፈቀደ የተገኘ ሳይሆን ሥርዓቱን በቅድሚያ አሟልተው አደቡን ጠብቀው በዚህ ላይ ባለ በሌለ ኃይላቸው ባደረጉት ጥረት እና ርብርብ ነው፡፡ የዚህን እውነታ ከሚያንፀባርቁት አባባሎችና የሚከተሉትን አቋም በተመለከተ እንደምሳሌ ያህል ለመጥቀስ ያክል፡-

‹‹ በአደብ ከመታነፅ በፊት ዕውቀትን መማር ሰውየውን (ተማሪውን) የልብ ልብ ተሰምቶት ለጉራና መሸወድ እንዲሁም ለስህተት እና ጥመት ያጋልጠዋል፡፡›› (አልኸጢቡል በግዳዲይ)

አልኸጥብ ፡- ከኢማሙ ማሊክ እንደዘገቡት ስለአንጋፋ (ታላላቅ) ታቢዒዮች ከሰሃቦች ስለወሰዱት ታላላቅ ስብዕናዎች መካከል ዋና ዋና ከሚባሉት ዕውቀትን እንደሚማሩት ሁላ መልካም አርአያነትን (ሡናይ-ምግባርን) ይማሩ ነበር፡፡(ኢቡኑ ሲሪን)

**የመጀመሪያዎችንም የመጨረሻዎችንም ዕውቀት የያዘን ሰው ሳላገኘው ብቀር (ቢያመልጠኝ) ምንም ቅር አይለኝም፤ ነገር ግን በአደቡ (ግብረ ገቡ) የተካነ ሰው መኖሩን አውቄ የመገናኘት ዕድሉ ቢያመልጠኝ በጣም አዝናለሁኝ፡፡**

ከኢብራሒም ብኒ ሐቢብ ብኒ አሽሂድ እንደተነገረው አባቴ እንዲህ አሉኝ፤

‹‹ ልጄ ሆይ ምሁራን እና ሊቃውንት (ዓሊሞችና ፉቀሃእ) ዘንድ ሒድ ከነርሱም ተማር አዳባቸውን፣ ፀባያቸውን፣ ሡናይ ምግባራቸውን ይዘህ ፈለጋቸውን ተከተል ብዙ ሐዲስ ከምትማር ይህንን መያዝህን እኔ ዘንድ ከሁሉ የተወደደና የተመረጠ ነው ፡፡

ኢማሙ ማሊክ ላንድ የቁረይሽ ወጣት ሲመክሩት እንዲህ አሉት፡-

‹‹ የወንድሜ ልጅ ሆይ! ዕውቀትን ከመማርህ በፊት አደብን ቅድሚያ ሰጥተህ ተማር እናቴ ገና ልጅ እያለሁ ጥምጣም ጠምጥማልኝ እንዲህ ትለኝ ነበር፡-

‹‹ ሂድ ወደ ረቢዓህ ከርሳቸው ዕውቀታቸውን ከመማርህ በፊት አደብን አስቀድመህ ተማር›› እንዲህ ዓይነቱ ዘገባ ስለ አቡ ሐኒፋም ተነግሯል፡፡

ያለ አደብ መማር ያለ ማገዶ (እንጨት) እሳት እንደማንደድ ሲሆን ያለ ዒልም (ከዕውቀት)፣ አደብ ደግሞ ያለሩህ አካል እንደማለት ነው፡፡

(አቡ ዘከሪያ አል - ዓንበሪይ)

ዐብደላህ ኢብኑ ሙባረክ እንዲህ አሉ ‹‹አደብን ሰላሣ ዓመት ተማርኩኝ ዕውቀትን ሃያ ዓመት ተማርኩኝ (ሰሃቦች እና ተከታዮቻቸው) አደብን ከዒልም (ከዕውቀት) አስቀድመው ይማሩ ነበር፡፡

‹‹አደብ የዒልም ሲሦ (1/3) ነው››

ዑመር ኢብኑል ኸጧብ እንዲህ አሉ፡-

***‹‹ዕውቀትን ከመማራችሁ በፊት አደብን ተማሩ ከዚያም ዕውቀትን ተማሩ፡፡***

ዐብደላህ ኢብኑ ሙባረክ እንዲህ አሉ፡- ‹‹ዕውቀትን ከመማራችሁ በፊት አደብን ተማሩ ከዚያም ዕውቀትን ተማሩ፡፡››

በሌላ አባባላቸው ደግሞ ፡- ‹‹የመጀመሪያዎችንም የመጨረሻዎችንም ዕውቀት የያዘን ሰው ሳላገኘው ብቀር (ቢያመልጠኝ) ምንም ቅር አይለኝም፤ ነገር ግን በአደቡ (ግብረ ገቡ) የተካነ ሰው መኖሩን አውቄ የመገናኘት ዕድሉ ቢያመልጠኝ በጣም አዝናለሁኝ፡፡

አልሐሰን እንደተናገሩት ፡-

‹‹ አንድ ሰው አደብን ለመማር ሲል ከዓመታት ወደ ዓመታት ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ ይጓዝ ነበር፡፡››

ስለ አደብ ያሎዎትን ስሜት ይግለፁ ተብለው ኢማሙ ሻፊዒይ ሲጠየቁ

‹‹ ከዚህ በፊት ሰምቼ ማላውቀውን ስሰማ (ስለአደብ ተምሬ ማላውቀውን ዕውቀት ስማር) አካሌ ሁላ (በፀጉሬ ልክ) ጆሮ ኑሮት እየሰማሁ ብረካበት እመኝ ነበር አሉ፡፡

የአደብ ትምህርት አወሳሰድዎ እንዴት ነው ሲባሉ

***‹‹አደብን የመማር ፍላጎቴ ብቸኛው ልጇ እንደጠፋባት እናት ዓይነት ነው››***

ሰለፎች ዘንድ የአደብ ጉዳይ ይህን ያህል ከፍተኛ ደረጃና ታላቅ ቦታ ያለው ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ በርዕሱ ዙሪያ መረባረብ አስፈላጊነትና አንገብጋቢነትን ይጠቁመናል፡፡ ነገሩን ሰምተው ቁምነገሩን( ሀቁን) ከሚከተሉት አደብና ስርዓቱን አሟልተው በዕውቀት አላህን በመገዛት ከፀኑት ያድርገን፤ ከዚህ ከሚያፈናቅሉ እንቅፋት እና መቅሰፍት አላህ ይጠብቀን፡፡

አሚ...ን

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

✍ **አቡ ከውሠር ሻሚል ሙዘሚል**

# ክብር ለሰሓባዎች

ውድ የነሲሓ መጽሄት ተከታታዮች፣ በዚህች ፅሁፍና ወደፊትም በዚሁ መጽሄት በተከታታይ ለመዳሰስ የወደድኩት ርእስ ስለ ሰሓባዎች ገድል፣ በኢስላም ያላቸው ደረጃና ለኢስላም ያበረከቱትን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይሆናል። በተለይ ከፍተኛ ቦታ ያላቸውን እና በታሪክ ውስጥ ትልቅ አሻራን አሳርፈው ያለፉትን ሰሓቦች እያነሳን ከታሪካቸው አንኳር ቁም ነገሮችን፣ በታሪኩ ዙሪያ የሚነሱ አሉባልታዎችንና እንቶፈንቶዎችን እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የአህሉሱና ወልጀማዓህ አቋምን ወደፊት የምንቃኝበት ንባብ ይሆናል ኢን ሻአ አላህ። አላህ ﷻእድሜውን እና እድሉን ከሰጠን ደግሞ ከዘመን ዘመን እየተሸጋገርን አንዳንድ ስብዕናዎችን እና ክስተቶችን እያወሳን ከታሪካቸው ቁምነገርን የምንቀስምበት ግዜ እንደሚመጣ በአላህ ላይ ተስፋን አደርጋለሁ።

በዛሬው ጽሁፌ ጥቂት ስለ ሰሓባዎች ደረጃ ላውሳ። እርግጥ ነው የሰሓባዎች ትውልድ ከነብዩ ሙሐመድ ﷺኡማ ምርጡና በላጩ ትውልድ ነው። አላህም ﷻበቁርአኑ በብዙ ቦታ ያወደሳቸው ህዝቦች ናቸው ። አላህ ﷻእንዲህ ይላል :- ﴿**የአላህ መልክተኛ ሙሐመድ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉት (ወዳጆቹ) በከሓዲዎቹ ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው አዛኞች ናቸው፡፡ አጎንባሾች፣ ሰጋጆች ኾነው ታያቸዋለህ፡፡ ከአላህ ችሮታንና ውዴታን ይፈልጋሉ፡፡ ምልክታቸው ከስግደታቸው ፈለግ ስትኾን በፊቶቻቸው ላይ ናት ......)**﴾አል ፈትሕ 29)

በሌላ ቦታም ﴿**ግን መልክተኛው እነዚያም ከርሱ ጋር ያመኑት በገንዘቦቻቸውም በነፍሶቻቸውም ታገሉ፡፡ እነዚያም መልካሞች ሁሉ ለነሱ ናቸው፡፡ እነዚያም እነሱ ምኞታቸውን ያገኙ ናቸው፡፡ ለእነሱም ገነቶችን በሥራቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ አላህ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይህ ታላቅ ማግኘት ነው፡፡)**﴾አል ተውባ 88) በማለት ያዘጋጀላቸውን ታላቅ መስተንግዶ ይገልጻል። እነዚህን የመሰሉ አንቀጾች በርካታ ናቸው።

መልዕክተኛውም ﷺልክ እንዲሁ በተለያዩ አጋጣሚዎች አወድሰዋቸዋል፤ በላጭ ህዝብ መሆናቸውንም መስክረዋል፣ እነርሱን መጻረር እና መሳደብንም አውግዘዋል:- ﴿**ምርጡ ትውልድ እኔ ያለሁበት ትውልድ ነው .....)** ﴾ቡኻሪ) እንዲሁም ﴿**ሰሓባዎቼን አትስደቡ...)**﴾ቡኻሪና ሙስሊም) በማለት መልዕክተኛው ﷺመመስከራቸውን ለግዜው ለአብነት ያህል በማውሳት እንብቃቃ።

ክብር ለሰሓባዎች!! ለዚህ ኡመት ቅናቻ (መቃናት) እነሱን ፈለግ አድርጎ ከመያዝ የተሻለ አማራጭ የለውም፤ ምክንያቱም መምህራቸው ነብዩ ሙሐመድ ﷺነበሩ፣ መመለሻቸውም ቁርአን ነበር፣ ጉዟቸውም ስለ ኢስላም ነበርና!

ኢብኑ መስዑድ﵁ እንዲህ ሲሉ ይመክሩናል :- ﴿**ፈለግን የፈለገ ሰው የሞቱትን ሰዎች (ሰሓቦችን) ፈለግ ይከተል፤ እነዚያ የሙሐመድ ﷺባልደረቦች የዚህ ኡመት ምርጡ፣ ልቦናቸው ቅን የሆነ፣ የጥልቅ እውቀት ባለቤትና ባለ ጥቂት ተከሉፍ ነበሩ! አላህ ﷻየመልዕክተኛው ﷺባልደረቦች ይሆኑ ዘንድ፣ ሐይማኖቱንም ለቀጣይ ትውልድ ያሳልፉ ዘንድ የመረጣቸው ህዝቦች ናቸው። ከእነርሱ ምግባርና አካሄድ ጋር ተመሳሰሉ። የሙሐመድ ﷺጓዶች በቀጥተኛው መንገድ ላይ ነበሩና!!)**﴾አል ሒልያ 1/305) ይላሉ። ከሰሓባዎች በኋላ ከእነርሱ የተሻለ ሰው ሊመጣ አይችልም፤ እነርሱ በሰላት፣ በፆም፣ በሰደቃ፣ በዙህድ፣ መጂሃድ ባጠቃላይ በሁሉም የዒባዳ መስኮች ከበስተኋላቸው የሚመጡትን ትውልዶች በልጠዋል፤ የሚስተካከላቸውም አይመጣም።

አቡ ሰዒድ አል ኹድሪ﵁ ባወሩት ሐዲሥ መልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል ﴿**ሰሓቦቼን አትሳደቡ ! አንዳችሁ የኡሁድን ተራራ ያህል ወርቅ (በአላህ መንገድ) ቢያወጣ እንኳ እነርሱ (ሰሓቦቼ) ያወጡትን እፍኝ ያህል አይደርስም፤ ግማሿንም አይደርስም)** ﴾ቡኻሪና ሙስሊም) ብለዋል። ይህ ሐዲሥ የነዚህን ሰዎች ልቅናና ክብር እንዲሁም አላህ ﷻዘንድ ያላቸውን ከፍተኛ ደረጃ ያሳየናል።

ኢብኑ ዑመርም﵁ ﴿**የሙሐመድን ﷺሰሓቦች አትስደቡ ! የእነርሱ የአንድ ሰዐት አምልኮ የእናንተን እድሜ ልክ አምልኮ ይልቃል)** ﴾ኢብኑ ማጃህ) በማለት እነዚህ የሃቢቢ ﷺጓዶች የላቁ መሆናቸውን አስገንዝበዋል!

አህለሱና ወልጀመዓህ ሰሓቦችን አስመልክቶ ሁሉም ፍትሃዊ (ተቀባይነት ያላቸው) መሆናቸውን ተስማምተዋል።

ኢብኑ ሃጀር አል አስቀላኒ እንዲህ ይላሉ ﴿**ሁሉም ሰሓባዎች ፍትሃዊ መሆናቸውን አህለሱናዎች ተስማምተዋል። ይህን ስምምነት አንዳንድ አፈንጋጭ ሙብተዲዖች እንጂ የተጻረረ የለም።)** ﴾አል ኢሷባ 1/10)

## ከሰሓባዎች በኋላ ከእነርሱ የተሻለ ሰው ሊመጣ አይችልም፤

በነገራችን ላይ ሰሓባዎች በደረጃ አንዱ ከሌላው እኩል አይደሉም። ከሁሉም በላጭ የሆኑት በጀነት የተመሰከረላቸው እና የሙእሚኖች መሪ የነበሩት አራቱ ሰሃባዎች ናቸው። ከእነርሱም በላጩ ሰሓባ አቡበከር አስሲዲቅ﵁ ሲሆን በመቀጠል ዑመር﵁ ከዛም ዑስማን﵁ ከዛም ዓሊይ﵁ በደረጃ ቅደም ተከተል እንደሚቀመጡ አህሉሱና ወልጀማአህ ያወሳሉ። የዚህን ዝርዝር በቀጣይ ጽሁፍ የምንዳስሰው ይሆናል ኢን ሻአ አላህ ። ኢስሃቅ ቢን ራህዌይ ﴿**ከአላህ መልዕክተኛ ﷺበኋላ በምድር ላይ በላጭና ምርጥ እንደ አቡበከር አልነበረም፤ ከእርሱ በመቀጠል ደግሞ በላጭ እንደ ዑመር አልነበረም፤ ከእርሱ ቀጥሎ እንደ ዑስማን በላጭ አልነበረም፤ ከዑስማን ቀጥሎ በምድር ላይ እንደ ዓሊይ በላጭ አልነበረም)** ﴾ጃሚዑ በያኒል ዒልም ሊብኒ ዐብዲል በር 2/226) ይላል።

አህሉሱናዎች ከእነዚህ አራት ሰሓባዎች ቀጥሎ የተቀኑትን ስድስት በጀነት የተበሰሩ ሰሓባዎችን ያስበልጣሉ። በመቀጠል የበድር ዘመቻ የተሳተፉትን ሰሓባዎች ያስበልጣሉ። ከእነርሱም በመቀጠል ከዛፏ ስር ከመልዕክተኛው ﷺጋር ቃል የተጋቡትን ሰሓቦች ያስበልጣሉ ። አላህ የሁሉንም ስራ ይውደድላቸው!!

ስለ አህሉሱና ወልጀማዓህ አቋም ካነሳን አይቀር አህሉሱናዎች የነብዩን ﷺሚስቶች ሁሉንም እንደሚወዱ ሳያነሱ ማለፍ አግባብነት የለውም። አላህ ﷻበቁርአኑ እንዲህ በማለት የነብዩን ﷺባለቤቶች እናቶቻችን መሆናቸውን ነግሮናል!

﴿**ነቢዩ በምእምናን ከነፍሶቻቸው ይበልጥ ተገቢ ነው፡፡ ሚስቶቹም እናቶቻቸው ናቸው፡፡)** ﴾አል አሕዛብ 6)

በተጨማሪም አህሉሱና ወልጀመዓህ የነብዩን ﷺ ቤተሰቦችና የቅርብ ዘመዶች ይወዳሉ ። እነዚያን በነብዩ ﷺመልዕክተኝነት አምነው እስልምናን የተቀበሉትን የነብዩ ﷺቤተሰቦችና ዘመዶችን ሁሉ ይወዳሉ። ይህንንም የሚያደርጉት የነብዩን ﷺአደራ ከመጠበቅ አንፃርም ነው። መልዕክተኛው ﷺሶስት ግዜ ﴿**ቤተሰቦቼን አደራ** ﴾ብለዋልና። አህሉሱናዎች የነብዩን ﷺሰሓቦች፣ ሚስቶችና ዘመዶች ከመውደዳቸው ጋር በአንዳቸውም ላይ ድንበርን አያልፉም፤ ለአንዳቸውም ከስህተት መፅዳትን (መእሱም መሆንን) አይሞግቱም። ለሁሉም የሚገባውን ሐቅ መስጠት እንጂ በሐይማኖት ድንበር ማለፍ የተከለከለ ነውና! አላህ ﷻእንዲህ ይላል :- ﴿ **የመጽሃፉ ባለቤቶች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ድንበርን አትለፉ ......)** ﴾አል ኒሳእ 171)

ውድ አንባቢያን ሆይ! እነዚህን ብርቅዬ የነብዩ ﷺባልደረቦች፣ ሚስቶችና ቤተሰቦች ከመስደብ፣ከመዝለፍ፣ከማንቋሸሽና ከመውቀስ የከበደ ምን አስቀያሚ ነገር አለ? በእርግጥ ኢማም አቡ ዙርዓህ እንዲህ ሲል እውነት ተናገረ፡-

﴿**ከመልዕክተኛው ﷺሰሓባዎች ውስጥ አንዱን ሲዘልፍ አንድን ሰው ካየኸው፣ ይህ ሰው ዚንዲቅ (አማኝ መሳይ ሰላይ) መሆኑን እወቅ፤ ምክኒያቱም መልዕክተኛው ﷺእኛ ዘንድ ሃቅ ናቸው፤ ቁርአንም እኛ ዘንድ ሃቅ ነው፤ ይህን ቁርአንና ሱና ወደ እኛ ያስተላለፉት ደግሞ የረሱል ﷺሰሓቦች ናቸው። ይህ ሰው (በዘለፋው) የሚፈልገው ቁርአንና ሱናን መጣል ነው። ዚንዲቅ ነውና ከዚህ ሰው ማስጠንቀቅ ይገባል፡፡)** ﴾አል ካፊያ ሊልኸጢብ 49)

ስለ ሰሓቦች መልካም ነገራቸውን ማውሳት እንጂ እነርሱን መስደብ፣ ማጣጣል፣ በመጥፎ ባህሪያት መግለጽ፣ ፍትሃዊነታቸውን ጥያቄ ውስጥ መጣል እና በሐይማኖታቸው እና ስነምግባራቸው ጉድለትን መሞገት የአህሉሱና ወልጀመዓን አካሄድ መፃረር ነው። እነርሱን የመተቸት ቀላሉ እርከን ፊስቅ (አመፀኝነት) ሲሆን እስከ ኩፍር የሚደርስ ደረጃም እንዳለው ዑለማዎች ይተነትናሉ።

ኢማሙ አህመድ አስሱና በተሰኘው ድርሳናቸው ﴿**የሁሉንም ሰሓባዎች መልካም ገፅታ መጥቀስና በመካከላቸው የተከሰተውን ነገር አስመልክቶ እጅን መሰብሰብ ከሱና ነው። እነሱን የሰደበ አንዱን እንኳ ቢሆን፣ ይህ ሰው ሙብተዲዕ ራፊዲ ነው። እነሱን መውደድ ሱና ነው። ለነሱ ዱዓ ማድረግ ወደ አላህ መቃረብ ነው፤ እነሱን መሪ አድርጎ መያዝ አድራሽ ነው፤ ፋናቸውን መያዝ ልቅና ነው።** ﴾ይሉናል(አስሱና 17)።

አቡ ጃዕፈር አጠሃዊም እንዲህ ይላሉ:- ﴿**የመልክተኛው ሰሓቦችን እንወዳለን፤ አንዳቸውንም ከውዴታ አናሳንስም፤ ከአንዳቸውም ራሳችንን አናርቅም፤ የሚጠላቸውና ከመልካም ውጪ የሚያወሳቸውን ሰው እንጠላለን)** ﴾ዓቂደቱ ጠሓዊያ 33) ይላሉ።

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ አልዓቂዳ አልዋሲጢያ በተሰኘው ድርሳናቸው ይህን ያስነብቡናል፡-

﴿**(አህሉሱና ወልጀማዓ) ከእነዛ ሰሓባዎችን ከሚጠሉትና ከሚሳደቡት ራፊዳዎች አካሄድ የራቁ ናቸው፤ ከእነዛ አህሉል በይትን በንግግርም ይሁን በተግባር ከሚያስቸግሩት ነዋሲቦች መንገድም የጠሩ ናቸው፤ በሰሓባዎች መካከል የተከሰተውን ጉዳይ አስመልክቶ (ያለ አግባብ ከመዘባረቅ) ራሳቸውን ይቆጥባሉ።)** ﴾ አልዓቂዳ አልዋሲጢያ 32)

ውድ አንባቢ ሆይ እርግጥ ነው በሰሓቦች ዙሪያ በበቂ ሁኔታ ለመደስኮር ባለ ብዙ ገፅ መፅሓፍ ይፈልጋል። የዚህ ፅሁፍ አላማም በርእሱ ላይ ሁሉን ነገር ማሳወቅ ሳይሆን በርእሱ ዙሪያ የሚነሱ ጉዳዮችን በጥቅሉ ለመጠቆምና ለቀጣዩ ፅሁፍም መንደርደሪያ ይሆንዘንድ ነው። አላህ ﷻየነብዩ ﷺባልደረቦችን ውዴታ ይለግሰን፤ መንገዳቸውንም የምንከተል ያድርገን፤ በቀጣይ ፅሁፍ እስከምንገናኝ ወሰላሙ ዐለይኩም።

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

✍ አቡ ዑሠይሚን ኑጋ

ቅጽ 1 ቁጥር 1 | መጋቢት 2011

# የመልካም መክፈቻ ሁን!

عن أنس بن مالك رضي الله عنه قال : قال رسول الله صلى الله عليه وسلم :

إِنَّ مِنْ النَّاسِ مَفَاتِيحَ لِلْخَيْرِ مَغَالِيقَ لِلشَّرِّ ، وَإِنَّ مِنْ النَّاسِ مَفَاتِيحَ لِلشَّرِّ مَغَالِيقَ لِلْخَيْرِ ، فَطُوبَى لِمَنْ جَعَلَ اللَّهُ مَفَاتِيحَ الْخَيْرِ عَلَى يَدَيْهِ ، وَوَيْلٌ لِمَنْ جَعَلَ اللَّهُ مَفَاتِيحَ الشَّرِّ عَلَى يَدَيْهِ .

*"ከሰዎች መካከል የመልካም መክፈቻ ቁልፍ የሆኑና የመጥፎ ዘጊዎች የሆኑ አሉ ፤ እንዲሁም ከሰዎች መካከል የሸር (መጥፎ) በር ከፋች የሆኑና የመልካም በር ዘጊ የሆኑ አሉ። አላህ የመልካም በር መክፈቻ ቁልፍ በእጁ ያደረገለት "ጡባ" አለለት ፤ አላህ የመጥፎ በር መክፈቻ ቁልፍ በእጁ ላደረገበት "ወይል" አለለት።"*

[ኢብኑ ማጃህ (237) ዘግበውታል። ኢማሙ አልባኒ ሰሒሕ ኢብኑ ማጃህ (194) ላይ ሐዲሡን ሐሰን ብለውታል ።]

"ጡባ" :- የእድለኝነት ምልክት ፣ የጀነት ሰው ለመሆኑ መገለጫ ወይም በጀነት ውስጥ ያለች ዛፍ ነችም ተብሏል።

"ወይል" :- ወየውለት ፣ የጀሀነም ሰው ለመሆኑ ምልክት ወይም ጀሀነም ውስጥ ያለ ሸለቆ ነው ተብሏል።

ነፍሱ የ"ጡባ" ባለቤት የመልካም በር ከፋች ፣ የመጥፎ በር ዘጊ እንድትሆንለት የፈለገ ሰው ። በሚከተሉትን ወሳኝ ነጥቦች ላይ አደራ እላለሁ፡-

## 1/ ኢኽላስ

ንግግርንም ሆነ ተግባርን በኢኽላስ ለአላህ ብቻ ጥርት ማድረግ ። ምክንያቱም እርሱ የመልካም ነገሮች ሁሉ መሰረትና ምሰሶ የልዕቅና ሁሉ ምንጭ ነው። ከእዩልኝና ይስሙልኝን ሊርቅ ይገባል። በኢኽላስ ላይ ያልተመሰረተ ማንኛውም ተግባርና ጥረት ከንቱ ልፋት የእምቧይ ካብ ነው።

## 2/ ዱዓ

ይህን መልካም ነገር አላህ እንዲገጥመንና እንዲወፍቀን ሌት ተቀን በዘውታሪነት ልንለምን ይገባል። ምክንያቱም ዱዓ የመልካም ነገሮች ሁሉ መክፈቻ ቁልፍ ነውና። አላህ ባሪያው ለምኖት ልመናውን ከንቱ አድርጎ አያስቀርበትም ተመላሽ አያደርግበትም። ሙእሚን ለጌታው ተዋርዶና ተናንሶ በምስጢር ያደረገውን ዱዓ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አያልፍበትም።

ከሶስት በአንዱ መንገድ ለልመናው ምላሽ ይሰጠዋል! ለልመናው አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል።ወይም የመጣበትን በላ ይመልስለታል። አልያ ደግሞ ለየውመል ቂያማ ያስቀምጥለታል።

አደራ! ለመንኩ ለመንኩ መልስ አልሰጠኝም ብለህ ተስፋ አትቁረጥ ነብዩ ኢብራሂም ለረጅም ዓመታት ጌታቸውን ሲማፀኑ ከርመው ከሰባ ዓመታቸው በኋላ ልጅ እንደሰጣቸው አትርሳ! ኢብራሂም ያንን ሁሉ ጊዜያት ጌታቸውን ሲማጸኑ ቆይተው የዱዓቸው ፍሬ በስተርጅና ሲመጣ ከመማረር ይልቅ ይህን ነበር ያሉት፡-

***"ጌታዬ ልመናን ሰሚ ነው።"*** *(ኢብራሂም: 39)*

## 3/ ዒልም

ዕውቀት ለመፈለግና ለማግኘት መልፋት ፣ መትጋትና መጓጓት (እንዲሁም) ለመገብየትም መጣር ግድ ይላል። ዕውቀት ወደ ልዕቅና እና ክብር ሲጠራ (ሲያደርስ) ከመጥፎና ውዳቂ ነገሮች ሁሉ ይከለክላል።

ዕውቀት ብርሃን ሲሆን ጅህልና ጨለማ ነው።ድቅድቅ ያለ ጨለማ! ጃሂል የመልካም በረ ከፋች ከመሆን ይልቅ የሸር በሮችን ቁልፍ በጠቅላላ ሸክፎ ለመዞር የቀረበ ነው። ምክንያቱ ከመሰረቱ ኸይር ምን እንደሆነ ሸር ምን እንደሆነ ለይቶ በአግባቡ አያውቅምና።

## 4/ ዒባዳን መፈጸም

ዒባዳ (አምልኮ) ተግባራትን መፈጸም። በተለይም ደግሞ ግዴታ የሆኑ የአምልኮ ተግባራትን መተግበር። ከነዚህ ግዴታ ተግባራት ደግሞ ልዩ በሆነ መልኩ ለሶላት ትልቅ ትኩረት መስጠት (ያስፈልጋል)። ምክንያቱም ሶላት ከጸያፊና መጥፎ ከሆኑ ተግባራት (ሁሉ) ትከለክላለችና።

## 5/ መልካም ስነ ምግባር!

(ድምጽ አልባ ዳዕዋ!) መልካም ስነ ምግባር መላበስ ፣ ላቅ ባሉና በመጠቁ ባህሪያት መዋብ ፣ መልካም ስነ ምግባርን ከሚያጎድፉ ከሚያቆሽሹ ተግባራት እና የመጥፎ ስነ ምግባር መገለጫ ከሆኑ አጸያፊና ውዳቂ ከሆኑ ባህሪያት መራቅ ።

መልካም ስነግባር ከተቅዋ ጋር ተደምረው አንድን ሙእሚን ጀነት ለመግባት እንደሚረዱት መልክተኛው አስተምረዋል። በምርጥ ባህሪው ምክንያትም ቀን የሚፆሙና ለሊት የሚቆሙ ዓቢዶች የሚያገኙትን ምንዳም እንደሚሸምትም ተናግረዋል። በቂያማ እለትም በስራ ሚዛን ላይ በከፍተኛ ደረጃ ሚዛን እንደሚያነሳ አውስተዋል። ሌላም ሌላም ለመልካም ባህሪ ባለቤቶች ታላላቅ የምስራቾችን አበስረዋል።

ሙስሊምም ይሁን ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር ባለን መስተጋብር ላይ ጥሩ ስነምግባር ልንላበስ ፣ በመልካም ልንኗኗራቸው ይገባናል።

በተለይም ሙስሊሞች መገለጫቸው ከነበረው መልካም ስነ ምግባር እየራቁ ባሉበት እና እንኳን የውጪውን የውስጡንም የሚያስወጣ አስቸጋሪ ባህሪን ተላብሰው ባሉበት ወቅት መልካም ባህሪን መጎናፀፍና ለሌሎች አርዓያ መሆን ታላቅ ጅብድ ነው።

በምናሳየውም ስነ ምግባር ተማርከው ስለኛ ጀርባ ለማጥናት እንዲነሳሱና የምናንፀባርቀውን የኢስላምና የሱንና ብርሃን ፈልገው አግኝተው እንዲቋደሱ ማድረግ ይቻላል።

***"ከሰዎች መካከል የመልካም መክፈቻ ቁልፍ የሆኑና የመጥፎ ዘጊዎች የሆኑ አሉ ፤ እንዲሁም ከሰዎች መካከል የሸር (መጥፎ) በር ከፋች የሆኑና የመልካም በር ዘጊ የሆኑ አሉ።"***

## 6/ ጓደኛ ምርጫ

ከመልካም ሰዎች ጋር መጎዳኘት እና ከመልካም ሰዎች ጋር መቀማመጥ። ከእነርሱ ጋር መቀማመጥ መላኢኮች በክብር ክንፋቸውን ዝቅ እንዲያደርጉልን የአላህ እዝነት እንዲያካበን ያደርጋል። (በተቃራኒው) ከመጥፎና ክፉ ሰዎች ጋር ከመቀማመጥ ልንጠነቀቅ ይገባል ። ምክንያቱም (የእነርሱ መሰብሰቢያ) የሸይጧኖች መከማቻ ስፍራ ነውና።

የጓደኛው መልካም ነገር መስራት ለመልካም ነገር መሯሯጥ በዲኑ ላይ መፅናት የሚያበግነው አይኑን የሚያቀላው ነፍ ነው ። ከመልካም ነገር ርቆ የሸይጧን ሰራዊት እንዲሆን የሚጎተጉትና በል በል የሚል ጓደኛ የትየለሌ ነውና ጓደኛን በጥንቃቄ መምረጥ ያሻል። ለአኼራህ የሚጠቅምህን የሚመክሩ ፣ ችግርህን የሚካፈሉ ፣ ስትሳሳትና ስታጠፋ በእዝነት የሚመክሩህ ፣ ወደ መልካም ነገር የሚገፋፉ ውድ ጓደኞችም አሉና እነርሱን መርጦ መጎዳኘት ያስፈልጋል።

## 7/ ነሲሐ

(ከመቆርቆር ጋር ምክር መለገስ መመካከር )

ለአላህ ባሮች በሚገናኛቸውና አብሮ በሚኗኗራቸው ጊዜ ነሲሓ መስጠት። በመልካም ነገር ላይ እንዲጠመዱ ማድረግ እና ከመጥፎ ነገሮች እንዲርቁ ማድረግ።ያለንበት ጊዜ ሙስሊሞችን ከቀጥተኛው ጎዳና አስፈንጥሮ ለማውጣት ፣ እርስ በእርስ ለማባላትና ለማለያየት ፣ ከዲናቸውን ለማቆራረጥና ክብራቸውን ለማርከስ ከየአቅጣጫው እየተዘመተበት ያለበት ነው። ስለሆነም ሙስሊሞች ከምግብና ከመጠጥ ኧረ እንደውም ከአየርም የበለጠ ትክክለኛ ነሲሓ ያስፈልጋቸዋል።

በመሆኑም በኢኽላስ በወንድማዊነትና በተቆርቋሪነት ስሜት በእዝነት ሊመክራቸው ግድ ይላል። የጥፋት ኃይሎች በየአቅጣጫቸው እየጎተቷቸው የጥፋት አዘቅት ውስጥ ሊዶሏቸው (ሊከቷቸው) እየተውተረተሩ ነውና ሊደርስላቸው ይገባል።

በተቃራኒው መናገር ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ ሰዎችን በእልህ ከሐቅ እንዲሸሹ በማድረግ ለጥፋት ሀይሎችና ለሸይጣንና ጋሻጃግሬዎቹ ቀንደኛ ረዳት ከመሆን ሊታቀብ ይገባል። የመልካም በር ከፋች መሆን ቢያቅተን የመጥፎ በር ከፋች አንሁን።

## 8 አኼራን ማስታወስ

ሞቶ መቀስቀስ እንዳለና የዓለማቱ ጌታ ፊት ቆሞ መተሳሰብ መኖሩን ማስታወስ። መልካም የሰራ በመልካም ስራው ልክ እንደሚመነዳና መጥፎ የሰራም በመጥፎ ስራው ልክ እንደሚቀጣ ማስታወስ።

***"የብናኝ ክብደት ያክልም መልካም የሰራ ሰው ያገኘዋል። ۞የብናኝም ክብደት ያክል ክፉን የሰራ ሰው ያገኘዋል።" (አል ዘልዘላህ 7 -8)***

አኼራ አለብኝ ብሎ የሚያስብ ሰው ስሜቱንና ፍላጎቱን እየተከተለ ሰዎችን ወደጥፋት አይነዳም የሸር በሮችን ለመከፋፈት አይታትርም አላህ ፊት መቆምን ይፈራል።

## 9 ቅን አሳቢ መሆን!

የነዚህ ሁሉ መሰረትና ምሰሶው ደግሞ አንድ ሰው ለኸይር ነገር ክጃሎት ያለውና የአላህ ባሮችን ለመጥቀም ፍላጎት ያለው መሆኑ ነው። በዚህ ክጃሎቱም ላይ ቀጥ ካለ፣ በሀሳቡም ላይ ከጸናና በጉዳዩም ላይ በአላህ ከታገዘ ፣ ትክክለኛውንም መንገድ ይዞ ከተጓዘ በአላህ ፍቃድ የመልካም በር ከፋች የመጥፎ በር ዘጊ ይሆናል።

አላህ ባሮቹን ለመልካም ነገር በመግጠም ይረዳቸዋል። በፈለገው ሰው በኩል ደግሞ በእውነት ይከፍታል።

አላህ የመልካም በር ከፋች የመጥፎ በር ዘጊ ያድርገን!

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

በዐብዱረዛቅ ቢን ዐብዱል ሙሕሲን አባድ አልበድር (አላህ ይጠብቃቸው) የተዘጋጀ።

ትርጉምና ተጨማሪ ሀሳብ፡-

**✍ አቡ ሐማድ ሐይደር ኸድር**

# خطورة التسرع في التكفير والقيام بالتفجير

## بيان هيئة كبار العلماء حول خطورة التسرع في التكفير والقيام بالتفجير

الأمانة العامة لهيئة كبار العلماء

الحمد لله والصلاة والسلام على رسول الله وعلى آله وصحبه ومن اهتدى بهداه أما بعد

فقد درس مجلس هيئة كبار العلماء في دورته التاسعة والأربعين المنعقدة بالطائف ابتداءً من تاريخ 2/4/1419 هجريه ما يجري في كثير من البلاد الإسلامية وغيرها من التكفير والتفجير وما ينشأ عنه من سفك الدماء وتخريب المنشآت ونظراً إلى خطورة هذا الأمر وما يترتب عليه من إزهاق أرواح بريئة وإتلاف أموال معصومة وإخافة للناس وزعزعة لأمنهم واستقرارهم فقد رأى المجلس إصدار بيان يوضح فيه حكم ذلك نصحاً لله ولعباده وإبراءً للذمة وإزالة للبس في المفاهيم لدى من اشتبه عليهم الأمر في ذلك فنقول وبالله التوفيق

**أولاً**_التكفير حكم شرعي مرده إلى الله ورسوله فكما أن التحريم والتحليل و الإيجاب إلى الله ورسوله فكذلك التكفير وليس كل ما وصف بالكفر من قول أو فعل يكون كفراً أكبر مخرجاً من الملة ولما كان مرد حكم التكفير إلى الله ورسوله لم يجز أن نكفر إلا من دل الكتاب والسنة على كفره دلالة واضحة فلا يكفي في ذلك مجرد الشبهة والظن لما يترتب على ذلك من الأحكام الخطيرة وإذا كانت الحدود تُدرأ بالشبهات ولذلك حذر النبي صلى الله عليه وسلم من الحكم بالتكفير على شخص ليس بكافر فقال((أيُما امرئ قال لأخيه يا كافر فقد باء بها أحدهما إن كان كما قال وإلا رجعت عليه)) وقد يرد في الكتاب والسُنة ما يُفهم منه أن هذا القول أو العمل أو الاعتقاد كُفر ولا يكفر من اتصف به لوجود مانع يمنع من كفره وهذا الحكم كغيره من الأحكام التي لا تتم إلا بوجود أسبابها وشروطها وانتفاء موانعها كما في الإرث سببه القرابة_مثلاً_وقد لا يرث بها لوجود مانع كاختلاف الدين وهكذا الكفر يكره عليه المؤمن فلا يكفر به وقد ينطق المسلم بكلمة بالكفر لغلبة فرح أو غضب أو نحوهما فلا يكفر بها لعدم القصد كما في قصة الذي قال((اللهم أنت عبدي وأنا ربك))أخطأ من شدة الفرح

والتسرع في التكفير يترتب عليه أمور خطيرة من استحلال الدم والمال ومنع التوارث وفسخ النكاح وغيرها مما يترتب على الردة فكيف يسوغ للمؤمن أن يُقدم عليه لأدنى شبهة وإذا كان هذا في وُلاة الأمور كان أشد لما يترتب عله من التمرد عليهم وحمل السلاح عليهم وإشاعة الفوضى وسفك الدماء وفساد العباد والبلاد ولهذا منع النبي صلى الله عليه وسلم من منابذتهم فقال((إلا أن تروا منهم كفراً بَواحاً عندكم من الله فيه برهان)) فأفاد قوله((إلا أن تروا))أنه لا يكفي مجرد الظن والإشاعة وأفاد قوله((كفراً))أنه لا يكفي الفسوق ولو كَبُر كالظلم وشرب الخمر ولعب القمار والاستئثار المحرم وأفاد قوله ((بواحاً))أنه لا يكفي الكفر الذي ليس ببواح أي صريح ظاهر وأفاد قوله((عندكم فيه من الله برهان))أنه لابد من دليل صريح بحيث يكون صحيح الثبوت صريح الدلالة فلا يكفي الدليل ضعيف السند ولا غامض الدلالة وأفاد قوله((من الله))أنه لا عبرة بقول أحد من العلماء مهما بلغت منزلته في العلم والأمانة إذا لم يكن لقوله دليل صريح صحيح من كتاب الله أو سنة رسول الله صلى الله عليه وسلم وهذاه القيود تدل على خطورة الأمر

وجملة القول أن التسرع في التكفير له خطره العظيم لقول الله تعالى((قُل إنما حرم ربي الفواحش ما ظهر منها وما بطن والإثم والبغي بغير الحق وأن تشركوا بالله ما لم ينزل به سلطاناً وأن تقولوا على الله ما لا تعلمون)) [الأعراف33]

**ثانياً**_ما نَجَمَ عن هذا الاعتقاد الخاطئ من استباحة الدماء وانتهاك الأعراض وسلب الأموال الخاصة والعامة وتفجير المساكن والمركبات وتخريب النشآت فهذه الأعمال وأمثالها محرمة شرعاً بإجماع المسلمين لما في ذلك من هتك لحرمة الأنفس المعصومة وهتك لحرمة الأموال وهتك لحرمات الأمن والاستقرار وحياة الناس الآمنين المطمئنين في مساكنهم ومعايشهم وغدوهم ورواحهم وهتك للمصالح العامة التي لا غنى للناس في حياتهم عنها وقد حفظ الإسلام للمسلمين أموالهم وأعراضهم وأبدانهم وحرم انتهاكها وشدد في ذلك وكان من آخر ما بلغ به النبي صلى الله عليه وسلم أمته فقال في خطبة حجة الوداع ((إن دماءكم وموالكم وأعراضكم عليكم حرام كحرمة يومكم هذا في شهركم هذا في بلدكم هذا)) ثم قال صلى الله عليه وسلم((ألا هل بلغت اللهم فاشهد)) متفق عليه. وقال صلى الله عليه وسلم((كل المسلم على المسلم حرام دمه وماله وعرضه))

وقال عليه الصلاة والسلام((اتقوا الظلم فإن الظلم ظلمات يوم القيامة))وقد توعد الله سبحانه وتعالى مَن قَتَل نفساً معصومة بأشد الوعيد فقال سبحانه في حق المؤمن((ومن يقتل مؤمناً متعمداً فجزآؤه جهنم خالداً فيها وغضب الله عليه ولعنه وأعد له عذاباً عظيماً))[النساء93]

وقال سبحانه في حق الكافر الذي له ذمة في حكم قتل الخطأ((وإن كان من قومٍ بينكم وبينهم ميثاقٌ فديةٌ مسلمةٌ إلى أهله وتحرير رقبة مؤمنة))[النساء92]

فإذا كان الكافر الذي له أمان إذا قُتل خطأً فيه الدية والكفارة فكيف إذا قُتل عمداً فإن الجريمة تكون أعظم والإثم يكون أكبر وقد صح عن رسول الله علي الصلاة والسلام أنه قال((مَن قَتَلَ مُعاهِدا لم يَرح رائحة الجنة))

**ثالثاً**_إن المجلس إذ يبين حكم تكفير الناس بغير برهان من كتاب الله وسنة رسوله صلى الله عليه وسلم وخطورة إطلاق ذلك لمَا يترتب عليه من شرور وآثام فإنه يعلن للعالَم أن الإسلام برئ من هذا المُعتقد الخاطئ وأن ما يجري في بعض البلدان من سفك للدماء البريئة وتفجير للمساكن والمركبات والمرافق العامة والخاصة وتخريب للمنشآت هو عمل إجرامي والإسلام برئ منه وهكذا كل مسلم يؤمن بالله واليوم الآخر برئ منه وإنما هو تصرُف من صاحب فكر منحرف وعقيدة ضالة فهو يحمل إثمه وجرمه فلا يحتَسب عمله على الإسلام ولا على المسلمين المهتدين بهدي الإسلام المعتصمين بالكتاب والسنَة المستمسكين بحبل الله المتين وإنما هو محض إفساد وإجرام تأباه الشريعة والفطرة ولهذا جاءت نصوص الشريعة قاطعة بتحريمه محذرة من مصاحبة أهله قال تعالى((ومن الناس من يعجبك قوله في الحياة الدنيا ويشهد الله على ما في قلبه وهو ألد الخصام وإذا تولى سعى في الأرض ليفسد فيها ويهلك الحرث والنسل والله لايحب الفساد وإذا قيل له اتق الله أخذته العزة بالإثم فحسبه جهنم و لبئس المهاد))[البقرة204_206]

والواجب على جميع المسلمين في كل مكان التواصي بالحق والتناصح والتعاون على البر والتقوى والأمر بالمعروف والنهي عن المنكر بالحكمة والموعظة الحسنة والجدال بالتي هي أحسن كما قال الله تعالى((وتعاونوا على البر والتقوى ولا تعاونوا على الإثم والعدوان واتقوا الله إن الله شديد العقاب))[المائدة 2]

وقال تعالى ((والمؤمنون والمؤمنات بعضهم أولياء بعض يأمرون بالمعروف وينهون عن المنكر ويقيمون الصلاة ويؤتون الزكاة ويطيعون الله ورسوله وأولئك سيرحمهم الله إن الله عزيزٌ حكيمٌ)) [التوبة 71] وقال عز وجل ((والعصر إن الإنسان لفي خُسر إلا الذين أمنوا وعملوا الصالحات وتواصوا بالحق وتواصوا بالصبر)) [سورة العصر]

وقال النبي صلى الله عليه وسلم {الدين النصيحة}قيل لمن يا رسول الله ؟ قال {لله ولكتابه ولرسوله ولأئمة المسلمين وعامتهم} وقال عليه الصلاة والسلام {مَثل المؤمنين في توادهم وتراحمهم وتعاطفهم مثل الجسد إذا اشتكى منه عضو تداعى له سائر الجسد بالسهر والحمى}والآيات والأحاديث في هذا المعنى كثيرة ونسأل الله سبحانه بأسمائه الحسنى وصفاته العُلى أن يكف البأس عن جميع المسلمين وأن يُوفق جميع ولاة أمور المسلمين إلى ما فيه صلاح العباد والبلاد وقمع الفساد والمفسدين وأن ينصر بهم دينه ويُعلي كلمته وأن يصلح أحوال المسلمين جميعاً في كل مكان وأن ينصر بهم الحق وإنه ولي ذلك والقادر عليه وصلى الله وسلم على نبينا محمد وآله وصحبه.

**رئيس المجلس:عبد العزيز بن عبد الله بن باز**

وعضوية كل من :صالح بن محمد اللحيدان_عبد الله بن سليمان بن منيع_محمد بن صالح العثيمين_عبد العزيز بن عبد الله بن محمد آل الشيخ_د/عبد الله بن محمد بن إبراهيم آل الشيخ_د/ عبد الله بن عبد المحسن التركي_د/عبد الوهاب بن إبراهيم أبو سليمان_راشد بن صالح بن خنين_عبد الله بن عبد الرحمان الغديان _عبد الله بن عبد الرحمان البسام_ناصر بن حمد الراشد_محمد بن سليمان البدر_محمد بن زيد آل سليمان_د/صالح بن عبد الرحمان الأطرم_محمد بن إبراهيم بن جبير_د/صالح بن فوزان الفوزان_حسن بن جعفر العتمي_محمد بن عبد الله السبيل_عبد الرحمان بن حمزة المرزوقي_د/بكر بن عبد الله أبو زيد

{مجلة البحوث الإسلامية عدد(56)صفحة(357_362)}

# Dursa gabaabaa waa’ee Islaamaa

## Bu’uura Islaamaa baradhu

## Waa’ee Islaamaa

Islaamni adeemsa hunda walitti qabataafi seera jireenyaa guutuudha. Hariiroo Rabbii waliin qabuufi waliin jireenya ummata waliin qabu haaromsuutti nama kakaasa. Barnoonni Islaamaa akka namni kamuu milkuu dhugaafi tasgabbii keessoo Rabbiin baruufi hojii gaggaarii Inni ajaje hojjachuun malee hin arganne ibsa. Isheen immoo bu’aa namichumaaf argamsiifti. Akkuma kana bu’aa hawaasaafis ni argamsiifti.

Islaamni amantiiwwan hordoftoota baay’ee qaban addunyaa keessaa isa tokko. Muslimoonni ummata addunyaa keessaa tokko shanaffaa ta’u. Rabbiin gabbaramaa ta’uutti amanuufi waan biraa irraa ibaadaadhaan Isa kophaa baasuun kaayyoo bu’uura jireenya kanaati. Inni akkuma kana bu’uura tu’oon mana Islaamaa irratti ijaarameedha.

Jechi “Islaam” jedhu Afaan Arabaa keessatti Rabbii tokkichaaf “of gadi qabuufi ajajamuu” jechuudha. Namni fedhii Rabbiitiif ajajamuuf jecha of gadi qabu Muslima jedhama. Kun immoo bifa, sabaafi gosa isaa odoo adda hin baasini.

Wanti Islaama amantii biraa irraa adda baasu tokko inni saba wahiitiin yookiin nama dhuunfaadhaan hin waamamne.

### Arkaana ibaadaa (Islaamaa) shanan
### Arkaana jireenya Muslimaa shanan

### 1. Iimaana

Rabbii ol ta’etti amanuu mirkaneessuu jechuun “akka Rabbiin malee dhugaan gabbaramaan hin jirreefi Muhammad Ergamaa Rabbii ta’uu” ragaa bahuudha.

Ragaan kun amantii qalbii gadi seenaadhaan ishee amanuu, ishee dubbachuufi ergaa isheetiin hojjachuu keessatti Rabbiin qofaaf qulqulleessuu irratti hundaa’uu qaba. Ragaa kanaan gabrichi waan Rabbii gaditti gabbaramu hundatti kafara; “Rabbiin qofatu gabbaramaa dhugaati; wanti Isaan alatti gabbaramu dhara” jechuu mirkaneessa. Muhammad dhuma nabiyyootaafi ergamaa Rabbii ta’uus ni mirkaneessa. Ogga kana namni Muslima ta’a.

### 2. Salaata shanan

Salaanni hariiroo nafsiifi ruuhii jidduu Muslimaafi Uumaa isaa jirtu irraa argamti. Hariirottiin utubaan ishee iimaanaafi dhugoomsuu, jaalala, yaada toluu guddisuufi qulqulleessuu waliin ta’eedha.

Salaanni shanan booda shahaadaa lamaaniitii utubaa Islaamaa isa akkaan barbaachisaadha. Waqtiileen salaata shanan kanaa yeroo fajrii, Zuhrii, Asrii, magribaafi ishaati.

Salaanni kamuu yeroo gabaabaa, daqiiqaa lakkaa’amtuu fudhatti. Qur'aana qara’uu, Rabbiin kadhachuu, Isa guddisuufi faarsuu irraa ijaaramte.

Muslimni kamuu qaama isaa murtaa’aa kan akka fuulaafi harka lamaanii dhiqachuudhaan xahaaraa isaa mirkaneeffatee salaataaf qophaa’uu qaba. Kanaan qulqullina gubbaafi keessaa argata.

> Jechi “Islaam” jedhu Afaan Arabaa keessatti Rabbii tokkichaaf “of gadi qabuufi ajajamuu” jechuudha. Namni fedhii Rabbiitiif ajajamuuf jecha of gadi qabu Muslima jedhama. Kun immoo bifa, sabaafi gosa isaa odoo adda hin baasini.

### 3. Zakaa

Zakaan dirqama Rabbiin qabeenya Muslima nisaaba (hanga zakaan itti dirqama ta’u) dhaqqabee hunda keessatti kallattii murtaa’aadhaan dirqama godheedha.

Waggaa keessatti namoottan ulaagaa kana bifa Qur'aanni dubbateen (hiyyeessaaf, harka qalleeyyiif, ..) guuttateef shallaga xiqqoo qabeenya keessaa baafamuudha.

Zakaan qabeenya Muslimaa ni qulqulleessiti; ni dabalti. Isa kenneefi fudhateefis bu’aa buufti. Bu’aa ishee keessaa tokko jibbaa jidduu dureessaafi hiyyeessaa hir’ifti. Namoottan hawaasa keessa jiraatan hunduu akka isaan dhimma isaanii kan bu’uuraa argatan taasifti.

### 4. Sooma

Muslimoonni hunduu ji’a Ramadaanaa keessa yeroo fajriin bahu irraa eegalanii hanga biiftuun seenutti soomu. Yeroo kana keessa nyaata, dhugaatiifi wal qunnamtii irraa fagaatu.

Soomni lubbuu namaa ni qulqulleessa. Obsaafi wal danda’uu oomishuuf sababa gargaaruudha. Dabalata immoo bu’aa fayyaa baay’ee qaba.

Ramadaanni lakkoofsa Islaamaa keessatti ji’a saglaffaadha.

### 5. Hajjii

Umurii keessa yoo xiqqaate si’a tokko mana Rabbii kabajamaa Makkaan jiru hajjii gochuun Muslima qaamaafi qabeenyaan danda’e hunda irrattuu dirqama.

Hajjiin taatee waggaa keessa ji’a Zulhijjaa keessa deddeebi’uudha. Inni ruknii isa keessatti odoma bifti, sabni, sadarkaafi umuriin isaanii wal dhabuu tokkummaan Muslimootaa ibaadaa Rabbii keessatti mullatuudha.

Imalli guddaan kun ibaadaa baay’ee walitti qabamte kan akka wareegamaa, imalaafi bakka adda addaatti salaatuu irraa ijaaramte. Muuxannottiin kun of gadi qabuufi obsa gabricha barsiifti.

Warri hajjii godhan hundinuu huccuu wal fakkaataa huccuu harramannaa jedhamu uffatu. Isa keessatti dureessiifi hiyyeessi, cimaafi laafaan, hojjataafi hojjachiisaan wal qixxaatu. Hundi isaaniituu fuuldura Rabbii dhaabachuu keessatti wal qixxaatu.

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# وَقُلْ رَبِّ زِدْنِي عِلْمًا

[“ጌታዬ ሆይ እውቀትን ጨምርልኝ” በል!]

## ስለ ነሲሓ አካዳሚ ምን ያውቃሉ?

وَقُلْ رَبِّ زِدْنِي عِلْمًا

«ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ» በል።

ነሲሐ አካዳሚ "ኢስላማዊ ዕውቀት ለሁሉም" በሚል መሪ ቃል በነሲሓ ቲቪ የሚተላለፉ ተከታታይ ትምህርቶች ላይ የተመረኮዘ መርሃ ግብር ሲሆን ትምህርቱ ሁለት አይነት አርከኖች አሉት:-

### 1) መሰረታዊ የዲን ትምህርት ለሁሉም

ይህ ለጀማሪዎች እንዲስማማ የተቀረፀ መርሃ ግብር ሲሆን በውስጡም:-

የተፍሲር፣ የሐዲሥ፣ የፊቅህ፣ የተዉሂድ፣ የሲራ፣

የዐረብኛ ቋንቋ እና የተርቢያ

ዘርፎችን ያካተተ ይሆናል።

ትምህርቶቹን ከተከታተሉ የማጠናቀቂያ ፈተና ወስደው ሰርተፊኬት የሚያገኙበት ልዩ የትምህርት መርሐ–ግብር ነው።

### 2) ነሲሓ ተከታታይ የኪታብ ቂራአት

ይህ አረከን የተለያዩ እውቅ ኪታቦችን መማር የሚሹ ተማሪዎችን (ጠለበተል—ዒልም) ን ታሳቢ ያደረገ ነው። በተለያየ ግዜ የሚተላለፉ የኪታብ ቂራአት ፕሮግራሞች ሲጠናቀቁ፤

√ ማንኛውም ተማሪ በአካዳሚው ለዚህ ትምህርት የሚሰጠውን ፈተና በመውሰድ በተማረው ኪታብ ላይ የተገደበ የተሳትፎ የምስክር ወረቀት ያገኛል።

√ የተለያዩ ኪታቦችን በርቀት በመማር ነጥቦችን አጠራቅሞ የነሲሐ አካዳሚን የዲፕሎማ መስፈርት እንደሚያሟላ ከተረጋገጠ የዲፕሎማ ሰርተፊኬት ፈተናዎችን በመውሰድ እንደውጤቱ የዲፕሎማ ሰርቲፊኬት ያገኛል።

«من يرد الله به خيرا يفقهه في الدين»[رواه البخاري ومسلم]

«አላህ መልካም የሻለትን ዲኑን ያስገነዝበዋል» [አል-ቡኻሪ እና ሙስሊም]

### ነሲሓ አካዳሚ ለመመዝገብ

ወደ ድረገፃችን የሚወስደውን ሊንክ በመጠቀም የመመዝገቢያ ቅፁን ሞልተው የነሲሓ አካዳሚ ተማሪ ለመሆን ይመዝገቡ!

http://nesiha.tv/acadamy.php



ነሲሓ ቲቪ
ኢስላማዊ እውቀት ለሁሉም
Nesiha TV
الدين النصيحة
Islamic Knowledge For All
Frequency - 11555
Symbol Rate - 27500
Polarization - vertical
Fec 5/6